facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART ONE
ሰውን ለተሻለ ነገር እናጥምድ!

ሰውን ለራስ ዓላማ፣ ለራስ ጥቅም፣ ለራስ እውቅናና ለራስ መሳሪያነት ማጥመድ አልበዛም ትላላችሁ???

“እርሱም። በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ አላቸው።” (ማቴ 4:19)

ከላይ የተጠቀሰው መልዕክት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በገሊላ ባሕር አጠገብ ሲመላለስ ያገኛቸውን ሁለት ዓሣ አጥማጅ ወንድማማቾች (ጴጥሮስ እና ወንድሙ እንድርያስ) የተመለከተ ነው።

ዓሣ ማጥመድ እንደ ማንኛውም ተግባር (ሙያ) መልካም ተግባር (ሙያ) ነው። ሰውን የሚያህል ክቡር ፍጡር ደግሞ ከአሣ አጥማጅነት ሐዋርያ (መልዕክተኛ) አድርጎ ሰው አጥማጅ ማድረግ ደግሞ የበለጠ።

ስለዚህ ወገኖቼ ጌታ ኢየሱስ እንዳደረገው ማንንም ሰው ለራሳችን አጀንዳ ሳይሆን ለተሻለ ነገር፣ ለማህበረሰብ እድገትና ጥቅም እናጥምድ!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART TWO
ወደ ሴት ያየ ሁሉ.....!

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ “ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።” (ማቴ5:28) ሲል የተመልካቹ እይታ ወደአገባት እና የእርሱ ወደሆነች ሴት ማለቱ እንዳልሆነ ግልጽ ይመስለኛል።

ታዲያ እኛ ዛሬ ወደማን እያየን ነው? ማንን እየተከታተልን እና እያገኘን (contact) ነው? ከማን ምን እየፈለግን ነው? በምን ዓላማ ነው የሆነ ሰውን እያየንና እየተከተልን ብሎም እያገኘን ያለነው?

እንመለስ! ይሄ ጉዞና ምኞት መጨረሻው ማመንዘር ነው። “ “ይህን እወቁ፤ አመንዝራ ... በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት የለውም።” (ኤፌ 5:5)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART THREE
የዕለት እንጀራ......!

ጌታችን መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ” ብሎ ጸሎት ባስተማረበት የማቴዎስ ወንጌል (ማቴ 6:11) ክፍል “የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፤” የሚል ይገኝበታል።

የአብዛኛው ሰው ሩጫ ግን ቃሉ እንደሚለው ለዕለት እንጀራ አይመስልም።

ጥሩ ምሳሌ ከመጽሐፍ ላንሳ “እግዚአብሔርም ሙሴን... እነሆ ከሰማይ እንጀራን አዘንብላችኋለሁ፤ ሕዝቡም ወጥተው ለዕለት ለዕለት የሚበቃቸውን ይልቀሙ። ... ነገር ግን ሙሴን አልሰሙትም፤ አንዳንድ ሰዎችም ከእርሱ ለነገ አስቀሩ፥ እርሱም ተላ፣ ሸተተም፤ ” (ዘጸ 16:4-20)”

ሰዎቹ ምን ነካቸው? ከሰማይ የዘነበላቸው ንፁህ እንጀራ አፍታም ሳይቆይ ተላ፣ ሸተተ። ምክንያቱ ግልጽ ነው። ለዕለት (በልክ) የተፈቀደውን ከዕለት (ከልክ) ባለፈ ለመሰብሰብ ፈለጓ።

የተላ እና የሸተተ ነገር ደስ አያሰኝም። ከዕለት (ከልክ) ያለፈ ነገር ለማግኘት የሚደረግ ጥረት ውጤቱ መትላት እና ሽታ ነው። ሁሉ ለዕለት (በልክ) እና የተገባን ይሁን። ገንዘብ በልክ፣ ዝና በልክ፣ ሹመት በልክ፣ ብቻ ሁሉም በልክ።

አይመስላችሁም?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART FOUR
የጠበበው ደጅ.....!

የጥቅሱን አቀማመጥ ለግንዛቤ እንዲረዳ በማሰብ የመልዕክት ቤት በሚመታበት መልኩ ከመጽሐፉ እንዲህ ወስጄዋለሁ።

“በጠበበው ደጅ ግቡ። ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው። ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ፥ መንገዱም ትልቅ ነውና፥ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፤ “ (ማቴ 7:13-14)

ብዙ ሰው ሰፊ ነገር ወደደ። ሰፊ ትዳር (እዛም፣ እዛም ሚስት)፣ ሰፊ ተጠቃሚነት (እዛም፣ እዛም ኮንደሚኒየም)፣ ሰፊ ሃብት (እዛም፣ እዛም መሬት)፣ ሰፊ ስም (እዛም፣ እዛም ትንቢት)፣ ሰፊ የገቢ ምንጭ (እዛም ገንዘብ፣ እዛም ገንዘብ)፣ ሰፊ ዝና (ሁልጊዜ እኔ፣ ሁልጊዜም እኔ)፣ ወዘተ። በዚህ አባዜ የተጠመዱ መጽሐፉ እንዳለው እጅግ በዝተዋል።

ዛሬ ዛሬ ከፀሎት ቤት ጠጅ ቤት ይሰፋል። ለፀሎት ከሚሰበሰቡ ሰዎች ይልቅ ለጠጅ የሚሰበሰቡ ይበዛሉ። ዛሬ ዛሬ ከወንጌል ስርጭት ወሬ ስርጭት ይሰፋል። ለወንጌል ስርጭት ከሚሰበሰቡ ሰዎች ይልቅ ለወሬ ስርጭት የሚሰበሰቡ ይበዛሉ። ከመልሚያው መጥፊያው ይሰፋል። ግዴላችሁም ጠበብ እንበል፣ የሚያዋጣው እሱ ነው። ዝም አትበሉ፣ እስኪ እንነጋገርበት።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART FIVE
ተገዥና ገዥ.......!

"እኔ ደግሞ ለሌሎች ተገዥ ነኝና፥ ከእኔም በታች ጭፍራ አለኝ፤ አንዱንም ሂድ ብለው ይሄዳል፥ ሌላውንም ና ብለው ይመጣል፥ ባሪያዬንም ይህን አድርግ ብለው ያደርጋል አለው" (ማቴ 8:9)

ከዚህ በላይ ያለው ንግግር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ያስደነቀ የአንድ መቶ አለቃ ንግግር ነው። ሰውየው ለሌሎች መገዛትን ያውቃል፣ ራሱ መግዛትንም ያውቃል። አንድ በታ ገዥ ነው፥ ሌላ በታ ተገዥ። ኢየሱስ የተደነቀበትም ስለዚህ ነው። እርሱ ራሱ መጽሐፍ እንደሚል "ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል።" ይላል (1ቆሮ 15:28)

በዚህ ዘመን የቸገረን ሁሉ መግዛት ፈለገ። ማንም መገዛት አይፈልግም። ከቃሉ ርቀናል። ይሄ ትልቅ ህመም ነው። ታምመናል። ፈውስ ያስፈልገናል። አይመስላችሁም? ዝም አትበሉ እንጂ። በእግዚአብሔር ቃል እንነጋገር፣ እንፈወስ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART SIX
አቁማዳው ፈነዳ፣ የወይን ጠጁም ፈሰሰ፣
አቁማዳውም ጠፋ.....! (ማቴ 9:17)

በደረስንበት በዚህ ዘመን እየሆነብን ያለው እንዲህ ነው። “በአረጀ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ” ፣ ባልተቀየረና በድሮ ማንነት አገልጋይነት፣ ዶክተርነት፣ ሊህቅነት፣ ተንታኝነት፣ ወዘተ። አብዛኛው ራሱ አልተቀየረም፣ “ተረዳሁት” ያለውን ጉዳይ በማስተላለፍ ተከታይ ለማግኘት ይጥራል። ትርፍ የለውም። ቃሉ “ባለ መድኃኒት ሆይ፥ ራስህን ፈውስ” ይላል። (ሉቃ 4:23)። የራስ ፈውስ ይቀድማል።

“አቁማዳው ይፈነዳል፥የወይን ጠጁም ይፈሳል አቁማዳውም ይጠፋል” ሁለቱንም እያጣን ነው። አብዛኞቹ እየፈነዱ፣ በውስጣቸው ያለው አቅም እንደ ቀድሞው አባይ ያለቦታው በከንቱ እየፈሰሰ፣ ትውልዳቸውን በጽድቅ ሳያገለግሉ፣ እያየናቸው ጠፉብን።

“አዲሱን የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ያኖረዋል፥ ሁለቱም ይጠባበቃሉ።” ነበር ነገሩ። እኛ አገር ወይን ጠጅና አቁማዳ ሁለቱም እንዳይጠባበቁ ነው የሆኑት። ጌታ ይርዳን። በብርቱ መፀለይ አለብን። ተጎድተናል፣ ይበቃናል! አይመስላችሁም?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART SEVEN
አይበልጥም.....!

“እኔና አብ አንድ ነን።” ያለ ጌታ (ዮሐ 10:30) ስለ አባቱ ፈቃድ መፈፀም ሲል ከአባቱ ጋር መተካከልን እንደመቀማት ሳይቆጥር (ፊሊጵ 2:6) “ከእኔ አብ ይበልጣልና” ይለናል። (ዮሐ14:28)

ሕይወት በልጦ መገኘት ብቻ አይደለም ማለት ነው። ለመበለጥም ፈቃደኛ መሆን ከስም ሁሉ በላይ የሆነ ስም ለማግኘት ቁርጠኝነት የሚጠይቅ መንገድ ነው። ችግሩ ሁሉም ከሁሉ በላይ በልጦ መገኘት ፈለገ። ብንፈልግም ባንፈልግም የማንበልጣቸው አሉ። ምንም አይነት ስትራቴጂ ዘርግቶ ማንም መምህሩን አይበልጥም።እጅግ የተንጠራራና ለየት ያለ መገለጥ አመጣሁ ላለ፥ ድንበር ተበጅቶለታል፡- ‘እንደ መምህሩ መሆን ይበቃዋል።’

“ደቀ መዝሙር ከመምህሩ፥ ባሪያም ከጌታው አይበልጥም። ደቀ መዝሙር እንደ መምህሩ፥ ባሪያም እንደ ጌታው መሆኑ ይበቃዋል። “ (ማቴ 10:25-24)

“አይበልጥም” የሚለው ቃል ለብዙዎች አይመችም። ቃሉን የተናገረው ግን ጌታ ኢየሱስ ነው። Am sorry.

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART EIGHT
ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ......!

ሰው ያልተሰጠውን (ጥሪው ያልሆነን) ነገር መስራት ሲጀምር ብዙም ሳይቆይ ሸክም ይሆንበታል።ያልተሰጠንን ጉዳይ ሆኖ ለመገኘት መውተርተር ትርፉ ሸክም ነው።

በዚህ ዘመን ሸክም በዝቷል። ተጠቃሚ ለመሆን የሚደረግ ሩጫ ሸክም፣ ታዋቂ ለመሆን የሚደረግ ሩጫ ሸክም፣ ከአንድ በላይ የመጥበስ ብሎም የማግባት ሸክም፣ ባልተቀቡበት ጥሪ የማገልገል ሸክም፣ 'የእኔን ብቻ ተቀበሉ' ሸክም፣ የሆነ ቦታ/አገር ተደብቆ ማህበረሰቡን የማዋጋት ሸክም፣ ችሎታ እንዳለው ሰው የማከት (act) ሸክም፣ በፎርጅድ ሰነድ የመኖር ሸክም፣ የስልጣን ጥማት ሸክም ብሎም 'አንዴ ወንበሩ ላይ ከወጣሁ' የአታውርዱኝ ሸክም፣ የፉክክር እና የመናናቅ ሸክም፣ ወዘተ። ብቻ ማንም ሰው ስለ ራሱ የጽድቅ እርግጠኝነት ላይ ካልደረሰ ባይታወቅበትም ስጋት በውስጡ አለ። ስጋት ትልቅ ሸክም ነው።

ጌታ ሲናገር "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ" (ማቴ11:28)። ከዚህ በኋላ ለማረፍ የሚፈልግ፥ የእርሱን ፊት ይፈልግ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በነጻ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART NINE
እርስ በርሱ የሚለያይ ...አይቆምም!

መጽሐፍ “ድልም ብዙ ምክር ባለበት ዘንድ ነው።” ይላል (ምሳሌ 24:6)። የወቅቱ ድላችን መለያየት ሆኖአል። ከሰው ማን ነው የመከረን? ምንስ ተመክረን ነው?

በትዳር መለያየት፣ በብሔር መለያየት፣ በባንክ መለያየት፣ ባልተረጋገጠ መረጃ (ወሬ) መለያየት፣ በሚድያ ዲስኩር መለያየት፣ በፖለቲካ ፖትላኪዎች መለያየት፣ ወዘተ።

ኢየሱስ ሲናገር “እርስ በርስዋ የምትለያይ መንግሥት ሁላ ትጠፋለች፥ እርስ በርሱ የሚለያይ ከተማም ሁሉ ወይም ቤት አይቆምም” አለ (ማቴ 12:25)። ቃሉ እንደሚለው የቆመ ነገር ናፈቀን:- የቆመ መንግስት፣ የቆመ ከተማ፣ የቆመ ቤት።

ወገኖቼ የሰው ምክርና ቅስቀሳ በቃን፤ ትርፉ መለያየት ነው። ወደ እግዚአብሔር እንመለስ “ከሰው ልጆች ይልቅ በምክር ግሩም ነው።” (መዝ66:5)።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART TEN
በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል......!

ንግግር እና ተናጋሪ በዝቷል። ፖለቲካ እና የፖለቲካ ተንታኝም እንዲሁ። ትርክት እና ተራኪ ቁጥሩ አየጨመረ ነው። አባባል እና ባይም እንዲሁ። ትንቢት እና ተንባይ በዝቷል። አስተንባይ የትዬለሌ ስለሆነ አናንሳው። ተቃውሞ እና ተቃዋሚ በዝቷል ሳይሆን፥ ሳይሆኑ መገኘት እንደ ወንጀል ሊቆጠር ምንም አልቀረ።

ንግግር፣ ትንታኔ፣ ትርክት፣ አባባል፣ ትንቢት፣ ተቃውሞ፣ ወዘተ መፈፀሙ ሳይሆን ችግሩ ተመርምሮ ከንቱ ሆኖ ሲገኝ ዛሬ ባንጠየቅበትም ለፍርድ ቀን ተቀጥሯል። ጌታ ኢየሱስ ይህን ሲያረጋግጥ "እላችኋለሁ፥ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል" ይላል (ማቴ 12:36)።

ታዲያ መፍትሔው ምንድን ነው? መፍትሔውማ፡-
"ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር።" ነው። (1ጴጥ4:11)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 11
ከዮናስ፣ ከሰሎሞን፣ የሚበልጥ .......አለ!

ማን ነው ዮናስ? የታላቂቱ ነነዌ ከተማ ሰዎችን በስብከቱ ኃይል ንሰሃ ያስገባ። ማን ነው ሰሎሞን? ሰዎች ጥበቡን ለመስማት ከምድር ዳር እጅ መንሻ ይዘውለት የሚመጡ። መጽሐፍ ከዮናስም ሆነ ከሰሎሞን የሚበልጥ አለ ይላል። (ማቴ12:41-42)

ዛሬ በእኛም ዘመን እንደ ዮናስ እና ሰሎሞን የሆነ ነገር ሰርቶ ዝነኛ ወይም ታዋቂ የሆነ ማን ነው? ማን ነው እንትና? ማን ናት እንትናስ? እነማን ናቸው እነንትና?

ዮናስ እና ሰለሞን የትላንት፣ እንትና እና እነእንትና ደግሞ የዛሬ፣ ስፍራውን የያዙ ሰዎች ናቸው፣ ከምድር ናቸው። የሰዉ ሁሉ ነፍስ የተጠማው ግን የሚበልጠውን ነው።

መጽሐፍ “ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው፤ ከምድር የሚሆነው የምድር ነው የምድሩንም ይናገራል። ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው።”ይለናል ኢየሱስን። (ዮሐ 3:31)

እውነቱ ይህ ከሆነ፡- በምንም ጉዳይ ዙሪያ ያጠነጠነ እና ለመታወቅ የሚደረግ ምንም ዓይነት ምድራዊ ቅስቀሳ (propaganda) ይበቃናል። አይመስላችሁም?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 12
ወንድሜ ማን ነው? እኅቴ ማን ናት? እናቴስ?

ጌታ ኢየሱስ አንድ ቀን የጠየቀው ጥያቄ ነበር (ማቴ12:48) በወቅቱ አንድ ሰው “እናትህና ወንድሞችህ ሊነጋገሩህ ፈልገው በውጭ ቆመዋል” ብሎት ነበር። ብቅ ብሎ ያነጋግራቸዋል ተብሎ ሲጠበቅ ከነአካቴው “እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው? ብሎ እርፍ አለ (ማቴ12:48)።

ዛሬም እኮ ቤተሰብ የሚሆን ጠፋ። ወንድም የሚሆን፣ እኅት የምትሆን፣ እናት የምትሆን አጣን። ቤተሰብ ይሆኑናል ብለን ያሰብናቸውን ጥቅም ነጠቀን፣ ፖለቲካው ዘረፈን፣ ዝና ቀየረብን፣ የተፈጠረ ትርክት ወሰደብን። የእኛስ እውነተኛ ወንድም፣ እውነተኛ እህት እንዲሁም እናት እነማን ናቸው?

ጌታ ኢየሱስ ሲመልስ “በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፥ እርሱ ወንድሜ እኅቴም እናቴም ነውና አለ (ማቴ 12:50)። ከዚህ ውጪ የሆነ፣ የገዛ ፍላጎትና ፈቃዱን የሚያራምድ እኔም በቃኝ፣ አልፈልግም። እናንተስ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 13
ጽሁፍ (Article) 13
እንክርዳዱ ከወዴት መጣ?

ጌታ ኢየሱስ ምሳሌውን ሲመስል "የባለቤቱም ባሮች ቀርበው። ጌታ ሆይ፥ መልካምን ዘር በእርሻህ ዘርተህ አልነበርህምን? እንክርዳዱንስ ከወዴት አገኘ" አሉት ይላል (ማቴ 13:27)።

አነሳሳችን(አጀማመራችን) እንደ ዘር መልካም ነበር። መጽሐፍ ቀጥሎ "ስንዴው በበቀለና በአፈራ ጊዜ እንክርዳዱ ደግሞ ያን ጊዜ ታየ" እንዳለ ልንክደው የማንችለው የባህሪ ለወጥ ታይቶብናል። መጽሐፍ "ወርቁ እንዴት ደበሰ! ጥሩው ወርቅ እንዴት ተለወጠ!" (ሰቆ.ኤር4:1) እንደሚል ሳናውቀው በሆነ ነገር ተለውጠናል። ምክንያቱ ምንድን ነው?

ኢየሱስ ምሥጢሩን ሲገልጥ"ሰዎቹ ሲተኙ ግን ጠላት መጣና በስንዴው መካከል እንክርዳድ ዘርቶ ሄደ"አለ (ማቴ13:25)።

የምንለያይ አልነበርንም። ተኝተን ገንዘብ ተዘራ፣ ፖለቲካ ተዘራ፣ ወሬ ተዘራ፣ ጥቅም ተወራ፣ ትርክት ተዘራ። አጨዳ ሳይጀመር ንስሐ እንግባ፣ ምህረት እንጠይቅ እናድርግም!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 14
ሁሉም በልተው ጠገቡ..........!

“በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው። በታው ምድረ በዳ ነው አሁንም ሰዓቱ አልፎአል፤ ወደ መንደሮች ሄደው ለራሳቸው ምግብ እንዲገዙ ሕዝቡን አሰናብት አሉት።” (ማቴ14:15)

ሲመሽ (ራት ተበልቶ በሚታረፍበት ሰዓት) የሚያሰናብቱ ደቀ መዛሙርት ምን ዓይነት ደቀ መዛሙርት ናቸው? እንዲህ ያለ ስብዕናና አመለካከት ምን ይሉታል? ሰው ሲመሽበት፣ ሰው ሲጨልምበት፣ ሰው መሔጃ ሲያጣ አይሰናበትም።

ኢየሱስ “ሊሔዱ አያስፈልግም” ብሎ ያለውን አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረከ፥ ቆርሶም ሰጠ፥ ሁሉም በልተው ጠገቡ፥ የተረፈውንም አሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ አነሡ። (ማቴ14:16-20)

እኔም እላችኋለሁ አንዳችን አንዳችንን “መሸ” ብለን ማሰናበቱ ይብቃ። ያለውን ይዘን አሻቅበን እያየን እንባርክ፤ ይበቃናል፣ ያጠግበናል፣ ይተርፈናል። አይመስላችሁም?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 15
ጽሁፍ (Article) 15
የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት.......!

ጌታ ኢየሱስ የኢሳይያስን ትንቢት ጠቅሶ ሲናገር “ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፥ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው” አለ (ማቴ 15:8)።

ከከንፈር ያልዘለለ መከባበር ባህል ሆኖአል። ከልብ ባይሆንም (ባናምንበትም) ዶ/ር...፣ ፕ/ር...፣ ሐዋርያ...፣ ነቢይ...፣ አርቲስት...፣ አክቲቪስት... የተከበሩ...፣ ወዘተ ስንባባል እንውላለን።እንዲህ ያለ ከንቱ አምልኮ ከየት መጣ?

ጌታ ጉዳዩን ሲገልጠው “የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ” ይላል (ማቴ 15:9)። ለካስ ችግሩ ትምህርቱና ልምምዱ ነው። ሥርዓት ብቻ (commandments of men)፣ የተኖረ የሕይወት ተካፍሎት የሌለው?

ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ “እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው” እንዳለ ትምህርታችን ከተለመደው የሰው ሥርዓት ወደ መንፈስ እና ሕይወት በፍጥነት ይሻገር እላለሁ (ዮሐ 6:63)። አለዚያ አሁንም በሩቅ ልብ የከንፈር ጨዋታው ይቀጥላል። ጌታ ሁላችንንም ራርቶ ያድነን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 16
ጽሁፍ (Article) 16
እኔን መከተል የሚወድ..........!

ጌታ ኢየሱስ “እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ” ይላል (ማቴ16:24)። ‘ራስን መካድ’ ማለት ደግሞ ምን ማለት እንደሆነ መጽሐፍ በማያሻማ ቋንቋ “ሁሉን ትተን” ሲል ያስቀምጣል። (ማቴ 19:27)

ያልተውናቸው እና ያልተዉን ነገሮች ያሉ አይመስላችሁም? እሱን መከተል እየፈለግን ግን.................።

ሐዋርያው ጳውሎስ “የማደርገውን አላውቅምና፤የምጠላውን ያን አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም” ይላል። (ሮሜ 7:15)

እንደ ሐዋርያቱ እውነተኛ የእርሱ ተከታይ ለመሆን እንተወው፤ ምኑን? ያ አልለቅ ያለንን።ስለዚህ ፊቱን እንፈልግ (እንፀልይ)፣ በእርግጥ ጌታ ስለሚወደን ፈጥኖ ይረዳናል።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 17
ጽሁፍ (Article) 17
ማንን እንስማ? ..........!

በዚህ የመጨረሻ ዘመን በእያንዳንዷ ክፍልፋይ ሴኮንድ (fraction of second) የሚለቀቅ ድምጽ አለ። የቃላት፣ የምስል፣ የምልክት፣ የማይ፣ የዝምታ...። ሁሉም መልዕክት ነው። እየመረጥን ባይሆን ሰው አይተርፍም።

ሁሉ መልዕክት አለኝ፣ መረጃ አለኝ፣ እንደ ወረደ ልንገራችሁ ባይ ተበራክቷል። “ሰበር” የሆነ ድምጽና መልዕክት በዝቷል።

ታዲያ ማንን እንስማ?

እግዚአብሔር መልሱን በአጭሩ ሲሰጥ “በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት” አለ (ማቴ17:5)። ከዚህ በኋላ ድምጽ አለን የምትሉ ከእርሱ ድምጽ ውጪ ሌላ ድምጽ አታሰሙን፣ በራሳችሁ ድምጽ አታድክሙን።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 18
ጽሁፍ (Article) 18
ከጸሎትና ከጦም በቀር አይወጣም ..........!

በዕለት ከዕለት ሕይወታችን አያሌ ችግሮች እና ተግዳሮቶች ይገጥሙናል። ለመከላከል፣ ለመቋቋም፣ ለመቀነስ ብሎም ለማጥፋት የተለያዩ ስትራቴጂዎችን እንጠቀማለን። ሆኖም አንዳንዶቹ አሁንም አልለቀቁንም፣ ከጀርባ የሚሠራው ጋኔን አልወጣም።

ደቀ መዛሙርቱ እኛ እንደገጠመን ገጥሟቸው ሰው ሳይሰማ "ብቻቸውን ወደ ኢየሱስ ቀረቡና። እኛ ልናወጣው ያልቻልን ስለ ምን ነው? አሉት።" ይላል (ማቴ17:19)።

ጌታም ምስጢሩን ሲነግራቸው "ይህ ዓይነት ግን ከጸሎትና ከጦም በቀር አይወጣም አላቸው"(ማቴ 17:21)።

ስለዚህ ወገኖች በግልም ሆነ በአገር ደረጃ ከገባንበት ማጥ ለመውጣት ሌላውን ሆያ ሆዬ ትተን እንፀልይ፡እንጡም፡በቃ!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 19
ጽሁፍ (Article) 19
መምህራችሁ ሁለቱን ዲናር አይገብርምን?

ከላይ በርዕሱ የተመለከተው ጥያቄ ከግብር ሰብሳቢዎች ለሐዋርያው ጴጥሮስ የቀረበ ነበር። (ማቴ17:24)

ይህን ተከትሎ ኢየሱስ ስምዖንን “የምድር ነገሥታት ቀረጥና ግብር ከማን ይቀበላሉ? ከልጆቻቸውን ወይስ ከእንግዶች?” ሲለው ጴጥሮስም “ከእንግዶች” ሲል ፣ ኢየሱስ “እንኪያስ ልጆቻቸው ነጻ ናቸው።” አለ። (ማቴ 17:25-26)

ኢየሱስ ቀጠለና “እንዳናሰናክላቸው፥ ወደ ባሕር ሂድና ..ዓሣ ውሰድና አፉን ስትከፍት እስታቴር ታገኛለህ፤ ያን ወስደህ ስለ እኔና ስለ አንተ ስጣቸው አለው።” (ማቴ17:27)

በእኛም ዘመን የመሰናከላችን (ያለመባረካችን) ምክንያት የመሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው ከግብር እና አሥራት ነፃ መሆን ይሆንን? ጌታ ሆይ እንዲከፍሉ እርዳቸው!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 20
መልዕክት (message) 20
የፍች ጽሕፈት...............!

ፈሪሳውያን "ሰው በሆነው ምክንያት ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን?" ጌታ ኢየሱስን ጠየቁት። (ማቴ 19:3) ቀጥለውም "እንኪያስ ሙሴ የፍችዋን ጽሕፈት ሰጥተው እንዲፈቱአት ስለ ምን አዘዘ? አሉት።" (ማቴ19:7)

እርሱም "ስለ ልባችሁ ጥንካሬ።" ብሎ መለሰ። (ማቴ 19:8) ከሙሴ ዘመን ይልቅ የልብ ጥንካሬ አሁን አልባሰም? ልሸነፍ የሚል ጠፋ። ሁሉ አሸናፊ፣ ሁሉ የበላይ፣ ሁሉ ገዢ፣ ሁሉ... መሆን ፈለገ። ስለዚህም አንድ የነበርነው፣ የተጎራበትነው፣ የተዋለድነው፣ አብረን የሠራነው፣ አብረን ያገለገልነው፣ በፍቺ ወረቀት ተንበሻበሽን።

ኢየሱስ "ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም" አለ (ማቴ19:8)። እውነት ነው በፊት፣ ያኔ፣ ስንጀምር፣ ...እንዲህ አልነበርንም። እግዚአብሔር "በመመለስና በማረፍ ትድናላችሁ" ይላል። (ኢሳ 30:15)። እኛ ሳንመለስ ሌላውን ለመመለስ የሚደረግ አገልግሎት ግብዝነት ነው።

"ራሳቸው የጥፋት ባሪያዎች ሆነው። አርነት ትወጣላችሁ እያሉ ተስፋ ይሰጡአቸዋል፤ ሰው ለተሸነፈበት ለእርሱ ተገዝቶ ባሪያ ነውና"(2 ጴጥ2:19)ንስሐ እንግባ፣ እንመለስ!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 21
መልዕክት (message) 21
ሁሉን ትተን ተከተልንህ................!


በዓለም አቀፍ ደረጃ የብዙ አገልግሎት እና አገልጋዬች ሥራ አጀማመር መልካም ነው። ስለ ስሙ ቤቶችን፣ ወንድሞችን፣ እኅቶችን፣ አባትን፣ እናትን፣ ሚስትን፣ ልጆችን፣ እርሻን፣ ወዘተ በመተውና ጌታን ብቻ በመከተል ይጀመራል። (ማቴ19:29)

እየቆየ ሲሄድ ሳናውቀው ስለስሙ ብለን የተውናቸው ነገሮች መልካቸውን ቀይረው አሁንም አስከትለውናል። ገንዘብ፣ ዝና፣ ቤት፣ መሬት፣ ንብረት፣ ጎሰኝነት፣ ገዥነት፣ ወዘተ። እኛ ጌታን እየተከተልን መስሎናል፥ ከርሱ ግን፥ተራርቀናል። የቀደመውን ፍቅር ተዘናግተን ትተናል። (ራእይ 2:4)። ንስሐ ያስፈልገናል።

ወገኖቼ እንደቀድሟችን፣ ልክ እንደ ሐዋርያቱ ሁሉን ትተን ጌታን እንከተል፤ ውጤቱን መጽሐፍ ሲነግረን "በምድር መቶ እጥፍ በሰማይ የዘላለም ሕይወት" ይለናል። (ማቴ19:29)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




**Aynalem Mersie**

PART 22
መልዕክት (message) 22
እነማን ናቸው የተመረጡ (ምርጦች)?

ጌታ ኢየሱስ “የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸው” ይለናል(ማቴ 20:16)፤ጥያቄው እነማን ናቸው ታዲያ የተመረጡ? እነማን ናቸው ምርጦች?


እግዚአብሔር ከመመረጥ ጋር ተያይዞ በግልጥ “ምርጤ” “ምርጦች” ብሎ የመሠከረላቸው አሉ።

አንደኛው “ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ምርጤ” ብሎ ባህሪውን ሲዘረዝር”አይጮኽም፣ቃሉንም አያነሣም፣ድምፁንም በሜዳ
አያሰማም፣ የተቀጠቀጠም ሸምበቆ አይሰብርም፣ የሚጤስ ክር አያጠፋም፤” ብሎታል (ኢሳ 42:1-3)። ስለዚህ እየጮኹ ፣ ቃል እየሰነጠቁ፣ ድምፅ እየፈጠሩ፣ እየሰበሩ እና እያጠፉ ምርጥ መሆን አይቻልም።

ሁለተኞቹ “ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ የሚጮኹ ምርጦቹ”ይላል (ሉቃ18:7)። እነዚህ ቀንም ሆነ ሌሊት ዋና ሥራቸው ፀሎት (ምልጃ) ነው። አሁን ከመካከላችን ምርጥ/የተመረጠ ማን እንደሆነ ግልጽ መሰለኝ። እርሱ አድሎ አያውቅም፤ ይባረክ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




**Aynalem Mersie**

PART 23
መልዕክት (message) 23
ምሕረት ይቀድማል...........!

“ሁለት ዕውሮች በመንገድ ዳር ...ኢየሱስ እንዲያልፍ በሰሙ ጊዜ፥ ጌታ ሆይ፥ የዳዊት ልጅ፥ ማረን ብለው ጮኹ።ሕዝቡም ዝም እንዲሉ ገሠጹአቸው፤እነርሱ ግን ጌታ ሆይ፥የዳዊት ልጅ ማረን' እያሉ አብዝተው ጮኹ።” (ማቴ 20:30-31)

የሚገርመው ሰዎቹ እውሮች ሆነው ምህረት መጠየቃቸው ነው። የዓይን ጥያቄ መቅደም አልነበረበትም ትላላችሁ? እኔ እንደዛ ነበር የሚመስለኝ።

መጽሐፍ”ምሕረትህ
ከሕይወት ይሻላልና”ይላል(መዝ63:3)።

ዛሬ ሰው ሁሉ አጣሁ፣ጎደለኝ፣ ይሄ የለኝም፣ይሄ ያስፈልገኛል፣ ይሄ የኔ ቢሆን፣ እንዲህ ብሆን፣ ያን ባገኝ፣ ወዘተ ሲፈልግ እና ሲመኝ ይውላል፤የሚቀድመውን አላወቀም።መጽሐፍ ሲናገር “በእናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ....በብርቱም ትፈልጋላችሁ፥ ልታገኙም አትችሉም፤” ይላል። (ያዕ4:1-2)

እንግዲህ እኛ ዓይን ያለን፣ “እያየን ነው” የምንል ከእውሮቹ እንማር። ከአቅም በላይ በሆነና በማያራምድ፣ በብዙ ችግር ውስጥ ነን።ችግሩ ራሱ አሳውሮናል፤ ቅድሚያ እሚያስፈልገን ምሕረት ነው። ምሕረት ይቀድማል። አይመስላችሁም?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 24
መልዕክት (message) 24
ሁለት አገር የለም..............!

ሐዋርያው ጳውሎስ “ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶቹ ሆነው ይመላለሳሉና፤ ...አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላለሁ።.. አሳባቸው ምድራዊ ነው፤ እኛ አገራችን በሰማይ ነው” አለ። (ፊልጵ 3:18-20)

ሁለት አገር የለም። ሁለት መንግስት የለም። ሁለት ዜግነትም የለም።እንደክርስትያን የትውልድ አገርን አለማወቅ የመስቀሉ ጠላት መሆን ነው። አገራችን በሰማይ ከሆነ አሁን መጽሐፍ እንደሚል “በስደት” ነን። (2ቆሮ 5:6-7)

ስለዚህ ወገኖቼ በምድራዊ አስተሳሰብ፥ ምድር ላይ፡ አገሬ፣ ወገኔ፣ ዘሬ፣ ቅርሴ ወዘተ ስንል የተገኘንበት የእግዚአብሔር መንግሥት ከእጃችን እንዳይወሰድ። መጽሐፍም ሲያስረዳን “የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ ትወሰዳለች ፍሬዋንም ለሚያደርግ ሕዝብ ትሰጣለች” ይላል።(ማቴ21:43)። ምድር ትብቃን፤ አታልላ አገራችንን (ሰማይ) ልታሶስድብን ነው፤ ንቁ!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 25
መልዕክት (message) 25
በሰው ትከሻ አንጫን..............!

ቁጥራቸው ብዙ ያልሆነ ጥቂት ሰዎች በብዙ አገርና ተቋም ውስጥ አሉ። የሆነ ቦታ (ስፍራ) ሆነው ይቀሰቅሳሉ፣ እሆነ አገር ተቀምጠው ሕዝብ ያነሳሳሉ፣ ትዕዛዝ ይሰጣሉ፣ ከባድ እና አስቸጋሪ፥ ሸክም የሆነ ተልዕኮ ይጫናሉ። የሚገርመው ግን ጉዳዩን እነርሱ ራሳቸው በጣታቸው ሊነኩት አይወዱም፤ እንዲህ ያሉትን ሰዎችም ሆነ መሠል ሃሳብ የሚያራምዱትን መጽሐፍ ሲጠራቸው፡- “ጻፎችና ፈሪሳውያን” ይላቸዋል።

ዝርዝር ቃሉ ከተፈለገ

“ጻፎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል። ስለዚህ ያዘዙአችሁን ሁሉ አድርጉ ጠብቁትም፥ ነገር ግን እየተናገሩ አያደርጉትምና እንደ ሥራቸው አታድርጉ። ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጫናሉ፥ እነርሱ ግን በጣታቸው ስንኳ ሊነኩት አይወዱም።” (ማቴ23:2-4)

ስለዚህ ማንም የትም ሆኖ፣ በምንም ሁኔታ እርሱ በጣቱ ሊነካው የማይወደውን በሰው ትከሻ አይጫን። መጽሐፍ “ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም።” ይላል (ማቴ5:20)።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 26
መልዕክት (message) 26
ፍቅር ለምን ቀዘቀዘ?

“ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል....፤ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም።” (1ቆሮ 13:4-8)


ፍቅር ይህ ከሆነ ባህሪው፥ መጽሐፍ “...የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች”ስለሚል (ማቴ24:12)፥በብዙ ሰው ዘንድ ፍቅር ለምን ቀዘቀዘ? ምንድን ነው ምክንያቱ?

መጽሐፍ ምክንያቱን ሲጠቁም “ከዓመፃ ብዛት የተነሣ”ይላል (ማቴ24:12)። “ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ ዓመፅን ደግሞ ያደርጋል፥ ኃጢአትም ዓመፅ ነው።” (1ዮሐ 3:4)።

ከምንም ወይም ከማንም ጋር ተያይዞ እቀዘቀዘ ፍቅር ውስጥ ካለን፥ አመፅ ውስጥ ነን። ዛሬ ነገ ሳንል ንሰሐ እንግባ፤ ይቅር ይለን ዘንድ ምህረት እንጠይቅ፥ እርሱም ይምረናል!!!

መልዕክቱን መሞገት፤ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




**Aynalem Mersie**

PART 27
መልዕክት (message) 27
ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ..........!

ማንንም ለማጥፋት የምናነሳው መሳሪያ የነገ መጥፊያችን ነው። ጌታ ኢየሱስ ይህን ሲያረጋግጥ “ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉ” ይላል (ማቴ 26:52)።


ንጉስ አዶኒቤዜቅም ለዚህ ማሳያ ጥሩ ምሳሌ ነው “ሸሸ፥ አሳድደውም ያዙት፥የእጁንና የእግሩንም አውራ ጣት ቈረጡ፤ አዶኒቤዜቅም፥የእጅና እግራቸው አውራ ጣት የተቈረጡ ሰባ ነገሥታት ከገበታዬ በታች ፍርፋሪ ይለቅሙ ነበር፤ እኔ እንዳደረግሁ እግዚአብሔር እንዲሁ መለሰልኝ አለ።”
(መሳ 1:6-7)።

ስለዚህ ከዚህ በኋላ ከጥፋት ለማምለጥ ምን እናድርግ?

ጌታ ኢየሱስ መፍትሔውን ሲያስቀምጥ “ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ።” ይላል (ማቴ 26:52)። እኔም ለአንድ ሰው እላለሁ፥ በምንም ጉዳይ ላይ ልታነሳ ያሰብከውን ሰይፍ ጌታ እንዳለ አባክህ “ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ”።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




**Aynalem Mersie**

PART 28
መልዕክት (message) 28
ዶሮ ይጬኽ.....................!

ክህደት በዝቷል። መካካድ ባህል እየሆነ መጥቷል። ትላንት አብረው የኖሩ፣ አብረው የሠሩ፣ አብረው ያገለገሉ፣ አብረው የመከሩና አብረው ብዙ ያሳለፉ፥ ያ ሁሉ ቀርቶ እና ተረስቶ እንደማይተዋወቅ እና ምንም ዓይነት የጋራ ታሪክ እንደሌለው አካል፥ መደምደሚያው ክህደት ሆኗል።

ለእንዲህ ዓይነቱ ተግባር ስምዖን ጴጥሮስ ጥሩ ምሳሌ ነው። አብሮት የኖረውን ጌታ ሦስት ጊዜ "የምትዪውን አላውቀውም ብሎ በሁሉ ፊት ካደ። ዳግመኛም ሲምል፥ ሰውየውን አላውቀውም ብሎ ካደ። ሰውየውን አላውቀውም ብሎ ሊራገምና ሊምል ጀመረ"ይላል መጽሐፍ (ማቴ 26:70-74)

ጴጥሮስን ለንሰሐ ያነቃው ዶሮ ጬኾ ነው። ለእኛ፣ ተካክደን ለተራራቅነው፣እያማረን መቀራረብ ላልቻልነው፣ ዶሮ ይጬኽ!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




PART 29
መልዕክት (message) 29
እንደ ተናገረ ተነሥቶአል......!

ዓለም ከተፈጠረ እና ከመጀመሪያው ሰው (አዳም) ጀምሮ እስከ አሁን ‘ሞተ’ የተባለ ሁሉ እተኛበት ስፍራ ቀርቷል። ሁሉ፥ ሞቱ ሲቃረብ ተናገረም አልተናገረ፥ አሳቡ ወይንም ወሬው ከ “አሟሟቴን አሳምርልኝ” አይዘልም። የበረታ “እዚህ ወይንም እዚያ ቅበሩኝ” ማለት የተለመደ ነው።

ከሰው ልጆች መካከል አንዱ የተለየ ሆነ። በሕይወት እያለ ራሱ ስለራሱ አስቀድሞ ተናገረ “የሰው ልጅ በሰዎች እጅ አልፎ ይሰጥ ዘንድ አለው፥ ይገድሉትማል፥ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል።” (ማቴ 17:22-23)

ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ፥ ሁሉ እንደተናገሩት፣ እንደተናዘዙት፥ ሞተዋል፣ ቅበሩኝ ባሉት ስፍራ ተቀብረዋል። እርሱ መጽሐፍ እንደሚል“እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚያ የለም፤ የተኛበትን ስፍራ ሂዱና እዩ።” (ማቴ 28:6)

ኢየሱስ፤ ይሄ ነው የኔ ጌታ “ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለም።” (ሐዋ2:24)፣ ሞት እንዳይዘኝ ሞት ያልያዘውን እከተለዋለሁ። እናንተስ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 30
መልዕክት (message) 30
ላቅ ያለ ነገር ያላቸው አሉ....!


እውነት ነው፥ ክፉም ይሁን ደግ በተናጥልም ሆነ በቡድን እኛ የሠራነው ነገር አለ። ክፉው ለማንም ስለማይጠቅም እርሡን እንተወው። እስከሚገባኝ፥ ይህን መልዕክት ለማንበብ እድል ያገኘ ሁሉ ላረጋግጥለት የምወደው "ባይወራም የሠራኸው/የሠራሽው መልካም ሥራ አለ"። ጥሩ ነው።

ማንም ምንም ዓይነት የላቀ ሥራ ቢሠራም፥ሌሎች ከዚያ ላቅ ያለ ነገር ያላቸው እንዳሉ ማወቅ እና፥ ማወቅ ብቻ አይደለም እውቅና መስጠት ታላቅነት ነው።መጽሐፍ ይህን ሲያረጋግጥ "ተጎንብሼ የጫማውን ጠፍር መፍታት የማይገባኝ ከእኔ የሚበረታ በኋላዬ ይመጣል። እኔ በውኃ አጠመቅኋችሁ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል" (ማር 1:7-8)።

እውነቱ ይህ ከሆነ፥ ከእንግዲህ"እኔ/እኛ ብቻ"ማለት ይብቃ። ከእኛ የተሻለ ነገር ያላቸው፣እኛ በሠራነው መልካም ሥራ ላይ የተፈጠሩ ልጆች እየመጡ ነው። ጌታ ማስተዋልን ይስጠን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ




**Aynalem Mersie**

PART 31
መልዕክት (message) 31
እንሰልል (scout out).....!

መጽሐፍ ጌታ ኢየሱስ በአንድ ወቅት “በሰንበት ወደ ምኵራብ ገብቶ አስተማረ።” ይላል (ማር 1:21)። አስገራሚው ነገር “እንደ ባለ ሥልጣን ያስተምራቸው ነበር እንጂ፥ እንደ ጻፎች አይደለምና በትምህርቱ ተገረሙ”ደግሞ ይላል፤(ማር1:22)


ጻፎች በመሠረቱ ያስተምራሉ ነገር ግን አያደርጉትም ወይም አይኖሩትም፣ ትምህርታቸው አያስገርምም (ማቴ 23:2-4)።

እንደ በላስልጣን ማስተማር ይቻላል፣ እንደ ጻፎችም ደግሞ ማስተማር ይቻላል። ልዩነቱ ውጤቱ ነው። አንዱ ይለውጣል አንዱ አይለውጥም።

ከተለወጥን(እየተለወጥን) ከሆነ ባለስልጣን የሆነ መምህር አግኝተናል አለዚያ የጻፎች ሰለባ ሆነናል። ያለንበትን ሁኔታ እንሰልል (scout out)!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




**Aynalem Mersie**

PART 32
መልዕክት (message) 32
ከአገራችን በፍፁም አይወጣም!

አንዴ እንዲህ ሆነ። ጌታ ኢየሱስ ከታንኳ በወጣ ጊዜ፥ ርኵስ መንፈስ የያዘው ሰው ከመቃብር ወጥቶ ወዲያው ተገናኘው (ማር 5:2)። ኢየሱስም፥ርኵሳን መናፍስቱ ወጥተው በቅርብ ወዳሉ እሪያዎች እንዲገቡ አዘዘ። ሁለት ሺ የሚያህል መንጋ ከአፋፉ ወደ ባሕር ተጣደፉና በባሕር ሰጠሙ። (ማር 5:13) ኢየሱስ ይህን በማድረጉ መጽሐፍ ሲናገር የአገሬው ሰው "ከአገራቸውም እንዲሄድላቸው ይለምኑት ጀመር።" ይላል። (ማር 5:17)

ከሰው እሪያ የበለጠበት ግብዝ ሕዝብ።

ጌታ ኢየሱስ ከአገራችን በፍፁም አይወጣም። እሪያ የሆነብን ነገር ሁሉ ሕዝባችንን ለቀቆ ይወጣል፣ ይሰጥማል እንጂ።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 33
መልዕክት (message) 33
ባለመድኃኒት በቃን............!

በዚህ በደረስንበት የመጨረሻ ዘመን "መፍትሄ እኔ/እኛ ዘንድ አለ" ባይ መድኃኒተኞች በሁሉ መስክ ተበራክተዋል። በሁሉ መስክ ሲባል፥በሁሉ መስክ ነው። ትርፉ ስቃይና ኪሳራ ነው።


መጽሐፍ ይህን ጉዳይ በተመለከተ "ከአሥራ ሁለት ዓመትም ጀምሮ ደም የሚፈሳት ሴት ነበረች፥ከብዙ ባለ መድኃኒቶችም ብዙ ተሠቃየች፤ገንዘብዋን ሁሉ ከስራ ባሰባት እንጂ ምንም አልተጠቀመችም፤" ይላል። (ማር 5:25-26)

ይቺ ሴት የኢየሱስን ወሬ ሰምታ"ልብሱን ብቻ የዳሰስሁ እንደ ሆነ እድናለሁ"ብላ በሰዎች መካከል መጥታ ልብሱን ዳሰሰች ወዲያውም የደምዋ ምንጭ ደረቀ ከሥቃይዋም እንደዳነች በሰውነትዋ አወቀች። (ማር 5:27-29)

ባለመድኃኒት በቃን። አሁን የሚያስፈልገን ራሱን መድኃኒቱን (ኢየሱስን) ዳስሶ፥ የሚያስዳስሰን ነው። (1ዮሐ 1:1-2)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




**Aynalem Mersie**

PART 34
መልዕክት (message) 34
እመን ብቻ .....................!

አንድ አንድ ዘገባዎች (reports) ሁኔታው ሲፈፀም ስፍራው በነበሩ እማኞች ይቀርባሉ፥ተዓማኒነታቸውም የዛኑ ያህል ከፍ ያለ ነው። መጽሐፍ "ከምኲራብ አለቃው ቤት ዘንድ የመጡት ልጅህ ሞታለች፤ ስለ ምን መምህሩን አሁን ታደክመዋለህ? አሉት።" ይላል፥ ስለዘገባቸው (ማር 5:35)

ኢየሱስ ግን "የተናገሩትን ቃል (ዘገባ) አድምጦ ለምኲራቡ አለቃ።'እመን ብቻ እንጂ አትፍራ' አለው" ይላል(ማር 5:36)። ከዚያም ኢየሱስ ወደ ምኲራብ አለቃው ቤት መጣ፣ የሟችን እጅ ይዞ "ቁሚ" አላት፥ ቆማም ተመላለሰች(ማር 5:38-42)

ምን ዓይነት ዘገባዎች እየተሰሙ ነው? እነማ፥ ምን እያወሩና ምን እያሰራጩ ነው? "ሞተ/አለቀለት"የተባለ ሰው (አገር) አለ? አይዞን!!!

"እመን ብቻ እንጂ አትፍራ" የሚለው፥ የጌታ ኢየሱስ ቃል ዛሬም ሕያው ነው። እንደገና ቆመን እንመላለሳለን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 35
መልዕክት (message) 35
መናገርም ሆነ መስራት አልቻሉም!


“በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል”እንዲሉ፥ብዙ ሰዉ እንግዳ ማህበረሰብ የሚሰጠው እውቅናና ክብር ከወጣበት ማህበረሰብ ይልቃል። ኢየሱስም በዚህ ጉዳይ “ነቢይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ዘመዶቹ ከገዛ ቤቱም በቀር ሳይከበር አይቀርም ” ብሏል (ማር 6:4)። ከዚህ ጋር ተያይዞም “ይህስ ጸራቢው የማርያም ልጅ፣ የያቆብም፣ የዮሳም፣ የይሁዳም፣የስምዖንም ወንድም አይደለምን?እኅቶቹ በዚህ በእኛ ዘንድ አይደሉምን? አሉ፤ ይሰናከሉበትም ነበር።” ይላል (ማር 6:3)

በዚህ ምክንያት “በዚያ በጥቂቶች ድውዮች ላይ እጁን ጭኖ ከመፈወስ በቀር፥ ተአምር ሊያደርግ ምንም አልቻለም”ይላል (ማር 6:5)።

ዛሬም አያሌ የአብራካችን ክፋዩች፥ ብቃት እያላቸው፣ አቅም እያላቸው፥ መናገርም ሆነ መስራት አልቻሉም። ተገቢውን ትኩረት ነፍገናቸዋል፣ ገፍተናቸዋልም። ጌታ “ንስሐ ግቡ” አለ (ማር 1:15)። ሁሉ ስለፈፀመው ንስሐ ሊገባ ጊዜው ነው!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




**Aynalem Mersie**

PART 36
መልዕክት (message) 36
ዝቅ ብሎ ሁሉን የሚያገለግል!

ወገኖቼ እስከ አሁን፣ በመካከላችን መልስ እያለው፣ መልስ ያላገኘ ጥያቄ አለ። "ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው?"

ይሄ ጉዳይ ጌታ ኢየሱስን ገጥሞታል"ወደ ቅፍርናሆም መጣ በቤትም ሆኖ፣ በመንገድ እርስ በርሳችሁ ምን ተነጋገራችሁ? ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ጠየቃቸው። እነርሱ ግን በመንገድ፥ ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን? ተባብለው ነበርና ዝም አሉ።" ይላል (ማር 9:33-34)።

በልጦ ለመገኘት የሚደረገው ጥረት በሁሉ መስክ ተፋፍሟል፤ከሁሉ የሚበልጠውን ግን እስከ አሁን መለየት አልተቻለም።

ጌታ ኢየሱስ መንገዱን ሲጠቁም "ሰው ፊተኛ ሊሆን ቢወድ ከሁሉ በኋላ የሁሉም አገልጋይ ይሁን" ብሏል (ማር9:35)። አሁን የሚያስፈልገን ዝቅ ብሎ ሁሉን የሚያገለግል ነው።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 37
መልዕክት (message) 37
የማይቃወመን እርሱ ከእኛ ጋር ነው!

ጳውሎስ “በአንድም ነገር እንኳ በተቃዋሚዎች አትደንግጡ፥ ይህም ለእነርሱ የጥፋት፥ ለእናንተ ግን የመዳን ምልክት ነው ፥ ይህም ከእግዚአብሔር ነው፤” ይላል (ፊልጵ 1:28)። ሁሉ ድጋፊ አይደለም ማለት ነው። ሕይወት አንፃራዊ ነው። ስለ ስሙ በምታደርጉት ጉዞ ሁሉ ደጋፊ እንዳለ፥ተቃዋሚም አለ።

ጌታ ኢየሱስ “የማይቃወመን እርሱ ከእኛ ጋር ነው” ይላል። (ማር 9:40)። ‘የማይቃወመን’ የሚለውን ሲገልጽ “በስሜ ተአምር ሠርቶ በቶሎ በእኔ ላይ ክፉ መናገር የሚችል ማንም የለም” በማለት (ማር 9:39)።

ስለዚህ ስራዬ ወይም አገልግሎቴ ብለን የያዝነውን ነገር በማ ስም፥ እያደረግነው እንዳለ ቆም ብለን እንመልከት። የእርሱን (የኢየሱስ) ስም እየተጠቀሙ፥በደሙ የገዛቸውን፥ የአብራኩን ክፋዬች መቃወም፣ ማሳደድ እና ስም ማጠልሸት ይበቃል።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 38
መልዕክት (message) 38
ምላስ ይቆረጥ................!

ጌታ ኢየሱስ ሲናገር፥የተወሰኑ የሰውነት ክፍሎች (እጅ፣እግር፣ ዓይን) አሰናክለውን፥ገሃነም ከመሄድ፥ተቆርጠው (ተቀንሰው) ወደ ሕይወት መግባት ይሻላል፡ ይላል። (ማር 9፡43-48)

እኔ በበኩሌ"ምነው ፈረድክብን" አትበሉኝና "ምላስ ይቆረጥ" ብያለሁ።

ጌታችን ኢየሱስ እንዳለ እኔም እላለሁ፥ ምላስ ኖሮን ትላቸው ወደ ማይሞትበት፥ እሳቱም ወደ ማይጠፋበት፥ ወደ ገሃነም፥ ወደ ማይጠፋ እሳት ከመጣል፥ ምላስ አልባ ሆነን (መናገር ተስኖን) ወደ ሕይወት መግባት ይሻለናል። አይመስላችሁም?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




PART 39
መልዕክት (message) 39
ያልተሸጠ ነገርማ አለ........!

አንድ አንድ ሰው የእግዚአብሔርን መንግስት ለመውረስ ሲል ፥ ባሳለፋቸው ዓመታት ራሱን ከብዙ ነገር ጠብቆ መጥቷል። ጥሩ ልምምድ ነው።ጌታ ኢየሱስ በአንድ ወቅት ለዚህ ምሳሌ የሚሆን፣ ከሕፃንነቱ ጀምሮ “አታመንዝር፥አትግደል፥አትስረቅ፥ በሐሰት አትመስክር፥አታታልል፥ አባትህንና እናትህን አክብር” የሚሉትን ትዕዛዛት ሲጠብቅ የኖረ ሰው አገኘ፤(ማር 10:19)

ኢየሱስም ወደደውና “አንድ ነገር ጎደለህ፤ ሂድ፥ ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለድሆች ስጥ፥...ና፥ ተከተለኝ” አለው(ማር 10:19)።

እኛም የሆነ የጎደለን ነገር አለ።አንድ ያልተሸጠ ነገርማ አለ። ቶሎ ሸጠን፥ እሱን ብቻ እንከተል። አይመስላችሁም?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 40
መልዕክት (message) 40
ማገልገል እንጀምር እንጂ...!

ዮሐንስ፥ ስለ ኢየሱስ “ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው፤” ሲል ይመሰክራል (ዮሐ 3:31)።

ከላይ የመጣውና ከሁሉ በላይ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ደግም፥ የመጣበትን ዓላማ ሲናገር“የሰው ልጅም ሊያገለግል፣ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።” ይላል። (ማር10:45)

ዛሬ ዛሬ፥ በሁሉም መስክ፥ ለማገልገል ሳይሆን-ለመገልገል፣ ለመጥቀም ሳይሆን-ለመጠቀም የሚደረግ ከፍተኛ ሩጫ ይታያል።እርሱ ከላይ የመጣው፥ለማገልገል ከሆነ፥እኛ ታዲያ ፥ ከየት መጣን ለማለት ነው ሩጫው? ማገልገል እንጀምር!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 41
መልዕክት (message) 41
እሱን ብቻ አራምዳለሁ.......!

መጽሐፍ ሲናገር “ሆሣዕና፤ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው” ይላል (ማር 11:9)።

በሌላ አንድ ስፍራ ደግሞ”ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ እርሱን ትቀበሉታላችሁ። እናንተ እርስ በርሳችሁ ክብር የምትቀባበሉ ከአንዱም ከእግዚአብሔር ያለውን ክብር የማትፈልጉ፥” ሲል ይወቅሳል። (ዮሐ 5:43-44)

ማንን ነው የተቀበላችሁት? የማንንስ ሃሳብ ታራምዳላችሁ? በጌታ ስም የመጣ አለ፣ በራሱ ስም ደግሞ የመጣ አለ። እኔ ማንም ይሁን ምንም አጀንዳ በጌታ ስም የመጣውን ልፈጽም ፥ ወድጄ ተቀብያለሁ። በቀሪው የሕይወት ዘመኔ፥ እሱን ብቻ አራምዳለሁ። እናንተስ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 42
መልዕክት (message) 42
ሽያጭና ግዥ.......!

መጽሐፍ ቅዱስ "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችሁ።" ይላል። (1 ቆሮ 3:17)

በሌላ ስፍራ ደግሞ ጌታ "ወደ መቅደስም ገብቶ በመቅደስ የሚሸጡትን የሚገዙትን ያወጣ ጀመር፥የገንዘብ...ገበታዎች የርግብ ሻጭዎች ወንበሮች ገለበጠ" ይላል (ማር 11:15)፤

መቅደስ እኛ ከሆንን፥ ዛሬ እኛ ውስጥ ምን እየተከናወነ ነው? ምን እያሰብን፥እያደረግንስ ነው ያለነው? ሽያጭና ግዥ አለ? ከጥሪያችን ውጪ ከሆነ፥ሽያጭና ግዥ ነው። ንስሐ እንግባ!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዳያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 43
መልዕክት (message) 43
........የማያውቅ ሁሉ ስቷል!

ማን ነው ስህተት?ማን ነው እየሳተ ያለ?ማንስ ነው "ስህተት" ብሎ ማረጋገጫ ሰጪ?

ኢየሱስ "መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ስለዚህ የምትስቱ አይደለምን?" ይላል (ማር 12:24)።

ለካስ ስህተት የሚመጣው መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል ካለማወቅ ነው። እከሌ ከከሌ የለም፥ መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል የማያውቅ ሁሉ ስቷል። በዚህ ጌታ ራሱ ማረጋገጫ በሰጠበት ርዕስ ጉዳይ ላይ ማረጋገጫ በመስጠት የተሰማራን፥ ቆም ብለን ራሳችንን እንመርምር። ይህም ሆኖ እንኳ፥ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል "የወደቁ አይነሡምን? የሳተስ አይመለስምን?"፥(ኤር 8:4) ይበረክ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 44
መልዕክት (message) 44
እንተዋቸው፤ ይሥሩበት.....!

መጽሐፍ ሲናገር “አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ የከበረ ጥሩ ናርዶስ ሽቱ የመላበት የአልባስጥሮስ ቢልቃጥ ይዛ መጣች፤ ቢልቃጡንም ሰብራ በራሱ ላይ አፈሰሰችው” (ማር14፡3)። “ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው” ይሏል እንዲህ ነው። (ሐዋ 20:35)

አንዳንዶች እንዲህ ያለ ነገር አይመቻቸውም። ታሪኩ ሲቀጥል “ይህ የሽቱ ጥፋት ለምንድር ነው? ይህ ሽቱ ከሦስት መቶ ዲናር በሚበልጥ ዋጋ ተሽጦ ለድሆች ሊሰጥ ይቻል ነበርና ብለው” ሴቲቱን ተቆጡ፣ ነቀፉአትም ይላል። (ማር 14፡4-5)

ኢየሱስ ግን “ተዉአት፤ ስለ ምን ታደክሙአታላችሁ? መልካም ሥራ ሠርታልኛለች” አለ። (ማር 14፡6)

ጌታ እንዳለ እኔም እላለሁ፡ መልካም ሥራ የሚሠሩ ሰዎችን በቃ፡ እንተዋቸው፤ ይሥሩበት!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 45
መልዕክት (message) 45
አሳልፎ መስጠት..............!

መጽሐፍ፥ የአስቆሮቱ ይሁዳ፥ ጌታን አሳልፎ ሊሰጠው ወደ ካህናት አለቆች እንደሄደ ይናገርና "በሚመች ጊዜም እንዴት አድርጎ አሳልፎ እንዲሰጠው ይፈልግ ነበር" ይላል። (ማር 14፥ 10-11)

ዛሬም፥ ይሄ የይሁዳ አገልግሎት ተጠናክሮ ቀጥሏል። ጊዜ ጠብቆ ስም ማጥፋት፣ ጊዜ ጠብቆ ብዕር ማሾል፣ ብቻ ጊዜ ጠብቆ ማጥቃት። ይመስለኛል አሁንም፥ እንደ አገልግሎት፥ የሆነ ሰውን አሳልፎ ለመስጠት የሚመች ጊዜ እየተጠበቀ ነው።

ይሁዳ፥ በዚህ አገልግሎቱ፥ አንጀቱ ተዘርግፎ ነው የሞተው። (ሐዋ 1:18)። በሰው ነገር አንግባ። ለተጠራንበት ዓላማ እና ለጠራን ጌታ ብቻ እንኑር። አይመስላችሁም?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 46
መልዕክት (message) 46
ጽህፈታችን ለጥሪያችን......!

“የሰው ልጅ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይሄዳል፤ ነገር ግን የሰው ልጅ አልፎ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮለት፤ ... ባልተወለደ ይሻለው ነበር።” (ማር 14:21)

በዚህ የጌታ ኢየሱስ፥ የፋሲክ እራት ንግግር “የሰው ልጅ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይሄዳል” ካለና የሰው ልጅም እንደ ተጻፈው ሊሄድ ግድ ከሆነ፣ ዛሬ እኛ እከሌን አሳልፎ ለመስጠት፥ለምን ሌላ ጽህፈት እናዘጋጃለን?

ሰውን አሳልፎ ለመስጠት ጽህፈት የምታዘጋጁ፥ ከዚህ በኋላ ይብቃችሁ፣ ጥሪያችሁን እወቁና ሥሩ። እምቢ ለሚል ሰው ቃሉ ዛሬም ህያው ነው። ምን እሚለው?”ለዚያ ሰው ወዮለት፤ ያ ሰው፥ ባልተወለደ ይሻለው ነበር።” ይላል (ማር 14:21)። ከዚህ በኋላ፥ ጽህፈታችን ለጥሪያችን!!! አይሻልም?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 47
መልዕክት (message) 47
የእኛ ትዝ ይበለን እና እናልቅስ!

ኢየሱስ “እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ በዚች ሌሊት ዶሮ ሁለት ጊዜ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ አለው”(ማር 14:30) እዚህ ጋ አስገራሚው ነገር፥ ጴጥሮስ ገና በመጀመሪያው ጩኸት ነው ጌታን ሦስት ጊዜ የካደው።

በዚህ ዘመንም ክህደት፥ ልክ በጴጥሮስ እንደሆነው ፈጣን እየሆነ መጥቷል። የሚያውቋትን ማህበረሰብ አላውቀውም፣ የተበደሩትን ገንዘብ (ንብረት) አልተበደርሁም፣ አግብተው አላገባሁም፥ ወዘተ ለማለት፣ የዶሮ ጩኸት አይጠበቅም።

ጴጥሮስ ዶሮ ሁለተኛ እንደጮኸ “ትዝ አለው፤ ነገሩንም አስቦ አለቀሰ።”ይላል መጽሐፍ (ማር 14:72)። እስኪ እኛም፥ የእኛ ትዝ ይበለን እና አልቅሰን ንሰሐ እንግባ። አይመስላችሁም?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 48
መልዕክት (message) 48
የመጨረሻ ምሽት እና ጸሎት!

ጌታ ኢየሱስ ተላልፎ በሚሰጥበት የመጨረሻ ምሽት ላይ ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን አስከትሎ “ሊደነግጥም፥ ሊተክዝም ጀመረ።” ይልና “ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፤በዚህ ቈዩ ትጉም አላቸው” ይላል (ማር 14:33-34)

ቆይቶ “መጣም ተኝተውም አገኛቸው፥ ጴጥሮስንም፥ ስምዖን ሆይ፥ ተኝተሃልን? አንዲት ሰዓት ስንኳ ልትተጋ አልቻልህምን? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉ ጸልዩም... አለው።” ይላል (ማር 14:37-38)

አገርና ሕዝብ እመጨረሻ ምሽት ላይ ሆኖ፥የምን መኝታ ነው? “ወደ ፈተና እንዳትገቡ” አንባልም፤ ገብተናል። ሁላችን፥ አንድ እድል ይቀረናል፣ ወደ ባሰ ፈተና እንዳንገባ፥ ተጠራርተን እና ተያይዘን፥ ተግተን እንጸልይ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 49
መልዕክት (message) 49
ማንም ባይኖር፥ ያለ አለ.....!

ጌታ ኢየሱስ በተያዘበት ምሽት፥ መጽሐፍ “ሁሉም ትተውት ሸሹ።” ይልና “ዕርቃኑን በነጠላ የሸፈነ አንድ ጎበዝ ይከተለው ነበር፥ ጎበዛዝቱም ያዙት፤ እርሱ ግን ነጠላውን ትቶ ዕራቁቱን ሸሸ።” ይላል (ማር 14:50-52)።

ወደ ጥሪያችን መጨረሻ ስንደርስ፥ ሁሉም ይተወናል ወይም ይሸሽናል ማለት ነው? ማን ነው፥ ማንንም (ምንም) ሳይፈራ የሚከተለንስ?

ጌታ ኢየሱስ አስቀድሞ “እኔንም ለብቻዬ የምትተዉበት ሰዓት ይመጣል...ግን አብ ከእኔ ጋር ስለ ሆነ ብቻዬን አይደለሁም” ብሏል (ዮሐ 16:32)። ብቻችሁን አይደላችሁም። ያለ አለ፤ ግን አንድ ነገር አድርጉ፣ ትኩረት እቀጣዩ ጥሪ ምዕራፍ ላይ!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




PART 50
መልዕክት (message) 50
ያልተስማማ ተቃውሞና ምስክርነት

“የካህናት አለቆችም፥ ሸንጎውም ሁሉ እንዲገድሉት በኢየሱስ ላይ ምስክር ይፈልጉ ነበር፥ አላገኙምም።” ይላል መጽሐፍ። (ማር 14:55)።ለነገሩ የተወሰኑ የሐሰት ምስክሮች ተገኝተው ነበር ነገር ግን “ምስክርነታቸው ግን አልተሰማማም።” ይላል (ማር 14:56)።

ምስክሮቹንም አስጠንተዋቸው”ይህን በእጅ የተሠራውን ቤተ መቅደስ አፈርሰዋለሁ በሦስት ቀንም... በእጅ ያልተሠራውን እሠራለሁ ሲል ሰማነው”በሐሰት መሰከሩ። “ምስክርነታቸው እንዲሁ እንኳ አልተሰማማም።” ይላል (ማር 14:57-59)።

ያልተስማማ ተቃውሞና ምስክርነት በበዛበት፥የሚያዋጣው፥ ልክ እንደ ኢየሱስ ዝም ማለትና ቀጣዩን ምዕራፍ መጓዝ ነው!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 51
መልዕክት (message) 51
የማይለወጠው ቅዱስ ወንጌል

ትውልድ ይሄዳል፥ትውልድ ይመጣል፤ከዚህ ጋር ተያይዞ ነገር በፍጥነት ይለዋወጣል።በደረስንበት ዘመን፥ ታሪክ እንኳ ራሱ በሚፈጠሩ አዳዲስ ትርክቶች መለዋወጥ ከጀመረ ሰነበተ። በሰውና በሁኔታዎች መለዋወጥ የእውነት ዝለናል። ነፍሳችን የማይለዋወጥ ነገር ተጠምታለች።

መጽሐፍ ሲናገር “ኢየሱስ ራሱ ለዘላለም ድኅነት የሆነውን የማይለወጠውን ቅዱስ ወንጌል ከፀሐይ መውጫ እስከ መጥለቂያው ድረስ በእጃቸው ላከው” ይልና (ማር 16:8)፥ “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ” ይላል (ማር 16:15)። ተለዋዋጭ የሆነ ምድራዊ አጀንዳ ማራመድ ይብቃ።ቀሪ ዘመንዎ ለማይለወጥ ቅዱስ ወንጌል!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 52
መልዕክት (message) 52
መዳን ብቻ.....................!

መጽሐፍ ሲናገር “ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።” ይላል (ማር 16:16)።

ጥያቄው “እምነት የሚባለው ነገር ከየት ይመጣል?” የሚል ነው። መጽሐፍ ሲመልስ”እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።” ይላል (ሮሜ 10:17)።

ስለዚህ ሰዎች እባካችሁ ሌላ ነገር አታሰሙን። ሌላ መረጃ አትስጡን፣ይልቅ”እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና” ስለሚለው ብቻ አውሩልን፣ ተርኩልን። መዳን ብቻ ነው ያማረን!!! (ሐዋ 4:12)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 53
መልዕክት (message) 53
ማቱሳላ እድሜው አጭር ነው

መጽሐፍ የመለአኩ ገብርኤልን ንግግር ጠቅሶ" ... ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ።እርሱ ታላቅ ይሆናል...ለዘለላም ይነግሣል ፥ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም"ይላል(ሉቃ 1:31-33)።

የረጅም እድሜ ጌታው"ማቱሳላ የኖረበት ዘመን ሁሉ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ዘጠኝ ዓመት ሆነ" ይላል መጽሐፍ። (ዘፍ 5:27) ይህ ሰው ሙሉ ዘመኑን መንግስት ቢሆን ሊገዛ የሚችለው 969 ዓመት ነው፣ ሲጨርስ በሞት ነው። ያሳዝናል!

ማቱሳላና መሰሎቹ እድሜያቸው አጭር ነው፤ አያዋጣም። እኔ ለመንግሥቱ መጨረሻ የሌለው ኢየሱስን መርጫለሁ። እናንተስ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 54
መልዕክት (message) 54
የችሎታ አገልግሎት..........!

መጽሐፍ “በዘመናችን ሁሉ ያለ ፍርሃት በቅድስናና በጽድቅ በፊቱ እንድናገለግለው ሰጠን።” ይላል (ሉቃ 1:74-75)። ለማገልገል፥ ማነው ቅዱስ? ማን ነውስ ጻድቅ?

መጽሐፍ ሲመልስ “እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለምና፥ እንደ አምላካችንም ጻድቅ የለምና”ይላል(1ሳሙ 2:2)። ቅድስናም ሆነ ጽድቅ ልኩ እርሱ ከሆነ፥ እንድናገለግል የጠራን በእርሱ ልክ (እርሱ እንደሚፈልግ) ነው።

በዚህ መሠረት፥ የትኛውም የችሎታ (የልምድ) አገልግሎት ከቅድስናና ጽድቅ ጎድሎ መገኘት ነው። አይመስላችሁም?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 55
መልዕክት (message) 55
ሌላ ስም አይጠራም.........!

ምድር ከተፈጠረች ጀምሮ አያሌ ሰዎች በመወለድ ሥርዓት ወደ ምድር መጥተዋል። አንዳንዶቹ ከመወለዳቸው በፊት፥ አንዳንዶቹ ደግሞ ከተወለዱ በኋላ ስለማንነታቸው ወይንም ስለብቃታቸው የተተነበየ ወይም የተነገረ ነገር አለ። ሲወለድ “መድኃኒት” የተባለ ግን በታሪክ አላስታውስም።

መጽሐፍ “ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና።” ይላል (ሉቃስ 2:11)። በሌላ ስፍራ ደግሞ “እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።” ይላል (ማቴ 1:21)

እንግዲህ፥ ይህን መልዕክት የምናነብ ሁሉ፥ ከኃጢአታችን አሁን ለመዳን ሌላ ስም አይጠራም። “የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና።” ተብሎ እንደተፃፈ (ሮሜ 10:13)!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 56
መልዕክት (message) 56
“አንዴ ድኛለሁ” አይሠራም!

የእግዚአብሔር ቃል፥ ወደ ዘካርያስ ልጅ ወደ ዮሐንስ የመጣ “..አሁንስ ምሳር ደግሞ በዛፎች ሥር ተቀምጦአል እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል።” ይላል (ሉቃ 3:2-9)።

መልካም ፍሬ ማፍራት ላለመቆረጥ ብቸኛው ዋስትና ነው። መቆረጥ እና በእሳት መቃጠል፥ መልካም ፍሬ ያለማፍራት ውጤቶች ናቸው። ነገ ከሕይወት መስመር ድንገት ተቆርጠን ለመቃጠል እንዳንበቃ፥ ዛሬ በተሰለፍንበት መስክ መልካም ፍሬ እናፍራ።

“እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ”(1ቆሮ 10:12)። “አንዴ ድኛለሁ” አይሠራም።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 57
መልዕክት (message) 57
ዘንድሮ ምርጫዬ.............!

ስለ ኢየሱስ፥ “ቃሉ በሥልጣን ነበርና በትምህርቱ ተገረሙ” ይላል መጽሐፍ(ሉቃ 4:32)።በሌላ ስፍራ ደግሞ “በሥልጣን ርኵሳን መናፍስትን ያዝዛል፤ እነርሱም ይታዘዙለታል...ብለው እስኪጠያየቁ ድረስ አደነቁ።” ይላል (ማር 1:27)።

ስለዚህ አስገራሚ የስልጣን ወሰን (ክልል)፥ ኢየሱስ ሲናገር “ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።” ይላል (ማቴ 28:18)። የምድር ምርጫ ብቻውን ውሃ አያነሳም። ዘንድሮ ምርጫዬ ኢየሱስ ነው። እርሱ ሥልጣን በሰማይና በምድር already ወስዷል።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 58
መልዕክት (message) 58
አሮጌው ይጣፍጣል ይላል...!

አዲስ ነገር ስንል አንጻራዊው ጉዳይ አሮጌ ነው። አሮጌ ነገር አፍቃሪ፥ አዲስ አይመቸውም፣ አይሻውምም። መጽሐፍም ጉዳዩን ሲያረጋግጥ “አሮጌ የወይን ጠጅ ሲጠጣ አዲሱን የሚሻ ማንም የለም፤ አሮጌው ይጣፍጣል ይላልና።” ይላል። (ሉቃ 5:39)

አሁን ወደ አደባባይ ፈጥጦ የወጣው ችግራችን ይሄ ነው። በሁሉም መስክ፥ በአንድ ወገን አዲስ አቀራረብና አራማጆቹ ከነደጋፊዎቻቸው ተሰልፈዋል፤ በሌላ ጎን የአሮጌው (ውራጅ፣ ዕብ 8:13) አራማጆችና የአቀንቃኞቻቸው ሰልፍ አለ።

የእኔ ምርጫ አዲሱ ነው። ምንድን ነው ማስረጃህ እንዳትሉኝ ፤ ያለንበት ኪዳን ራሱ፥ አዲስ ኪዳን፥ አይደል እንዴ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 59
መልዕክት (message) 59
ክብር ለሰው ሁሉ.............!

“በሰንበት...ደቀ መዛሙርቱም እሸት ይቀጥፉ፥ በእጃቸውም እያሹ ይበሉ ነበር። ከፈሪሳውያን ግን አንዳንዶቹ፥ በሰንበት ሊደረግ ያልተፈቀደውን ስለ ምን ታደርጋላችሁ?” ሲሉአቸው፤ ኢየሱስም መልሶ “የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነው አላቸውም” ይላል። (ሉቃ 6፥1-4)

በክርስቶስ ደም የተገዛን ክቡር ሰው፥እርሱ ጌታ ከሆነባቸው ነገሮች ወይም ለእርሱ ከተፈጠሩ ነገሮች፥ አለያም የእርሱ ውጤት ከሆነ ነገር ጋ አነጻፅሮ ዝቅ ማድረግ ፈሪሳዊነት ነው፤

ሲጀመር፥ ሰውን ያከበረው ሰው ሳይሆን፥ ራሱ እግዚአብሔር ነው (ኢዮብ7:17)።ከምንም ነገር በላይ፥ ክብር ለሰው ሁሉ!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 60
መልዕክት (message) 60
"አላውቃችሁም" እንዳንባል!

ማን ነው የጠራን?ማን ነው የመረጠን?ማንስ ነው የሰየመን?

መጽሐፍ "በነጋም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ፥ ከእነርሱም አሥራ ሁለት መረጠ ደግሞም ሐዋርያት ብሎ ሰየማቸው፤" ይላል (ሉቃ 6:13)።

እሱ ነው የጠራኝ፣ እሱ ነው የመረጠኝ፣ እሱ ነው የሰየመኝ ያልን ሁሉ፥ የእርሱ መምጫ ደርሷልና፥ ኋላ "አላውቃችሁም" እንዳንባል፥ ራሳችንን እንመርምር። መጽሐፍም "ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብን" ይላልና፤ (1ቆሮ 11:31)

መልዕክቱን መጨገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 61
መልዕክት (message) 61
የብልጥግና ልካችን..........!

የጽድቅን (right standard) መንገድ ስለተከተልን ወይም ደግሞ በጠባቡ በር ስለገባን፥ "ድሆች" እየተባልን ይሆን? ሳንባል አልቀረንም። ሐዋርያው ጳውሎስ "ድሆች ስንሆን ብዙዎችን ባለ ጠጎች እናደርጋለን፤ አንዳች የሌለን ስንሆን ሁሉ የእኛ ነው።" ይላል (2 ቆሮ 6:10)

የዚህ ጉዳይ መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ እንዳይረሳ፥ "ሀብታም ሲሆን፥ እናንተ በእርሱ ድህነት ባለ ጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሀ ሆነ።" ይላል መጽሐፍ (2ቆሮ 8:9)።

አትፍሩ! ቃሉ ዛሬም ህያው ነው፣ ይሠራል፡- "እናንተ ድሆች ብፁዓን ናችሁ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት የእናንተ ነውና።" (ሉቃ 6:20)። የምድር ብልጥግና አይመጥናችሁም!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 62
መልዕክት (message) 62
የዘላለም ጥጋብ፣ የዘላለም ሳቅ አለ

መጽሐፍ"የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤" ይላል (2 ቆሮ 4:17)

አሁን የሚታየውና እየሆነ ያለው ነገር ሁሉ፥ አይነካ፣ይቀጥል፥ ቢባል እድሜው በጣም አጭር ነው፣የጌታን ምጽአት ሊሻገር አይችልም "የማይታየው ግን የዘላለም ነው።" (2 ቆሮ 4:19)

እና "እናንተ አሁን የምትራቡ ብፁዓን ናችሁ፥ ትጠግባላችሁና ። እናንተ አሁን የምታለቅሱ ብፁዓን ናችሁ፥ ትስቃላችሁና።" (ሉቃ 6:21)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




PART 63
መልዕክት (message) 63
“ለእኔ ቢሆን፥ የቱን እወድዳለሁ”

ምን እንዲደረግላችሁ ትወዳላችሁ? ምን ሲደረግላችሁ ነው ደስ የሚላችሁ? ማ ምን ቢያደርግላችሁ ነው፥ የእውነት ደስ የምትሰኙትስ? ምን ብታገኙ(ሰው ምን ቢሰጣችሁ) በርግጥ ትወድዳላችሁ?

ለዚህ ነው ኢየሱስ “ሰዎችም ሊያደርጉላችሁ እንደምትወዱ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው።” ያለው (ሉቃ 6:31)።

ስለዚህ ወገኖቼ፥ ከአሁን በኋላ፥ ለማንም ሰው ምንም ነገር ከማድረጋችን በፊት፥ “ለእኔ ቢሆን፥ የቱን እወድዳለሁ” ብለን እንነሳ። ያኔ ለማንም የሚገባውን የማድረጉ አቅም ይኖረናል። በየትኛውም ድርጊታችን ሰው መጉዳት እናቆማለን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 64
መልዕክት (message) 64
ሕይወት ይናገር...............!

መጽሐፍ “ደቀ መዝሙር ከመምህሩ አይበልጥም፤ ፈጽሞ የተማረ ሁሉ ግን እንደ መምህሩ ይሆናል” ይላል(ሉቃ 6:40)

አሁን አሁን የደቀ መዝሙር ትምህርት እንጂ፥ ደቀ መዝሙር ያለ አይመስልም። “ፈጽሞ የተማረ ሁሉ ግን እንደ መምህሩ ይሆናል” የሚለውን አባባል አይተን፥ለአብነት”እከሌ ተማሪው ነው፤ እከሌ ደግሞ አስተማሪው” የምንልበት እድል የለም። መለኪያው የዕለት ከዕለት ሕይወት ነው። ሕይወት ይናገር።

በማስተማር ዘዴ ሳይንስ ጥናት (pedagogy)፥ “LIFE IS EDUCATION, EDUCATION IS LIFE” የሚል አባባል አለ። ዛሬ ዛሬ፥ ቃል እንጂ ሕይወት የሚያካፍል እጥረት አለ፤ በተመሳሳይ፥ ሕይወት አልባ ቃል (ፊደል) የጠገቡ በዝተዋል!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




PART 65
መልዕክት (message) 65
ጉድፋም ሆኖ ተቺነት፥ ግብዝነት

“በዓይንህ ያለውን ምሰሶ ራስህ ሳታይ፥ እንዴት ወንድምህን፥ ወንድሜ ... በዓይንህ ያለውን ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ ልትል ትችላለህ? አንተ ግብዝ፥ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ ከዚያ በኋላ በወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ።” (ሉቃ 6:42)

ማን ነው ዛሬ ከመካከላችን በዓይኑ ምሰሶ እንዳለ ሚያምን? ማንስ ነው ወንድሙን አስፈቅዶ ከዓይኑ ጉድፍ የሚያወጣ? እስኪ እከሌ ብላችሁ፥አንድ አጥርቶ የሚያይ፥ለአብነት ጥሩ፤ እስኪ ወደ ራሳችን ዓይን (ጓዳ) መለስ እንበል። የራሳችንን ቤትና ሕይወት እናስተካክል። ከዚያ የሌላውን ቤትና ሕይወት ከጉድፍ ለማንጻት እንችላለን።

ጉድፋም ሆኖ ተቺነት፥ ግብዝነት። ጣታችንን እንመልስ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 66
መልዕክት (message) 66
የአዲስ ኪዳን ቃየንነት.......!

“እግዚአብሔርም ቃየንን አለው። ወንድምህ አቤል ወዴት ነው? እርሱም አለ። አላውቅም፤ የወንድሜ ጠባቂው እኔ ነኝን? አለውም። ምን አደረግህ? የወንድምህ የደሙ ድምፅ ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል።” (ዘፍ 4:9-10)

ወንድምን ያህል ነገር ገድሎ፥ ምንም ነገር እንዳልተፈፀመ “አላውቅም” ማለት ከየት የመጣ ባህል ነው? “የወንድሜ ጠባቂ ነኝ?” እንዴት ይባላል? ሰው ወንድምን ያህል ነገር ካልጠበቀ፥ ማንን ሊጠብቅ ነው?

ጌታ ኢየሱስ “ነገር ግን የማይገለጥ የተከደነ፥ የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለም”ይላል(ሉቃ 12:2)።ከድነን (ሰውረን) የምናደርገው/እያደረግነው ያለ ነገር ሁሉ ተከድኖ አይቀርም ፣ ይገለጣል። ወንድምን ያህል ነገር በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ማዋረድ፣ ማናናቅ፣ ማጠልሸት፥ ከዛም ምንም እንዳላደረገ ሰው ሽር ጉድ ማለት፥ የአዲስ ኪዳን ቃየንነት ነው። ንሰሐ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 67
መልዕክት (message) 67
ተቃውሞ አቅም የለውም!

ኢየሱስ “ሥጋን የሚገድሉትን በኋላም አንድ ስንኳ የሚበልጥ ሊያደርጉ የማይችሉትን አትፍሩ... ገሃነም ለመጣል ሥልጣን ያለውን ፍሩ።” አለ (ሉቃ 12:4)።

ከሥጋ ሞት፥የከፋ ሞት አለ ማለት ነው፤ ገሃነም። ተቃውሞ፥ ምንም አቅም የሌለው ለካ ለዚህ ነው። ተቃውሞን የሚረዳ ቅባት (ፀጋ) የለም። ተግባሩ ላይ የተሰማሩት ሰዎችም ሆኑ ደጋፊዎቻቸው፥ እንደ ክረምት ፀሐይ ናቸው። የሆነ ጊዜ ነው ብቅ የሚሉት።

መጽሐፍ “በአንድም ነገር እንኳ በተቃዋሚዎች አትደንግጡ፤ ይህም ለእነርሱ የጥፋት፥ለእናንተ ግን የመዳን ምልክት ነው ፥ ይህም ከእግዚአብሔር ነው፤” ይላል (ፊልጵ 1:28)። ቻው ተቃዋሚዎች!!!!!!!!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 68
መልዕክት (message) 68
አንነፃፀርም......................!

የሰው ዋጋው ምን ያህላል? ከማን (ከምንስ) ጋር ሊነፃፀር ይችላል? ጌታ ኢየሱስ “አምስት ድንቢጦች በአሥር ሳንቲም ይሸጡ የለምን?” ይላል።አምስት ድንቢጦች በአሥር ሳንቲም ፥በጣም ርካሽ ነው። ጌታ ሲቀጥል “ከእነርሱም አንዲቱ ስንኳ በእግዚአብሔር ፊት አትረሳም።” ይላል (የሉቃ 12:6)

እኛስ ጌታ ሆይ?

“የእናንተ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ የተቈጠረ ነው፤አትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች ትበልጣላችሁ።” (የሉቃ 12:6)። ወገኖቼ እኛ በልጁ ደም የተገዛን፥ ከማንም እና ከምንም ነገር ጋር አንነፃፀርም። “ትበልጣላችሁ” ያለንም እሱ ነው፥ ይባረክ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 69
መልዕክት (message) 69
መንፈስ ቅዱስን የሚሰድብ...!

“በሰው ልጅ ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሰረይለታል፤ መንፈስ ቅዱስን የሚሰድብ ግን አይሰረይለትም።” (ሉቃ 12:10)

መንፈስ ቅዱስ እንዴት ይሰደባል? ስድብስ ሊደረሰበት ያለው እንዴት ነው? ይህን ለማወቅ፥አንድ ምሳሌ ማንሳት በቂ ነው።
“ሌላውን የምታስተምር ራስህን አታስተምርምን? አትስረቅ ብለህ...ትሰርቃለህን? አታመንዝር የምትል ታመነዝራለህን?.. ቤተ መቅደስን ትዘርፋለህ?ሕግን በመተላለፍ እግዚአብሔርን ታሳፍራለህን? በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ይሰደባል” (ሮሜ 2፡21-24)። ከዚህ የምንረዳው፥ ሥርዓት አልበኝነትን፣ ለጠቀስነው ቃል አለመገዛትን ነው።

ሐ.ጳውሎስ ከመንፈስ ቅዱስ መገለጥና አሠራር ጋር ተያይዞ ያለውን ዝርዝር መረጃዎች፥ያስቀምጥና ሲያጠቃልል “ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን” ይላል (1ቆሮ 14:40)

ቤተክርስትያን ከዚህ በኋላ መንፈስ ቅዱስን ላለማሰደብ እና ከሚጠበቀው መነቃቃት (revival) ጋር ለመገናኘት ወደ 1ኛ ቆሮንቶስ14 ፈቷን መመለስና ሁሉን በሥርዓት ልታደርግ እና ልታስደርግ ጊዜው ነው። አይመስላችሁም?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 70
መልዕክት (message) 70
ከጐታቾች የመዳን ት/ቤት..!

“ወደ ምኵራቦች፣መኳንንቶችም፣ገዢዎችም ሲጐትቱአችሁ፥ እንዴት...ምን እንድትመልሱ ወይም እንድትናገሩ አትጨነቁ፤” ይላል ጌታ ኢየሱስ። (የሉቃ 12:11)

በምኩራብ(ቤ/ክ)፥ምን ተፈልጎ እንደሆን በውል ባይታወቅም ጉተታ አለ።ሲታዩ ለስሙ መኳንንቶች ናቸው ግን ይጐትታሉ። የገዢዎችን ባናነሳው ይሻላል።

ማንም ይጐትታችሁ፥ለጥያቄ(የሆነ ነገር ሊጠይቃችሁ)ነው። መፍትሄው፥ ቁርጥ ያለና የማያዳግም መልስ መስጠት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ “መንፈስ ቅዱስ በዚያች ሰዓት ልትናገሩ የሚገባችሁን ያስተምራችኋልና” ስለሚል፥ ከጐታቾች ነፃ ሆኖ ለመገኘት፥ ወደ መንፈስ ቅዱስ ት/ቤት። (ሉቃ 12:12)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 71
መልዕክት (message) 71
ለራስ የእስካሁኑ ይበቃል...!

ለማን ነው የምንኖረው? ለማን ነው በዲግሪ እምንመረቀው? ለማነው ገንዘብ የምንሰበስበው? ለማን ነው ፀጋ የተፈለገው ? ሹመት ለምን ተፈለገና ተገኘስ? ታዋቂ መሆን የተፈለገው ለማን ነው? የምናስብና የምናደርገው ነገር ሁሉ ለማን ነው?

ለራስ?

ለራስ ብቻ የሆነ፣ ከራስ እና ከራስ ክልል ያልዘለለ መሯሯጥ፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ባዶነት ነው። መጸሐፍ “ለራሱ ገንዘብ የሚያከማች፥በእግዚአብሔር ዘንድም ባለ ጠጋ ያልሆነ እንዲህ ነው።” ይለናል (ሉቃ 12:21)።

እስኪ፥ ከዚህ በኋላ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ለሌሎች!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 72
መልዕክት (message) 72
የሚያዋጣው መታረቅ ነው!

እርቅ፥ የሕይወትን ምዕራፍ ከተወሳሰበ ሁኔታ ነጻ እሚያወጣ መልካም መንገድ ነው። መጽሐፍ “የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና” ይላል (ማቴ 5:9)

እርቅ የሚጠሉ (የማይቀበሉ) ሰዎች፥ የመጨረሻው ዘመን ምልክቶች ናቸው፣”ዕርቅን የማይሰሙ” ይላል (2ጢሞ 3:3)

እርቅ አለመስማት ከፍተኛ ዋጋ ያስከፍላል። “ከባላጋራህ ጋር ወደ ሹም ብትሄድ፥ወደ ዳኛ እንዳይጐትትህ፥ዳኛ ለሎሌው አሳልፎ እንዳይሰጥህ፥ ሎሌውም በወኅኒ እንዳይጥልህ፥ገና በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ እንድትታረቅ ትጋ። እልሃለሁ፥ የመጨረሻዋን ግማሽ ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ ከዚያ ከቶ አትወጣም። (ሉቃ 12:58-59)

ለማንም የሚያዋጣው መታረቅ ነው። በተለይ ለክርስትያን፥ ሳይታረቅ፥ “በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ።” ብሎ መጥቀስ አይከብድም? (2 ቆሮ 5:19)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 73
መልዕክት (message) 73
ዘግናኝ ወሬ አቀባዮች.........!

በዚህ ዘመን በግል፣ በቡድን፣ በማሕበራዊ ሚዲያና አንጋፋ በሆኑ የመገናኛ ብዙሃን፥ የሰዎችን ስም እየጠቀሱ፥ እንዲህ አደረገ (አደረጉ)፣ እንዲህ አድርጓል (አድርገዋል)፣ እንዲህም ሊደረግ ነው፣... የሚሉ ዘግናኝ ወሬ አቀባዮች በዝተዋል ።

ይህን መሠል ወሬ አቀባዮች ኢየሱስ ጋ መጥተው “ጲላጦስ ደማቸውን ከመሥዋዕታቸው ጋር ስላደባለቀው ስለ ገሊላ ሰዎች አወሩለት።” ይላል። ኢየሱስም ሲመልስላቸው “እነዚህ የገሊላ ሰዎች፥ ይህ ስለደረሰባቸው፥ ከገሊላ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ኃጢአተኞች የሆኑ ይመስሉአችኋልን? እላችኋለሁ፥ አይደለም፤ ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላ
ችሁ።” አለ ይላል። (ሉቃ 13:1-3)

የሌላውን ኃጢአት የምንዘግብ ሁሉ፥ በቃ፤ ይበቃል። ራሳችን እንዳንጠፋ ንስሐ እንግባ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 74
መልዕክት (message) 74
የቀረን፥ የንስሐ ጊዜ ነው....!

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፥ በተናጠል (በጅምላ)፥ በዓለም አቀፍም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ፥ እዚህም እዚያም፥ የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር እየተበራከተ መጥቷል።"በኮቪድ ነው የሞተው/ችው" ከተባለ፥ የሚወራው እንደ በደለኛ (ኃጢአተኛ) ነው።

ጌታ ኢየሱስ "በሰሌሆም ግንቡ የወደቀባቸውና የገደላቸው እነዚያ አሥራ ስምንት ሰዎች በኢየሩሳሌም ከሚኖሩት ሁሉ ይልቅ በደለኞች ይመስሉአችኋልን? አይደለም፥ እላችኋለሁ፤ ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋላችሁ" አለ። (ሉቃ 13:4-5)

በምንም ጉዳይ እየሞቱ ያሉ ሰዎችን፥ በደለኛ (ኃጢአተኛ) አድርጎ መገመትም ሆነ ማስወራት ከዚህ በኋላ ይበቃል። እኛም እንደነሱ እንዳንጠፋ፥ በቀረን ጊዜ፥ ንስሐ እንግባ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 75
መልዕክት (message) 75
አንድ እድል ነው የቀረን......!

ጌታ ኢየሱስ ይህንም ምሳሌ ተናገረ፥ “ለአንድ ሰው በወይኑ አትክልት የተተከለች በለስ ነበረችው፥ ፍሬም ሊፈልግባት መጥቶ ምንም አላገኘም። የወይን አትክልት ሠራተኛውንም፥ ‘እነሆ፥ ከዚህች በለስ ፍሬ ልፈልግ ሦስት ዓመት እየመጣሁ ምንም አላገኘሁም፤ ቍረጣት፤ ስለ ምን ደግሞ መሬቱን ታጐሰቍላለች?’ አለው።እርሱም መልሶ ‘ጌታ ሆይ፥ ዙሪያዋን እስክኰተኵትላትና ፋንድያ እስካፈስላት ድረስ በዚች ዓመት ደግሞ ተዋት። ወደ ፊትም ብታፈራ፥ ደኅና ነው፤ ያለዚያ ግን ትቈርጣታለህ’ አለው።” (ሉቃ 13:6-9)

ወገኖቼ፥ እንድንለወጥ፣ እንድንቀየር፣ ሰው እንድንሆን ብዙ እድል ተሰጥቶናል።አሁን ግን ሁኔታዎች እንደሚነግሩን፥አንድ እድል ነው የቀረን። ቆረጣ ተጀምሯል! ቶሎ ንስሐ እንግባ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 76
መልዕክት (message) 76
ቀና ብሎ መኖር አልናፈቃችሁም?

አንድ አንድ ጊዜ ካላስተዋልን፥ ክፉ መንፈስ፥ በአንድ ጉዳይ እስረኛ ያደርገንና ሳናውቀው ጎብጠን እንቀራለን፣ ቀና ማለት ሳንችል ዓመታት ይቆጠራሉ። ትምህርት ጀምሮ ማቋረጥ፣ ሥራ ጀምሮ ማቋረጥ፣ አገልጎሎት ጀምሮ ማቋረጥ፣ የሆነ ነገር ጀምሮ ማቋረጥ፥ ጉብጠት ነው፣ ቀና ብሎ አለመኖር።

መጽሐፍ ሲናገር"እነሆም፥ አሥራ ስምንት ዓመት... የድካም መንፈስ ያደረባት ሴት ነበረች፥እርሷ ጐባጣ ነበረች ቀንታም ልትቆም ከቶ አልተቻላትም።ኢየሱስ ባያት ጊዜ ጠራትና 'አንቺ ሴት፥ ከድካምሽ ተፈትተሻል' አላት፥እጁንም ጫነባት፤ያን ጊዜ ቀጥ አለች፥ እግዚአብሔርንም አመሰገነች።" ይላል። (ሉቃ 13:11-13)።

ማን ነው ከመካከላችን በሆነ ልምምድ ጎብጦ የቀረ? ቀና ማለት እየፈለገ፥ ቀና ማለት ያልቻለ? ጌታ ኢየሱስ " እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ወደ እኔ ኑ፥ አሳርፋችኋለሁ" ይላል (ማቴ 11:28)። ቀና ብሎ መኖር አልናፈቃችሁም???

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 77
መልዕክት (message) 77
እረፍት ተብሎ፥ መቃምና መጠጣት!

መጽሐፍ "ሊሠራ የማይወድ አይብላ" ይላል (2ተሰ 3:10)። ስንት ቀን ነው የምንበላው?ስንት ቀን ሠርተን? የመብላት ቀን ከመሥራት ቀን አልበዛም ትላላችሁ?

የምኵራብ አለቃው ደግሞ ከዚህ ይብሳል "ኢየሱስ በሰንበት ስለ ፈወሰ ተቈጥቶ መለሰና ሕዝቡን። ሊሠራባቸው የሚገባ ስድስት ቀኖች አሉ፤ እንግዲህ በእነርሱ መጥታችሁ ተፈወሱ እንጂ በሰንበት አይደለም" ይላል (ሉቃ 13:14)። ሰባተኛውን ቀን አይታችሁታል? እረፍት ተብሎ፥ መቃም፣ መጠጣት፣...

ኢየሱስ፥ በስድስት የሥራ ቀናት ባተሌ (busy) የሆነ ሕዝብ ይልቁን በሰንበት ይብስበታል ብሎ ነው እሱም ሥራ ሊሠራ በሰባተኛው ቀን የመጣው። በሰባተኛው ቀን ሥራ ክልክል ከሆነ፥ የስድስቱ ቀን መጣራት አለበት።

"ሊሠራ የማይወድ አይብላ" ከተባለ፥ ከመብላት የሚጀምር ሕይወት የለም። ሥራ እማትሠሩ፣ እንዳይሠራ እምትከለክሉ፣ የሚሠሩትንም የምታሳጡ፥ ኢየሱስ "ግብዞች" የሚል ስም ሰጥቷችኋል። ቃሉን አጥኑት፥ ያኔ በንስሐ ነጻ ትወጣላችሁ።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 78
መልዕክት (message) 78
ሦስተኛው ቀን ተቃርቧል....!

ከፈሪሳውያን አንዳንዱ ቀርበው፥ኢየሱስን “ሄሮድስ ሊገድልህ ይወዳልና ከዚህ ውጣና ሂድ አሉት”ይላል፤ ሲመልስላቸውም “ሄዳችሁ ለዚያች ቀበሮ እነሆ፥ዛሬና ነገ አጋንንትን አወጣለሁ በሽተኞችንም እፈውሳለሁ፥ በሦስተኛውም ቀን እፈጸማለሁ በሉአት።” ይላል። (ሉቃ 13:31-32)

መልዕክተኛን በቀላሉ መቃወምም ሆነ ማስወጣት፥ እንዲህ እንደሚታሰበው ቀላል አይደለም። እርሱ ጥሪውን ሳይፈጽም ወይ ፍንክች። ላኪውን ነው መፍራት።

ስለዚህ ቀበሮዎች፥ ሦስተኛው ቀን ተቃርቧልና፥ ትንሽ ታገሱ!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 79
መልዕክት (message) 79
የሆነ ሰው አየወገርን እንዳይሆን!

ጌታ ኢየሱስ ሲናገር “ኢየሩሳሌም፥ ኢየሩሳሌም፥ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርስዋ የተላኩትንም የምትወግር፥” ይላል። (ሉቃ 13:34)

ማሕበረሰባችን፥ የተከበረ፣ ማክበርንም ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ ሁሉን አቀፍ እንደ ነበር፥ ቀደምት ጸሐፍት በተየቧቸው ሰነዶች ተመላክተዋል። ማሕበረሰብ ስንል፥ ስለ አገር እያወራን ነው። ዛሬ ዛሬ ግን አገር፥አገር አልመሰለም። እንኳን ለአገር የተላከ፣ ሊላክ ይችላል ተብሎ እሚገመት፥አቀባበሉ ተቃውሞ ሆኗል፤

በኢየሩሳሌም የሆነው፥ እየሆነብን ይሆን? እባካችሁ ወገኖች እከሌ ከእከሌ ሳንል፥ ምናልባት እኛም የሆነ ሰው አየወገርን እንዳይሆን፥ ስለአካሔዳችን ንስሐ እንግባ፣ በተለይ ደግሞ... መጽሐፍ “ባለ መድኃኒት ሆይ፥ ራስህን ፈውስ፤” ይላልና። (ሉቃ 4:23)፣ ጌታ ይራራል፣ ይምራልም!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 80
መልዕክት (message) 80
ጠሪው ካላይ እያየን ነው....!

ጌታ ኢየሱስም በምሳሌ “ማንም ለሰርግ ቢጠራህ በከበሬታ ስፍራ አትቀመጥ፤ ምናልባት ከአንተ ይልቅ የከበረ ተጠርቶ ይሆናልና፥ አንተን እርሱንም የጠራ መጥቶ፥ ለዚህ ስፍራ ተውለት ይልሃል፥ በዚያን ጊዜም እያፈርህ በዝቅተኛው ስፍራ ልትሆን ትጀምራለህ።” ሲል ይናገራል። (ሉቃ 14:8-9)

በሕይወት መንገድ ጠሪ እና ተጠሪ አለ። ጠሪ ያስቀምጣል፥ ተጠሪ ይቀመጣል። የማስቀመጥ፣ የማስነሳት፣ የማስቀየር ወይም ከዚህ ያለፈ ስልጣን፥ የጠሪው ነው።

ማንንም፥ በምንም መንገድ ወይም መልኩ፥ ለማስቀመጥ፣ ለማስነሳት ለማስቀየር አለያም....፥ ጥረት ላይ ያለን ሰዎች፥ በተቻለ አቅም፥ ቀዝቀዝ ብንል መልካም ነው። ስልጣኑ የእኛ አይደለም። ጠሪው ካላይ እያየን ነው፣ ሁላችንንም የጠራው!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በነ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 81
መልዕክት (message) 81
የሆነማ፥ የጎደለ ነገር አለ...!

መጽሐፍ ሲናገር "አሥር ድሪም ያላት አንድ ድሪም ቢጠፋባት መብራት አብርታ ቤትዋንም ጠርጋ እስክታገኘው...አጥብቃ የማትፈልግ ሴት ማን ናት? ባገኘችውም ጊዜ ወዳጆችዋንና ጐረቤቶችዋን በአንድነት ጠርታ ... ድሪሜን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ ትላቸዋለች" ይላል። (ሉቃ 15:8-9)

በጉድለት ማጌጥ አይቻልም።ማጌጥ በሙላት ነው። ከነበረን ነገር አንድ ነገር ከጎደለ፥ ሙሉነት የለም። ቀድሞ ወደነበረን አሁን ግን ወደ አጣነው ነገር መመለስ አለብን።ባለታሪኳ ሴት ከአሥር ድሪም፥ አንድ ነው የጠፋባት፤በቀራት ዘጠኝ ማጌጥ አልቻለችም፣ እርሷ የለመደችው በአሥር ነው።

ወገኖቼ በጉድለት መኖር ይበቃል። ወደ ቀድሞው ሙሉነት፥ እንመለስ። መጽሐፍ "የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፥ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃል"ይላል(ራዕ 2:4)፤ የሆነማ የጎደለ ነገር አለ!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 82
መልዕክት (message) 82
አደራችንን እንወጣ..........!

ጌታ ኢየሱስ “በሌላ ሰው ገንዘብ ካልታመናችሁ፥ የእናንተን ማን ይሰጣችኋል?” ይላል። (ሉቃ 16:12)

በብዙዎቻችን እጅ ላይ፥የግለሰብ፣ የተቋም፣ የሕዝብ፣ የአገር ወዘተ ገንዘብ ወይም ንብረት ወይም ደግሞ አደራ አለ።ሁሉን ተቀብለን ነው። መጽሐፍ “ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? .... እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድር ነው?”ይላል (1ቆሮ 4:7)። “ሳይማር ያስተማረን ማሕበረሰብ”፥ የሚል ብሂልም አለ።

የራሳችን የሆነ ነገር ለመያዝ እና ራሳችን ነገር ላይ ለመድረስ ፥ አንድ ነገር ማድረግ ይጠበቅብናል። በቅድሚያ አደራችንን እንወጣ፤ የራስ አደራ፣ የሕዝብ አደራ፣ የአገር አደራ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 83
መልዕክት (message) 83
ክብር እና አድናቆት የማሰባሰብ ዘመቻ

ጌታ ኢየሱስ ፈሪሳውያንን እንዲህ አላቸው “ራሳችሁን በሰው ፊት የምታጸድቁ...ናችሁ፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ልባችሁን ያውቃል፤ በሰው ዘንድ የከበረ በእግዚአብሔር ፊት ርኩሰት ነውና።” (ሉቃ 16:15)

ክብር እና አድናቆትን፥ በልዩ ልዩ መንገድ ከሰው የማሰባሰቡ ዘመቻ ይበቃል ባይ ነኝ።በእግዚአብሔር ዘንድ፥ርኩሰት ከሆነ ትርፍ የለውም።ጌታ ሆይ፥ እያንዳንዳችን ምን እያደረግን ነው ? እባክህ እርዳን፣ እራራልንም!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 84
መልዕክት (message) 84
ምህረት እናድርግ፣ እንደራረግ

ጌታ ኢየሱስ ሲናገር “ሚስቱንም የሚፈታ ሁሉ ሌላይቱንም የሚያገባ ያመነዝራል፥ ከባልዋም የተፈታችውን የሚያገባ ያመነዝራል።” ይላል። (ሉቃ 16:18)

መፋታት በራሱ፥ ፈትቶ ሌላ ከማግባት በንጽጽር እንደ ጽድቅ እሚቆጠርበት አሰራር ላይ ደርሰናል። ያም ሆነ ይህ መጽሐፍ “መፋታትን እጠላለሁ” ይላል። (ሚልክ 2:16)

ሰው እግዚአብሔር እሚጠላውን መንገድ መርጦ፥ በየትኛው ቃል ነው እየኖረ ያለው? የቃል ሰው ነን እያልን፥ በሌለ ቃል ሕይወት መምራት፥ይከብዳል።ክርስቶስ ራሱ ቤተክርስትያንን ላይፈታት፥ ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጥቷል።(ኤፌ 5:26)

ምነው እኛ፥ ስለ አንድ፥ ስለ አገባነው ሰው ራሳችንን አሳልፈን መስጠት አቃተን? ቢያንስ፥ ምህረት እናድርግ፣ እንደራረግ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 85
መልዕክት (message) 85
ወዮለት፥ እየተባለ ነው.......!

ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ አለ"መሰናክል ግድ ሳይመጣ አይቀርም፥ ነገር ግን መሰናክሉን ለሚያመጣው ወዮለት።" (ሉቃ 17:1)

ብዙ ሰዎች የቀድሞ ቅንነታቸውን፣ ንጽሀናቸውን፣ ትጋታቸውን ፣በጎነታቸውን፣ ታማኝነታቸውን፣ ቸርነታቸውን፣ወዘተ፥ጥለዋል። ከዚህ ነገር ጀርባ፥መሰናክል የሆነና ተጠያቂ አካል አለ።ለዚያ አካል ወዮለት እየተባለ ነው።

በስብከታችን፣በትምህርታችን፣በስልጣናችን፣በመልዕክታችን ፣በፕሮግራማችን፣በአገልግሎታችን፣በንግግራችን፣በይታችን፣ በባህርያችን፣ በጽሁፋችን፣ በጫካኔያችን፣ በንቀታችን፣ወዘተ ስንት ሰው አሰናክለን ይሆን?

ድሮ ድሮ፥ ያሰናከለ ሰው ነበረ የሚሸማቀቀው። አሁን ዘመኑ ተሻሽሎ፥ ለአሰናካዩም ጭምር የሚሸማቀቀው፥ ተሰናካይ ሆኗል። ዘንድሮ የደፈረ ጀግና ነው፣ "ክብራቸው በነውራቸው ነው" አለ መጽሐፍ(ፊልጵ 3:19)፤ለሁላችንም ምህረት ይሁን!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 86
መልዕክት (message) 86
ዘጠኙስ ወዴት አሉ..........?

ጌታ ኢየሱስ ወደ አንዲት መንደር ሲገባ አሥር ለምጻሞች ተገናኙትና እየጮኹ “ኢየሱስ ሆይ፥ አቤቱ፥ ማረን” አሉ። አይቶም “ሂዱ፥ ራሳችሁን ለካህናት አሳዩ” አላቸው። ጥቂት ቆይቶ፥ አንዱ ብቻ ለምስክርነት ተመለሰ። ኢየሱስም መልሶ “አሥሩ አልነጹምን? ዘጠኙስ ወዴት አሉ?...”አለ፥ ይላል። (ሉቃ 17:12-18)

ወደ ጌታ ቤት ስንት ለምጻም ሰው መጥቷል? ሳይነጻ የቀረስ ማን ነው? ሁሉ ነጽቷል።ጥያቄው፥አብዛኛው ሰው ከነጻ በኋላ ስፍራው ላይ የለም። ምን ወሰደው?

ሐዋርያው ጳውሎስ “ዴማስ የአሁኑን ዓለም ወዶ ትቶኛልና፥” ይላል። (2 ጢሞ 4:10)። ሲመስለኝ፥ ብዙ ሰው፥ መመለስ ያልቻለው፥ እንደ ዴማስ፥በወደደው ነገር ተጠምዶ ነው። ጌታ ባለንበት ምህረቱን ያብዛ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 87
መልዕክት (message) 87
የሚያዋጣው፥ ኋላን መርሳት ነው!

ጌታ ኢየሱስ፥ ወደ ኋላ የመመለስን አደገኛነት ሲያመለክት “የሎጥን ሚስት አስቡአት” ይላል። (ሉቃ 17:32)

መጽሐፍ “የሎጥም ሚስት ወደ ኋላዋ ተመለከተች፥ የጨው ሐውልትም ሆነች” ይላል (ዘፍ 19:26)

ሕይወት ወደ ፊት ነው፣ሕይወት ወደ ኋላ የለም።በዚህ ዘመን አያሌ ሰዎች፥ እንደ ሎጥ ሚስት፥ የጨው ባይሆንም፥ የሆነ ሐውልት ሆነዋል። አኗኗራቸው በትዝታ፣ በታሪክ፣ በተፈጠረ ትርክት፣ ወዘተ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ሲመክር “በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ። በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ።” ይላል (ፊልጵ 3:13-14)። የሚያዋጣው ወደ ኋላ መመለስ ሳይሆን፥ ኋላን መርሳት ነው!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 88
መልዕክት (message) 88
ዋ! እዛው፥ እንዳትቀሩ............!

ጌታ ኢየሱስ ሲናገር “በዚያች ሌሊት ሁለት ሰዎች በአንድ አልጋ ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል ሁለተኛውም ይቀራል” አለ።
(ሉቃ 17:34)

በአንድ አልጋ አብረን ስለተኛን፥አንድ ላይ አንነጠቅም። አንድ ላይ ስለአበርን ውጤታችን አንድ ነው ማለት አይደለም።አንድ ላይ ስለዘመትን፥ሽልማቱ አንድ ነው ማለት አይደለም። አንድ ተቋም ላይ አብረን ስለሠራን እኩል ነን ማለት አይደለም። መረሳት የሌለበት ነገር “ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና” (ገላ 6:7)።

ከማንም ጋር እንሥራ፥ከማንም ጋር እናገልግል፣ ከማንም ጋር እንኑር፣ ከማንም ጋር ለመሆን እድል ይግጠመን፣... ውጤቱ የሚወሰነው፥ እንደ ዘራነው ዘር ነው። በቡድን የሚታይ ፍርድ የለም፣ እኩልነትም የለም። አንድ አልጋ ላይ የተኛችሁ (አንድ ርእዮተ-ዓለም የምታራምዱ) ንቁ፣ ትጉ፣ የምትወሰዱበትን መልካም ሃሳብ አራምዱ፥ተግብሩትም፤ዋ! እዛው፥እንዳትቀሩ!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 89
መልዕክት (message) 89
መጮኽ እና መጮኽ........!

ጌታ ኢየሱስ “እግዚአብሔር እንኪያስ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ ለሚታገሣቸውም ምርጦቹ አይፈርድላቸውምን? እላችኋለሁ፥ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል”ሲል፥ ስለ ሚጸልዩ ሰዎች ተናገረ። (ሉቃ 18:7-8)

እነማን ናቸው ምርጦች? ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ የሚጮኹ።

ወገኖቼ፥ ቀሪውን ዘመን፥ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ እንጩኽ! መጽሐፍ “ወደ እኔ ጩኽ፥ እኔም እመልስልሃለሁ፤ አንተም የማታውቀውን ታላቅና ኃይለኛ ነገርን አሳይሃለሁ” እያለ ነው። (ኤር 33:3)

ታላቅና ኃይለኛ ነገር ሰናይ ዘመኑ ነጎደ። ታላቅና ኃይለኛ ነገር ውስጥ የሚገባው፥ ወደ እርሱ ቀንና ሌሊት በመጮኽ እና በመጮኽ ብቻ ነው። ሌላውን ነገር እንተወው፤ ትርፉ ኪሳራ ነው። አይመስላችሁም?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 90
መልዕክት (message) 90
ሞቶ ግን አልቀረም..........!

ጌታ ኢየሱስ “ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፥ ራሱን ግን የሚያዋርድ፥ ከፍ ይላል።” ይላል። (ሉቃ 18:14)።

ምን ሙያ ላይ ተሰማርታችኋል? እንዴትስ ነው፥ አገልግሎት የምትሰጡት? በተሰማራችሁበት መስክ፥ ሩጫው ራስን ከፍ ለማድረግ ነው? ራስን ከፍ ለማድረግ፥ ታቅዶ የሚደረግ ማናቸውም ሃሳብም ሆነ እንቅስቃሴ፥ መጨረሻው ውርደት ነው። የያዝነው ዘመን ጉልህ ማሳያ ነው።

መጽሐፍ ስለ ዲያብሎስ ውርደት ሲናገር “አንተም በልብህ፥ ወደ ሰምይ ዐርጋለሁ፥ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ...አደርጋለሁ፥ከዳመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፥ በልዑልም እመስላለሁ አልህ። ነገር ግን ወደ ሲኦል ወደ ጉድጓዱም ጥልቅ ትወርዳለህ። ይላል፥ (ኢሳ 14:13-15)

ቃሉ “ራሱን ግን የሚያዋርድ፥ ከፍ ይላል”እያለን ነው። የሞተ እንዳለ እንዳትረሱ፥ እሱም ኢየሱስ። ሞቶ ግን አልቀረም። ተነስቷል!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በነ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 91
መልዕክት (message) 91
ሽማቂዎች (በቃል የሚያጠምዱ)

መጽሐፍ፥ የካህናት አለቆችና ጻፎች፡ ጌታ ኢየሱስን" ወደ ገዢ ግዛትና ሥልጣን አሳልፈው እንዲሰጡት ጻድቃን መስለው በቃሉ የሚያጠምዱትን ሽማቂዎች ሰደዱበት።" ይላል። (ሉቃ 20:20)

በቃል የሚያጠምዱ ሽማቂዎች ዛሬ የሉም ትላላችሁ? አሉ እንጂ። ተመጣጥኖ (balance) አድርጎ ለመሄድ የነርሱ መኖር የረዳ ይመስላል።የመልዕክተኞች(በለራዕዮች)መኖር የሽማቂዎች (የአሳልፎ ሰጪዎች) የሥራ በር ነው ባይ ነኝ። ሕይወት አንጻራዊ አይደል።

ሐዋርያው ጳውሎስም በዚህ ጉዳይ ሲናገር "ሥራ የሞላበት ትልቅ በር ተከፍቶልኛልና ተቃዋሚዎችም ብዙ ናቸው" ይላል (1ቆሮ 16:9)። ተቻችሎ መሄድ ነው፣ ርዳታው የጌታ ነው።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 92
መልዕክት (message) 92
የሚሰጥ ብፁዕ ከሆነ፥ የማይሰጥ ምንድን ነው?

መጽሐፍ ሲናገር ጌታ ኢየሱስ “ዓይኑንም አንሥቶ መባቸውን በመዝገብ የሚጥሉ ባለ ጠጎችን አየ፤አንዲትም ድሀ መበለት ሁለት ሳንቲም..ስትጥል አየና እውነት እላችኋለሁ ይህች ድሀ መበለት ከሁሉ ይልቅ አብልጣ ጣለች፤” አለ። (ሉቃ 21፡1-3)

መስጠት እከሌ ከእከሌ አይልም፣ ባለ ጠጋም፣ መበለትም፣ ማንም ይሰጣል፣ መስጠትም አለበት። ጥያቄው፥ መስጠት የማን ባህሪ ነው? ነው። ስለ መስጠት ስናወራ፥ የምናወራው ስለ እግዚአብሔር ነው።

መጽሐፍ “እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ” ይላል። (1 ጢሞ 4:7)። አንዱ እግዚአብሔርን ለመምሰል ራሳችንን የምናስለምድበት መንገድ የመስጠት ሕይወት ነው ።ለነገሩ የምንሰጠው የተቀበልነውን እንጂ እኛ እምንፈጥረው ነገር የለም፣መጽሐፍ“ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ?”ይል የለ፤ (1 ቆሮ 4:7)። “የሚሰጥ ብፁዕ ነው” (ሐዋ20:35)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 93
መልዕክት (message) 93
ማምለጫ መንገድ ተገኘ!

ጌታ ኢየሱስ"ልባችሁ በመጠጥ ብዛትና በስካር ስለ ትዳርም በማሰብ እንዳይከብድ፥ ያ ቀንም ድንገት እንዳይመጣባችሁ፤...ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ፥በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትጸልዩ ሁል ጊዜ ትጉ።" አለ። (ሉቃ 21:34-36)

ምን እያሰብን እና ምን እየሠራን ነው? የሚያስመልጠን ነው? ከላይ እንደተገለጸው "ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ ... እንድትችሉ ስትጸልዩ ሁል ጊዜ ትጉ"ተብሏል፤የጸሎት ሕይወታችሁን ቆም ብላችሁ ተመልከቱ።ማምለጫ ነው፣ግን ጊዜ ትወስዳላችሁ? ከሌላው የዕለት ከዕለት ተግባር የተሻለ ጊዜ ትሰጡታላችሁ? ከሆነ ታመልጣላችሁ። ዕለት በዕለት እየሠራችሁት ነገር ግን እማያስመልጥ አጀንዳ ምድራዊ ነው፣በመጠን ይደረግ፥በቃ!

መጽሐፍ "ገንዘብን እንጀራ ላይደለ፥ የድካማችሁንም ዋጋ ለማያጠግብ ነገር ለምን ትመዝናላችሁ?"ይላል።(ኢሳ 55:2) ስለዚህ ወገኖቼ፥ አሁን ተግተን ጸለይን ማለት፡ አምልጠናል!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 94
መልዕክት (message) 94
አሳልፎ ለመስጠት አንቀናጅ!

ኢየሱስ ከየት ነው? “ጲላጦስ ግን ‘ገሊላ’ ሲሉ በሰማ ጊዜ ከሄሮድስ ግዛት እንደ ሆነ ባወቀ ጊዜ ወደ ሄሮድስ ሰደደው ...ሄሮድስና ጲላጦስም በዚያን ቀን እርስ በርሳቸው ወዳጆች ሆኑ፤ ቀድሞ በመካከላቸው ጥል ነበረና” (ሉቃ 23:6-12)።

በዚህም ዘመን የማይወዳጁ ሰዎችም ሆኑ ቡድኖች የጋራ ጠላታችን ነው በሚሉት አካል ምክንያት መወዳጀት ብሎም መቀናጀትን ባህል አድርገውታል።

መቀናጀት ለለውጥ (ለልማት) አንጂ፤ ለመቃወም ወይም አሳልፎ ለመስጠት (ለማጥፋት) አይሁን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 95
መልዕክት (message) 95
እምንለውን እንኑር.............!

መጽሐፍ “እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።” ይላል። (ዮሐ 1:18)

“ልጅ ነኝ” ብሎ ማውራት(confession) ልጅነት አይደለም፤ ልጅነት አባትን መተረክ ነው። መተረክ ማለት ደግሞ ቃሉን መኖር ነው። ያልኖሩትን ሕይወት የሚያስተምሩ(የሚሰብኩ)፥ ተራኪዎች ሳይሆኑ ዜና አንባቢዎች ናቸው። ‘ዜና አንባቢዎች’ የሚለው አባባል ባለሙያዎቹን አያመለክትም።

እምንለውን እንኑርና እግዚአብሔርን እንተርከው። ያንጊዜ፥ ልጅ መሆናችን ይታወቃል፤ያልተኖረ ሕይወት እግዚአብሔርን አይተርክም።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 96
መልዕክት (message) 96
የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ሆነ!

መጥምቁ ዮሐንስ “እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራልና፤” ይላል። (ዮሐ 3:34) በሌላ ስፍራ ደግሞ መጽሐፍ ሲናገር“ከራሱ የሚናገር የራሱን ክብር ይፈልጋል፤ የላከውን ክብር የሚፈልግ ... እርሱ እውነተኛ ነው በእርሱም ዓመፃ የለበትም” ይላል። (ዮሐ 7:18)

እንግዲህ ንግግር ከእግዚአብሔር በመላክ ነው፥ አልያም ከራስ ነው። ከእግዚአብሔር ሲሆን፥ ክብሩ የእግዚአብሔር፣ ከራስ ሲሆን፥ ክብሩ የራስ ነው።

ከዚህ አንፃር፥ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የአገራችን አገልግሎት ብላቴናው ሳሙኤል በዔሊ ፊት እግዚአብሔርን ሲያገለግል የተፈጠረውን ያስታውሰኛል፣ “በዚያ ዘመን የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ነበረ” ይላል(1ሳሙ 3:1)። በእኛ ብርቅ አልሆነም ትላላችሁ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 97
መልዕክት (message) 97
የጉድለት ጥማት እያቃጠለን ነው

ሳምራዊቲቱ ሴት ጌታ ኢየሱስን “አንተ የይሁዳ ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ መጠጥ እንዴት ትለምናለህ?” አለችው። አይሁድ ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩም ነበርና። ኢየሱስ መልሶ “የእግዚአብሔርን ስጦታና። ውኃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን መሆኑንስ ብታውቂ፥ አንቺ ትለምኚው ነበርሽ የሕይወትም ውኃ ይሰጥሽ ነበር” አላት። (ዮሐ 4:9-10)

መተባበር ነው የሚያዋጣው።ሁሉ ነገር የለንም። የሚጎድለን ነገር አለ።ሌላው ነው የሚሞላልን።ሴቲቱ የጉድጓድ ውኃ ነው ያላት፤ኢየሱስ ግን የሕይወት ውኃ።የጉድጓድ ውኃ ጥሩ ነው፤ የሕይወት ውኃ ደግሞ የበለጠ።

ባለመተባበራችን (በመለያየታችን) የጉድለት ጥማት በጣም እያቃጠለን ነው። ሁላችንንም ጌታ በምህረቱ ይርዳን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 98
መልዕክት (message) 98
መኖር ለመብላትና ለመጠጣት?

ደቀ መዛሙርቱ ጌታ ኢየሱስን “መምህር ሆይ፥ ብላ” ብለው ለመኑት።እርሱ ግን “እናንተ የማታውቁት የምበላው መብል ለእኔ አለኝ  አላቸው። … ደቀ መዛሙርቱ፥ የሚበላው አንዳች ሰው አምጥቶለት ይሆንን?ተባባሉ።ኢየሱስም “የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው” አለ ። (ዮሐ 4:31-34)

የእኛ መብል ምን ይሆን? የማንን ፈቃድ እያደረግን ይሆን? እንደ ደቀ መዛሙርቱ ለእንጀራ ብቻ እየሮጥን ይሆን? እንደዛ ከሆነ ከሰው ሁሉ ምስኪን ነን።መኖር ለመብላት፣ለመጠጣት ፣ለመልበስ፣ ወዘተ ከሆነ ከተክሎች አልተሻልንም።

በቀረው እድሜያችን፥ የእርሱን ፈቃድ እናድርግ። በመጨረሻ ወደ እሱ ለመሰብሰብም አይደል መሻታችን? ሰው እንዴት የእርሱን ፈቃድ ሳያደርግ ኖሮ፥ መጨረሻ እርሱ ጋ ለመሄድ ያቅዳል? “አላውቃችሁም”የሚል ነገር የመጣው ለዚህ ነው!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 99
መልዕክት (message) 99
ወደ ቃል ክብር እንደግ.......!

ጌታ ኢየሱስ፥ በቅፍርናሆም ልጁ ለታመመበት ከንጉሥ ቤት ለሆነ ሹም "ምልክትና ድንቅ ነገር ካላያችሁ ከቶ አታምኑም" አለው።ሹሙም"ጌታ ሆይ፥ብላቴናዬ ሳይሞት ውረድ"አለው። ኢየሱስም "ሂድ፤ ልጅህ በሕይወት አለ አለው።" ሰውዬውም ኢየሱስ የነገረውን ቃል አምኖ ሄደ። ሲወርድም ሳለ ባሮቹ ተገናኙትና "ብላቴናህ በሕይወት አለ" ብለው ነገሩት። (ዮሐ 4:48-51)

የሹሙ ብላቴና የተፈወሰው በቃል ነው።ፈውሱ ምልክት ነው ፣ፈውሱ ድንቅ ነው።ፈውስም ሆነ ድንቅ ከቃል ውጪ የለም። እንደ ክርስትያን ማደግ ያለብን ወደ ቃል ክብር ነው። ሹሙ "ብላቴናዬ ሳይሞት ውረድ"ነው ያለው።ጌታ ግን አልወረደም ፤ቃል ነው የተናገረው። በዚያው ሰዓት ብላቴናው ተፈውሷል።

እንዲህ ያለ፣ ከፍ ያለ አገልግሎት አልናፈቃችሁም? የወቅቱ አገልግሎት ከዚህ በኋላ ስንት ዓመት ያስቀጥለን ይሆን?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 100
መልዕክት (message) 100
የሚብስ ነገር እንዳይደርስብን!


ቤተ ሳይዳ በምትባል አንዲት መጠመቂያ ከሠላሳ ስምንት ዓመት ጀምሮ የታመመ አንድ ሰው ነበረ። ኢየሱስ “ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ።” አለው። ቆይቶ ኢየሱስ በመቅደስ አገኘውና “ድነሃል፤ ከዚህ የሚብስ እንዳይደርስብህ ወደ ፊት ኃጢአት አትሥራ” አለው።(ዮሐ 5:2-14)

መጽሐፍ “ስሕተትን ማን ያስተውላታል? ከተሰወረ ኃጢአት አንጻኝ፤ የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ” ይላል። (መዝ19፥12-13)

ስህተት ሲያድግ የተሰወረ ኃጢአት ይሆናል፤ ከዚያ ሲልቅ የድፍረት ኃጢአት ይጀመራል። አሁን የተደረሰው የድፍረት ኃጢአት ላይ ነው። ሁሉን በድፍረት ማድረግ። በድፍረት መተንበይ፣ በድፍረት መናገር፣ በድፍረት...፣በድፍረት... ለሁሉ ድፍረት፣ አቅም (ብቃት) አይጠየቅም። አልታወቀንም እንጂ ኃጢአት ላይ ነን፣ አዘቅት (የባሰ ነገር) ውስጥ እየገባን ነው። የሚብስ ነገር እንዳይደርስብን፥መፍትሄው ከኃጢአት መራቅ ነው።(መዝ19፡13)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




Aynalem Mersie

PART 101
መልዕክት (message) 101
እግዚአብሔር በእርሱ አይገለጥም!

ኢየሱስ እንዲህ አለ “አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ።” (ዮሐ 5:17)

ሰው “አባቴ እግዚአብሔር” ነው ካለ፥አንዱ ማረጋገጫ ሥራን መሥራት (ኃላፊነትን መወጣት) ነው። እግዚአብሔርን እውን መግለጥ  የሚፈልግ ሰው፥ከኢየሱስ ተምሮ ሥራውን ይሥራ

መጽሐፍ “ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበርና። ሥራ ከቶ ሳይሠሩ፥ በሰው ነገር እየገቡ፥ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናል።እንደነዚህ ያሉትን በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን እንመክራቸውማለን” ይላል። (2 ተሰ 3:10-12)

ሥራ የማትሠሩ፣ ከመሥራት ይልቅ በሰው ነገር የምትገቡ፣ ከዚህ የተነሳ ያለ ሥርዓት የምትሄዱ፣እባካችሁ በጸጥታ ሥራ ሥሩ፣ የገዛ እንጀራችሁን ብሉ። ያኔ እግዚአብሔር በእናንተ ይገለጣል። ሊሠራ በማይወድ ሰው፥ እግዚአብሔር በእርሱ አይገለጥም!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 102
መልዕክት (message) 102
የተረገመ ይሁን..................!


ጌታ ኢየሱስ ሲናገር “ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም።” አለ። (ዮሐ 5:24)

ማነው አሁኑኑ የዘላለም ሕይወት የሚፈልግ? ማነው አሁኑኑ ከሞት ወደ ሕይወት፥ መሻገርን የሚፈልግ? ማነው አሁኑኑ፥ ከፍርድ ማምለጥ የሚፈልግ? መፍትሄው አንድና አንድ ብቻ ነው፣የጌታ ኢየሱስን ቃል መቀበል እና በላከው ማመን ነው።

እውነትን የምትፈልጉ፣ እውነትን የተጠማችሁ፣ እውነቱ ይሄ ብቻ ነው። ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከዚህ የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን። (ገላ 1:8)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




**Aynalem Mersie**

PART 103
መልዕክት (message) 103
መዘከር ይበቃል................!

ሕዝቡ ኢየሱስን“እንግዲህ የእግዚአብሔርን ሥራ እንድንሠራ ምን እናድርግ?” አሉት። ኢየሱስ መልሶ“ይህ የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው” አላቸው። (ዮሐ 6:28-29)

እንግዲህ የሆነ ነገር ሠርተን ነው እምንድነው (ሠርተን ነው የምንጸድቀው) ለሚል ሁሉ፥ የምሥራች፥ ሥራው ታውቋል፣ ሥራውም ከላይ በተላከው(በኢየሱስ ክርስቶስ)ማመን ነው። “ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው፤ ከምድር የሚሆነው የምድር ነው፥የምድሩንም ይናገራል። ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው።” (ዮሐ 3:31)

ከምድር የተነሱትን መዘከር ይበቃል። ሁሉ ሞተዋል። ከላይ የመጣው፣ የሞተው፥ ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።” (ሮሜ 8:34)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 104
መልዕክት (message) 104
ጌታ መለኪያውን ተናገረ.......!


አይሁድ “ይህ ሰው ሳይማር መጻሕፍትን እንዴት ያውቃል?” ብለው ይደነቁ ነበር። ስለዚህ ኢየሱስ መለሰ “ትምህርቴስ ከላከኝ ነው... ከእኔ አይደለም፤ ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር፥ እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ያውቃል።” አለ። (ዮሐ 7:15-17)

እንደ አይሁድ፥ መንፈሳዊ ነገርን የትምህርት ክ/ጊዜ(class) ይዞ የተማረ ሰው፥ ድንገት መልዕክተኛ ሆነህ ስትመጣ ግር ይሰኛል፣ ከዛ ጥያቄ ያነሳል “ሳይማር” ይላል። ራሱ ጥያቄው የሚነሳው ከምቀኝነት ሳይሆን፥ ጌታ ኢየሱስ እንዳለ፥ ፈቃዱን ለማድረግ ካለመውደድ ነው። ፈቃዱን ለማድረግ የሚወድ ግን፥ መልዕክቱ ከእግዚአብሔር ይሁን ወይም ተልኬአለሁ ከሚለው፥ ብቻ ከማናቸው እንደሁ በቀላሉ መለየት ይችላል።

ይህን መልዕክት እንኳ ወንጌል ነው ብሎ ለመቀበል ፈቃዱን ለማድረግ መውደድ በቂ መስፈርት ነው።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!






**Aynalem Mersie**

PART 105
መልዕክት (message) 105
ቀርቶ የሚያጽናና አለ...........!

ጻፎችና ፈሪሳውያንም በምንዝር የተያዘችን ሴት ወደ እርሱ አመጡ “ይህች ሴት ስታመነዝር ተገኝታ ተያዘች። ሙሴም እንደነዚህ ያሉት እንዲወገሩ በሕግ አዘዘን፤ ስለ እርስዋ ምን ትላለህ?” አሉት። “ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት አላቸው” ደግሞም ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ። (ዮሐ 8፡3-8)

አንድ አንድ እያሉ ወጡ። ኢየሱስም ብቻውን ቀረ። ሴቲቱም በመካከል ቆማ ነበር፤ ቀና ብሎ ከሴቲቱ በቀር ማንንም ባላየ ጊዜ “አንቺ ሴት፥ እነዚያ ከሳሾችሽ ወዴት አሉ? የፈረደብሽ የለምን? ” አላት። እርስዋም “ጌታ ሆይ፥ አንድ ስንኳ” አለች ኢየሱስ “እኔም አልፈርድብሽም፤ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ” አላት። (ዮሐ 8፡9-11)

የከበባችሁ፣ ያስጨነቃችሁ፣ የተቃወማችሁ፣ የተሰለፈባችሁ ሁሉም አንድ አንድ እያለ ይሄዳል። የማይፈርደው፣እሚራራው ፣ ቀርቶ እሚያጽናናው ኢየሱስ ብቻ ነው። አለ እሱ፤ አይዞን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 106
መልዕክት (message) 106
በማጥናት ጊዜ ማቃጠል፥ በቃ!

ኢየሱስ ሲናገር “ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤ ሕያው የሆነ የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም” አለ። (ዮሐ 11፡25-26)

አሁን ትንሳኤ ሃሳብ ሳይሆን አካል ነው። ሕይወትም ሃሳብ ሳይሆን አካል ነው፤ትንሳኤም ሆነ ሕይወት የተባሉት ጉዳዮች አካል አላቸው፣ ተጨባጭ ሆነዋል። ከዚህ በኋላ “ትንሳኤ ምንድን ነው?” አይባልም፥ ትንሳኤ ራሱ ኢየሱስ ነው። ከዚህ በኋላ “ሕይወት ምንድን ነው?” አይባልም፥ ሕይወት ራሱ ኢየሱስ ነው።

ሞትን ማየት የማይፈልግ፣ ሕይወትን ማጣጣም የሚፈልግ ቀጥታ ወደ አካሉ (ወደ ኢየሱስ) መምጣት ነው። ስለ ትንሳኤ ወይም ስለ ሕይወት በማጥናት ጊዜ ማቃጠል በቃ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 107
መልዕክት (message) 107
ይወደናል (ይወድሃል/ይወድሻል!

አልዓዛር ከሞተ ከአራት ቀን በኋላ፥ እህቱ ማርያም፥ ኢየሱስ መጥቶ ባየችው ጊዜ በእግሩ ላይ ወድቃ “ጌታ ሆይ፥ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር” አለችው። ኢየሱስም እርስዋ ስታለቅስ ከእርስዋም ጋር የመጡት አይሁድ ሲያለቅሱ አይቶ በመንፈሱ አዘነ በራሱም ታወከ። ... እንባውን አፈሰሰ። ስለዚህ አይሁድ፦

“እንዴት ይወደው እንደ ነበረ እዩ” አሉ። (ዮሐ 11:32-36)

ልክ ነው፥ ኢየሱስ በጣም ይወደናል (ይወድሃል/ይወድሻል)!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 108
መልዕክት (message) 108
የክብር ጊዜ ሲመጣ............!

“አንቺ የጽዮን ልጅ አትፍሪ፤ እነሆ፥ ንጉሥሽ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ ይመጣል” ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ ኢየሱስ የአህያ ውርንጫ አግኝቶ በእርሱ ተቀመጠ። ደቀ መዛሙርቱ ይህን ነገር በመጀመሪያ አላስተዋሉም፤ ነገር ግን ኢየሱስ ከከበረ በኋላ በዚያን ጊዜ ይህ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይህንም እንዳደረጉለት ትዝ አላቸው። (ዮሐ 12:14-16)

አንድ አንድ ሰው አሁን የተቀመጠበት ወይም ያለበትን ሁኔታ ማንም ልብ ሊለው አይችል ይሆናል። የክብር ጊዜ ሲመጣ ግን፥ ቢፈለግም ባይፈለግም ይታወሳል። ለሁሉ ጊዜ አለው!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

በርሳቸንART 109
መልዕክት (message) 109
እስከ ፍጻሜው ድረስ...........!

መጽሐፍ ሲናገር “ይህን ያህል ምልክት በፊታቸው ምንም ቢያደርግ፤ ነቢዩ ኢሳይያስ ‘ጌታ ሆይ፥ ማን ምስክርነታችንን አመነ?የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገለጠ?’የሚለው ቃል ይፈጸም ዘንድ በእርሱ አላመኑም” ይላል (ዮሐ 12:37-38)

አንድ አንድ ጊዜ ምንም እውነት የሆነ ነገር ብትናገር፥ ወይም እውነት የሆነ ነገር ብትሠራ ሰዎች አያምኑህ ይሆናል፥ ችግር የለም፤ መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡-

“አንተ ግን እስከ ፍጻሜው ድረስ ሂድ፤ አንተም ታርፋለህ፥ በቀኑም መጨረሻ በዕጣ ክፍልህ ትቆማለህ።”(ዳን 12:13)

መልዕክቱን መሞገት፤ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 110
መልዕክት (message) 110
ጠብ፣ ክርክር፣ ተቃውሞ ያበቃለታል!


ኢየሱስም ጮኸ፥ እንዲህም አለ “በእኔ የሚያምን በላከኝ ማመኑ ነው እንጂ በእኔ አይደለም፤ እኔንም የሚያይ የላከኝን ያያል።” (ዮሐ 12:44-45)

በዚህ ዘመን ጎልቶ የሚታየው የመሪ እና የተከታዮች ግጭት የተፈጠረው፥ ላኪውን ካለማመን ወይም ካለማየት የመነጨ ይመስለኛል። ኢየሱስም የጮኸው ለዚህ መሰለኝ።

እምነታችንንም ሆነ እይታችንን በላኪው ላይ እናድርግ ያን ጊዜ፥በማንም ላይ የተስተካከለ እምነት እና እይታ ይኖረናል። ጠብና ክርክር እንዲሁም ተቃውሞ፥ ያኔ፥ ያበቃለታል!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




**Aynalem Mersie**

PART 111
መልዕክት (message) 111
ማቋረጥ የለም..................!

ስምዖን ጴጥሮስም ኢየሱስን “ጌታ ሆይ፥ አንተ የእኔን እግር ታጥባለህን?” አለው። ኢየሱስም መልሶ “እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቅም፥ በኋላ ግን ታስተውለዋለህ” አለው። (ዮሐ 13:6-7)

የአንድ አንድ መንፈሳዊ እንቅስቃሴያችንን (ተግባራችንን) ውጤት አሁን ላናውቀው ወይም ላናስተውለው እንችላለን፥ በኋላ ግን ማስቸዋላችን አይቀርም። ስለዚህ ምን እናድርግ?

መጽሐፍ “አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ፥ መከራን ተቀበል፥ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፥ አገልግሎትህን ፈጽም።” ይላል። (2 ጢሞ 4:5)። ስለዚህ ማቋረጥ የለም!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 112
መልዕክት (message) 112
ጌታ እንዳዘዘን እናድርግ......!

ጌታ ኢየሱስ ሲናገር “እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፥ ... እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል።እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና።” አለ (ዮሐ 13:14-15)

ከዚህ በኋላ አንዳችን አንዳችንን እናሳድፍ። ጌታ እንደ አዘዘን እርስ በርሳችን እግራችንን እንተጣጠብ፤አንዱ አንዱን አሳልፎ መስጠት ይብቃ። ኢሳይያስ “ምክርን ምከሪ፥ ፍርድን አድርጊ፤ በቀትር ጊዜ ጥላሽን እንደ ሌሊት አድርጊ፤ የተሰደዱትን ሸሽጊ፥ የሸሹትን አትግለጪ።” ይላል። (ኢሳ 16:3)

በጉዳዩ ላይ ወስናችሁ ወይም ፈርዳችሁ ለተቀመጣችሁ፥ መጽሐፍ “ምሕረትን ለማያደርግ ምሕረት የሌለበት ፍርድ ይሆናልና፤ ምሕረትም በፍርድ ላይ ይመካል።” ይላል (ያዕ 2: 13)። ጌታ ሆይ ለሁላችን ምህረት ይሁን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 113
መልዕክት (message) 113
ይሄ ነው ለእኔ ምርጫ..........!

ጌታ ኢየሱስ "እኔ የመረጥኋቸውን አውቃለሁ።" ይላል (ዮሐ 13:18)።በሌላ ስፍራ ደግሞ"እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤" ይላል (ዮሐ 15:16)።

በልዩ ልዩ አገሮች፥ በተለያየ ጊዜ አገራዊ ምርጫ ይካሄዳል። ባለን ተሞክሮ፥ ሁሉ ሰው መሪውን ለመምረጥ ምርጫ ካርድ ይወስዳል፣ ቀኑ ሲደርስ ተሰልፎ መሪውን ይመርጣል።

የኢየሱስ ይለያል። መሪ ሆኖ የምረጡኝ ቅስቀሳ አላደረገም። በምርጫ ካርድም አልመረጥነውም። ይገርማል! እርሱ ግን በካርድ ሳይሆን፥በክቡር ደሙ መረጠን። ይሄ ነው ምርጫ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 114
መልዕክት (message) 114
እውቅና ሊሰጣቸው ይገባል..!

ጌታ ኢየሱስ ሲናገር “እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ማናቸውን የምልከውን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፥ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል።” ይላል (ዮሐ 13:20)።

ከዚህ አንጻር፥ኢየሱስን የላከው አባቱ ነው፤ ኢየሱስ የላካቸው መልዕክተኞች ደግሞ በመካከላችን አሉ ማለት ነው።ስለዚህ ነው መጽሐፍ “ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?” የሚለው። (ሮሜ 10:15)

ሐዋርያው ጳውሎስ “ሰውን በክርስቶስ አውቃለሁ፥... እንዲህ ያለው ሰው ከአሥራ አራት ዓመት በፊት እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ።...” ይላል። (2 ቆሮ 12፡2-3)።

እኔም ባሳለፍኳቸው የአገልግሎት ዓመታት፣ የማይደጋገምና ወጥ የወንጌል መልዕክት እያስተላለፈ የመጣ መልዕክተኛ አውቃለሁ። ጳውሎስ እንዳለ፥ በሥጋ እንደ ሆነ ወይም ያለ ሥጋ እንደ ሆነ አላውቅም፥ እግዚአብሔር ያውቃል።እናንተም የምታውቋቸው እንደሚኖሩ አምናለሁ። ጌታ መልዕክተኞችን ያብዛልን። መጽሐፍ እንደሚል እኛም እውቅና እንስጣቸዋለን “እንግዲህ እንደነዚህ ያሉትን እወቁአቸው።” (1 ቆሮ 16:18)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 115
መልዕክት (message) 115
ሰው ሁሉ እርግጠኛ ሊሆን ይገባል!

ጌታ ኢየሱስ ሲናገር “እኔም አብን እለምናለሁ፥ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው፣... ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውሥጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ።” ይላል። (ዮሐ 14:15-17)

ሰው ሁሉ እንዲህ ያለው መንፈስ (መንፈስ ቅዱስ) በውስጡ መኖሩን እርግጠኛ ሊሆን ይገባል። ይሄ መንፈስ ከሌለ፥ ሌላ መንፈስ በውስጣችን አለ ማለት ነው።እራሳችንን እንመርምር ፤መጽሐፍ “ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር”
ይላል። (1ቆሮ 11:31)።

ይህንን መንፈስ ለመቀበል መሥፈርቱ ኢየሱስን መቀበል ነው። ራሱ ኢየሱስ “በሩ እኔ ነኝ” ብሏል (ዮሐ 10:9)።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 116
መልዕክት (message) 116
ልባችሁ አይታወክ፥ አይፍራም!

ጌታ ኢየሱስ “ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም። ልባችሁ አይታወክ አይፍራም።” ይላል (ዮሐ 14:27)።

ይህን የሚያነብ አንድ ሰው፥ የአገራችንን ነባራዊ ሁኔታ አይቶ “ለምን አልፈራም?ለምን አልታወክም? የት አለ ሰላሙ?”ሊል ይችላል። ጌታ ኢየሱስ የሚሰጠው ሰላም፥ ምንጩ ራሱ ጌታ ኢየሱስ ነው። ከራሱ ዓለም የሆነ ሠላም ነው። የዓለም እጅ ወይም የሰዎች ተሳትፎ የለበትም። የተኩስ አቁም ዓይነትም አይደለም። ከዚህ ዓለም ጋር አይገናኝም።

አትርሱ፥ “እሰጣችኋለሁ” ብሏል። ታዲያ እኛ ምን እናድርግ?

መጽሐፍ “ለምኑ ይሰጣችሁማል፤” ይላል (ማቴ 7:7)። ወሬ እንተው፤ ወደ እልፍኛችን እንግባ መዝጊያችንንም እንዝጋ። በስውር ወዳለው አባታችን እንጸልይ፤ በስውር የሚያይ አባት በግልጥ ይከፍለናል። (ማቴ 6:6)

መልዕክቱን መሞገት፤ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 117
መልዕክት (message) 117
ዝም ብሎ ሪቫይቫል የለም....!

ጌታ ኢየሱስ “እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤ ገበሬውም አባቴ ነው”(ዮሐ 15:1) ይልና “እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ” ይላል (ዮሐ 15:5)።

ለየት ያለው “ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል፤ፍሬ የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል።” የሚለው አባባሉ ነው። (ዮሐ 15:2)

ከዚህ በኋላ በግልጽ በምድራችን ላይ የምናየው ነገር ቢኖር በእርሱ ያለውን ቅርንጫፍ፥ ነገር ግን ፍሬ የማያፈራውን ሁሉ ያስወግደዋል፤ፍሬ የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል። ከተጠቀምንበት ጥቂት የንሰሐ ቀናት ሳይኖሩን አይቀርም፤ እንጠቀምበት፤ ዝም ብሎ ሪቫይቫል የለም።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 118
መልዕክት (message) 118
... እንረሳዋለን፣ እንዳለፈ ውኃም እናስበዋለን!

ጌታ ኢየሱስ ሲናገር "...ኀዘናችሁ ወደ ደስታ ይለወጣል።ሴት በምትወልድበት ጊዜ ወራትዋ ስለ ደረሰ ታዝናለች፤ ነገር ግን ... ከወለደች በኋላ፥ ሰው በዓለም ተወልዶአልና ስለ ደስታዋ መከራዋን አታስበውም።" ይላል (ዮሐ 16:20-21)።

ለሁሉ ጊዜ አለው። ኀዘን እንዳለ ደስታ አለ፣ምጥ እንዳለ ሁሉ መውለድም አለ።

ኀዘናችን ወደ ደስታ ይለወጣል፤አምጠን አንቀርም ይወለዳል ። መከራችንንም እንረሳዋለን፣ እንዳለፈ ውኃም እናስበዋለን። (ኢዮብ 11:16)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 119
መልዕክት (message) 119
ሳያቋርጡ በስሙ መለመን ነው

ጌታ ኢየሱስ አለ"እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም ፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ" (ዮሐ 16:24)

እስከ አሁን ተመኘን እንጂ አልለመንም፣ እስከ አሁን አሰብን እንጂ አልለመንም፣ እስከ አሁን አቀድን እንጂ አልለመንም፣ እስከ አሁን አወራን እንጂ አልለመንም፣ እስከ አሁን ተነበይን እንጂ አልለመንም፣ እስከ አሁን አገለገልን እንጂ አልለመንም ፣ እስከ አሁን ሠራን እንጂ አልለመንም፣ እስከ አሁን ኖርን እንጂ አልለመንም።

ጌታ "ለምኑ ትቀበሉማላችሁ" እያለን ነው። የተዘረዘሩትን ሁሉ በቦታው ማድረግ ክፋት የለውም፤ በጽድቅ ለመኖር መሠረቱ ግን፥ ሳያቋርጡ በስሙ መለመን ነው!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 120
መልዕክት (message) 120
ምድር ብትነዋወጥ፥ አንፈራም!

ጌታ ኢየሱስ ሲናገር እንዲህ አለ፥ "እነሆ፥እያንዳንዳችሁ ወደ ቤት የምትበታተኑበት እኔንም ለብቻዬ የምትተዉበት ሰዓት ይመጣል፥ አሁንም ደርሶአል፤ ነገር ግን አብ ከእኔ ጋር ስለ ሆነ ብቻዬን አይደለሁም።" (ዮሐ 16:32)

መበታተን ቢሆን፣ ለብቻ መቅረት ቢፈጠር፣ ይሄ ሁኔታ ወደ መታየት ቢደርስ፣ ብቻችንን አይደለንም፤ ከእኛ ጋር ያለ፥ አለ።

"አምላካችን መጠጊያችንና ኃይላችን፥ ባገኘን በታላቅ መከራም ረዳታችን ነው።ስለዚህ ምድር ብትነዋወጥ፥ ተራሮችም ወደ ባሕር ልብ ቢወሰዱ አንፈራም።" (መዝ 46:1-2)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 121
መልዕክት (message) 121
በማይመለከተን ጉዳይ መሳተፍ.....

ጌታ ኢየሱስ ሲናገር “እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ፤” ይላል (ዮሐ 17:4)

ማን ነው ከመካከላችን፥ እግዚአብሔርን በምድር ማክበር የሚፈልግ?

ለራሱ የተሰጠውን ሥራ ይፈጽም(አርፎ ኃላፊነቱን ይወጣ)።

በማይመለከተን (ባልተሰጠን) ጉዳይ ሁሉ መሳተፍ፥ እርሱን ፈጽሞ አያስከብረውም።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 122
መልዕክት (message) 122
እዚህ ዓለም ላይ ምን ክብር አለ?


ጌታ ኢየሱስ ሲጸልይ “አሁንም፥ አባት ሆይ፥ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ።” አለ። (ዮሐ 17:5)

ዓለም ሳይፈጠር የነበረ ክብር ካለ፥እዚህ ዓለም ላይ/እወደቀ ዓለም ላይ ምን ክብር አለ? ለየትኛው ክብር ነው ውጊያው? ለየትኛው ክብር ነው ፉክክሩ?ለየትኛው ክብር ነው መናናቁ? ለየትኛው ክብር ነው ሩጫው? ለየትኛው ክብር ስንል ነው አሁን የምናደርገውን እያደረግን ያለነው?

ኢየሱስ እንደ ጸለየው “ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል፤ መታመኛዬም እግዚአብሔር ነው” (መዝ 73:28)!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




**Aynalem Mersie**

PART 123
መልዕክት (message) 123
ድምጽ አይከለከልም...........!

ጌታ ኢየሱስ ሲናገር "ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል" አለ። (ዮሐ 18:37)

ብዙ ድምጽ እሚሰማበት ዘመን ላይ ደርሰናል፥"ከጌታ ድምጽ ሰማሁ" የሚሉ እዚህም እዛም አሉ ነገር ግን የአንዱ ከአንዱ ጋር ሊናበብ አልቻለም፤ ይሄ የሆነበት ምክንያት፥ ይመስለኛል ሁሉ ሰው ሰማሁት የሚለውን ድምጽ አስበልጦ ለማቅረብ ከሚያደርገው ጥረት የመነጨ ሳይሆን አይቀርም።

ድምጽ ልስማም አልስማ፥ ከእውነት መሆን እንዴት መልካም ነው። ከእውነት ሲኮን ጌታ እንዳለው ድምጽ አይከለከልም!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 124
መልዕክት (message) 124
እርሱ ነው የወቅቱ በርባን.....!

ገዢው ጲላጦስ “ነገር ግን በፋሲካ አንድ ልፈታላችሁ ልማድ አላችሁ፤ ... የአይሁድን ንጉሥ ልፈታላችሁ ትወዳላችሁን?” አላቸው። ሁሉም ደግመው “በርባንን እንጂ ይህን አይደለም” እያሉ ጮኹ። በርባን ግን ወንበዴ ነበረ። (ዮሐ18:39-40)


ወንበዴው በርባን ተፈታ፣ኢየሱስ እንደ ወንበዴ ታሰረ፤ በርባን ነጻ ሆነ፥ ኢየሱስ ተወነጀለ፤ በርባን ሕያው ሆነ፥ኢየሱስ ሞተ፤ ልውጫ ሆነ።

ምን ዓይነት በርባን ነው? ከመቼው ረሳው የሆነውን? የቦታ ልውጫውን? ምንም እንዳልተፈጠረ፥በርባን አሁንም ያምፃል ውንብድናውን አሻሽሏል፤ አሁንም የማይገባውን ያደርጋል።

ማን ነው በርባን?እኔ ነኝ፣አንተ ነህ፣ አንቺ ነሽ። ወንብድና ላይ የተሠማራ ሁሉ፥ እርሱ ነው የወቅቱ በርባን። በርባን እባክህ ንሰሐ ግባ!!!!!!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




**Aynalem Mersie**

PART 125
መልዕክት (message) 125
እረፍት ተገኘ.....................!

መጽሐፍ “በዚያን ጊዜም ጲላጦስ ኢየሱስን ይዞ ገረፈው፤ ... ደግሞ ... ‘እነሆ፥ አንዲት በደል ስንኳ እንዳላገኘሁበት ታውቁ ዘንድ እርሱን ወደ ውጭ አወጣላችኋለሁ’ አላቸው።” ይላል። (ዮሐ 19:1-4)

ኢየሱስ አንዲት በደል ስንኳ አልተገኘበትም ነገር ግን ተገረፈ ፤ ለምን? ለማን ብሎ ነው?

መጽሐፍ ያስታውሰናል “እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥” (ኢሳ 53:5)

በድህነት መገረፍ አይበቃም? በበሽታ መገረፍ አይበቃም? በጭንቀት መገረፍ አይበቃም?በርግማን መገረፍ አይበቃም ? በኃጢአት መገረፍ አይበቃም? በሞት ፍርሃትስ መገረፍ አይበቃም?

ይበቃል! የተገረፈልን አለ፡- ኢየሱስ። “ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ” አለ (ማቴ 11:28)። ኢየሱስ እረፍት ነው!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 126
መልዕክት (message) 126
ቄሣር ዛሬ ቢኖር...

መጽሐፍ ሲናገር" ጲላጦስ ኢየሱስን ሊፈታው ፈለገ፤ነገር ግን አይሁድ 'ይህንስ ብትፈታ የቄሣር ወዳጅ አይደለህም፤ ራሱን ንጉሥ የሚያደርግ ሁሉ የቄሣር ተቃዋሚ ነው' እያሉ ጮኹ" (ዮሐ 19:12)

ቄሣር በዚህ ዘመን ቢኖር ሰው አይተርፍም፤ ሁሉ ተቃዋሚው ይሆን ነበር፤ ምክንያቱም ሁሉ ራሱን በራሱ ነው የሾመው፣ ሁሉ ራሱን በራሱ ነው የቀባው፣ ጥቅስ ያስፈልጋል?

"የቀባን እግዚአብሔር ነው"(2 ቆሮ 1:21)፤ደስ ሲል፥(ፈገግ)

ለማንኛውም ጌታ "በቶሎ እመጣለሁ"ብሏል (ራዕ 22:20)፤ ያኔ በእሱ የተሾመም ሆነ የተቀባ፥ራሱን በራሱ ከሾመና ከቀባ በግልጽ ይለያል። "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና!!!"(ራዕ 22:20)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 127
መልዕክት (message) 127
ንጉስ ንጉስን ሰቀለ.............!

መጽሐፍ ሲናገር "ጲላጦስም ደግሞ ጽሕፈት ጽፎ በመስቀሉ ላይ አኖረው፤ ጽሕፈቱም፣ 'የአይሁድ ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ' የሚል ነበረ።" (ዮሐ 19:19)


ንጉስ የነገስታቱን ንጉስ ሰቀለ። ምስኪን ጲላጦስ፤ እርግጠኛ ነኝ ዛሬ አግኝተን ብንጠይቀው "ሳላውቅ"ነው ሊለን ይችላል።

ዛሬም በመካከላችን የሚሰቅሉት አልታጡም።መጽሐፍ ይህን ሲያረጋግጥ "አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን፣ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን፣ ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው፣ የነበሩትን...የእግዚአብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን በኋላም የካዱትን እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው፤ ለራሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታልና " ይላል። (ወደ ዕብ 6:4-6)

"እባካችሁ፥ ተመለሱ፤ በደል አይሁን፤" (ኢዮብ 6:29)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!



facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 128
መልዕክት (message) 128
153 ታላላቅ ዓሦች............!

ጌታ ኢየሱስ በትንሳኤ ከሠራቸው ተዓምራት አንዱ "ስምዖን ጴጥሮስም ወደ ጀልባይቱ ገብቶ መቶ አምሳ ሦስት ታላላቅ ዓሦች ሞልቶ የነበረውን መረብ ወደ ምድር ጐተተ፤ ይህንም ያህል ብዙ ሲሆን መረቡ አልተቀደደም" የሚለው ይገኝበታል (ዮሐ 21:11)

በመቶ አምሳ ሦስት ታላላቅ ዓሦች ሞልቶም የነበረው መረብ ወደ ምድር ተጐተተ፤..መረቡ አልተቀደደም። የእግዚአብሔር ስጦታ አቅምን ያገናዘበ ነው፤ ሁሉ በልክ ነው። ስለዚህ የሆነ ክፍተት የለም፣ አይፈጠርምም።

የእኔ ጥያቄ፡ለምንድን ነው በዚህ ዘመን ሰዎች "ተቀብቻለሁ" ወይም "ተመርቄአለሁ" ካሉ በኋላ የሆነ ክፍተት ይስተዋላል፤ ምናልባት በተቀቡበትም ሆነ በተመረቁበት ትምህርት መስክ ሲያገለግሉ የዓሦቹ ቁጥር መቶ አምሳ አራት እና ከዚያ በላይ ደርሶ ይሆን? (ፈገግ)፣ "ጥቅስ አለ ወይ?" ስትሉ ሰማሁ?

"ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል" (ዮሐ 14:12)፤አቤቱ እርዳን!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!



What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 129
መልዕክት (message) 129
ላስታጣቂ ተላልፈን እንዳንሰጥ!

ጌታ ኢየሱስ ሲናገር “ጐልማሳ ሳለህ ወገብህን በገዛ ራስህ ታጥቀህ ወደምትወደው ትሄድ ነበር፤ ነገር ግን በሸመገልህ ጊዜ...ሌላውም ያስታጥቅሃል ወደማትወደውም ይወስድሃል አለው።” (ዮሐ 21:18)

ባለንበት ዓለም ሁልጊዜ ያው መሆን አይቻልም። ከሆነ ጊዜ በኋላ የሆነ ለውጥ ይስተዋላል። እንደ ቀድሞ ጊዜው መሆን እየፈለግን፥መሆን ግን አይቻልም፤በመንፈሳዊ ሕይወት ሲሆን ደግሞ ትንሽ ይከብዳል።

አካላዊውንም ሆነ መንፈሳዊውን የሚገዛ አንድ የጋራ ጉዳይ ግን አለ። ጊዜ ነው። እግዚአብሔር እንኳ ነገርን ውብ አድርጎ የሚሠራው በጊዜው ነው። (መክ 3:11)

ዘማሪ ተስፋዬ ጋቢሶ
“ነፍሴም ወደ አምላኳ፥ ስጋም ወደ አፈሩ ሳይመለስ፣ ቶሎ ቶሎ ብዬ ሥራዬን ልጨርስ”እንዳለው፣ያልተሰጠንን ሥራ ስንሠራ፥ ዘመናችን አልቆ፥ ላስታጣቂ ተላልፈን እንዳንሰጥ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!



Aynalem Mersie

PART 130
መልዕክት (message) 130
ከውኃ ጥምቀት በኋላ ያለ ጥምቀት

መጽሐፍ ሲናገር “ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና፥ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኃላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ” ይላል። (ሐሥ 1:5)

በውኃ መጠመቅ እንዳለ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅም አለ፤ መንፈስ ቅዱስ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ የዳንንበት የርስት መያዣ ነው። መጽሐፍ ይህን ሲያረጋግጥ “እናንተ ደግሞ የእውነትን ቃል የመዳናችሁን ወንጌል፥ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ፥..በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ”ይላል(ኤፌ 1:13)

የእውነትን ቃል መስማት፣ ቃሉን ማመን እና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ የማይነጣጠሉ የመዳን ሥርዓቶች ናቸው። እዚህ ጋ “የቱ (ምንድን) ነው የእውነት ቃል?” የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። መጽሐፍ መልሱን ሲሰጥ:-

“በአፍህ በልብህም ሆኖ ቃሉ ቀርቦልሃል፤ ይህም...የእምነት ቃል ነው”ይልና ቃሉን ሲገልጥ“ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና።” ይላል (ሮሜ 10:8-10)

እኔ፥ ቃሉ እንዳለው፥ ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፌ መስክሬና በልቤ አምኜ፥በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቄአለሁ።ይህ ከመሆኑ በፊት ሌላ መንፈስ ውስጤ እንደ ነበር አስታውሳለሁ። ከሌላ መንፈስ የማምለጫ ብቸኛ መንገዱ ኢየሱስ ነው!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 131
መልዕክት (message) 131
አስማት (ምትሃት)፥ የጠላት ኃይል ነው!

መጽሐፍ ሲናገር “መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥” ይላል። (ሐሥ 1:8)

ከራስ የሚመነጭ ኃይል የለም። ኃይል የምንቀበለው ነገር ነው። መንፈስ ቅዱስ በእኛ ላይ በወረደ ጊዜ የምንቀበለው የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነው። (ሮሜ 1:16)

ኃይል ተብሎ ከማዳን ውጪ የሆነ መንፈሳዊ ኃይል ሁሉ የጠላት ኃይል ነው። ይህን ለማረጋገጥ፥ እባክዎን ሐዋርያት ሥራ 8:9-13 ያንብቡ። ሰዎችም በዚህ ዘመን ካለ አስማት (ምትሃት) እንዲያመልጡ፥በዚህ መልዕክት መነሻነት ሰዎችን ይምከሩ፤ ያሳስቡ። ዘመንዎ ይባረክ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 132
መልዕክት (message) 132
ያልተገለጠ አምላክ መቼም አላመልክም!

መጽሐፍ ሲናገር “ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያቸሁት፥ እንዲሁ ይመጣል” ይላል(ሐሥ 1:11) “ወደ ሰማይ የወጣው፥ መጀመሪያ የት ነበር?” የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። መጥምቁ ዮሐንስ እያጠመቀ ሳለ መሰከረም “ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው።” (ዮሐ 3:31)

እንግዲህ ኢየሱስ፥ ከሰማይ ነው የመጣው፣ ወደ ሰማይ ነው የወጣው፣ ዳግመኛ እሚመጣውም ከሰማይ ነው። መጽሐፍ “ያለና የሚኖር” ይለዋል። (ዘጸ 3:14)

እኔ የማመልከው፥ መኖሩ የተረጋገጠውን፥ ይህንን ጌታ ነው። ኢየሱስ እርሱ አልፋ ነው፣ እርሱ ኦሜጋ ነው። ኢየሱስ እርሱ መጀመሪያ ነው፣ እርሱ መጨረሻ ነው። “ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።” (ዕብ 13:8)። ይሄ ነው ጌታ፤ ያልተገለጠ አምላክ መቼም አላመልክም!!! እናንተስ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 133
መልዕክት (message) 133
በአግባቡ ካልተያዘ የሚወሰድ ነገር ነው፤ ሹመት

በመጽሐፍ “መኖሪያው ምድረ በዳ ትሁን፣ የሚኖርባት አይኑር ደግሞም ሹመቱን ሌላ ይውሰዳት” ተብሎ ተጽፎአል (ሐሥ 1:20)። ይህ ክፍል፥ ስፍራውን ወይም ሹመቱን፥ በአግባቡ ስላልጠበቀውና በኋላም ስፍራው ስለተወሰደበት ሐዋርያው የአስቆሮቱ ይሁዳ የተነገረ ነው።

በሌላ ስፍራ ደግሞ መጽሐፍ “መኖሪያቸውን የተዉትን እንጂ የራሳቸው አለቅነት ያልጠበቁትን መላእክት በዘላለም እስራት ከጨለማ በታች እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ ጠብቆአቸዋል” ይላል። (ይሁዳ 1:6)

ሰው ወይም መላዕክ ወይም ደግሞ ኪሩብ የራሱ የሆነውን ስፍራ/መኖሪያ/ሹመት በአግባቡ ካልጠበቀ፥ ሊያጣው እና ከእጁ እንደሚወሰድ ሊያውቅ ይገባል።

“እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው፥ እንዴት እናመልጣለን?” (ዕብ 2:2)። ጌታ ማስተዋልን ይስጠን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 134
መልዕክት (message) 134
አንዷት ጥምቀት................!

ሐዋርያው ጴጥሮስ ሲናገር " ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤" አለ። (ሐሥ 2:38)

ዮሐንስ ደግሞ ስለኢየሱስ ሲናገር"ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን፥" ይላል። (ራእይ 1:5)

ሐዋርያው ጳውሎስም ይህንኑ ከኃጢአት የዳንንበትን ወይም የነጻንበትን ጥምቀት "አንዷት ጥምቀት፤" በማለት ይናገራል። (ኤፌ 4:5)። ራሱ ጳውሎስም ተጠምቋልና፤ (ሐሥ 22:16)

እንግዲህ ወገኖቼ፥ምንም እንኳ መጽሐፍ"ወደ ፍጻሜ እንሂድ መሠረትን ደግመን አንመሥርት"በሚለው ክፍሉ 'ጥምቀቶች' በሚል ቃል የተለያዩ የጥምቀት ዓይነቶች እንዳሉ ቢናገርም፥ የመዳናችን ጥምቀት ግን "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" የሆነው እንደሆነ ልብ ይሏል። (ዕብ 6:1-2)

እኔ፥ አንዷት ጥምቀት በተባለችው፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠምቄ፥ ድኛለሁ፤ እርስዎስ?

መልዕክቱን መሞገት፤ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 135
መልዕክት (message) 135
አንድ ስም .......................!

መጽሐፍ ስለ ኢየሱስ ስም ሲናገር “መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።” ይላል። (ሐሥ 4:12)

ከሰማይ በታች የሚጠሩ ስሞች አሉ፦የመለአክ ስም፣ የሰው ስም፣ የአማልክት ስም፣ ወዘተ።

አንድ ስም ግን ይለያል፣ ጌታ ኢየሱስ።

መጽሐፍ “የጌታን ስም የሚጠራም ሁሉ ይድናል።” ይላልና፥ መዳን የሚፈልግ ማንም፥ አሁኑኑ ይህን ስም ጠርቶ ይዳን። ማንም በይሉኝታ ከዚህ ስም ራሱን ቢያሸሽ፥ ምንም ዓይነት የሕይወት ዋስትና አይኖረውም (ሐሥ 2:21)

“ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም።” (1ዮሐ 5:12)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 136
መልዕክት (message) 136
ጣዕም ያጣ ሕይወት..........!


በሐዋርያት የወቅቱ እንቅስቃሴና በሊቀካህናቱ ይደርስባቸው የነበረውን ተቃውሞ አስመልክቶ የሕግ መምህሩ ገማልያል ሲናገር “ይህ አሳብ ወይም ይህ ሥራ ከሰው እንደ ሆነ ይጠፋል። ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ ግን ታጠፉአቸው ዘንድ አይቻላችሁም፥ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ጋር ስትጣሉ ምናልባት እንዳትገኙ። ይላል። (ሐሥ 5:38-39)

ከእግዚአብሔር የሆነን ሃሳብ፣ ሥራ ወይም ጥሪ በየትኛውም ዘመን ማጥፋት አይቻልም። ሙከራው ራሱ ከእግዚአብሔር ጋር ጥል ነው። መጽሐፍም “ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣሉ ይደቅቃሉ” ሲል ያስጠነቅቃል። (1 ሳሙ 2:10)

ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቶ የደቀቀ ማለት፥የመጀመሪያውን የሕይወት ጣዕም ያጣ ማለት ነው።ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው የወደቀው ኪሩብ (ዲያብሎስ) ነው። እንመለስ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




**Aynalem Mersie**

PART 137
መልዕክት (message) 137
ስም ማጠልሸት................!

መጽሐፍ ስለ እስጢፋኖስ አገልግሎት ሲናገር "ይናገርበት የነበረውንም ጥበብና መንፈስ ይቃወሙ ዘንድ አልቻሉም።" ይላል። (ሐሥ 6:10-13)

ተቃዋሚዎቹ ማድረግ የቻሉትን ሲናገር "በዚያን ጊዜ፥በሙሴ ላይ በእግዚአብሔር፥ ላይ የስድብን ነገር ሲናገር ሰምተነዋል የሚሉ ሰዎችን አስነሡ፤ ሕዝቡን፣ሽማግሌዎችንና ጻፎችንም አናደዱ፥ ቀርበውም ያዙት፥ ወደ ሸንጎም አመጡትና፥ ይህ ሰው በዚህ በተቀደሰው ስፍራ በሕግም ላይ የስድብን ነገር ለመናገር አይተውም" አሉ፥ ይላል። (ሐሥ 6:11-13)

በዚህም ዘመን እንዲሁ ነው። ሰዎች የተገለጡበትን ጥበብና መንፈስ መሞገት ያልቻሉ ሰዎች፥ በእስጢፋኖስ እንደሆነው ሁሉ፥ ስም ማጠልሸት ቢያንስ የመጀመሪያ እርምጃቸው ነው
። እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ፥ማህበራዊ ሚዲያውን ማየት በቂ ነው። መንፈሱ፥ያው በእስጢፋኖስ ዘመን የነበረው ነው።
ጌታ ሆይ፥ ለሁሉ ምህረት ይሁን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 138
መልዕክት (message) 138
ማሕበራዊ ድህረገጽ፤ የዘመናችን ቅርጫት


መጽሐፍ ሳውልን (ሐዋርያው ጳውሎስ) አስመልክቶ ሲናገር “እየበረታ ሄደ፥ በደማስቆም ለተቀመጡት አይሁድ ይህ ክርስቶስ እንደ ሆነ አስረድቶ መልስ ያሳጣቸው ነበር። ብዙ ቀንም ሲሞላ አይሁድ ሊገድሉት ተማከሩ፤ ... ይገድሉትም ዘንድ በሌሊትና በቀን የከተማይቱን በር ሁሉ ይጠብቁ ነበር” ይላል። (ሐሥ 9:22-24)

መጽሐፉ፥ እንዴት እንዳመለጠ ሲቀጥል” ደቀ መዛሙርት ግን በሌሊት ወስደው በቅጥር ላይ አሳልፈው በቅርጫት አወረዱት።” ይላል (ሐሥ 9:22-25)

የኛ ዘመኑ ቅርጫት፣ ሰውን የምንወርፍበት፣ የመግደል ያህል ስም የምናጠፋበት፣ ሰውን በቀላሉ እና በተቀነባበረ መልኩ አሳልፈን የምንሰጥበት፡-ማሕበራዊ ድህረገጻችን መቼ ይሆን እንደ ደቀ መዛሙርቱ ሰው የምናድንበት?የምናስመልጥበት? ጌታ ሆይ ማስተዋልን ስጠን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!



facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 139
መልዕክት (message) 139
መለያየትን የሚያነሣ ሰው፥ ጠማማ.....!

ሐዋርያው ጴጥሮስ ሲናገር"አይሁዳዊ ሰው ከሌላ ወገን ጋር ይተባበር ወይም ይቃረብ ዘንድ እንዳልተፈቀደ..ታውቃላችሁ፤ ለእኔ ግን እግዚአብሔር ማንንም ሰው ርኩስና የሚያስጸይፍ ነው እንዳልል አሳየኝ፤" (ሐሥ 10:28)

አንድ ወገን ከአንድ ወገን፣ አንድ ብሔር ከአንድ ብሔር ጋር እንዳይተባበር የሚከለክል ትርክት ሊፈጠር ይችላል፣ ደንብ ሊደነገግ ይችላል። በትርክቱ ወይም በደንቡ ዙሪያ በድህረ-
ገጽ እየቀሰቀሱ የገቢ ምንጭ ማግኘትም እንደ ሥራ ፈጠራ ሊታይ ይችል ይሆናል። ሁሉም የሰው ቀመር ነው። ጥያቄው "የእግዚአብሔር ቃል በዚህ ጉዳይ ምን ይላል?"የሚል ነው።

"አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና። እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ የአብርሃም ዘር እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ።" ይላል። (ገላ 3:28-29)።
ስለዚህ እኛ፦

1. በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ነን፣
2. የአብርሃም ዘር እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች ነን።

አንድ እንዳንሆን ለምትጥሩ ሁሉ ቲቶ 3:10-11ላይ ያለ ቃል እንደ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷችኋል፤ እኔ ሳልሆን፥ ጳውሎስ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።
በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 140
መልዕክት (message) 140
ወኅኒ ለማስገባት የሚደረግ ጥረት

መጽሐፍ ሲናገር “ጴጥሮስም በወኅኒ ይጠበቅ ነበር፤ ነገር ግን በቤተ- ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር።” ይላል። (ሐሥ 12:5)

በሐዋርያው ጴጥሮስ ዘመን አገልጋይ ወኅኒ ሲገባ፥ በቤተ- ክርስቲያን አጥብቆ ይጸለይ ነበር። በእኛ ዘመን ደግሞ ጸሎቱ ወኅኒ ለማስገባት ነው።

መቼም ማስረጃ አቅርብ እንደማትሉኝ እርግጠኛ ነኝ። ስም ማጥፋት እና ተቃውሞ፥ የዕለት ከዕለት ትዕይንት ነውና።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!



facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 141
መልዕክት (message) 141
የማንን አሳብ እያገለገልን ነው?

መጽሐፍ ሲናገር “ዳዊትም በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን አሳብ ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ፥” ይላል። (ሐሥ 13:36)

በራሳችሁ በሆነው ዘመን፥ የማንን አሳብ እያገለገላችሁ ነው?

እኔም ሆንኩ የእኔ ትውልድ አገልግሎት፥ እንደ አዲስ ሳይሆን እንደቀደሙት አባቶቻችን በዘመናችን የእግዚአብሔርን አሳብ አገልግለን ማለፍ ነው። የተስማማ፥ አሜን ይበል!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 142
መልዕክት (message) 142
እስከ አሁን ላልዳነ ሰው.......!

መጽሐፍ ሲናገር "እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?"ይላል (ሐሥ 16:30)

መጽሐፍ መልሱን ሲሰጥ "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ" ይላል (ሐሥ 16:30-31)

ለመዳን ምን እያደረግን ይሆን? እስከ አሁን ካልዳንን ከሰው ሁሉ ምስኪን ነን።በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ መዳን ከተጀመረ ሁለት ሺ ዓመታት አለፈ።

ላልዳነ ሰው፡-"የመዳን ቀን አሁን ነው" (2 ቆሮ 6:2)፤ ኢየሱስ ያድናል!"ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወድ ቢኖር የተረገመ ይሁን።" እኔ አይደለሁም ያልኩት፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። እኔም እላለሁ "መልአክም ይሁን፣ ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወድ ቢኖር የተረገመ ይሁን።" (1 ቆሮ 16:22)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 143
መልዕክት (message) 143
ነፍስዎን፥ በምን ለውጠው እየኖሩ ነው?

ሐዋርያው ጳውሎስ ሲናገር “ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ።” ይላል። (ሐሥ 20:24)

ጳውሎስ ነፍሱን ስለ ወንጌል አሳልፎ ሰጥቷል፤ በጳውሎስ ህይወት ልውጫው ነፍስ በወንጌል ነው። ጥያቄው በእኛስ ህይወት ነው? ነፍሳችን በምን ተይዛለች (ተለውጣለች)?

በገንዘብ፣ በፖለቲካ፣ በዝና፣ በምንድን ነው?ከወንጌል ውጪ የሆነ ልውጫ ሁሉ ምድራዊ ነው። ነፍሳቸው በምድር ጉዳይ ስለተያዘ ሰዎች መጽሐፍ ሲናገር”መጨረሻቸው ጥፋት ነው፥ ሆዳቸው አምላካቸው ነው፥ ክብራቸው በነውራቸው ነው፥ አሳባቸው ምድራዊ ነው።” ይላል። (ፊልጵ 3:19)

“ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል?” (ማቴ 16:26)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!



facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 144
መልዕክት (message) 144
ሁላችንም እንመለስ............!

ቤተክርስትያን ዛሬ፥ውል እሌለው ጫፍ ደርሳለች።በገዛ ደሙ የዋጃት ነበረች። መንፈስ ቅዱስም ብዙ አገልጋዮችን ሹመት ሲሰጥ ለመንጋው እና ለራሳቸው ይጠነቀቃሉ በሚል እሳቤ ነበር። ቆይተው ግን ለመንጋው የማይራሩ ጨካኝ ተኩላዎች ሆኑ። ቅን ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላ ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ የራሳቸውን ሰዎች በመካከል አስነሱ። የመሪ (አባቶች) ተግሣጽ ከቁብ ሳይቆጠር ለዚህ ቀን ተበቃ።

ይህ በእኛ የሆነብን ነገር፥ ከዘመናት በፊት በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ሆኖ እንደ ነበር ሐዋርያው ጳውሎስ ጽፏል። (ሐሥ 20:28-31)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል “ወደ እኔ ተመለሱ፥ ...እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ፥” (ዘካ 1:3)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!



facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 145
መልዕክት (message) 145
መመረጥ፤ መከተል............!

አምላካችን እግዚአብሔር፥ በብዙ ዘመናት፥ በብዙ ትውልዶች መካከል፥ ለራሱ ሥራ፥ ሰዎችን ከሰዎች መካከል መርጧል። የመረጠበትም መንገድ ልዩ ልዩ ነው።

የሐዋርያው ጳውሎስን አመራረጥ፥ ራሱ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲተርክ “እርሱም አለኝ፥ የአባቶቻችን አምላክ ፈቃዱን ታውቅ ዘንድና ጻድቁን ታይ ዘንድ ከአፉም ድምፅን ትሰማ ዘንድ አስቀድሞ መርጦሃል” ይላል። (ሐሥ 22:14)

በእኛ ዘመን፥ እነማንን፥ እንዲህ በግልጽ ራሱ ጌታ ጠርቷቸው ይሆን? እኔ አላውቅም፥ ጌታ ያውቃል።

ጢሞቴዎስ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር ነበረ። ትምህርቱንና አካሄዱን፤አሳቡንም፤እምነቱንም፤ትዕግሥቱንም፤ፍቅሩንም መጽናቱንም፤ ስደቱንም መከራውንም ተከትሏል። (2 ጢሞ 3:10)

በእኛ ዘመን፥ጥሪ ያላቸውን፤ መሪዎቻቸውን እንደ ጢሞቴዎስ የተከተሉ ሰዎች ይኖሩ ይሆን? ባሳለፍናቸው አመታት አፋኞች እና የማፋታት አገልግሎት ሰፍኖ ታይቷል። እንኳን የሚተካ ለዋኖቹም ልክ እንደ ጳውሎስ መከራ በዝቷል፤ምህረት ይሁን!

መልዕክቱን መሞገት፤ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 146
መልዕክት (message) 146
አንድ ሰው የማጥፋት ዘመቻ !

ጌታ ከነሳቸው ሆኖ ባያበረታቸው፥ ጥሪ ያላቸው ሰዎች ዛሬን ባላዩ ነበር። ገና ብዙ ምስክርነት አላቸው። ብዙ ሰው ያስነሱ እና አገር ይቀይሩ ዘንድ ሩጫቸውን አልጨረሱም። ገና መቼ ተጀመረና፤ ይሰሩ ዘንድ ጌታ በቃሉ "አይዞአችሁ" ይላል።

የሚያስተዛዝበው፥አንድን ሰው(አንድን ባለራዕይ) ለማጥፋት የሚደረገው ዘመቻ ነው። በሐዋ. ጳውሎስ የተደረገው ዘመቻ ጥሩ ማሳያ ነው፦

"በጠባም ጊዜ አይሁድ ጳውሎስን እስኪገድሉት ድረስ እንዳይበሉና እንዳይጠጡ በመሐላ ተስማሙ። ይህንም ሴራ ያደረጉት ሰዎች ከአርባ ይበዙ ነበር፤ እነርሱም ወደ ካህናት አለቆችና ወደ ሽማግሌዎቹ መጥተው። ጳውሎስን እስክንገድል ድረስ ምንም እንዳንቀምስ ተረጋግመን ተማምለናል።" አሉ ይላል። (ሐሥ 23፡12-14)

ጌታ ሆይ፥ ቃልህ እንደሚል፥የእስራኤል መብራት (ባለራዕይ፣ መልዕክተኛ) የሆነ ቁልፍ ሰውን ለማጥፋት በተደረገ ወይም በሚደረግ ዘመቻ፥ አውቀንም ይሁን ሳናውቅ ለተሳተፍን ሁሉ ከጌታ ዘንድ ምህረት ይሁን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 147
መልዕክት (message) 147
ሰዎች ማንን ያምናሉ?

ከእርሱ ጋር ታስረው ከነበሩ እስረኞች ጋር ጉዞ ወደ ኢጣልያ በሆነ ጊዜ፥ ሐዋርያው ጳውሎስ ተነሳና እንዲህ አለ “እናንተ ሰዎች፥ ይህ ጉዞ በጥፋትና በብዙ ጉዳት እንዲሆን አያለሁ ፤ ጥፋቱም በገዛ ሕይወታችን ነው እንጂ በጭነቱና በመርከቡ ብቻ አይደለም” ብሎ መከራቸው። (ሐሥ 27:10)

የመቶ አለቃው ግን ጳውሎስ ከተናገረው ይልቅ የመርከብ መሪውንና የመርከቡን ባለቤት ያምን ነበር። (ሐሥ 27:11)

ታሪክ ራሱን ይደግማል እንደሚባለው፥በእኛም ዘመን ቢናገር የሚደመጠው ከመልዕክተኛ ይልቅ የወቅቱ የመርከብ መሪ (አክቲቪስት፣ ፖለቲካ ተንታኝ፣ መረጃ አቀባይ፣ ወሬ አቀባባይ
፣ ወሬ አቀጣጣይ፣ ጥቅሜ ተነካ ባይ፣ ወዘተ) ነው።

“የወቅቱ የመርከቡ ባለቤትስ ማነው?” ስትሉ ሰማሁ ልበል? ትንሽ ብር የቋጠሩና በገንዘብ ማሰብ የሚሹ ናቸዋ።መጽሐፍ ሲጠራቸው “ባለ ጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ” ይላቸዋል።(1ጢሞ 6:9)። እውነተኛው ባለጠጋ እግዚአብሔር ነው። ከእርሱ ውጪ ያሉት ገና ፍላጎት ላይ ስላሉ፥ መጽሐፍ “በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ።” ይላል። (1 ጢሞ 6:10)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie



PART 148
መልዕክት (message) 148
አሳብ ለመለወጥ መገደድ....!

አረማውያንም በሐዋርያው ጳውሎስ እጁ እባብ ተንጠልጥላ ባዩ ጊዜ፥ እርስ በርሳቸው "ይህ ሰው በእርግጥ ነፍሰ ገዳይ ነው፥ ከባሕርም ስንኳ በደኅና ቢወጣ የእግዚአብሔር ፍርድ በሕይወት ይኖር ዘንድ አልተወውም"አሉ፤እርሱ ግን እባቢቱን ወደ እሳት አራገፋት አንዳችም አልጐዳችውም። እነርሱም፥ "ሊያብጥ(ወዲያው ሞቶ ሊወድቅ)ነው" ብለው ይጠባበቁት ነበር።

ብዙ ጊዜ ግን ሲጠባበቁ በእርሱ ላይ የሚያስገርም ነገር ምንም ባላዩ ጊዜ "ይህስ አምላክ ነው" ብለው አሳባቸውን ለወጡ። (ሐሥ 28:4-6)

ብንፈልግም ባንፈልግም፥ ስለ አንዳንድ ሰዎች አሳባችንን የምንለውጥበት ቀን እየመጣ ነው። ተቃውመናችዋል፥ ግን ምንም አልሆኑም፣ አሳድደናችዋል ግን ምንም አልሆኑም፣ አሳጥተናችዋል፥ ግን ምንም አልሆኑም፣ አዋርደናችዋል፥ ግን ምንም አልሆኑም፣ ሰድበናችዋል፥አሁንም ምንም አልሆኑም፤ በወቅታዊው መሣሪያ(ማህበራዊ ድህረ-ገጽ) መትተናችዋል ወይ ፍንክች። መጽሐፍ "እንዳስጨነቁአቸው መጠን እንዲሁ በዙ፥ እጅግም ጸኑ፤" ይላል (ዘጸ 1:12)። ክብር ለጌታ ይሁን!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

Aynalem Mersie

ART 149
መልዕክት (message) 149
የመተመን አገልግሎት.........!

መጽሐፍ አለ "እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል" (ሮሜ 2:6)

"እርሱ" ከተባለ፥ እኛ እነማን ነን?ማን ነው ተማኝ፣ደልዳይ እና ከፋይ ያደረገን?

በዚህ ዘመን፥ በጥናት ሳይሆን በጭፍን፥ ማንንም በቀላሉ ለመተመን፣ ለመደልደልና ዋጋ ለመስጠት፥አቋራጩ መንገድ ማህበራዊ ድህረ-ገጽ ከሆነ ሰነባብቷል።ጥያቄው ግን፥"ከማ በተሰጠ ስልጣን ነው?" የሚል ነው።

መጽሐፍ ሲናገር "በዓይንህ ያለውን ምሰሶ ... ሳታይ እንዴት ወንድምህን፥'ወንድሜ ሆይ፥በዓይንህ ያለውን ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ ልትል ትችላለህ?'...ግብዝ፥ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ ከዚያም በኋላ በወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ።" ይላል።(ሉቃ 6:42)

አንዳንዶች፥ምንም እንኳ በዓይናቸው ምሰሶ(ጉድፍ) ቢኖርም ፥ ያንን በከፍተኛ ተጋድሎ አልፈው፥ ዛሬም ሌላውን እየተመኑ ነው። ጌታን ለማገዝ ይሆንን? ጌታ ምህረቱን ያብዛላቸው!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




ART 150
መልዕክት (message) 150
አፈጻጸም የወጣበት ፍርድ....!

መጽሐፍ “እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላም” ይላል፤ (ሮሜ 2:11)። “አያዳላም” ማለት ምን ማለት ነው?

ክፉ ለሚያደርጉ ሰዎች፡-
“ሁሉ መከራና ጭንቀት ይሆንበታል፥” (ሮሜ 2:9)

በጎ ለሚያደርጉ ሰዎች፡-
“ሁሉ ምስጋናና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል” (ሮሜ 2:10)

እነማን ምን ላይ ነን? መከራና ጭንቀት ላይ ነን? ቀደም ሲል ያደረግነውን መለስ ብሎ ማየት ነው።

ምስጋናና ክብር ሰላምም ከሆነልን፥ እሰየው፥ የበጎ ሥራችን ውጤት ነው።

እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፥ዋጋ መስጠትህን በአገር ውስጥ ጨርስና ከውጪም የፈለጉ አካላት እየተንቀሳቀሱ ስለሆነ እባክህ አትርሳቸው። አንተ ጻድቅ ፈራጅ ነህ!!! (2ጢሞ 4:8)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 151
መልዕክት (message) 151
በሕግም ያለሕግም ማምለጥ አይቻልም!

ከዓለም አቀፍ ሕጎች ባሻገር፥ በዓለም ላይ ባሉ ብዙ አገሮች፥ እንደ አገሩ ተጨባጭ ሁኔታ፥ ማህበረሰቡ የሚተዳደርባቸው ልዩ ልዩ ሕጎች ይረቀቃሉ።

በመርህ ደረጃ፥ ሕገ መንግስት፥ የሕጎች ሁሉ የበላይ ነው። ሕገ መንግስትን፥ለራስ እንደሚመች አድርጎ ማርቀቅ ብሎም መፈጸም ሲፈልጉ ደግሞ አለመፈጸም ከተጠያቂነት አያድንም።

ታላቁ መጽሐፍ ይህን ጉዳይ ሲያረጋግጥ “ያለ ሕግ ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ ያለ ሕግ ደግሞ ይጠፋሉና፤ ሕግም ሳላቸው ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል” ይላል። (ሮሜ 2:12)።

በዚህ ዘመን እየሆነ ያለው እና እያየን ያለነው ይሄን ነው።ጌታ ሆይ እባክህ ምህረትህን አብዛ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

Aynalem Mersie




PART 152
መልዕክት (message) 152
ንስሐ እና ሥራ..................!

በደረስንበት ዘመን፥ በሃይማኖት ተቋማት ብቻ ሳይሆን፥ በልዩ ልዩ መንግስታዊ (መንግስታዊ ባልሆኑ) ተቋማት፥ እንዲሁም የግል ድርጅቶች ትምህርትና ስልጠና ይሰጣል፣ሥነ ምግባር ይሰበካል።

አብዛኛውን ትምህርትና ስልጠና ሰጪዎች ብሎም የተቋሙን ርዕዮተዓለም ሰባኪዎች፥ ራሳቸው የተቋሙ መሥራቾች እና እነሱ የመለመሏቸው ሰዎች ናቸው።ይሄ ባልከፋ ነበር።ችግሩ ራሳቸው አስተማሪዎቹ (አሰልጣኞቹ፣ ሰባኪዎቹ) የሚሉትን አልኖሩትም፣ አይኖሩትምም። እድሜ ለነበሩን አስተማሪዎች (አሰልጣኞች፣ሰባኪዎች)እንዲህ ያለ ማህበረሰብ አተረፍን።

መጽሐፍ እንዲህ ይላል “አንተ ሌላውን የምታስተምር ራስህን አታስተምርምን? አትስረቅ ብለህ የምትሰብክ ትሰርቃለህን?
አታመንዝር የምትል ታመነዝራለህን? ጣዖትን የምትጸየፍ ቤተ መቅደስን ትዘርፋለህን?” (ሮሜ 2:21-22)

ጣት መጠንቆል ይበቃል። እከሌ ከእከሌ የለም። የቀረን ጊዜ የንስሐ እና የሥራ ነው።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 153
መልዕክት (message) 153
“እኔ እንትን ነኝ” ባዮች፥ እንትን አይደሉም!

ስለ ተገኙበት ወገን(ብሔር) በግልጥ “እኔ እንትን ነኝ” የሚሉ እና ጉዳዩንም የሚያራግቡ ሰዎች፥ በእርግጥም የዚያ፥ወገን (ብሔር) አይደሉም።ሥራቸው ጉልህ ምስክር ነው። ከልፍለፋ እና መለያየትን ከማድረግ የዘለለ ውጤት አያስመዘግቡም።

እኔ አይደለሁም ያልኩት፥ መጽሐፍ ነው፤”በግልጥ አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ አይደለምና፥ በግልጥ በሥጋ የሚደረግ መገረዝም መገረዝ አይደለምና፤” (ሮሜ 2:28)

በሥጋ የሚደረገው እውነት ካልሆነ፥ በመንፈስ (in spirit) የሆነ ማንነት፥ አለ ማለት ነው። እሱ ነው እውነቱ። ተጽእኖ መፍጠር የሚቻለውም መንፈሱን (spirit) መያዝ ከተቻለ ብቻ ነው። መንፈሱን የያዙ ያስታውቃሉ፤ ማንም እና ምንም አያቆማቸውም፣ ያሉትን ያደርጉታል፣ ይኖሩታልም።

ከዚህ በኋላ፥ሥጋዊ የሆነ፥ መንፈስ አልባ፥የዕወቁልኝ ቅስቀሳ ብዙም አይሠራም። ጥፋት ነው ትርፉ። (ፊልጵ 3:19)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 154
መልዕክት (message) 154
ሞትና ትንሳኤ ሸሸት............!

ብዙ ለመሞት ቁርጠኛ የሆነ ሰው፥ በመጥፋቱና የሞተ ሰው ማግኘት ባለመቻሉ፥ የተነሳና በሕይወት የሚኖር ሰው ጠፋ። መቼም፥ ለመነሳት መሞት ይቀድማል።

ገና አልሞትንም፡- ለገንዘብ አልሞትንም፣ ለዝና አልሞትንም፣ ለሥልጣን አልሞትንም፣ ለዘረኝነት አልሞትንም፣ ለመሳደብ አልሞትንም፣ ለባህል አልሞትንም፣ ለሴረኝነት አልሞትንም፣ ለዓለም አልሞትንም፣ ለራሳችን ቴክኒክ አልሞትንም፣ ለሆነ ጉዳይ እንዳልሞትን ልቦናችን ያውቃል፣ ሥራችን ይናገራል።

መጽሐፍ ሲናገር "ሞቱንም በሚመስል ሞት፥ ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፤" ይላል። (ሮሜ 6:5)

ሌላው ነገር ሁሉ ይቅርብን፣ሞቱን በሚመስል ሞት እንሙት፣ ለመሞት እንተባበር፣ቀሪ ዘመናችን የትንሳኤ ይሆናል። የሥጋ ሞት ያለጊዜው የተስፋፋው፣ እውነተኛውን ሞትና ትንሳኤ ስለሸሸን ነው። አንሽሽ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie



PART 155
መልዕክት (message) 155
በብሉይ ኪዳን የሚኖሩ፥ የአዲስ ኪዳን ሰዎች

ውል ማፍረስ በዛ። ኪዳን ማፍረስ ጨዋታ ሆነ። ሕግ መጣስ የዘመኑ ጌጥ ሆኖአል። ስለ እውነት መኖር የሞኞች (ፋሮች) እጣ ፈንታ ተደርጎ መቆጠር ከጀመረ ሰንብቷል። “የተከበሩ” ፣ “ስጦታችን” “ዕንቊአችን”፣ “ምሳሌያችን”፣ ወዘተ የሚባሉትም በዚህ የተካኑት ናቸው።

መጽሐፍ “ያገባች ሴት፥ ባልዋ በሕይወት ሲኖር፥ ከእርሱ ጋር በሕግ ታስራለች፥...ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ ትባላለች ፤ ባልዋ ቢሞት ግን ከሕጉ አርነት ወጥታለችና ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ አይደለችም። ይላል (ሮሜ 7:2-3)

ሳይሞት ወይም ሳትሞት በላዩ (በላይዋ) ላይ የሚደረገው ጋብቻ፥ መሞቱ (መሞቷ) አይቀርም ከሚል እሳቤ የመጣ ይሆን?

በብሉይ ኪዳን፥ ስለ ሰዎች የልብ ጥንካሬ፥ ሚስቱን መፍታት ለሚፈልግ ሁሉ የፍችዋን ጽሕፈት እንዲሰጥ ሙሴ አዝዟል። (ማቴ 19:7)። ያሳዝናል! የአዲስ ኪዳን ሰዎች ነን፣ ኑሮአችን ግን የብሉይ ኪዳን ነው። አቤቱ፥ ምህረትህን አብዛልን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 156
መልዕክት (message) 156
የኩነኔ መድሐኒት ተገኘ........!

ኩነኔ ያለበት ሰው፥ፈውስ ያስፈልገዋል።ኩነኔ፥ብቻ ቀርቶ ብቻ የመታገል ውጤት ነው። ስለዚህም ሰዎች፥ ከኩነኔ ነጻ ሆኖ ለመገኘት አጋር (ተባባሪ) ይፈልጋሉ።

እንኳን ሰው አይደለም፥ መላእክትን አጋር(ተባባሪ) ለማድረግ ቢሞከር፥ ከኩነኔ ነጻ መሆን አይቻልም። መጽሐፍ አለ “እነሆ፥ በባሪያዎቹ አይታመንም፤መላእክቱንም ስንፍና ይከስሳቸዋል (ኢዮብ 4:18)

ታዲያ፥ ከኩነኔ እንዴት ነጻ መሆን ይቻላል? መጽሐፍ መልሱን እንዲህ ይሰጣል፥ “እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም።” (ሮሜ 8:1)

“አሁን” በማለቱ፥ ማንም “አሁን” በተባለው ጊዜ ከማን ጋር እንደሆነ ራሱን ይመልከት። እኔ ከኢየሱስ ጋር ነኝ። እናንተስ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!



facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 157
መልዕክት (message) 157
ለስጋ ጥቅም ሲባል መሞት..!

በምድር ላይ፥ ለጥቂት ጊዜ ቢሆንም፥ በስጋ የተሻለ ሕይወት መኖር መልካም ነው።መጽሐፍም ሲናገር “ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና፤” ይላል(1ጢሞ 4:8)

ለስጋ ጥቅም ሲባል ግን፡-

ራዕይ ሳይኖር አገር ወይም ተቋም መምራት፣ ጥሪ ሳይኖር ማገልገል፣ ብቃቱ ሳይኖር በማዕረግ መጠራት፣ያልሠሩበትን ገንዘብ እንደ አልቅት አልመጥገብ፣በእውቀት ከማሰብ ይልቅ በገንዘብ ማሰብ፣ እንደ ኃያላን ዝቅ ብሎ ሕዝብን ከማገልገል ይልቅ ሁልጊዜ ከላይ ለመሆን መመኘትና መዳከር፣ሕዝብንና አገርን አሳልፎ መስጠት፣ ወዘተ መጨረሻው ሞት ነው። እኔ ሳልሆን መጽሐፍ ነው ያለው፥ “ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው።”(ሮሜ 8:6)

እንደውም መጽሐፍ “ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤...በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም። ይላል (ሮሜ 8:7-8)። እግዚአብሔር በማን ደስ እያለው ይሆን?ጥል ላይ ያለውን ቤት ይቁጠረው! ምህረት!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 158
መልዕክት (message) 158
ሰይጣን ሙያውን ይነጠቅ ይሆን? ክስ!

የእግዚአብሔር ቃል ሲናገር “እግዚአብሔር የመረጣቸውን፥ ማን ይከሳቸዋል?” ይላል። (ሮሜ 8:33)

እዚህም እዚያም ክስ ነው።በማህበራዊ ሚዲያ የሚደረገው ይብሳል። በተመረጡት ላይ ሲሆን ከበድ ይላል። የስድቡ መነሻ ወይም መንደርደሪያ “ማን መረጠኽ/ሽ?”የሚል ነው።

ሳይታወቀን ከቃሉ በተቃራኒ የመኖር ባህል አዳበርን፤ ጌታም የተስማማ ሳይመስለን አልቀረም። ቃሉ “አፍህ ክፋትን አበዛ ፥ አንደበትህም ሽንገላን ተበተበ። ተቀምጠህ ወንድምህን አማኸው፥ለእናትህም ልጅ ዕንቅፋት አኖርህ ይህን አድርገህ ፥ዝም አልሁህ፤ እኔ እንደ አንተ እሆን ዘንድ ጠረጠርህ፤ እዘልፍሃለሁ በፊትህም እቆማለሁ” ይላል(መዝ 50:19-21)

ጌታ ሆይ፥ እባክህ ለሁላችን ምህረት ይሁን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**



PART 159
መልዕክት (message) 159
የያዝኩት እና የያዘኝ እውነት..!

መጽሐፍ አለ" ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ ግዛትም ቢሆን፥ ያለው ቢሆን፥የሚመጣውም ቢሆን ፥ ኃይላት ቢሆኑ፥ ከፍታ ቢሆን፥ ዝቅታ ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።" (ሮሜ 8:38-39)

ይሄ ሁሉ ሊለየኝ ካልቻለ፥በዚህ ዘመን የሚደረገው የነማንም ዘመቻ ከያዝኩት እና ከያዘኝ እውነት ሊለየኝ አቅም የለውም።

"ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም" (1 ቆሮ 13:8 )። ሌላው ነገር ሁሉ ይሻራል።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 160
መልዕክት (message) 160
ወድቀን አንቀርም...............!

ሥር፣ ግንድ፥ ቅርንጫፍ፣ቅጠል እና ፍሬ የአንድ ዛፍ ዋና ዋና አካል ክፍሎች ሊሆኑ ይችላሉ። የሁሉም ተግባር ለየቅል ነው ። ሥር ግንድ ሊሆን አይችልም፣ ቅርንጫፍ ደግሞ ቅጠል።

መጽሐፍ "ሥሩ አንተን ይሸከምሃል እንጂ ሥሩን የምትሸከም አንተ አይደለህም።" ይላል። (ሮሜ 11:18)

በእኛ ዘመን በዙ ቅጠሎች "እኔ ሥር ነኝ፣ አገሩን እና ሕዝቡን ለእኔ ተዉት፣ እኔ እሸከመዋለሁ" በማለታቸው፥ በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ በማህበራዊ ሕይወትና በኃይማኖት መስኮች አይወድቁ አወዳደቅ ወደቅን።

አይዘን፣ወድቀን አንቀርም "ዛፍ ቢቈረጥ .... ሥሩም በምድር ውስጥ ቢያረጅ፥ ግንዱም በመሬት ውስጥ ቢሞት፥ ከውኃ ሽታ የተነሣ ያቈጠቍጣል፤ ....።" (ኢዮብ 14፡7-9)።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።


በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!



facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 161
መልዕክት (message) 161
ትንቢት እና የትንቢት መጠን (ልክ)

ነገር ሁሉ በመጠን ሲሆን መልካም ነው። ከመጠን ሲያንስ ወይም ሲበዛ የሚስተዋለው ችግር ቀላል አይደለም። "ብዙ ማር መብላት መልካም አይደለም፤" ይላል መጽሐፍ (ምሳሌ 25:27)። ማር ጣፋጭ ነገር ነው፥መጠኑን ሲያልፍ ግን ጥሩ እንዳልሆነ በቃሉ ተመልክቷል።

መጠን ወሳኝ ጉዳይ ነው። መጽሐፍ"እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን፤...እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር" ይላል። (ሮሜ 12:6)። በዘመናችን እንደ እምነታችን መጠን ከምንናገረው ይልቅ እንደ መጣልን የምንናገረው ይበዛል።

የትንቢት አገልግሎት መልካም ነው። ችግሩ መጠን ሲያልፍ ነው። ከእምነት መጠን የዘለሉ ትንቢቶች፣ሕይወት ያበላሻሉ። የትንቢት አገልግሎት በዋናነት የሚፈልገው "ነብይ ነኝ" ባዩን ሳይሆን መጠን የሚያውቀውን የትንቢት አገልጋይ ነው። ጥሩ ምሳሌ ላንሳ፥ ኤልሳዕም "ነገ በዚህ ጊዜ በሰማርያ በር አንድ መስፈሪያ መልካም ዱቄት በአንድ ሰቅል፥ ሁለትም መስፈሪያ ገብስ በአንድ ሰቅል ይሸመታል" አለ፣ እንዳለውም ሆነ። (2 ነገሥ 7:1፣16)።ጌታ ሆይ፣እንዲህ ያለ እና መጠኑን የጠበቀ አገልግሎት አብዛልን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 162
መልዕክት (message) 162
ባለ ሥልጣንን የሚቃወም...!

ማን ነው ባለ ሥልጣንን የመሾም ሥልጣን ያለው? መጽሐፍ ሲመልስ “ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው።” ይላል። (ሮሜ 13:1)

ቀጣዩን መመሪያ ደግሞ መጽሐፍ “ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ”ሲል ያስቀምጣል(ሮሜ 13:1)።ከዚህ መመሪያ በተቃራኒ ማሰብም ሆነ መንቀሳቀስ ጥሉ ከማንም ጋር ሳይሆን ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር ነው። ከእርሱ ጋር የሚጣሉ ደግሞ “ይደቅቃሉ” ተብሎ ተጽፏል (1ሳሙ 2:10)

ስለዚህ ባለ ሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፤የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድ ይቀበላሉ። (ሮሜ 13:2)

የዛሬው መልዕክቴ፥ከወቅታዊ የአገራችን ሁኔታ አንጻር፥ ሁለት ዓይነት ስሜት ሊፈጥር ይችላል። መጽሐፍ እንዲህ እንደሚል “ታናሺቱን መጽሐፍ ወስጄ በላኋት፥ በአፌ እንደ ማር ጣፋጭ ሆነች፤ ከበላኋት በኋላም ሆዴ መራራ ሆነ።” (ራዕ 10:10)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 163
መልዕክት (message) 163
ታምመናል፥ ፈውስ ያስፈልገናል!

ግብር መክፈል፣ ቀረጥ መክፈል፣ መፈራት የተገባውን አካል መፍራትና ክብር ለሚገባው አካል ክብር መስጠት ከዕለታት አንድ ቀን በሆነ መንግስት ተጽዕኖ የተጀመረ ባህል እንደሆነ ተደርጎ መታሰብ የለበትም። እንዲህ ዓይነት ርዕሰ ጉዳይ ሲነሳም፥ጉዳዩን ከመንግስት ወይም"ይሄ ጉዳይ የሚያያዘው ከነ እከሌ ጋር ነው" ብሎ ማሰብ ንጹህ ግብዝነት ነው።

ሩጫው ሁሉ ግብር ላለመክፈል እና ቀረጥ ላለመክፈል ነው ፤ቅስቀሳው ሁሉ ስለ ድፍረትና ከማክበር/ከመከባበር ይልቅ ስለመናቅ(መናናቅ)ነው፤ከዚህ በላይ እንድንታመም መፍቀድ የለብንም፤ ታምመናል፥ ፈውስ ያስፈልገናል።

እኔ ግብር የምከፍለው፣ ቀረጥ የምከፍለው እና በየደረጃው መፈራት/መከበር የሚገባቸውን ሁሉ የምፈራና የማከብረው የእግዚአብሔር ቃል ስለሚል ብቻ ነው። "ለሁሉ የሚገባውን አስረክቡ፤ ግብር ለሚገባው ግብርን፥ ቀረጥ ለሚገባው
ቀረጥን ፥ መፈራት ለሚገባው መፈራትን፥ ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ።" (ሮሜ 13:7)።

ቅድሚያ፥ ክብር ለእግዚአብሔር ቃል!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 164
መልዕክት (message) 164
ዘፈን፣ ዓለሙና ሥራ አስኪያጁ!

ሌሊት እና ቀን፣ ጨለማና ብርሃን የተባሉት ጉዳዮች ጎን ለጎን ወይም በንጽጽር(ሳይነጣጠሉ)ዘወትር ይነሳሉ።ሌሊት እና ቀን ጨለማና ብርሃን መገለጫቸው ተግባር (ሥራ) ነው።መጽሐፍ "እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ።" ይላል (ሮሜ 13:12)

ጨለማ ራሱን የቻለ ዓለም ነው፣ ገዥም አለው (ኤፌ 6:12)፤ ገዥው (ሥራ አስኪያጁ) ሰይጣን ነው (ዮሐ 14:30)። የዚያ ዓለም ዋና ዋና ሥራዎች ከሚባሉት መካከል ዘፈን፣ መጠጥ ፣ዝሙት፣ መዳራት፣ ክርክር እና ቅናት ይገኙበታል። በነዚህና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ራሳችሁን ያሰማራችሁ ሰዎች፥ ቶሎ ውጡ። "ሌሊቱ አልፎአል፥ ቀኑም ቀርቦአል።" (ሮሜ 13:12)

መጽሐፍ "በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ፤ በዘፈንና በስካር አይሁን፥ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፥ በክርክርና በቅናት አይሁን፤" ይላል። (ሮሜ 13:13)

"ገንዘብን እንጀራ ላይደለ፥የድካማችሁንም ዋጋ ለማያጠግብ ነገር ለምን ትመዝናላችሁ?" ይላል ጌታ (ኢሳ 55:2)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 165
መልዕክት (message) 165
መኖርና መሞት፤ ስለ ምን?

ሐዋርያው ጳውሎስ ሲናገር"ከእኛ አንድ ስንኳ ለራሱ የሚኖር የለምና፥ ለራሱም የሚሞት የለም፤ በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለንና፥ ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን። እንግዲህ በሕይወት ሆነን ብንኖር ወይም ብንሞት የጌታ ነን። ይላል። (ሮሜ 14:7-8)

ይህን ክፍል ደጋግሜ ሳነበው፥ ከእኛ ዘመን አስተሳሰብ እና አኗኗር ጋር አልቀራረብ አለኝ። ለጌታ መኖር? ለጌታ መሞት? መቼ ለራሳችን ኖረን ጨረስን? መቼስ ለራሳችን ሞትን? ገና ስንት የምንኖርለት እና የምንሞትለት ጉዳይ አለ። ገንዘብ፣ ሥልጣን፣ መብት፣ ብሔር፣ ቋንቋ፣ ባህል፣ ኃይማኖት፣ ዝና፣ ወዘተ፣የተባሉትን ጉዳዮች፥መቼ ኖርንላቸው? ሞትንላቸውስ?

ይሄን መልዕክት የሚያነብ አንድ ሰው፥ስለ ራሱ እንዲህ ብሎ ሊጠይቅ ይችል ይሆናል፣ "እኔ ለምን እየኖርኩ ነው? ለምንስ ጉዳይ እየሞትኩ ነው?" መልሱ፡-

"ሰው ለተሸነፈበት ለእርሱ ተገዝቶ ባሪያ ነው"(2ጴጥ 2:19)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 166
መልዕክት (message) 166
ምን፥ እንድንኖር ነው፥ የተፈለገው?

እንዴት ነው የምንኖረው? እንደ ተማርነው ነዋ። እንዴት ነው የምናስበውስ? እንደ ተማርነው ነዋ። እንዴት ነው ሕይወትን የምንመራው? እንደ ተማርነው ነዋ። በትምህርት (እውቀት) ሳይሆን፥ በደመ-ነፍስ ሕይወቱን የሚመራ ሰው ካለ፥ እርሱ ሰው ሳይሆን እንስሳ ነው። ሕይወት ትምህርት ከሆነ፥ሰው ለምን የተማርነውን ትምህርት ይቃወማል? አንድ አንድ ሰው “የስህተት ትምህርት”ሲል እሰማለሁ፤ምን ችግር አለው ጊዜ ይገልጠዋል፣”የማይገለጥ የተከደነ፥የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለም።” (ሉቃ 12:2)

ለመኖር የተሰጠንን ትምህርት ከሚቃወሙ ሰዎች እንድንሸሽ መጽሐፍ “እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያ የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ፥ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ። እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙም በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ።” ይላል። (ሮሜ 16:17-18)

ከማንም ሰው ፈቀቅ የምንለው፥ ሰው ስለምንጠላ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ቃል ስለምናከብር ነው። የተማርነውን ቃል ከተቃወማችሁ፥ምን ኑሩ እያላችሁን ነው?ግን ምህረት ይሁን!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**



PART 166
መልዕክት (message) 166
ምን፥ እንድንኖር ነው፥ የተፈለገው?

እንዴት ነው የምንኖረው? እንደ ተማርነው ነዋ። አንዴት ነው የምናስበውስ? እንደ ተማርነው ነዋ። አንዴት ነው ሕይወትን የምንመራው? እንደ ተማርነው ነዋ። በትምህርት (እውቀት) ሳይሆን፥ በደመ-ነፍስ ሕይወቱን የሚመራ ሰው ካለ፥ እርሱ ሰው ሳይሆን እንስሳ ነው። ሕይወት ትምህርት ከሆነ፥ሰው ለምን የተማርነውን ትምህርት ይቃወማል? አንድ አንድ ሰው "የስህተት ትምህርት"ሲል እሰማለሁ፤ምን ችግር አለው ጊዜ ይገልጠዋል፣"የማይገለጥ የተከደነ፥የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለም።" (ሉቃ 12:2)

ለመኖር የተሰጠንን ትምህርት ከሚቃወሙ ሰዎች እንድንሸሽ መጽሐፍ "እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያ የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ፥ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ። እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙም በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኰል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ።" ይላል። (ሮሜ 16:17-18)

ከማንም ሰው ፈቀቅ የምንለው፥ ሰው ስለምንጠላ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ቃል ስለምናከብር ነው። የተማርነውን ቃል ከተቃወማችሁ፥ምን ኑሩ እያላችሁን ነው?ግን ምህረት ይሁን!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




PART 168
መልዕክት (message) 168
ማን ነው ጠቢብ? ........ሞኝ?

በዓለም ላይ ጠቢብ የሆኑ ሰዎች እነማን ናቸው? የተማሩ? የተመራመሩ? የተቀቡ? ራዕይ ያላቸው? መሪዎች? ሊቅሃን? ብዙ መጻህፍት ያነበቡ? ፖለቲከኞች? ባለሃብቶች? አባቶች? እናቶች?ወጣቶች?ህፃናት? ማህበራዊ ሕይወት ላይ የሠሩና ተጽዕኖ የፈጠሩ? ሕዝብ ያስከተሉ? ወዘተ? እነማን ናቸው?

ከተዘረዘሩት አብዛኞቹ "ጠቢብ ነኝ" እያሉና ለመሆን በስልት (በብልጠት)ጥረት እያደረጉ ራሳቸውን ያታልላሉ፤ከተዘረዘሩት ጠቢብ ማን ነው?ጠቢብ ለመሆንስ መስፈርቱ ምንድን ነው?

መጽሐፍ ሲናገር "ማንም ራሱን አያታልል፤ ከእናንተ ማንም በዚች ዓለም ጥበበኛ የሆነ ቢመስለው ጥበበኛ ይሆን ዘንድ ሞኝ ይሁን።" ይላል። (1 ቆሮ 3:18)

በልጦ ለመገኘት የሚደረግ የብልጠት እሽቅድድም ይበቃል! ስለ እግዚአብሔር ቃል ብለን፥ ሞኝ እንሁን፤ ያኔ ጠቢብ ነን።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 169
መልዕክት (message) 169
“እኔ እበልጣለሁ”፥ አይሠራም!


ብልጥግና ነው?ተቀብለን ነው።ስልጣን ነው?ተቀብለን ነው። ራዕይ ነው? ተቀብለን ነው። ፀጋ ነው? ተቀብለን ነው። ዲግሪ ነው? ተቀብለን ነው።ስም ነው?ተቀብለን ነው።እውቅና ነው? ተቀብለን ነው። ወዘተ ነው? ተቀብለን ነው። እንቅስቃሴያችን እና ንግግራችን ሁሉ ግን፥ እንዳልተቀበለ ሰው፥”እኔ ራሴ ነኝ” በሚል መንፈስ በልጦ የመገኘት ነው።

መጽሐፍ ከዚህ አመለካከትና እንቅስቃሴ ቀዝቀዝ እንድንል “አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጎሃል? ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? የተቀበልህ ከሆንህ ግን እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድር ነው?” በማለት ይመክረናል። (1 ቆሮ 4:7)

የዚህ ሩጫ ተወዳዳሪዎች፥ እባካችሁ ተመከሩ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!



facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 170
መልዕክት (message) 170
ልብ እንግዛ.......................!

የብዙ ሰው ሕይወት እንደ ትላንት አይደለም፥ ለውጥ አለው። ትላንት የማይታወቁ ሰዎች፥ ዛሬ የሚጠሩት በማዕረግ ስም ነው። ባለ ስልጣን እከሌ፣ አገልጋይ እከሌ፣ ባለ ሃብት እከሌ ፣ ምሁር እከሌ፣ አርቲስት እከሌ፣ የኃይማኖት አባት እከሌ፣ አክቲቪስት እከሌ፣ ጋዜጠኛ እከሌ፣ የፖለቲካ ተንታኝ እከሌ፣ የኢኮኖሚ ተንታኝ እከሌ፣የማሕበራዊ ሕይወት ተንታኝ እከሌ
፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች እከሌ እና ወዘተ እከሌ። ሁሉም በመስኩ ጠግቧል፣ ሁሉም በመስኩ ባለ ጠጋ ሆኗል። ግን አስተምረው፣ አሰልጥነውና መክረው ለዚህ ያበቁትን ሰዎች ያላገናዘበ እና ያላካተተ ጥጋብ እና ብልጥግና ነው።

መጽሐፍ፥ ቆም ብለን፥ አሁን ለደረስንበት ጥጋብና ብልጥግና ያበቁንን ሰዎች እንድናስብ ያስታውሰናል “አሁን ጠግባችኋል ፤ አሁንስ ባለ ጠጎች ሆናችኋል፤ ያለ እኛ ነግሣችኋል፤ እኛ ደግሞ ከእናንተ ጋር እንድንነግሥ ብትነግሡ መልካም ይሆን ነበር።” (1 ቆሮ 4:8)። ልብ እንግዛ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




PART 171
መልዕክት (message) 171
የሉም እንዳትሉኝ................!

በእኛ ዘመን፥ቁጥራቸው እጅግ ጥቂት ቢሆንም ስለ ክርስቶስ
ሞኞች፣ደካሞች፣የተዋረዱ፣የሚራቡ፣የሚጠሙ፣የሚራቆቱ፣
የሚጎሰሙ፣የሚንከራተቱ፣የተገባቸውን የሚሠሩ፣የሚደክሙ
፣ ሲሰደቡ የሚመርቁ፣ ሲያሳድዷቸው የሚታገሱ፣ ክፉ ሲናገ
ሩባቸው የሚማልዱ እና እስከ አሁን ድረስ፥ የዓለም ጥራጊና
የሁሉም ጉድፍ የሆኑ አገልጋዮች አሉ።

በእነዚሁ ሰዎች፥ አገልግሎት ደግሞ፥ በክርስቶስ ልባሞች፣
ኃይለኞች፣ የከበሩ፣ የጠገቡ፣ የረኩ፣ የበለጠጉ፣ የማይነኩ፣
የተደላደሉ፣ የማይደክሙ፣ የሚሳደቡ፣ የሚያሳድዱ እና ክፉ
የሚናገሩ ሰዎች ተፈጥረዋል። ኦ ጌታ ሆይ፥ ምን እየሆነ ነው
ያለው? አንድ ዘመን እየተደገመ ይሆንን? (1 ቆሮ 4:10-13)

ከአገልጋዮቹ ወገን መሆን ምንኛ መታደል ነው። ጌታ ይርዳን!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ
እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 172
መልዕክት (message) 172
አባትነት..........................!!

በመጽሐፍ ቅዱስ “አባት” ተብሎ፥ የመናፍስት አባት፣ የሥጋ አባት፣ የእምነት አባት፣ በወንጌል የወለደ (መንፈሳዊ) አባት፣ ወዘተ፥ በሚል እውቅና የተሰጠው ጉዳይ ነው፥ አባትነት።

“አባት” ተብሎ ግን፥ ብቸኛና ስልጣን ባለው አካል፥አንድ ብቻ ስለሚሰየም አይሻሻልም ወይም አይቀየርም። አባት መቼም አባት ነው። አባትነት፥ የመሰየምና የመደረግ ጉዳይ ስለሆነ ፍልስፍና አያሻውም። (ኤፌ 3:14-15፣ ዘፍ 17:15)

ሐዋርያው ጳውሎስ ሲመክር “በክርስቶስ አእላፍ ሞግዚቶች ቢኖሩአችሁ ብዙ አባቶች የሉአችሁም እኔ በክርስቶስ ኢየሱስ በወንጌል ወልጄአችኋለሁና።” ይላል (1ቆሮ 4:15)።

ጌታ ኢየሱስ እንኳ፥እርሱ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ “አባቴ” ሲል “እኔና አብ አንድ ነን”ያለውን ያን እግዚአብሔር አብ በአባትነት ተቀብሎ ያከብራል። ሰው፥ ያለ አባት በሚኖርበት ዘመን ሁሉ እሪያዎች ከሚበሉት አሰር ሊጠግብ ቢመኝ እንኳ የሚሰጠው አይኖርም (ሉቃ15:16)።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 173
መልዕክት (message) 173
ከውሾች ተጠበቁ...............!

አንድ አንድ ሰው በድብቅ(በድፍረት)ስለሚያከናውነው እኩይ ተግባር በሚያገለግለው ማህበረሰብ ውስጥ ይወራል ግን ክብር አይደለም።ዝሙት እንዴት ክብር ይሆናል? ስሪያ ለውሻ ነው።ውሻ"ስንት ሚስት አለህ?"አይባልም፥ምክንያቱም እርሱ እንሰሳ ነው። መጽሐፍ በዝሙት የተጠቃውን ሰው ሲገልጸው "ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለ አያውቅም፤ እንደሚጠፉ እንስሶች (ውሾች) መሰለ።" ይላል። (መዝ 49:12)

ወንድ ሆኖ ብዙ ሴት ማውጣት ወይም ደግሞ ሴት ሆኖ ብዙ ወንድ ማውጣት አሪፍ ማንነት ሳይሆን፥ አሪፍ ውሻነት ነው። በዝሙት አሪፍ ነን በዮች ሳያውቁት እኩይ ልምምዳቸው የት እንደደረሰ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲናገር "... በእናንተ መካከል ዝሙት እንዳለ ይወራል የዚያም ዓይነት ዝሙት በአሕዛብስ እንኳ የማይገኝ ነው፥ የአባቱን ሚስት ያገባ ሰው ይኖራልና።" ይላል፣ እግዚኦ ነው። (1ቆሮ 5:1)።

"ከሴት ጋር የሚያመነዝር አእምሮው የጐደለ ነው፤ እንዲሁም የሚያደርግ ነፍሱን ያጠፋል። ቍስልንና ውርደትን ያገኛል፥ ስድቡም አይደመሰስም። (ምሳሌ 6:32-33)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 174
(message) 174
ከጠማማ ጋር ጠማማ........!

ብዙ ጊዜ ሰዎች ወዳጅ ወይም ወንድም ከሚሉት ሰው ጋር አብረው የማይቀጥሉበት ጉዳይ እንደተፈጠረ እያወቁ ነገር ግን መለየት አይፈልጉም። አንዳንዶች ከጥቅም አንጻር ሊሆን ይችላል፣ አንዳንዶች ደግሞ፥ ሽፋን ለማግኘትና፥ፍላጎታቸውን ለመፈጸም ስለሚረዳቸው ይሆናል፣ አንዳንዶች ደግሞ፥ የሆነ አእምሮአቸውን የሚደልሉበትና ውሃ የማያነሳ፥ ተራ ምክንያት አላቸው።

ሐዋርያው ጳውሎስ “ ... ወንድሞች ከሚባሉት፥ አንዱ ሴሰኛ ወይም ገንዘብን የሚመኝ ወይም ጣዖት የሚያመልክ ወይም ተሳዳቢ ወይም ሰካር ወይም ነጣቂ ቢሆን ከእርሱ ጋር እንዳ ትተባበሩ እጽፍላችኋለሁ፤ እንደዚህ ካለው ጋር መብል እንኳን አትብሉ።” ይላል (1 ቆሮ5:11)

ሐዋርያው ጳውሎስ፥ እንዲያውም “...ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት” በማለት፥ ጉዳዩን ያከረረዋል (1 ቆሮ 5:13)። እኛ እንኳ፥እዚያ ደረጃ ላይ አልደረስንም ቢያንስ ግን ዛሬ እንለይ። አለዚያ የመጽሐፍ ቃል መፈጸሚያ እንሆናለን”...ከጠማማም ጋር ጠማማ ሆነህ ትገኛለህ።” (መዝ 18:26)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 175
መልዕክት (message) 175
ሰውና መላእክት................!

ሰውና መላእክት ሁለት የተለያዩ ማንነቶች፣ የተለያየ ዓለም ላይ የሚኖሩ እና የተለያየ የአኗኗር ዘይቤ ያላቸው ፍጥረቶች ናቸው። ፍጡራን ስለሆኑ ብቻ አንዳቸው አንዳቸውን ማምለክ አይችሉም። ግንኙነታቸው እንኳ የሚወሰነው በተጻፈው ቃል እና በተጻፈው ቃል ብቻ ነው። “ከተጻፈው አትለፍ” የሚለውን ልብ ይሏል። (1 ቆሮ 4:6)

አንድ አንድ ሰው እንደ ሰብዓዊ መብት ተሟጋች፥ የመላእክት መብት ተሟጋች መሆን ይፈልጋል። አንድ አንድ ሰው ደግሞ በአንጻሩ መላእክትን የማናናቅ አባዜ አለበት። ምን ነክቶናል? መከበር ያለበት ቃሉ ነው።

ታላቁ ሐዋርያው ጳውሎስ”የትዳር ጉዳይ ይቅርና በመላእክት እንኳ እንድንፈርድ አታውቁምን?” ይላል(1 ቆሮ 6:3)፤ በዚህ ጥቅስ”መላእክት ተደፈሩ” ብሎ የሚናደድ አይጠፋም።

በሌላ ሥፍራ ደግሞ “የመላክትንም እንጀራ ሰው በላ” ይላል (መዝ 78:25)፤ይህንን ጥቅስ አይቶ ደግሞ “ብንበላም ከነሱ በላይ ነን” የሚል ሌላ ጽንፈኛ አይጠፋም።

እባካችሁ፥ የእግዚአብሔርን ቃል፥ እኛ ለምንፈልገው ጉዳይ ሳይሆን እርሱ ለተናገረበት ዓላማ እናውለው!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 176
መልዕክት (message) 176
ምድራዊና ዘላለማዊ..........!

እጅግ ብዙ ሰው ምድራዊና ዘላለማዊ ጉዳይ የተምታታበት ይመስላል። ምድራዊ ኑሮ ከሰባ እስከ ሰማንያ ዓመት ባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ፥ እሚጠናቀቅ ሲሆን (መዝ 90:10)፤ ዘላለማዊው ደግሞ የጊዜ ገደቡ ዘላለም ነው።

መጽሐፍ ስለ ምድራዊው ኑሮ ሲናገር “ዘመኑ አጭር ሆኖአል ከእንግዲህ ወዲህ ሚስቶች ያሉአቸው፥እንደሌላቸው ይሁኑ የሚያለቅሱም፥ እንደማያለቅሱ፥ ደስ የሚላቸው ደስ እንደማ ይላቸው፥ የሚገዙ፥ ምንም እንደሌላቸው፥ በዚችም ዓለም፥ የሚጠቀሙ፥ በሙሉ እንደማይጠቀሙ ይሁኑ። የዚች ዓለም መልክ አላፊ ነውና።” ይላል። (1 ቆሮ 7:29-31)

ዘላለማዊ የሆኑ እና ምድራዊ የሆኑ ሰዎች በምን ይለያሉ? በጣም ቀላል ነው “በዚያን ጊዜ ሁለት ሰዎች በእርሻ ይሆናሉ ፤ አንዱ ይወሰዳል አንዱም ይቀራል፤ ሁለት ሴቶች፥ በወፍጮ ይፈጫሉ፤አንዲቱ ትወሰዳለች አንዲቱም ትቀራለች”(ማቴ 24 :40-41)። አይወራም እንጂ፥ የሚወሰዱ እና የሚቀሩ ሰዎች ታውቀዋል። እንዴት? ሁሉ እያደረገ ያለውን ያውቃል።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 177
መልዕክት (message) 177
አዋቂዎች እና ችግራቸው.....!

እውቀት መልካም ነገር ነው፤ ነገር ግን አዋቂዎች እየረበሹን ነው። ተናግረው መረበሽ፣ ጽፈው መረበሽ፣ ሰርተው መረበሽ ፣ተመርቀው እና አስመርቀው መረበሽ፣ አቋቁመው መረበሽ፣ ተቀብተው መረበሽ፣ተሰይመው መረበሽ፣ተሹመው መረበሽ፣
ሰብከው መረበሽ?አስተምረውና አሰልጥነው መረበሽ፣ ወዘተ መረበሽ። ለነገሩ "እውቀት ያስታብያል" አይደል የሚለው ቃሉ
(1 ቆሮ 8፡1)

የእውቀት ራስ የሆነውስ? በእውቀቱ ምን አደረገ? እርሱም ረበሸ? መጽሐፍ ሲናገር " ጻድቅ ባሪያዬም፥ በእውቀቱ፥ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል" ይላል (ኢሳ 53:11)። ይሄ ነው እንግዲህ የእውቀት ወጉ።

አዋቂዎች ነን የምንል ሁሉ፥ ቢያንስ ቢያንስ ሁለት ነገር፥ ልብ ልንል ይገባል። አንደኛው፥ ከላይ እንደተገለጸው እውቀታችንን ለራሳችን ጽድቅ ሳይሆን ለሌሎች ጽድቅ እናውለው። ሁለተኛ ደግሞ መጽሐፍ እንደሚል የደረስንበት የትኛውም የእውቀት እርከን ገና አለማወቃችንን ስለሚጠቁም ሰከን እንበል!!!
(1 ቆሮ 8፡1-2)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 178
መልዕክት (message) 178
ብንበላም፥ ባንበላም............!

አብዛኛው ሰው፥አብዛኛውን ሰዓት ስለምን ያስባል? ስለምንስ ሲል ይሠራበታል?ስለምንስ ነው የማግኘት ትግሉ? ስለምን ሲባል ነው ጥሎ ማለፉ?ከምናስበው እና ከምናደርገው ነገር ጀርባ ምንድን ነው ማግኘት የተፈለገው? መብል ነው? ከሆነ ያስቃል። "ለምን?" እንዳትሉኝ። ምክንያቱም "መብል ለሆድ ነው፥ሆድም ለመብል ነው፤እግዚአብሔር ግን ይህንም ያንም ያጠፋቸዋል።" (1 ቆሮ 6:13)

ብዙ ሰው፥ ስለሚበላው ነገር ሲል ክቡር ማንነቱን ለማይገባ ነገር አሳልፎ ይሰጣል።ይሄ ጉዳይ ገንዘብ የሌላቸውን ድሆች እንጂ፥ እኔን አይመለከትም፥ የሚል አስተሳሰብ ካለ የተሳሳተ አስተሳሰብ ነው።ስለሆዳቸው መብል ሲሉ ስልጣን አንለቅም የሚሉ ሰዎች በሁሉ ሴክተር፥ የበቀሉበት ነው፥ የሰለጠነው ክፍለ ዘመናችን (21ኛው ክፍለ ዘመን)። ድንቄም ስልጣኔ፣ ሆድን ማዕከል ያደረገ ስልጣኔ።

እግዚአብሔርን ለምትፈልጉ ለእናንተ ግን፥ መጽሐፍ ሲመክር "መብል ግን፥ ወደ እግዚአብሔር አያቀርበንም፤ ባንበላም፥ ምንም አይጎድለንም ብንበላም ምንም አይተርፈንም"ይላል። (1ቆሮ 8:8)። እምናተርፍበት ጉዳይ ላይ እናተኩር!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 179
መልዕክት (message) 179
የማንን ጽዋ ልጨልጥ?

ስንት ጽዋ ነው ያለው? ስንት ጽዋ ነው የምንጠጣው?ከስንት ጽዋስ ነው እንድንካፈል መጽሐፍ የሚነግረን?አንድ ነገር ልብ ልንል ይገባል፤ ሁሉ ተፈቅዶአል፥ሁሉ ግን አይጠቅምም፤ ሁሉ ተፈቅዷል፥በእኛ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳ አይሠለጥንብንም (1 ቆሮ 6:12)

መጽሐፍ ሲናገር “የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ፥ ልትጠጡ አትችሉም። ከጌታ ማዕድ እና ከአጋንንት ማዕድ፥ ልትካፈሉ፥ አትችሉም።” ይላል (1ቆሮ 10:21)። እንግዲህ ከዚህ በኋላ የተገኘውን ጽዋ አንስቶ መጠጣት ይበቃል። ጽዋ ከሆነ ወይ የጌታ ነው ወይም ደግሞ የአጋንንት ነው። የጌታ ጽዋ ከሆነ፥ ራሱ “እንካችሁ” ብሎ የሰጠን፥ የገዛ ስጋው እና ደሙ ነው። (ማቴ 26:26-28)። ይህን የሚጠጣ (የሚካፈል) የዘላለም ሕይወት ይካፈላል።

ከዚህ ውጪ ሊኖር የሚችለው ጽዋ የአጋንንት ነው።ውጤቱን ለአጋንንት ትቼዋለሁ። እንግዲህ የተገኘውን ጽዋ መጨለጥ፥ መዘዝ እንዳለው እንወቅ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 180
መልዕክት (message) 180
መምሰል የምፈልገው..........!

ልጅ ከተወለደ በኋላ"መልኩ ማንን ይመስላል/ትመስላለች? የሚል የተለመደ ጥያቄ አለ። "ቁርጥ አባቱን/አባቷን"፣"የለም እናቱን/እናቷን ነው" የሚሉ ክርክሮች የተለመዱ ናቸው።

በወጣትነት ወይም ጉልምስና ይሄ ጥያቄ ብዙም አይነሳም፥ ግን ወሳኝ ጉዳይ ነው። ሰዎች መምሰል የሚፈልጉት ማንነት አለ። ያንን አካል መምሰል የሚፈልጉትም፥መምሰል ስለፈለጉ ሳይሆን፥ መምሰል የፈለጉት አካል፥ ከፈጠረባቸው ተጽዕኖ፥ የተነሳ ነው።

ምድር ከተፈጠረች ጀምሮ፥ አያሌ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ወደ ምድር መጥተዋል፣ተጽዕኖ ፈጠረው አልፈዋልም፤እስከ አሁን ከመጡት ሰዎች መካከል፥ ጳውሎስ መምሰል የፈለገው እና እኛም እንድንመስል የተፈለገውን ሲጠቁም፥እንዲህ አለ "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ"(1ቆሮ 11:1)።

"ለምን ክርስቶስን አለ?" ብዬ ስጠይቅ፥ አንድ ነገር ገባኝ።ለካ እሱ የመጣው ከላይ ነው። ከላይ የሚመጣው ደግሞ ከሁሉ በላይ ነው (ዮሐ 3:31)።ከምድር የተነሳን ሰው መስዬ ምድር ላይ እንዳልቀር፥ እኔ መምሰል የምፈልገው ከላይ የመጣውን እርሱን ነው። እናንተስ????????

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie



PART 181
መልዕክት (message) 181
ከኖርን፥ ለማነጽ ብቻ...........!

የብዙ ሰዎች በተለይም ደግሞ ተከታይ አላቸው የሚባሉትን እንቅስቃሴ ስንመለከት በተናጥል ዓላማ የተቃኘ፣ ከሌላው ጋር መጣመር የማይፈልግ፣ ከጋራ አጀንዳ የራቀ፣ ዝቅ ብሎ ሌላው ከፍ የሚልበትን መርኽ መቼም ቢሆን የማይቀበል፣ የተለየ ሆኖ የመገኘት አባዜ የተጠናወተው፣ ከ"ተበድለናል" እና "ተጠቅተናል" ከሚል አስተሳሰብ የሚናሳ ሆኖ ይገኛል። ስለዚህ ግቡ ዝና (ታዋቂነት) ነው፤ አልያም የበላይነት።

መጽሐፍ "ምንድር ነው? በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው፥ትምህርት አለው፥ መግለጥ አለው፥ በልሳን መናገር አለው፥መተርጐም አለው፤ሁሉ ለማነጽ ይሁን" ይላል (1ቆሮ 14:26)

ማንም እንሁን፣ምንም ነገር ይኑረን፣ ምንም ያህል ተቀባይነት እናግኝ፣ የቱንም ያህል የሕዝብ ቁጥር ይከተለን፤ አንድ ቃል፥ መጽሐፉ ያለውን እንርሳ "ሁሉ ለማነጽ ይሁን"(1ቆሮ 14:26)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 182
መልዕክት (message) 182
ነቢያት፥ ሁሉም እንዲማሩ....!

በዓለም አቀፍ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በአገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ እውቅናን እያገኘ የመጣው የነቢያት አገልግሎት እንዴት እንደሆነ ባይታወቅም ሥር ሰድዶ በፖለቲካው ዓለም ሳይቀር “ተንብዩ፥የእርስዎ ትንቢት ይሠራል” አሚባሉ ሰዎችን አብቅሏል።

እንደውም መጽሐፉ “የነቢያትም መናፍስት ለነቢያት ይገዛሉ” ሁሉ ይላል (1ቆሮ 14: 32)። እንኳን መገዛዛቱ፥ መቀባበሉስ አለ? የነቢያት ቢሮ ምን እየሆነ ነው?

ቃሉ ነቢያቱ “...ሁሉም እንዲማሩ ሁሉም እንዲመከሩ” ይላል (1ቆሮ 14:31)። እውን የሚማሩ አሉ? ምክርስ የሚቀበሉት እነማን ናቸው? ለመውቀስ ሳይሆን እውነቱን ለመናገር፥ ማን ነው ከነቢያቱ መካከል የመማርና የመመከር ልብ ያለው?ኧረ ዝም ይሻላል።በቅንነት”አናስተምራችሁ፣እንምከራችሁ”ብለው የተነሱ ሰዎችን እንኳ በሕዝብ መገናኛ ብዙኃን ማብጠልጠል ከተጀመረ ሰነባበተ። ጌታ ሆይ፥ ክፍሉን አንድ ጊዜ አስብ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 183
መልዕክት (message) 183
መጠመድ.......................!

ድንገት ሳናውቀው፥ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ያለው የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ(ፖለቲካው፣ኢኮኖሚው፣ማህበራዊ ሕይወቱ ፣ባህሉ፣ኃይማኖቱ፣ትርክቱ፣ወዘተ)፥የነበረንን የቀድሞ ማንነት እና አቋም አስክዶ፥ "ይወዳጇታል" ተብሎ ከማይገመት ሰው (ማህበረሰብ) ጋር አጣምሮናል።

መጽሐፍ "ከማያምኑ ጋር፥ በማይመች አካሄድ አትጠመዱ። ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?" ይላል (2 ቆሮ 6:14)።

ወገኖቼ፥ ቀድሞ ማን ነበርን?ምንስ እያደረግን ነበር? ከነማን ጋርስ ነበርን? አሁንስ ከነማን ጋር፥ ምን እያደረግን ነው?

ሐ.ጳውሎስ "እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት፥ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ።" ይላል (2 ቆሮ 11:3)። ቆም ብለን ትላንትናችንን እና ዛሬን በንጽጽር እንመልከት!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በነ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 184
መልዕክት (message) 184
ስለማይነገር (unspeakable)....

ከጥንት ጀምሮ እስከ ተያያዝነው የስልጣኔ ዘመን ድረስ አገር ለአገር፣ ሕዝብ ለሕዝብ፣ ማህበረሰብ ለማህበረሰብ፣ ሰው ለሰው፣ ተቋም ለተቋም፥ ስጦታ ሲያበረክት ነው የመጣው። የትኛውም አካል ለየትኛውም አካል ያበረከተው ስጦታ ሁሉ መጠኑ የታወቀና ሊነገር(ሊዘገብ)የሚችል ነው፤ተነግሯልም፤

አንድ ስጦታ መጠኑ መነገር(መዘገብ) ከቻለ፥ በጣም ጥቂት ነው ማለት ነው። "ለምን" ትሉኝ ይሆናል። ሊነገር (ሊዘገብ) የማይችል ስጦታ አለና።

መጽሐፍ "ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን።" ይላል። (2 ቆሮ 9:15)።ዳዊት እግዚአብሔር ያደረገውን ነገር ሁሉ መዘርዘር የሚቻል መስሎት፣ለመናገር አስቦ ነበር። ነገር ግን"ባወራም ብናገርም ከቍጥር ሁሉ በዛ።"ብሎ ነው ቁጭ ያለው (መዝ 40:5)።

ለአገር፣ ለሕዝብ፣ለማህበረሰብ፣ለሰው ወይም ለተቋም አስር ብር ሰጥተን፥አስር ዓመት ይዘከርልን ባዮች፥ጌታ ማስተዋሉን
ይስጠን።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 185
መልዕክት (message) 185
ተመሳስሎ መቀጠል የለም...!

መጽሐፍ"ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና።" ይላል (2 ቆሮ 11:14)። መምሰል እና መሆን ሁለት የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው። በዕለት ከዕለት ሕይወታችን እየተፈተንን ያለነውም በሆኑ (ጥሪው ባላቸው) እና መስለው በቀረቡ ማንነቶች እየተሰጠ ባለው አምታች አገልግሎት ነው

ሁሉ ነገር እንደነበረ አይቀጥልም። ሁሉ ነገር ፍጻሜ አለው። ፍጻሜውም እንደ ተሠራው ሥራ ይሆናል።መጽሐፍም ሲናገር "አገልጋዮቹ፥ ... የጽድቅ አገልጋዮች እንዲመስሉ፥ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም፤ ፍጻሜአቸው እንደ ሥራቸው ይሆናል።" ይላል። (2 ቆሮ 11:15)

ብዙም ሳይርቅ በቅርቡ፥ ሁሉም ይለያል። (ማቴ 3:12)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 186
መልዕክት (message) 186
የተረገምኩ እንዳልሆን.........!

ወንጌል የማን ነው? ማንስ ነው ባለቤቱ? ወንጌል ስለ ማንስ ነው? መጽሐፍ ሲመልስ "ሐዋርያ...ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ። ይህም ወንጌል ... ስለ ልጁ ነው፤ እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።" ይላል። (ወደ ሮሜ 1:1-4)


ወንጌል የእግዚአብሔር አጀንዳ ከሆነ፣ወንጌል ስለ ልጁ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ከሆነ፥ ለምንድን ነው ስለ ሌላ አካላት ማውራት የተፈለገው? ለምንድን ነው ስለ ሌላ አካላት ማወቅ የተፈለገው? ጳውሎስ ራሱ ከዚህ ውጪ ማወቅ እንዳልፈለገ ተናግሯል "ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር፥ እርሱም እንደተሰቀለ፥ ሌላ ነገር እንዳላውቅ ቆርጬ ነበርና።" (1ቆሮ 2:2)

ሐዋርያው ጳውሎስ ቁርጡን ሲናገር፥ "ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን።" አለ። (ገላ 1:8)

እኔም የተረገምኩ እንዳልሆን፥ ከዚህ ዘመን በኋላ፥ ከኢየሱስ ክርስቶስ ውጪ ማንንም አልወቅ፣ ማንንም አልስበክ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!




**Aynalem Mersie**

PART 187
መልዕክት (message) 187
ማን ደስ ይበለው?

የወንጌልን መልዕክት፥ በቀጥታ ከራሱ ከኢየሱስ ክርስቶስ፥ በመቀበል ማገልገል እንዳለ ሁሉ ከሰው ተቀብሎ (ተምሮ) ማገልገል እንዳለም ከጳውሎስ መልዕክት መረዳት ይቻላል። "በእኔ የተሰበከ ወንጌል እንደ ሰው እንዳይደለ ... ኢየሱስ ክርስቶስ ገልጦልኛል እንጂ እኔ ከሰው አልተቀበልሁትም አልተማርሁትምም።" (ገላ 1:11-12)

"ኢየሱስ ክርስቶስ ገልጦልኛል" የሚለው አባባል ለአንዳንድ ሰዎች ብዙም አይመችም።ስለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ጉዳዩን ያነሳው። ግን ጉዳዩ የዚያ ዘመን መነጋገሪያ ብቻ ሆኖ አልቀረም። ዛሬም አጀንዳው ሲነሳ "አታንሱብን" ባዮች የሒስ ብዕራቸውን ከመቅጽበት ይመዠርጣሉ። "ተገለጠልኝ" የሚል ሰውም እንዳይሰነብት ይመስላል፥ተቃውሞው ቅጥ ያጣ ነው

እንግዲህ ምርጫው የባለቤቱ ነው። የተገለጠለትን ራዕይ መፈፀምና እግዚአብሔርን ማስደሰት፤ አለያም ስላነበረው የኖረ ባህል እና ሰውን ለማስደሰት ሲል ራዕዩን መተው። (ገላ 1:10)። እስከአሁን የተመጣው እንዲህ ነው። ጌታ ይርዳን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie



PART 188
መልዕክት (message) 188
ሐሰተኞችን አንታገስም........!

በአንድ የሆነ የማህበረሰብ አገልግሎት መስክ ላይ ከተሰለፉ አገልጋዮች መካከል፥ እውነተኞች እንዳሉ ሐሰተኞችም አሉ። ሐሰተኞቹ፥ አንዳንድ መለያ ጠባይ አላቸው። በሌሎች ድካም (ሌሎች አገልጋዮችን፥ በቴክኒክ፥ ባሪያ አድርጎ) መጠቀም፣ ሾልኮ በጉዳዮች ላይ ጣልቃ መግባት፣ በስውር መሰለል እና ለመሪ አእምሮ በሚመች መልኩ መረጃ ቀምሞና አቀነባብሮ ማቅረብ፣ የወንጌል እውነት (ራዕይ) እንዳይጸና መከፋፈልን ማድረግ፣ ወዘተ።

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ጉዳይ አልፎ እስከወሰደው ውሳኔ ሲገልጽ “ነገር ግን፥ ባሪያዎች ሊያደርጉን በክርስቶስ ኢየሱስ ያለንን አርነታችንን ይሰልሉ ዘንድ፥ ሾልከው በስውር ስለ ገቡ ስለ ሐሰተኞች ወንድሞች ነበረ።የወንጌልም እውነት በእናንተ ዘንድ ጸንቶ እንዲኖር አንድ ሰዓት እንኳ ለቅቀን አልተገዛንላቸውም።” ይላል (ገላ 2:4-5)

ሐሰተኞችን ዛሬም ቢሆን አንታገስም። ጳውሎስ ለአንድ ሰዓት ነው ያለው፥ እኛ ግን ለአንድ ሴኮንድ እንኳ እድል አንሰጥም። ምክንያቱም አባታቸው ዲያብሎስ ነው። (ዮሐ 8:44)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie



PART 189
መልዕክት (message) 189
መቆም የለም......................!

በየትውልዱ የወንጌል አደራ ተሰጥቷቸው የሚላኩ ሐዋርያት (የተላኩ/ባለራዕዮች)አሉ። እንዲህ ያለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት የማይመቻቸው ሰዎች ምናልባት ካሉ እነርሱ አለቆች ወይም አለቅነት የተጠናወታቸው አንዳች እንኳ የሚጨምሩት የሌላቸው ናቸው፤ ጳውሎስ ይህ ጉዳይ በገጠመውጊዜ ምን አለ"አለቆች የመሰሉት ግን፥በፊት ማን እንደ ነበሩ አይገደኝም እግዚአብሔር የሰውን ፊት አይቶ አያደላም፤አለቆች የመሰሉት አንዳች እንኳ አልጨመሩልኝምና፥" (ገላ 2:6)

የወንጌል አደራ ለአንድ ሰው ከተሰጠው፥ቆይቶም ቢሆን ሁሉ ያየዋል፣ አለቆች ሳይቀሩ። ምክንያቱም ከዚያ ተልዕኮ ጀርባ የሚሠራ አለ። ጳውሎስ ይህን ሲያረጋግጥ "ተመልሰው ግን ጴጥሮስ ለተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደ ተሰጠው፥ እንዲሁ፥ ለእኔ፥ ላልተገረዙት የሆነው ወንጌል፥ አደራ እንደ ተሰጠኝ አዩ፤" ይልና "ለተገረዙት ሐዋርያ እንዲሆ ለጴጥሮስ የሠራለት፥ ለእኔ ደግሞ ለአሕዛብ ሐዋርያ እንድሆን ሠርቶአልና" ይላል። (ገላ 2:6-8)

አደራ የተቀበለን ሰው መጽሐፍ እንዲህ ይለዋል "አንተ ግን እስከ ፍጻሜው፡፡ ድረስ ሂድ። አንተም፥ ታርፋለህ። በቀኑም መጨረሻ በዕጣ ክፍልህ ትቆማለህ።" (ዳን 12:13)፤ አደራ ተቀብሎ መቆም የለም!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 190
መልዕክት (message) 190
የሕግ አምሮት...................!

ሕግና የተስፋ ቃል ሁለት የተለያዩ ነገር ግን የማይቀዋወሙ ጉዳዮች ናቸው። ይህ ማለት ግን፥ ልዩነት የላቸውም ማለት እንዳልሆነ ልብ ይሏል። የሕግ ዋና ችግሩ ሰዎች ፈጽመውት ሕያው መሆን አለመቻላቸው ነው።"አትስረቅ"ይላል፤ይሄ ሕግ እንደ እድሜ ማራዘሚያ ኪኒን ዘወትር የሚዋጥ (የሚጠበቅ) ነው። ለደቂቃ ሳይውጥ(የተላለፈ)ሰው በዚያው ቅጽበት ሕጉ ገድሎታል።

የተስፋ ቃል ግን እንዲህ አይደለም፣ ይሰበካል እንሰማዋለን፣ እናምነዋለን ወዲያውኑ ያጸድቀናል (ህያው ያደርገናል)፤በቃ፤ መጽሐፍም፥ ይህንኑ የሕግና የተስፋ ቃል፥ ትክክለኛ ንጽጽር፥ በግልጽ ሲያስረዳ "እንግዲህ ሕግ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል የሚቃወም ነውን? አይደለም። ሕያው ሊያደርግ የሚቻለ ው ሕግ ተሰጥቶ ቢሆንስ በእውነት ጽድቅ ከሕግ በሆነ ነበር" ይላል (ገላ 3:21)።

ስለዚህ ወገኖቼ፥ የሕግ አምሮትም ካለባችሁ፥ ከተስፋ ቃል የሚመነጨውን በክርስቶስ ኢየሱስ ያለ የሕይወት መንፈስ ሕግ ተጠቀሙ። ያኔ ሕያው ትሆናላችሁ። (ሮሜ 8፡1-2)


መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 191
መልዕክት (message) 191
ትኩረት እና ርብርብ............!

ቁሳዊ በረከት እንዳለ ሁሉ መንፈሳዊ በረከትም አለ።በግዑዙ ዓለም ላይ እየኖርን ስለሆነ፥ ብዙ ጊዜ፥ ከቁሳዊ በረከት ጋር የተያያዘ ጉጉት እና ቅስቀሳ አለ።ተጓዳኝ ክርክሩም፣ንትርኩም ቀጥሎ ይመጣል። መንፈሳውያን ተቋማትም ሲሰብኩ ሰሙ ስለ መንፈሳዊ በረከት ይሁን እንጂ ወርቁ ቁሳዊ ነው። በዚህ ጉዳይ የሚነሳው ሙገት የሰም እና ወርቅ ቅኔ ነው።

ይመስለኛል"አስቀድሞ ፍጥረታዊው ቀጥሎም መንፈሳዊው ነው እንጂ መንፈሳዊ መጀመሪያ አይደለም"የሚለውን ጥቅስ ለማክበር ሳይሆን አይቀርም ምድራዊ በረከት(ብር) ላይ ልዩ ትኩረት እና ርብርብ ሲደረግ ይታያል። (1 ቆሮ 15:46)

እውነት መጨረሻችን ሰማይ ከሆነ፥በሰማያዊ ስፍራ ስላለው መንፈሳዊ በረከት በጥልቀት ማጥናቱ አይሻልም ትላላችሁ? (ኤፌ1:3)ምድራዊ በረከት እንደሆነ ቢፈልግም ባይፈልግም መርሁን እስከ ጠበቅን ድረስ መከተሉ የግድ ነው።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**



PART 192
መልዕክት (message) 192
የመጀመሪያው ምርጫ........!

በዓለማችን ላይ ከሚገኙና ቁጥራቸው 220 በላይ ከሚሆኑ አገሮች መካከል 19ኙ በተያዘው የፈረንጆቹ ዓመት (2021) ምርጫ በማካሄድ ላይ ናቸው። አገራችን ኢትዮጵያም ሰሞኑን ምርጫ ላይ ነች። ሁሉም የሚመርጠው መሪውን ነው። መሪ ራሱስ ይመርጣል? እንዴታ፤ መሪም፥ በተወዳደረበት ሥፍራ ሲመርጥ አይተናል።

እግዚአብሔር ግን መርጦ ያውቃል?

መጽሐፍ ሲመልስ "ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን"ይላል(ኤፌ 1:4)። የእግዚአብሔር ምርጫ፥ እንደውም የመጀመሪያውና ዓለም ሳይፈጠር የተካሔደ ነው። ምርጫ በርዱም (በሩ) ክርስቶስ ነው። (ዮሐ 10:9)

እኔ በቦርዱ(ክርስቶስ) በኩል ከተመረጡትና የእግዚአብሔር ልጆች ከሆኑት መካከል አንዱ ነኝ (ዮሐ 1:12 ። እናንተስ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 193
መልዕክት (message) 193
ራስ እና አካል....................!

ቤተ ክርስቲያን፥ ቤተ ክርስቲያን መሆኗ ከሚለይባቸው ቀላል መንገዶች አንዱ፥ አብይ ክፍሏን ማወቅ ነው። ቤተ ክርስቲያን ሁለት አብይ ክፍሎች፥ አሏት። ራስ እና አካል። ራስ፥ ክርስቶስ ነው። አካል ደግሞ፥ ራስ በሆነው በክርስቶስ፥ አዲስ ፍጥረት የሆነን ሰው ሁሉ ያጠቃልላል፤ከዚህ ራስ ከሆነው ከክርስቶስ አገዛዝ ውጪ ያለን የትኛውም ተቋም(ማንነት)ቤተ ክርስትያን ለማለት አይቻልም። ፧

መጽሐፍ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ሲናገር “ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲ ያን ሰጠው። እርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት።” ይላል። (ኤፌ 1:22-23)

ክርስቶስ ራስ ያልሆነበት፣ እርሱ ብቻ የማይጠራበትና እርሱ ብቻ የማይገነንበት ቤት(ማንነት)፥ ቤተ ክርስቲያን አይደለም፣ ሆኖም አያውቅም፤ግን የወንበዴዎች ዋሻ ነው፤(ሉቃ19:46)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 194
መልዕክት (message) 194
ማቀንቀን ሳይሆን፥ መኖር.....!

ሁሉ ነገር አንድ ነው።አንድ ተስፋ፣አንድ አካል፣አንድ መንፈስ፣ አንድ ጌታ፣ አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ጥምቀት፣አንድ አምላክ።

መጽሐፍም “በመጠራታችሁ፥ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ፥ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን፥ በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።” ይላል። (ኤፌ 4:4-6)። ጥቅሱን ማቀንቀን ሳይሆን፥ መኖር ነው።

ብዙ የማህበረሰብ ክፍል፣ በስሩ ያቀፈው ሕዝብ፣ አመራሮቹ እስከ አንድ ተራ ግለሰብ ድረስ፥ አሁን አሁን፡ አንድ የመሆን፣ በአንድነት የመኖር እና በአንድ ሃሳብ የመስማማት ህልምም ሆነ ፍላጎት የለም። እንዲህ ያለ ማህበረሰብ በእርግጥ አንድ እተባለው ተስፋ፣ አካል፣ መንፈስ፣ ጌታ፣ ሃይማኖት፣ ጥምቀት
ብሎም አምላክ ጋ ይደርስ ይሆን?

አንድ የመሆን ህልም የሌለው፣ አንድ ከሆነው አምላክ እጅግ እሩቅ ነው!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 195
መልዕክት (message) 195
ዋልታዎችን የረገጠ............!

መውረድና መውጣት ሁለት አንጻራዊ ዋልታዎችን የሚያሳዩ እንቅስቃሴዎች ናቸው። የመውረድ የመጨረሻ ጫፍ (ወኅኒ 1ጴጥ3:19)እንዳለ የመውጣት የመጨረሻ ጫፍ(ከሰማያት በላይ ኤፌ 4:10) አለ። እነዚህን ጫፎች የረገጠ አለ? ካለስ ፥ማን ነው?

መጽሐፍ "ወደ ላይ በወጣ ጊዜ፥ ምርኮን ማረከ፥ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ ...ወደ ምድር ታችኛ ክፍል ደግሞ ወረደ ማለት ካልሆነ፥ ይህ ወጣ ማለትስ ምን ማለት ነው? ይህ የወረደው ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው።" ይላል ክርስቶስ ኢየሱስን። (ኤፌ 4:8-10)

ኢየሱስ፥የመውጣትና የመውረድ ዋልታዎችን የረገጠ (እዳች ንን የከፈለ) ብቻ ሳይሆን፤እርሱ አልፋ (መጀመሪያ) ደግሞም እርሱ ኦሜጋ(መጨረሻ) በመሆን (ራዕ 22:13) መጀመሪያና መጨረሻ እንዲኖረን ያደረገ፣ሊወስደንም የሚመጣ ጌታ ነው ስለዚህ መጽሐፍ የሚለውን እላለሁ "ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወድ ቢኖር የተረገመ ይሁን።ጌታችን ሆይ፥ ና።" (1 ቆሮ 16:22)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 196
መልዕክት (message) 196
ውሸት እና ውሸታሞች.........!

እውነት እና ውሸት የንግግር ወይም የቃላት ጨዋታ ሳይሆን የዕለት ከዕለት ሕይወት መገለጥ ነው። ጌታ ኢየሱስ ሲናገር “እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ” አለ (ዮሐ 18:37)።ጌታ ኢየሱስ በምድር በነበረ ጊዜ አኗኗሩም ሆነ እንቅስቃሴው ሁሉ የእውነት ነበር
፤ ሲያስብ የእውነት፣ ሲናገር የእውነት፣ ሲያገለግል የእውነት፣ ሲወጣና ሲገባ የእውነት፣ ሲኖር የእውነት፣ ሲሞት የእውነት፣ ሲነሳ የእውነት፣ ሁሉ የእውነት ነው።

በእኛ ዘመን ውሸት በዝቷል።ለመኖር ሲባል(ለጥቅም ሲባል) እማናምንበትን ርዕዮተ ዓለም ማቀንቀን፣ እማንወደው ስፍራ መኖር፣ ጥሪያችን አልሆነ ጉዳይ ላይ መሠማራት፣ በሌለን እውቀት ተንታኝ መሆን፣ ባላዘንበት ጉዳይ ማልቀስ፣ ተጎድቶ መሳቅ፣ ተኝቶ የነቁ መምሰል፣ ተሸንፎ የድል ዜማ መልቀቅ፣ ተወስኖብን “ተወሰነልን” ማለት፣ ለቅቀን አስለቀቅን ማለት፣ ሞተን “አሉ እኮ” ማስባል፣ወዘተ።

ውሸት ያወረስነው እና የውሸት ሕይወት የዘራንበት ትውልድ የተሻለ ውሸታም እንደሚሆን እሙን ነው። ያልዘሩት አይበቅ
ልምና። መጽሐፍም “ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፥ እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ።” ሲል ይመክራል። (ኤፌ 4:25) ጌታ ሆይ ውሸት እና ውሸታሞችን በቃችሁ በለን። የእውነት ያለህ!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 197
መልዕክት (message) 197
ስም እና ተጽእኖው.............!

ስም ማግኘት መስዋዕትነት ይጠይቃል። ስም ማንነት ነው፣ ስም መለያ ነው፣ስም ስልጣን ነው።እውነተኛ ስም ለማግኘት እውነተኛውን መንገድ መሄድ ግን የግድ ነው፤የባሪያን መልክ መያዝ፣ ራስን ባዶ ማድረግ፣ ዝቅ ማለት፣ ሞት የሚጠይቅ ጉዳይ ካለ ለዚያ ራስን ማዘጋጀት ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው።

ጌታችን ኢየሱስም አዳኝ የሆነውን ስሙን የተቀበለው በዚህ ጎዳና አልፎ ነው "የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ...እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ።በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ
"(ፊልጵ 2:7-10)

ከዚህ አንጻር በሌላ መንገድ የሚገኝ ስም ሁሉ፥ ስም መሆን እንደማይችልና ተጽእኖ የሌለው እንደሆነ እናስተውላለን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 198
መልዕክት (message) 198
ላለመሆን እንጸልይ.............!

ውሾች ተናካሾች እና ወደ ትፋታቸው የሚመለሱ ፍጥረቶች ናቸው። እንዳይነክሱን እና ትፋታቸው እንዳያገኙን መጽሐፍ “ከውሾች ተጠበቁ” ይላል (ፊልጵ 3:2)።

ሠራተኞች(አገልጋዮች) ሆነው ነገር ግን ክፉዎች የሆኑ አሉ፤ እንደ ውሾቹ ሁሉ መጽሐፍ”ከክፉዎችም ሠራተኞች ተጠበቁ” ይላል (ፊልጵ 3:2)።

እውነተኛ መገረዝ(የልብ መገረዝ) እንዳለ ሐሰተኛ መገረዝም አለ። መጽሐፍ ከልብ መገረዝ ጋር ተያይዞ ከሐሰተኛ መገረዝ ተጠበቁ።” ይላል (ፊልጵ 3:2)

ውሾች፣ ክፉዎች ሠራተኞችና ሐሰተኛ መገረዝ በተስፋፋበት አገርም ሆነ ተቋም ለውጥ ሳይሆን ነውጥ ይነግሳል። ከዚህ ነጻ ሆኖ ለመገኘትና እኛም እንደ አንዱ ላለመሆን፥እንጸልይ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 199
መልዕክት (message) 199
የመስቀል ጠላት................!

የክርስቶስ መስቀል ታላቁ ግዳይ ነው። ሞት፣ኃጢአት፣በሽታ፣ ድህነት፣ እርግማን፣ ጭንቀት፣ ፍርሃት...ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በክርስቶስ ቤዛነት የተወገዱበት ሥፍራ ነው መስቀል።

ከመስቀል በኋላ አገር ተቀይሯል፤ “አገራችን በሰማይ ነውና” (ፊልጵ 3:20)። እንግዲህ ምድር ላይ ርስት፣ ስልጣን፣ ስም፣ ዝና፣ ታላቅነት፣ ሃብት፣ ወዘተ ለማከማቸት የሚደረግ የጽድቅ ያልሆነ የግልም ሆነ የመንጋ እንቅስቃሴ፣ሁከትና ዘመቻ ሁሉ የመስቀል ጠላትነት ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ “ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶቹ ሆነው ይመላለሳሉ፤ብዙ ጊዜ ስለ እነርሱ አልኋችሁ፥ አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላለሁ፤መጨረሻቸው ጥፋት ነው፥ሆዳቸው
አምላካቸው ነው፥ ክብራቸው በነውራቸው ነው፥ አሳባቸው ምድራዊ ነው።” ይላል (ፊልጵ 3:18-19)

“መንገዳችንን እንመርምርና እንፈትን፥ ወደ እግዚአብሔርም እንመለስ።” (ሰቆ ኤር3:40)። አይመስላችሁም?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 200
መልዕክት (message) 200
ከመሪህ የተማርከውን አድርግ!

ከመሪ መማር፣ ከመሪ መቀበል፣ ከመሪ መስማት እና ከመሪ ማየት የእውነተኛ ሕይወት ወግ ነው።ከዚህም በሻገር ከመሪ የተማርነውን፣ የተቀበልነውን፣ የሰማነውንና ያየነውን ማድረግ አምላክ ከእኛ ጋር እንዲሆን እና እንዲሠራ መርኹ ነው።

ጳውሎስም ሲናገር “ከእኔ የተማራችሁትንና የተቀበላችሁትን የሰማችሁትንም ያያችሁትንም እነዚህን አድርጉ፤ የሰላምም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል።” ይላል (ፊልጵ 4:9)።

ማንም የሚወድቀው መሪውን የጣለ ቀን ነው። ጌታ ኢየሱስ ስለ ላካቸው መልዕክተኞች(መሪዎች) ሲናገር “የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል እናንተንም የጣለ እኔን ይጥላል፤እኔንም የጣለ የላከኝን ይጥላል።” ይላል (ሉቃ 10:16)። እናስተውል!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 201
መልዕክት (message) 201
የሕይወት ጎዳና እና ኃይል

በሕይወት ጎዳና ከፍታ-ዝቅታ፣ መዋረድ-መክበር፣ መብዛት-መቀነስ፣መራብ-መጥገብ፣ወዘተ ተራውን ጠብቆ ይመጣል። መቆጣጠር(regulate)መቻል ትልቅ ብቃት ነው። ያለ ኃይል ግን የትኛውንም ሁኔታ መቆጣጠር ይቸግራል። ኃይል ከሌለ ሰው አንጻራዊ ከሆኑት ጉዳዮች በአንዱ የኃይል ሚዛን ብቻ ሊወድቅ ይችላል። አንዳንድ ሰው ዝቅታ ምን እነደሁ ሳያይ ከፍታ ብቻውን ይጥለዋል፤ ጉዳዩ የኃይል እጥረት ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ “መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ፤ በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንና መራብንም መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ”ይልና “ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ” ይላል (ፊልጵ 4:12 -13)። ሁሉ የሚቻለው በኃይል እና በኃይል ብቻ ነው።

ኃይል የሚሰጥና የኃይል ምንጭ አለ፤እርሱም ክርስቶስ ነው ፤ ኃይል ባለቤት እንዳለው መጽሐፍ “ኃይል የእግዚአብሔር ነው፥” በማለት ያረጋግጣል (መዝ 62:11)። የእግዚአብሔር ኃይል ደግሞ ለማዳን ነው። (ሮሜ 1:16) እንግዲህ ለማዳን ያልሆነ ኃይል ሁሉ ለጥፋት ነው። ኃይል ሆኖ ለጥፋት ከዋለ ደግሞ ምንጩ ክርስቶስ አይደለም።

ኃይል አጥሮን፥ አንድ ነጠላ ጉዳይ እንዳይጥለን እንጠንቀቅ!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 202
መልዕክት (message) 202
መስጠት፥ ኪዳናትን ተሻጋሪ..!

ጌታ ኢየሱስ “ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው።” ይላል (ሐዋ 20:35)። በደስታ የምናደርገው ስጦታችን ሁሉ የሰው ምስክርነት(ቲፎዞ) ሳያስፈልግ ብፅዕናችንን ማረጋገጫ ነው። የመስጠት ሕይወት “በብሉይ ኪዳን ነበረ፥ ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ቀርቷል” ብለን የምንከራከርበት አጀንዳ ሳይሆን ከዚያ ያለፈ፥ የራሱ የእግዚአብሔር ሕይወት ነው። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ሲሰጥ ነው የኖረው አሁንም በአዲስ ኪዳን እየሰጠ ነው።

መስጠት ዘርፈ ብዙ ነው። በኩራት፣አስራት፣መባ፣እናት አባት የሞተባቸውን ልጆች እና መበለቶችን መርዳት፣ ለድሃ ቸርነት ማድረግ፣ ወዘተ። ከነዚህ መካከል፥ አንዱ የመስጠት ዓይነት ልክ እንደ ፊልጲስዩስ ሰዎች፥ ጉዳዩን በደንብ በተረዱ ሰዎች እና በአገለገላቸው ሰው መካከል፥ የሚደረግ የመስጠት እና የመቀበል ስሌት ያለው ተካፍሎት ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ለፊልጵስዩስ ሰዎችሲናገር “ ... ከእናንተ ብቻ በቀር፥ ሌላ ቤተ ክርስቲያን በመስጠት እና በመቀበል ስሌት፥ ከእኔ ጋር እንዳልተካፈለች እናንተ ደግሞ ታውቃላችሁ፤ በተሰሎንቄ እንኳ ሳለሁ፥ አንድ ጊዜና ሁለት ጊዜ ያስፈለገኝን ሰዳችሁልኝ ነበር። በስሌታችሁ
የሚበዛውን ፍሬ እንጂ፥ ስጦታውን ፈላጊ አይደለሁም። ነገር ግን ሁሉ አለኝ ይበዛልኝማል፤...” ይላል (ፊልጵ 4:15-18)

መንፈሳዊ ነገር፥ በጽድቅ ያካፈሏችሁን ሰዎች ችላ አትበሉ!!! (1ቆሮ 9:11)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 203
መልዕክት (message) 203
የጐደለውን እፈጽማለሁ..........!

ተልዕኮ(ራዕይ) የተሰጠው ሰው ያስታውቃል። መከራው ራሱ ስኬቱ ነው።ሞትም ቢሆን የትንሳኤው መንደርደሪያና ለእርሱ የስኬቱ አካል ስለሆነ አይሸሽም። (ፊልጵ 2:8)

ሐዋርያው ጳውሎስ ጉዳዩን ሲያጠብቀው "አሁን በመከራዬ ስለእናንተ ደስ ይለኛል፥ስለአካሉም ማለት ስለቤተ ክርስቲያን በሥጋዬ በክርስቶስ መከራ የጐደለውን እፈጽማለሁ" ይላል። (ቆላስያስ 1:24)

ጳውሎስ "በክርስቶስ መከራ የጐደለውን እፈጽማለሁ" ካለ፥ እኛ ምን ለመፈጸም ነው እያገለገልን ያለነው? በምንስ ዓላማ ነው አሁን የምንሠራውን እየሠራን(እየፈጸምን) ያለነው?ለዝና? ለእንጀራ?ለገንዘብ?ለጥቅም? ከሆነ ያሳፍራል።እንስተካከል!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 204
መልዕክት (message) 204
የቁልምጫ አገልግሎት...

በየሥፍራው የቁልምጫ አገልግሎት በዝቷል። እግዚአብሔር እንደሚመሰክር እያመካኙ ማገልገል እና የመጐምጀት ሥራ (አገልግሎት)ተበራክቷል። ሃብት(ሕዝብና ገንዘብ) የማከማቻ ስትራቴጂ ይሆን?

ቁልምጫ የሌላባቸው፣ እግዚአብሔርም እንደሚመሰክር ማመካኘትን ስልት ያላደረጉ እና በመጐምጀት የማያገለግሉ ጉባኤዎች የህዝብ ቁጥር ልከኛ ነው። ግርግር የለም።

ጳውሎስ “እንደምታውቁ፥ እያቈላመጥን ከቶ አልተናገርንም፥ እግዚአብሔርም እንደሚመሰክር እያመካኘን በመጐምጀት አልሠራንም”ሲል በጉዳዩ ዙሪያ የወሰደውን አስተማሪ የሆነ ርምጃ ይገልጻል።(1ተሰ 2:5)

ከላይ በተዘረዘሩት ስልቶች የተሰበሰበ ሃብት(ሕዝብ/ገንዘብ) እያንዳንዱን ሠርተን ስላላመጣነው፥ የእኛ አይደለም!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 205
መልዕክት (message) 205
እንዳንናገር መከልከል.........!

እኛ አገር ሃይማኖተኛ መሆንና ባዕድ አምልኮተኛ ሆኖ መኖር መሳ ለመሳ ረጅም ዘመን ያስቆጠረ፣ ብዙ ማሕበረሰብ ያቀፈ ባህል ነው።ሰው"ሃይማኖትም ሆነ ባዕድ አምልኮ አይሻኝም" ብሎ በክርስቶስ ኢየሱስ ከዚያ ያፈነገጠ ማኅበርተኛ ሲሆን በገዛ አገሩ ሰዎች መከራን ይቀበላል። ቀድሞ በተጻፈ ታሪክ እንደሚታወሰው ጌታ ኢየሱስን የገደሉ፣ ነቢያትንም ያሳደዱ፥ ሰዎችን ሁሉ የተቃወሙ፥ በዚህ ምክንያት እግዚአብሔርንም ደስ ያላሰኙ እንደነበሩ እንብበናል። (1ተሰ 2፡15)

በሐዋርያው ጳውሎስ ዘመንም እንዲሁ ዓይነት ታሪክ ተፈጥሮ "ወንድሞች ሆይ፥ በይሁዳ የሚኖሩትን፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉትን የእግዚአብሔርን ማኅበሮች የምትመስሉ ሆናችኋልና
፤እነርሱ ከአይሁድ መከራ እንደ ተቀበሉ፥ እናንተ ደግሞ ያንን መከራ ከአገራችሁ ሰዎች ተቀብላችኋልና።...ሁልጊዜ ኃጢአ ታቸውን ይፈጽሙ ዘንድ አሕዛብ እንዲድኑ እንዳንናገራቸው ይከለክሉናል፤ነገር ግን ቍጣው ወደ እነርሱ ፈጽሞ ደርሶአል ይላል። (1ተሰ 2፡14-16)

ኃጢአት እንዳይሆንባችሁ እና ቁጣው እንዳይደርስባችሁ፥ ወንጌል እንዳንናገር የምትከለክሉን ሁሉ ለዘብ በሉ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 206
መልዕክት (message) 206
ከእርሱ ጋር ከሞትን... (2ጢሞ 2:11)

የምድር ኑሮ ዘላለማዊ አይደለም፥ “ሰባ ዓመት፥ ቢበረታም ሰማንያ ዓመት ነው፤” (መዝ 90:10)። ጉዳዩ ከማን (ከምን) ጋር ነው የኖርነው የሚል ነው። በትንሳኤ ቀን ያንቀላፉ ሁሉ ይነሳሉ። ለዘላለም ቅጣት ወይም ለዘላለም ሕይወት (ማቴ 25:46)።

መጽሐፍ ሲናገር “ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፥ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና።” ይላል። (1ተሰ 4:14)

ቃሉ ከላይ “በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና” እንደሚል፥ ሳናውቀው ከሌላ ማንነት ወይም ከሌላ ነገር ጋር ተጣብቀን እንዳናንቀላፋ፥ እናም መጨረሻችን የዘላለም ቅጣት እንዳይሆን፥በእርሱ እናንቀላፋ ዘንድ እርሱን ተቀብለን፥ ከእርሱ ጋር እንኑር!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 207
መልዕክት (message) 207
የሚደክሙ በጌታም የሚገዙአችሁ

በአንድ አገር፣ማሕበረሰብ ወይም በአንድ ተቋም ውስጥ ስለ ተሰጣቸው ኃላፊነት የሚደክሙ፣ በጌታ ገዥዎች የሆኑ እና የሚገስጹ እውቅና ይገባቸዋል። ስለ ሥራቸውም በፍቅር እና ከመጠን ባለፈ እናከብራቸው ዘንድ መጽሐፍ ያዝዛል። እንደ እድል ሆኖ እኛ አገር ረጅም ዓመታት የኖርነው የተገላቢጦሽ ነው። የዕውቅና ባለቤቶች የሚደክሙ ሳይሆኑ የሚያደክሙ ፣ በጌታ የተሾሙ ገዥዎች ሳይሆኑ በራሳቸው ወደ ገዥነት የመጡ፣ የሚገስጹ ሳይሆኑ መረን የሚለቀቁ ስናይ ኖረናል።

መጽሐፍ ግን ዛሬም ይላል "ወንድሞች ሆይ፥ በመካከላችሁ የሚደክሙትን በጌታም የሚገዙአችሁን የሚገሥጹአችሁንም ታውቁ ዘንድ፥ ስለ ሥራቸውም በፍቅር ከመጠን ይልቅ ታከብሩአቸው ዘንድ እንለምናችኋለን።" (1ተሰ 5:12-13)

እንኳን ልንደክም፥ በትውልዱ ውስጥ ምንም የሠራነው ሥራ የለም ነገር ግን የሚደክሙትን የምንንቅ እና የምንተች አለን። ገና እኛ ስላልበቃን፣ ጌታ ራሱ በቃችሁ ይበለን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 208
መልዕክት (message) 208
መልካም ምክር.................!

“ድልም ብዙ ምክር ባለበት ዘንድ ነው።” (ምሳሌ 24:6)

የድል ባለቤት ለመሆን፥ መንገዱ መልካም ምክር መስማት እና ምክሩን መፈጸም ነው። የመጽሐፍ ምክር እንካችሁ:-

“ወንድሞች ሆይ፥ እንመክራችኋለን፤ ያለ ሥርዓት የሚሄዱትን ገሥጹአቸው፤ድፍረት የሌላቸውን አጽኑአቸው፤ለደካሞች ትጉ ላቸው፤ ሰውን ሁሉ ታገሡ። ማንም ለሌላው በክፉ ፈንታ ክፉ እንዳይመልስ ተጠንቀቁ፥ ነገር ግን፥ ሁልጊዜ እርስ በርሳችሁ ለሁሉም መልካሙን ለማድረግ ትጉ።ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደእናንተ ነው፤መንፈስን አታጥፉ ፤ትንቢትን አትናቁ፤ ሁሉን ፈትኑ መልካሙን ያዙ፤ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ። (1ተሰ 5:14-22)

በክፉዎች ምክር የሄደ፥ሊደርስ እሚችለው፥እነሱ እደረሱበት ሥፍራ ነው (ማቴ 15:14)። “ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ።” (መዝ 1:1)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 209
መልዕክት (message) 209
የ"ሰው መንፈስ ነው" ትርፉ

እግዚአብሔር መቀደሳችን ፈቃዱ የሆነና የሚቀድስ አምላክ ነው። ቅድስና ደግሞ በሁለንተና ነው። የደረስንበት የስልጣኔ ዘመን ሆነና ሰው "መንፈስ ነኝ" ብሎ ድንኳን በሆነው የሥጋ ሰውነቱ፥ የወደደውን ሁሉ ያደርግ ዘንድ፥ ራሱን በራሱ ለሥጋ ሥራ መረን ለቀቀ።

ሐዋርያው ጳውሎስ "የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም፣ ነፍሳችሁም፣ ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ" ይላል። (1ተሰ 5:23)

የ"ሰው መንፈስ ነው" ትምህርት ትንተና (analysis) ጉዳዩን ያልሰማን አዲስ ሰው የማስገረምና የተከታይ የሕዝብ ቁጥር የማበራከት እድል ይፈጥር ይሆናል እንጂ በጽድቅ የታነጸ እና ራዕይ የሰነቀ ማሕበረሰብን፥ ከመፍጠር አንጻር፥ ያበረከተው አስተዋጽኦ፥ የቱ ጋ እንደሆነ፥ ቢፈለግ፥ ማግኘት ይቸግራል። ትምህርቱ መሰጠቱ ሳይሆን ጉዳዩ፥ ምን ያህል ጠቅሞናል/ ጎድቶናል? የሚለው ነው መታየት ያለበት።

"የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናችሁ" ሲባል በሁለንተናችን (መንፈሳችን፣ነፍሳችን፣ሥጋችን) ይመስለኛል። (1ቆሮ 3:16)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 210
መልዕክት (message) 210
ዛሬውኑ እንለይ..................!

መሪዎች የአንድ አገር፣ ማሕበረሰብ ወይም ተቋም ወግ እና ባህል እንዲሁም ሥርዓተ-ማህበር ቀያሽና ሰጪዎች ናቸው። ከዚያም ባለፈ አዛዦች ናቸው። ከወንድሞች መካከል ይሄ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ የመሪ ብቃት፣ ስልጣን እና አዛዥነት የማይመቸው እዚህና እዚያ ብቅ ማለቱ አይቀርም። ግጭቱ ለጊዜው ከሚያየው መሪ ጋር ቢመስልም እውነተኛው ጠብ ግን ከላኪው (ከሿሚው) ጋር ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ፥ ምክሩን ይለግሳል "ወንድሞች ሆይ፥ ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን።" በማለት። (2 ተሰ 3:6)

ወገኖቼ መሪ እንደዘረጋው ወግ ሳይሆን ያለሥርዓት ከሚሄድ ማናቸውም ወንድም (ወገን) ተብዬ ባንዳ ዛሬውኑ መለየት ይሻላችኋል። አባባሌ ይከብድ ይሆን? ጳውሎስ ያለውን ነው የደገምኩት!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 211
መልዕክት (message) 211
ከጉንዳን ያነሱ ሰዎች..........!

የሰው ልጅ፥ እንኳን በምድር በሚኖርበት ዘመን አይደለም፥ በዔደን ገነት በኖረበት ዘመን ሁሉ እንዲሠራ (እንዲያለማ) ታዝዟል (ዘፍ 2:15፣ 3:23)። ሰው ሥራ አይሠራም ማለት፥ ያለ ሥርዓት እየኖረ እና በሰው ነገር እየገባ ነው ማለት ነው።

መጽሐፍ "ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበር። ሥራ ከቶ ሳይሠሩ፥ በሰው ነገር እየገቡ፥ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ፥ ስለ አንዳንዶች ሰምተናልና። እንደ እነዚህ ያሉትንም፥ በጸጥታ እየሠሩ፥ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን፤ እንመክራቸውማ ለን።" ይላል። (2 ተሰ 3:10-12)

በነገራችን ላይ፥ ሥራ የማይሠሩ እና ታካች የሆኑ ሰዎች ሁሉ የሥራ ልምድ እንዲያገኙ "ሂዱ" የተባሉት ጉንዳን ጋ ነው። (ምሳሌ 6:6)። ከጉንዳን አንሶ መኖር አይከብድም???

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 212
መልዕክት (message) 212
ከሙሴ እና ከኢየሱስ

ሕግ፥ በሙሴ በኩል፥ ለሰው ልጆች የተሰጠ፥ የብሉይ ኪዳን መተዳደሪያ ደንብ ነበር(ዮሐ1:16)።ወቅቱ የሰው ልጆች ሁሉ ኃጢአት እና በደል ያየለበት ስለ ነበር፥ያንን ለማስታገስ ሲባል ሕግ በመካከል ገባ።

ጳውሎስ"ሰው እንደሚገባ ቢሰራበት ሕግ መልካም እንደ ሆነ እናውቃለን" ይልና "ሰው"ብሎ የሚመለከተውን የሰው ዓይነት ሲዘረዝር "በደለኞች፣ የማይታዘዙ፣ ዓመጸኞች፣ ኃጢአተኞች፣ ቅድስና የሌላቸው፣እርኵሳን፣አባትና እናትን የሚገድሉ፣ ነፍሰ ገዳዮች፤ሴሰኞች፣ከወንድ ጋር የሚተኙ፥በሰዎች የሚነግዱ፣ ውሸተኞች፣ በውሸት የሚምሉ፥የብሩክ እግዚአብሔርን ክብር እንደሚገልጥ ለእኔ አደራ እንደ ተሰጠኝ ወንጌል የሆነ..ደኅና ትምህርት የሚቃወሙ ለሌላ ነገር ሁሉ ሕግ እንደ ተሰራ"አለ (1ጢሞ1:8-11)

ከሰው ልጆች መካከል ሕግ የማይመለከተው አለን?ጳውሎስ ለዚህም ጉዳይ መልስ ሲሰጥ "ለጻድቅ እንዳልተሰራ" ይላል (1ጢሞ1:11)። ማን ነው ጻድቅ? በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የመጣውን ጸጋና እውነት አምኖ የተቀበለ። (ዮሐ1:17)

እንግዲህ መምረጥ ነው፤ እንደ ፈሪሳውያን ሙሴ ያመጣውን ሕግ ተቀብሎ የሙሴ ተከታይ(ደቀ መዝሙር)መሆን አልያም ኢየሱስ ያመጣውን ጸጋና እውነት ተቀብሎ የኢየሱስ ተከታይ (ደቀ መዝሙር) መሆን፤የእኔ ምርጫ ኢየሱስ ነው፤የእናንተስ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 213
መልዕክት (message) 213
በማን (በምን) ልሹም?

አሁን ላለንበት ሥራ (አገልግሎት) ማን ነው የሾመን? እንዴት ወደ ሥፍራውስ (position) መጣን? ኃይልስ ከየት አገኘን? በሰው ነው? በሰው ከሆነ፥ ኃይሉ የሰው ነው፥ ጊዜያዊ ነው። በትጥቅ ትግል ነው? በትጥቅ ትግል ከሆነ፥ ኃይሉ የመሣሪያ ነው፥ ጊዜያዊ ነው። በገንዘብ ይሆን? በገንዘብ ከሆነ፥ ኃይሉ ነዋይ ነው፥ ጊዜያዊ ነው። ጊዜያዊ፣ ጊዜያዊ፣ ጊዜያዊ...

ሐዋርያው ጳውሎስ"ለአገልግሎቱ ሾሞኝ ታማኝ አድርጎ ስለ ቈጠረኝ፥ኃይል የሰጠኝን ክርስቶስ ኢየሱስን...አመሰግናለሁ" ይላል(1ጢሞ1:12)ጳውሎስ የተሾመው በክርስቶስ ኢየሱስ ነው።ሹመቱ በክርስቶስ ኢየሱስ ከሆነ፥ኃይሉ የመለኮት ነው፥ ዘላለማዊ ነው።

እኔ ጊዜያዊ ነገር አይመቸኝም፡እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ሁሉ የእኔም ምርጫ በክርስቶስ ኢየሱስ መታመን እና በዘላለማዊ ኃይል መሾም ነው። ስለዚህ ኢየሱስን ተቀብያለሁ፤እናንተስ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 214
መልዕክት (message) 214
እርሱ የመጣበት ዓላማ.......!

ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ አያሌ ሰዎች ወደ ዓለም መጥተዋል ፤ አለማወቅ ካልገጠመ በቀር ሁሉ በሆነ ዓላማ (purpose) ወደዚህ ዓለም እንደመጣ (እንደሚመጣ) ግልጽ ነው። ትልቁ ጉዳይ ግን፥ ማንም የመጣበትን ዓላማ (purpose) አውቆ መገኘት ነው።

የኢየሱስ የመጣበት ዓላማ ይለያል፥ "ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው፤" ይላል መጽሐፍ። (1 ጢሞ 1:15)

አዳኙ ወደ ዓለማችን መጥቷል፤መድሐኒቱ ደርሷል።እንግዲህ ይህን ወደ ዓለማችን የመጣ መድኀኒት ተቀበሉና እርፍ በሉ። ሃይማኖት፣ባህል፣ፍልስፍና፣ወዘተ፥አያድክማችሁ። ጳውሎስ "የኢየሱስን ማኅተም በሥጋዬ ተሸክሜአለሁና ከእንግዲህ ወዲህ አንድ ስንኳ አያድክመኝ።" እንደሚል። (ገላ 6:17)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 215
መልዕክት (message) 215
ሄሜኔዎስና እስክንድሮስ

‘የእምነት እንቅስቃሴ’ የተባለው ጉዳይ የተጧጧፈበት ዘመን ላይ ነን። በጎ ሕሊና ግን የለም። በእምነት እያገለገሉ፥ መልሰ ያገለገሉትን ሕዝብ፥ በልዩ ልዩ መንገድ መጉዳት፥ በጎ ሕሊና የማጣት ምልክት ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ “እምነትና በጎ ሕሊና ይኑርህ፥ አንዳንዶች ሕሊናን ጥለው፥ መርከብ አለ መሪ እንደሚጠፋ፥ በእምነት ነገር ጠፍተዋልና፤ ከእነዚያም፥ … ሄሜኔዎስና እስክንድሮስ ናቸው።” ይላል (1ጢሞ1:19-20)

ስማቸው የተጠቀሰውን ሰዎች ያጠቃ መንፈስ በእኛም ዘመን ተንሰራፍቶ ሥራውን እየሠራ ነው፤የእምነት አገልግሎት ሰጥቶ ዘረፋ፣ ተጠቃሚ መሆን፣ ጾታዊ ጥቃት ማድረስ፣ ታዋቂነትን ማትረፍ(ዝና)፣ፈላጭ ቆራጭ መሆን፣ወዘተ እየተለመደ ነው። እንዲህ ያለ ልምምድ የሚመነጨው ጳውሎስ እንዳለው በጎ ሕሊና ከማጣት ነው።የዘመናችን ሄሜኔዎስና እስክንድሮሶች እባካችሁ ወደ ቀድሞ ቅንነታችሁ (በጎ ሕሊናችሁ) ተመለሱ!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 216
መልዕክት (message) 216
ጸጥና ዝግ ብለን ለመኖር.....!

በጸጥታ መኖር አላማራችሁም? ፤ በተረጋጋ መንፈስ በዝግታ መኖር አልናፈቃችሁም? በጭምትነት መውጣትና መግባት አልራባችሁም? እንደ እግዚአብሔር ዓይነት (እግዚአብሔርን መምሰል) ሕይወት አልተጠማችሁም? ማግኘት ይቻላል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ይመክራል "እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ።" (1 ጢሞ 2:1-2)

ከምንም ነገር በፊት፥ ጊዜ ወስዶ ልመናና ጸሎት፣ ምልጃም፣ ምስጋናም፥ ስለ አገራችን ሰዎች ሁሉ፣ ስለ ነገሥታትና፥ ስለ መኳንንትም ሁሉ ማድረግ ተገቢ ነው።ሰፊውን ጊዜ ለልመና፣ ለጸሎት፣ ለምልጃና ለምስጋና ካደረግነው፥ ጸጥና ዝግ ብለን እንኖራለን። ከዚህ ውጪ ሌላ አማራጭ የለም!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 217
መልዕክት (message) 217
ፍጡራንን አልዘክርም.........!

እንደ ሰው፥ ሰው ነኝ፤እግዚአብሔር ደግሞ አባቴ ነው።በእኔና በእግዚአብሔር መካከል ማን መግባት ይችላል ብዬ ሳስብ፥ ሁለታችንንም ሆኖ የተገኘ፥ ተገኘ። እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ (ወልድ እግዚአብሔር) ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ሲያረጋግጥ"አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው" ይላል። (1 ጢሞ 2:5)

እኔን እና ራሱ እግዚአብሔርን በትክክል የሆነ፥ እናም የወከለ ተገኝቷል።እንግዲህ፥መካከለኛ መሆን የማይችሉ እንደ ሰው እና መላዕክት ያሉ ፍጡራንን፥ 'ቅዱሳን/ጻድቃን' በሚል ሽፋን እንድዘክር ማንም አያድክመኝ። ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ ነው (ፊልጵ 1:21)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 218
መልዕክት (message) 218
ወንዶች..........................!

የተፈቀደ ተብሎ በንጽጽር የተከለከለ አለ። ወንዶች የተቀደሱ እጆቻቸውን አንስተው እንዲጸልዩ ተፈቅዷል። በአንጻሩ ደግሞ ክፉ አሳብ እና ቁጣ እንዳይፈጽሙ ተደንግጓል።

ጳውሎስ ሲናገር"እንግዲህ ወንዶች በስፍራ ሁሉ አለ ቍጣና አለ ክፉ አሳብ የተቀደሱትን እጆች እያነሱ እንዲጸልዩ እፈቅዳለሁ።" ይላል (1ጢሞ 2:8)

እንግዲህ ወንዶች ስለ ቃሉ ስትሉ ቁጣ እና ክፉ አሳብ ተወት አድርጋችሁ፥ በቀሪ የሕይወት ዘመናችሁ፥ የተቀደሱ የተባሉ እጆቻችሁን በማንሳት እንድትጸልዩ አደራ፣ አደራ፣ አደራ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!



facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 219
መልዕክት (message) 219
ሴቶች............................!

ሴቶች ደግሞ ራሳቸውን ከመሸለም ጋር ተያይዞ እንዲያደርጉ እና እንዳያደርጉ፥ የተላለፈ ምክር አለ። እጅግ ጠቃሚ ነው።

የሚገባ ልብስ፣እፍረት፣ ራስን መግዛት እና መልካም ማድረግ የተሰኙት ጉዳዮች የጥራት መለኪያ ሆነዋል።በአንጻሩ ደግሞ ባህልን ወይም ደግሞ ኢኮኖሚውን ተንተርሶ ሊሆን ይችላል ራሳቸውን እሚፈትን፥ በማህበረሰቡ ዘንድ ጥያቄ እሚያስነሳ ጉዳይ ውስጥ እንዳይገቡ ከወዲሁ ሲመክር፦

"ሴቶች በሚገባ ልብስ ከእፍረትና ራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸልሙ፤ እግዚአብሔርን እንፈራለን ለሚሉት ሴቶች እንደሚገባ፥ መልካም በማድረግ እንጂ፥ በሽሩባ እና በወርቅ ወይም በዕንቍ ወይም ዋጋው እጅግ በከበረ ልብስ አይሸለሙ" ይላል (1 ጢሞ 2:9-10)።

የሚሰማ፥ ጆሮ ያለው ይስማ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 220
መልዕክት (message) 220
እያሉ የሌሉ.......................!

በእኛ ዘመን በጣም ቀላል ከሚባሉ ተግባራት መካከል አንዱ “ቤተ ክርስቲያን መክፈት ነው” ፡ ተብሎ እስከሚታመን ድረስ ሩጫው ያለቅጥ ተጧጡፎ ሰንብቷል።ጉዳዩ ያን ያህል ቀላል የሆነበትን ምክንያት ሳጤን የገባኝ ነገር፥ አብዛኞቹ በጉዳዩ ላይ የተሠማሩት፥የራሳቸው ቤት የፈረሠና የሚያስተዳድሩት ቤት የሌላቸው በመሆኑ፥ መንገዳቸው ከቃሉ በተቃራኒ ነው።

መጽሐፍ የዚህን ሃሳብ እውነታ ሲያረጋግጥ “ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፥የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲ ያን እንዴት ይጠብቃታል?” ይላል። (1 ጢሞ 3:5)

ያለንባቸው ቤተ ክርስቲያናት፥ ማን እንደከፈታቸው እና በማን እንደሚመሩ መፈተሽ አለባቸው ባይ ነኝ።የራሱን ቤት (ትዳር) በበተነ፣ ትዳሩን መምራት በተሳነው እና ቤተሰቡን በኃይል በሚገዛ፣ ወዘተ ችግሮች ውስጥ ያለ ሰው ቤተ ክርስትያን ለመምራት ጥሪ አለው ከማለት፥ እያለ -የለም ቢባል ይሻላል።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 221
መልዕክት (message) 221
ከማዕድ በፊት፥ ጸሎት........!

ምግብ ከሠው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶች አንዱ ነው፤ሚበላ ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ቃል የተከለከለ ምንም የለም። ምንም የሚበላ ነገር ይሁን በቅድሚያ በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት ከተቀደሰ ሸጋ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ “እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና፥ ከምስጋናም ጋር ቢቀበሉት የሚጣል ምንም የለም፤ በእግዚአብሔር ቃል እና በጸሎት የተቀደሰ ነውና።” በማለት ማረጋገጫ ይሰጣል። (1 ጢሞ 4:4-5)

ወንጌል ይመስል፥ ጾም በገባ ቁጥር፥”ይሄ ይበላል፤ያ ደግሞ አይበላም”እያላችሁ የጾም የምግብ ሜኑ እምትሰብኩ ሰዎች እባካችሁ አመስግነን እንብላበት!!!

እናንተም ተመጋቢዎች፥ እባካችሁ እንደጥንቱ ከማዕድ በፊት ጸሎት ማድረግን አትርሱ። ምግቡ የትም አይሄድባችሁም!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 222
መልዕክት (message) 222
ማን ነው፥ ምሳሌያችን?

አማኝ የተባለው ማህበረሰብ፥ የሆነ አገልግሎት ፍለጋ ከቦታ ቦታ ሲዘዋወር ከሰነበተ ጥቂት አመታት ተቆጥረዋል። አሁን አሁን ሩጫው በተወሰነ ደረጃ ጋብ ያለ ይመስላል፤ከነአካቴው መሯሯጥ የሚቆምበት ጊዜ ቅርብ ነው። ጌታ ኢየሱስ ሲናገር "የማይገለጥ የተከደነ፥የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለም ።" ይላል (ሉቃ 12:2)። እየቆየን ስንሄድ ምሳሌ የሆኑ ሰዎች (አገልጋዮች) መፈለጋችን አይቀርም።ምሳሌነት በቃል፣በኑሮ፣
በፍቅር በእምነት እና በንጽሕና ነው።

መጽሐፍም "በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን" ይላል። (1 ጢሞ 4:11-12)

"በቃል" ሲል፥ የሰበከውን ቃል ራሱ የኖረ ማለት ነው። "የኖረ" ሲል፥የሰበከውን ቃል ሆኖ የተገኘ ማለት ነው።"በፍቅር"ሲል፥ ልዩነት ላይ ሳይሆን አንድነት ላይ የሚሠራ ማለት ነው። "በእ
ምነት"ሲል፥የሚታይ ነገርን ማዕከል የማያደርግ ማለት ነው። "በንጽህና" ሲል፥ በገንዘብና በጾታዊ ጉዳይ ስሙ የማይነሳ ማለት ነው።

እንግዲህ ማን ነው ምሳሌያችን? እንዲህ ዓይነት መሪ ሲኖር መቼም አይለቀቅም። ዛሬ የሚያስፈልገውና መቅደም ያለበት ምሳሌ የሆነ መሪ ነው።መጠለያው ቀስ ብሎ ይደርሳል።የወ
ቅቱ የመቀስቀሻ ሆያ ሆዬም፥ከዚህ በኋላ ብዙም የሚጨፈር አይመስለኝም።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 223
መልዕክት (message) 223
ወላጅ አልባ አገልግሎቶች.....!

ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲናገር “እስክመጣ ድረስ ለማንበብና ለመምከር ለማስተማርም ተጠንቀቅ። በትንቢት ከሽማግሌዎች እጅ መጫን ጋር የተሰጠህን፥ በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል። ማደግህ፥ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ ይህን አስብ፥ ይህንም አዘውትር። ለራስህ እና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፥ በእነዚህም ጽና፤ይህን ብታደርግ፥ራስህንም የሚ ሰሙህንም ታድናለህና።” ይለዋል። (1 ጢሞ4:13-16)

ጢሞቴዎስ ጳውሎስን የመሠለ የሚመክር፣የሚያስጠነቅቅ እና የሚያሳስብ መንፈሳዊ አባት ስላለው፥ አገልግሎቱ ምን ያህል ጠንካራ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

ጌታ ሆይ እባክህ ባለንበት ዓለም ላይ የተከፈቱ ወላጅ አልባ አገልግሎቶችን፥ሃይ ባይ ወላጅ(አባት)ያገኙ ዘንድ፥አንድ ጊዜ በምህረትህ አስባቸው! ............አሜን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 224
መልዕክት (message) 224
የአቅም ማነስ ምልክት........!

ከሰው አያያዝ ጋር ተያይዞ፥ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ሲመክር “ሽማግሌ የሆነውን አትገሥጸው፥ እርሱን ግን እንደ አባት፥ ጎበዞችን እንደ ወንድሞች፥ የሽመገሉትን ሴቶች እንደ እናቶች፥ቆነጃጅቱን እንደ እኅቶች በፍጹም ንጽሕና ለምናቸው፤ በእውነት ባልቴቶች የሆኑትን ባልቴቶች አክብር” ይለዋል (1 ጢሞ 5:1-3)።

አገልጋይ፥ የሚያገለግላቸውን (ከስሩ ያሉትን)፥ ከልጅ እስከ ሽመገሉ ሰዎች ድረስ፥ በጽድቅ በሆነና ከላይ በተዘረዘረው መንገድ ሊያስተዳድር ግድ አለበት። እግዚአብሔር ምድር ላይ እድል ፈንታው ሕዝቡ ነው። (ዘዳ 32:9)

ማንም ሁኑ፥አገልጋይ የሆናችሁ ሁሉ፥ለእግዚአብሔር ሕዝብ ክብር ይኑራችሁ። የእግዚአብሔርን ሕዝብ በልዩ ልዩ መንገድ ማናናቅና በሕዝቡ ላይ በልዩ ልዩ መንገድ መሰልጠን፥ችሎታ ሳይሆን የአቅም ማነስ ምልክት ነው። ንሰሐ እንገግባ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 225
መልዕክት (message) 225
ቅምጥል ባልቴቶች.............!

ባልቴት የሆነ፣ሴትም ሆነ ወንድ ቢሆኑ በእግዚአብሔር ተስፋ እንዲያደርጉ፥ ሌትና ቀን የልመናና የጸሎት ሰዎች እንዲሆኑ መጽሐፍ ሲመክር "ባልቴት የምትሆን በእግዚአብሔር ተስፋ ታደርጋለች፥ ሌትና ቀንም በልመና በጸሎትም ጸንታ ትኖራለች፤ ቅምጥሊቱ ግን በሕይወትዋ ሳለች የሞተች ናት። ያለ ነቀፋ እንዲሆኑ ይህን ደግሞ እዘዝ።" ይላል። (1ኛ ጢሞ 5፥5-7)

ምናልባት ቤተክርስቲያን በሌላ ጉዳይ ተይዛ(busy) ተቋሙ የቅምጥሎች መናኸሪያ እንዳይሆን፥ ትዕዛዙ ይከበር!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 226
መልዕክት (message) 226
ስም አልወጣላቸውም........!

መጽሐፍ “ባልቴት...የአንድ ባል ሚስት የነበረች እንድትሆን ያስፈልጋል። ልጆችን በማሳደግ፥ እንግዶችንም በመቀበል፥ የቅዱሳንንም እግሮች በማጠብ፥ የተጨነቁትንም በመርዳት በጎን ሥራ ሁሉ በመከተል፥ይህን መልካም ሥራ በማድረግ የተመሰከረላት ልትሆን ይገባል።” ይላል (1 ጢሞ 5:9-10)፤ ይህ እንግዲህ ለሴት ባልቴት ተብሎ ቢነገርም ወንዶቹንም ያካተተ እንደሆነ ልብ ይሏል።

ቤተ ክርስቲያን በውስጧ የያዘቻቸው ባልቴቶች እንደተጻፈው መሠማራታቸውን ማረጋገጥ አለባት። አለዚያ የቅምጥሎች መናኸሪያ ትሆናለች።

መልዕክቱ፥ የተመሠከረላቸውን ባልቴቶች እንጂ፥ ቤት ለቤት እሚዞሩ ሥራ ፈቶችን፥የማይገባውን እሚናገሩ ለፍላፊዎችንና በነገር ገቢዎችን እልፍ ሲልም ፈትተው የተቀመጡትንም ሆነ ሰው እንደ ልብስ የሚቀያይሩትን አይመለከትም።እነርሱ ስም አልወጣላቸውም።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 227
መልዕክት (message) 227
“ዝም አይነቅዝም” ባይ መሪዎች

መጽሐፍ ሲናገር “ ... ኃጢአትም ስንፍና፥ ስንፍናም እብደት እንደ ሆነች አውቅ ዘንድ እኔ በልቤ ዞርሁ”ይላል(መክ 7:25) በዚህ የመጽሐፍ ክፍል ኃጢአት እብደት እንደሆነ ተጠቁሟል ፤ ኃጢአት እብደት ከሆነ፥ በገዛ ፈቃዱ ወደ እብደት እሚሄድ ሁሉ፥ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚለው፥ሃይ ሊባል (ሊገሠጽ) ይገባዋል። “ሌሎቹ ደግሞ እንዲፈሩ፥ ኃጢአት የሚሰሩትን በሁሉ ፊት ገሥጻቸው።” (1 ጢሞ 5:20)

ዝምታው ሊሰበር ይገባል። ሰዎች ጸጋ ወይም ገንዘብ ወይም ችሎታ ወይም ስልጣን ወይም ዘመድ ወይም ደግሞ፥ ወዘተ ስላላቸው ብቻ፥ የፈለጉትን ሲያደረጉ እየታወቀ፥ ዝም ማለት ነውር ነውና፥ “ጥቅማችን ከሚቀር፥ ‘ዝም አይነቅዝም’ ” ባይ መሪዎች፥ እባካችሁ፣እባካችሁ፣እባካችሁ ዝምታው ይሰበር!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!



facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 228
መልዕክት (message) 228
ምግብና ልብስ..................!

መጽሐፍ ሲናገር"በመጠን ኑሩ"ይላል(1ጴጥ 5:8)፤ በመጠን መኖር የማጣት ወይንም የበታችነት ምልክት ሳይሆን፥ ቃሉን የመኖር የኃያልነት መንገድ ነው።

በሌላ ስፍራ "ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው፤ ወደ ዓለም፥ ምንም እንኳ አላመጣንምና፥ አንዳችንም ልንወስድ አይቻለንም፤ ምግብና ልብስ ከኖረን ግን፥ እርሱ ይበቃናል" ይላል።(1 ጢሞ 6:6-8)

ቃሉ እንዳለው፥ ወደ ዓለም ምንም ካላመጣን፥በመጨረሻም ምንም ይዘን የማንሄድ ከሆነ፥ በመጠን (በልክ) ኖሮ ማለፍ በራሱ እግዚአብሔርን የመምሰል ምስጢር ነው። "ምግብና ልብስ ከኖረን ይበቃናል" የሚለው፥ ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ ፈታኝ የሕይወት ምዕራፍ ነው። ይህን መስማት የማይፈልጉ፥ ገንዘብ ለማግኘት ብሎም ለማካበት፥ ሲሉ ራሳቸውን በብዙ ስቃይ ይወጋሉ። !(1 ጢሞ 6:10)። ጌታ ሆይ እርዳን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 229
መልዕክት (message) 229
የውሸት እውቀት ...............!

በደረስንበት ዘመን እውቀት በዝቷል።መልካም ነው። እውቀት ሆኖ ግን ለዓለም የሚመች ከንቱ መለፍለፍ ከሆነ ከክርክር የዘለለ ውጤት ስለማያመጣ፥ ውሉ ሲፈታ እውነት ሳይሆን ውሸት ነው። (1ጢሞ 6:20-21)

እወቀት አለኝ የሚል፥ እውቀቱን በምንም መልኩ ከማካፈሉ በፊት ቢያንስ ቢያንስ ውሸት አለመሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል ፤"ቢያንስ ቢያንስ" ስል፥ ለማለት የተፈለገው፥አንድ አንድ ጊዜ ለተቃውሞ ሲባል እንደ እውቀት የሚተላለፉ ግን አስተማሪ መሆን የማይችሉ የጨረባ ቃሎች(ጽሁፎች)እዚያም እዚያም ስለሚያጋጥሙ ነው።

እውቀት ሆኖ እውነት ሲሆን፥ መጽሐፍ እንደሚነግረን አርነት (ነጻነት) ያወጣል። (ዮሐ 8:32)። እውቀት ተብሎ ወደ ነጻነት የማያደርስ የማንም ዲስኩር (ልፍለፋ) ውሸት ነው። ይህንን ለማረጋገጥ ሩቅ መሄድ አያስፈልግም። በእኛ አገር የዩቲዩብ አገልግሎት ለመስጠት የእውነት እውቀት አይጠየቅም።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 230
መልዕክት (message) 230
አብሮ መሞትና መኖር.........!

መጽሐፍ ስለ ኢየሱስ ሲናገር “ከእርሱ ጋር ከሞትን፥ ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንኖራለን፤” ይላል። (2 ጢሞ 2:11) በሌላ ስፍራ ደግሞ፥ እግዚአብሔር ኢየሱስን “የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው፥ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና” ይላል። (ሐሥ 2:24)

እንግዲህ ሞትን አልፎ በሕይወት ለመኖር፥ ሞትን ድል ነስቶ በሕይወት ከሚኖረው ኢየሱስ ጋር መሆን የግድ ነው። ሞትን ያልተሻገረ አካል መከተል ትርፉ፥ የሞት ሰለባ መሆን ነው።

አሁንም ሆነ ወደ ፊት ከሞት በኋላ ያለውን ሕይወት ለመኖር፥ ዋና መንገድ የሆነውን እና የሞትና የሲኦል መክፈቻ ያለውን፥ ኢየሱስ ክርስቶስን እከተላለሁ። እናንተስ? (ራዕ 1፡18)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!



facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 231
መልዕክት (message) 231
ውርደት አይመጥነንም.......!

በሕይወት ጎዳና ንጽህና ዋጋው ከፍተኛ ነው። ራስን ማንጻት የክብር ባለቤት ያደርጋል። በተለይ በገንዘብና በጾታዊ ጉዳይ ራስን አንጽቶ መገኘት የክብር ዕቃ መሆን ነው። የክብር ዕቃ እንዳለ በአንጻሩ የውርደት እቃም አለ።

መጽሐፍ፥ ስለዚህ ጉዳይ ሲናገር “በትልቅም ቤት የእንጨትና የሸክላ ዕቃ ደግሞ አለ እንጂ የወርቅና የብር ዕቃ ብቻ አይደ ለም፥ እኵሌቶቹም ለክብር፥ እኵሌቶቹም ለውርደት ይሆናሉ፤ እንግዲህ፥ ማንም ራሱን ከእነዚህ ቢያነጻ፥ ለክብር የሚሆን፥ የተቀደሰም ለጌታውም የሚጠቅም ለበጎም ሥራ ሁሉ የተዘ
ጋጀ ዕቃ ይሆናል። (2 ጢሞ 2፡20-21)

ራሳችንን በማንጻት ለክብር የሚሆን፥ የተቀደሰም ለጌታውም የሚጠቅም ለበጎም ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ዕቃ እንሁን።ውርደት እና የውርደት ተግባር አይመጥነንምና አሁኑኑ እናቁም!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 232
መልዕክት (message) 232
አታሞካሹኝ......................!

መጽሐፍ “የጌታ ባሪያ” ብሎ “ለሰው ሁሉ ገር፣ለማስተማርም የሚበቃ፥ ለትዕግሥትም የሚጸና ሊሆን እንጂ ሊጣላ አይገባ ውም።” ይላል። (2ኛ ጢሞ 2:24)

እንግዲህ፥ “የጌታ ባሪያ” ተብሎ መጠራትና የጌታ ባሪያ ሆኖ መገኘት ለየቅል ናቸው። የእውነት የጌታ ባሪያ ሆኖ ለመገኘት ከላይ እንደተገለጸው ገርነት፣የማስተማር ብቃት እና ታጋሽነት ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው። ከጠብ ያልወጣ ማንነት ተይዞ የጌታ ባሪያ መሆን አይቻልም። ተብሎ ለመጠራትም ቢሞከር ራስን መሸንገል ነው።

ገርና ለማስተማርም ሆነ ለመታገስ ብቁ ያልሆንኩትን ጠበኛ ሰው፥ እባካችሁ “የጌታ ባሪያ” ብላችሁ አታሞካሹኝ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 233
መልዕክት (message) 233
እኛው እንፈርላቸው¡

“የአምልኮት መልክ አላቸው፥ ኃይሉን ግን ክደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ።”የተባሉት እነማን ናቸው?

“ወደ ቤቶች ሾልከው እየገቡ፥ ኃጢአታቸው የተከመረባቸውን በልዩ ልዩ ምኞት የሚወሰዱትን፥ ሁልጊዜ እየተማሩ እውነትን ወደ ማወቅ ሊደርሱ ከቶ የማይችሉትን ሞኞችን ሴቶች የሚ ማርኩ፥” (2 ጢሞ 3:6-7)

ሞኞችን ሴቶች መማረክ ክህሎቱ ካደረገ፣አእምሮ ከጎደለው ትንሽ ሰው መራቅ ብልህነት ነው። (ፊልጵ 3:19) “ክብራቸው በነውራቸው ነው፥” እንዲል መጽሐፉ፥ በየሄዱበት፥ ቅምጥ አላቸው ወይም ሴት አይለፈኞች ናቸው፤የሚያስገርመው ግን የማሕበረሰብ አገልጋዮች ናቸው። አማላይ፥ ደግሞ አገልጋይ በዚያ ላይ አስመሳይ። እነሱ መቼም አያፍሩም፥እንደፈረደብን እኛው አንገት እንድፋ፣ እኛ እንፈርላቸው¡

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 234
መልዕክት (message) 234
ከአንጥረኛ እንጠበቅ..........!

ሐዋርያው ጳውሎስ “የናስ አንጥረኛው እስክንድሮስ እጅግ ከፋብኝ፤ ጌታ እንደ ሥራው ይመልስለታል። አንተም ደግሞ ከእርሱ ተጠበቅ፥የምንናገረውን እጅግ ተቃውሞአልና”ይላል (2 ጢሞ 4፡14-15)

የእስክንድሮስ ችግር ምንድን ነው? የጳውሎስን መልዕክት መስማት አይፈልግም፤ ይቃወማል፤መቃወም ብቻ አይደለም እጅግ ክፉም ነው።

ጳውሎስ መልዕክተኛ ነው። ሥራው፥ መልዕክት ማስተላለፍ ነው። እስክንድሮስ ደግሞ የናስ አንጥረኛ ነው። የስክንድሮስ ትልቁ ችግር፥ የተሰጠውን ናስ ብቻ ሳይሆን፥ ተቃውሞን እና ክፋትን ጨምሮ ያነጥራል። ከእንዲህ ያለ እንጥረኛ ራሳችንን እንጠብቅ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 235
መልዕክት (message) 235
ሹመታችንን እናስረክብ........!

ታማኝነት፥ ሰው ለአገልግሎት የሚታጭበት እና የሚሾምበት መስፈርት ነው፣(1 ጢሞ 1:12)። የሚሾም ሰው ደግሞ ምን ዓይነት ሰው መሆን እንዳለበት ጳውሎስ ሲናገር"የማይነቀፍና የአንዲት ሚስት ባል የሚሆን፥ የሚያምኑም ልጆች ያሉት፥ ስለ መዳራትም ወይም ስለ አለመታዘዝ የማይከሰስ ማንም ቢኖር፥ ሹመው።" ይላል። ጳ(ወደ ቲቶ 1:6)

ነቀፋ ያለብን፣ በአንድ ሰው መወሰን ያልቻልን፣ የማያምኑ ልጆችን ያፈራን፣ በመዳራትና ባለመታዘዝ የምንከሰስ ግን ደግሞ ተሿሚዎች፥ ሳይመሽ ሹመታችንን እናስረክብ። ኋላ ቃሉ እንዳይፈርድብን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 236
መልዕክት (message) 236
የኢየሱስ ደም.................!

በራሱ ንጹሕ ወይም ርኩስ የሆነ ቁስ ወይም ሥፍራ የለም። በስፍራው (ቁሱ ላይ)፥ ከሚገለጠው ማንነት ወይም ደግሞ ከሚወጣው ቃል የተነሳ፥ ይነጻል ወይም ደግሞ ይረክሳል። መጽሐፍ “በሰማያት ያሉቱ ራሳቸው ... በሚበልጥ መስዋዕት ሊነጹ የግድ ነበረ።” ይላል (ዕብ 9:23)

መልዕክቱን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ “ሁሉ ለንጹሖች ንጹሕ ነው፤ ለርኵሳንና ለማያምኑ ግን ንጹሕ የሆነ ምንም የለም፤” (ቲቶ 1:15)

እንግዲህ፥ በኃጢአት ምክንያት ርኩስ ከመሆንና፥ ሁሉ ነገር ተያይዞ ከሚረክስብን፥ ንጹሕ ሆኖ ሁሉን በንጹሑ መጠቀም ይሻላል። እና ከኃጢያት ለመንጻት ምን እንጠቀም? መጽሐፍ “የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።” ይለናል(1ዮሐ1:7)።እኔ መንጻት ስለምፈልግ አሁኑኑ የኢየሱስ ክርስቶስን ደም ተቀብያለሁ። እናንተስ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!



facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 237
መልዕክት (message) 237
ክህደት በድርጊት ..............!

**ውሸት፥**
**ሲመስለኝ የቃልና የተግባር መለያየት ነው።**

እግዚአብሔር ከድርጊቱ በፊት ለሚናገረው ቃል የሚጠነቀቅ አምላክ ነው። “ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም።” (ማር 13:31)፤ “ከአፌ የሚወጣ ቃሌ ...የምሻውን ያደርጋል የላክሁትን ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም።” (ኢሳ55:11) እንዲህና እንዲያ የሚሉ ቃሎች ተመልክተዋል፤ እግዚአብሔር ለተናገረው ቃል፣ ለሰጠው ቃል ተግባራዊነትና እውነተኛነት ኃላፊነት የሚወስድ አምላክ ነው።

አሁን አሁን የቸገረን ነገር፥በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የሚናገሩ ነገር ግን የሚያጸይፉ፣ አዛዥ (የሚፈሩት ሰው) የሌለባቸው፣ እና መልካም ሥራ የሌላቸው ወይም ለበጎ ሥራም የማይበቁ በዝተዋል። ሥራቸው (ተግባራቸው) ሁሉ የውሸትና የክህደት ነው። የሚዲያው ውሸት ቁመቱ ከእውነት ስለረዘመ፥ ባይነሳ ይሻላል።

መጽሐፍም “እግዚአብሔርን እንዲያውቁ በግልጥ ይናገራሉ፥ ዳሩ ግን የሚያስጸይፉና የማይታዘዙ ለበጎ ሥራም ሁሉ የማይበቁ ስለ ሆኑ፥በሥራቸው ይክዱታል”ይላል(ቲቶ 1:16) ጌታ ሆይ እንዲህ ካሉ ሰዎች ጋር አብረው አንድቤት ለሚኖሩ ሰዎች እባክህ ራራላቸው!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 238
መልዕክት (message) 238
ጤናማ ሽማግሌ..............!

የጽድቅ ሽምግልና ቃል አለው "መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ... ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፥" (ኢዮኤል 2:28)። የሽመገለ ሁሉ ሕልም ያልማል (dream) ማለት አይደለም። ሽምግሎ፥ ልከኛ፣ጭምት፣ራሱን የሚገዛ፣ በነገር ሁሉ (በእምነትና በፍቅር በመጽናትም) ጤናማ የሆነ ለሕልም (dream) ቅርብ ነው። (ቲቶ 2:2)

ሽምግሎ ሕልም (dream) የሌለው ሰው ልኩን አያውቅም። ስለዚህ ሕይወት ይሰፋዋል፤ስለዚህም የሚያደርገውን አያውቅም። ከልማት ይልቅ ጥፋት ይቀልለዋል። ሽምግሎ፥ ሕልም (dream) የሌለው ሰው ጭምት ወይም ደግሞ ራሱን መግዛት ይቸግረዋል። ስለዚህ ሕልሙ ጥፋት ይሆናል። የያዝነው ዘመን የሽምግልናን ወግ ብዙም አያሳይም። ሽማግሌ ብለን ልከኛ ወይም ጭምት ወይም ደግሞ ራሱን የሚገዛ አልያም በእምነትና በፍቅር በመጽናትም ጤናማ የሆነ ማግኘት ትንሽ ይቸግራል።

የደረሰብን ሁሉ የደረሰብን፥ ሽማግሌዎች ስሌሉን ሳይሆን፥ ከላይ ሐዋርያው ጳውሎስ፥ ለቲቶ እንደጻፈው፥ ምክር ያላገኙ ሽማግሌዎች አገሩን ስለሞሉት ይመስለኛል። ጌታ ይርዳን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 239
መልዕክት (message) 239
አሮጊቶች ሴቶች................!

መጽሐፍ አሮጊት ሴቶችን በተመለከተ ሲመክር “ እንዲሁም አሮጊቶች ሴቶች፥ አካሄዳቸው ለቅዱስ አገልግሎት የሚገባ፥ የማያሙ፥ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይገዙ፥ በጎ የሆነውን ነገር የሚያስተምሩ ይሁኑ፤” ይላል (ቲቶ 2:3)።

“ከላይ የተጠቀሰው፥ የሚመለከተው አሮጊት ሴቶችን ነው”፥ በሚል ፈሊጥ፥ በተሰማራችሁበት አገልግሎት ሁሉ የማይገባ አካሄድ የምትሄዱ፣ሐሜት ቀለባችሁ የሆነ፣ “በአዩኝ - አላዩኝ” አኩኩሉ፥ አልኮል የምትጨልጡና በጎ የሆነውን ሳይሆን ክፉ የሆነውን ነገር የምታስተምሩና የምታስፋፉ ሴቶች፥ እባካችሁ አደብ ግዙ።

መልዕክቱ ወንዶችን መረን እየለቀቀ እንዳልሆነ ልብ ይሏል። “አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፤” (ገላ 6:7)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 240
መልዕክት (message) 240
ቆነጃጅት ሆይ....................!

በእነሱ ምክንያት የእግዚአብሔር ቃል እንዳይሰደብ፥ በማለት መጽሐፍ ስለ ቆነጃጅት “ባሎቻቸውን የሚወዱ፥ ልጆቻቸውን የሚወዱ፥ራሳቸውን የሚገዙ፥ንጹሖች፥በቤት የሚሠሩ፥በጎዎ
ች፥ ለባሎቻቸው የሚታዘዙ እንዲሆኑ”ሲል ይመክራል። (ቲቶ 2:4-5)

ያገቡትን ወይም ደግሞ የወለዱት ሰው መውደድ ክብር ነው
፤ መውደድ በዚህ ዘመን “እወድሃለሁ” እየተባለ በሚወረወር ባዶ የቁልምጫ ቃል እሚገለጽ መሸንገያ አይደለም።መጽሐፍ “ወድዶኛልና አዳነኝ” እንዲል፥ የመውደድ ልኩ ሞቶ እማዳን ድረስ ነው።(2ሳሙ 22:20)።በመውደድ ላይ ራስን መግዛት ከዚያም ንጽሕና ሲቀጥል በጎነት፥ እልፍ ሲል ደግሞ መታዘዝ ሲታከልበት ቁንጅናው ህያው ይሆናል።

ስለዚህ ቆነጃጅት፥ ቃሉን በማድረግ ቁንጅናችሁን ታረጋግጡ ዘንድ ጌታ በቃሉ ጥሪውን ያስተላልፋል። ትኩረት ለቃሉ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

Aynalem Mersie



PART 241
መልዕክት (message) 241
ዲያብሎስ እና ተቃዋሚ

መጽሐፍ "ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት።" ይላል (ኤፌ 4: 27)። "አትስጡት" ካለ በአንጻሩ ቢሰጠውና እድሉን ቢያገኝ ደግሞ የሚያደርገው ስለታወቀ ነው"ሌባው ሊሰርቅ ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤" (ዮሐ10:10)

በተመሳሳይ ለሚቃወም ሰው ሁሉ ፈንታ መስጠት አይገባም "የሚቃወም ሰው ስለ እኛ የሚናገረውን መጥፎ ነገር ሲያጣ እንዲያፍር፥ በነገር ሁሉ መልካምን በማድረግህ ምሳሌ የሚ
ሆን ራስህን አሳይ፤ በትምህርትህም ደኅንነትን፥ ጭምትነትን ፥ ጤናማና የማይነቀፍ ንግግርን ግለጥ።"የሚል ምክር አለና (ቲቶ 2:7-8)

በዲያብሎስም ሆነ በተቃዋሚ የተቸገርን ሰዎች፥ ችግሩን ለመቀነስ፣ ለማጥፋት፣ ቢቻል ደግሞ፥ ለቅድመ መከላከል ይረዳን ዘንድ፥ ከላይ የተሰጠውን ምክር፥ እንደ መድኃኒት፥ ተከታትሎ መዋጥ ቁልፉና አብይ መፍትሔ ነው።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 242
መልዕክት (message) 242
ባሪያ (አገልጋይ) .............!

ባሪያ ማለት ተጠሪነቱ ለበላይ አለቃ ወይም መሪው የሆነና፥ ፈቃዱን ለበላይ አካል የሰጠ አገልጋይ ማለት ነው፤ተጨባጭ ምሳሌያችን ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። “ከነፍሱ ድካም፥ ብርሃን ያያል ደስም ይለዋል። ጻድቅ ባሪያዬ በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፥ ኃጢአታቸውን ይሸከማል።” (ኢሳ 53:11)፣“በእግ ዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፥ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ” (ፊልጵ 2:6-7)

ጳውሎስ ለቲቶ ስለ ባሮች (አገልጋዮች) “ስለ መድኃኒታችን ስለ እግዚአብሔር የሚሆነውን ትምህርት በሁሉ ነገር ያስመ ሰግኑ ዘንድ፥ ለገዛ ጌቶቻቸው እንዲገዙ፥በሁሉም ደስ እንዲያ ሰኙ፥ ሳይቃወሙና ሳይሰርቁም፥ በጎ ታማኝነትን ሁሉ እንዲያ
ሳዩ ምከራቸው።” ይለዋል። (ቲቶ 2:9-10)

እንግዲህ በዚህ ዘመን “ባሪያ (አገልጋይ) ነኝ” የምንል ሁሉ ቃሉ እንደሚል፥ለመሪዎች የምንገዛ፣የማንቃወም፣የማንሰርቅ ፣ በጎ እና ታማኝ ልንሆን የግድ ነው። “ባሪያ (አገልጋይ) ነኝ” ብሎ መሪ(የበላይ)የሌለው፥እርሱ ባሪያ(አገልጋይ)አይደለም!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 243
መልዕክት (message) 243
ማሳሰቢያ.......................!




ገዦችና ባለ ስልጣኖች ጥንትም አሉ፣ዛሬም አሉ ወደ ፊትም በምድር ዘመን ሁሉ ይኖራሉ። ከእነርሱ ስልጣን ስር መገዛት፣ መታዘዝ፣ለበጎ ሥራ ሁሉ መዘጋጀት፣መተባበር፣ አለመሰደብ፣ አለመከራከር፣ ለሰው ሁሉ ገርና የዋህ መሆን ግን የማንም ግዴታ ነው። እኔ ሳልሆን ቃሉ ይላል፡-

“ለገዦችና ለባለ ሥልጣኖች የሚገዙና የሚታዘዙ፥ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጁ፥ ማንንም የማይሰድቡ፥የማይከራከሩ፥ገሮች፥ ለሰው ሁሉ የዋህነትን ሁሉ የሚያሳዩ እንዲሆኑ ኣሳስባቸው” (ቲቶ 3:1-2)

ይሄ ማሳሰቢያ፥ ቃሉ እሚለውን ስለ መፈጸም የቀረበ እንጂ ማንም እንደፈለገ፣ እንደወደደ ወይም እንደፈቀደ እንዲኖር የተጻፈ ማስታወቂያ አይደለም። ቃሉ ይተግበር፥ ይከበርም!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 244
መልዕክት (message) 244
ዘይት ነው.....................!

ፍጹሙ ደስታ ዘይት (ቅባት)ነው። ከዚያ ውጪ ያለ ደስታ ሁሉ ከሆነ ከድርጊት ጋር የተያያዘ ስለሆነ፥ጉዳዩ ሲቋረጥ ደስታው አብሮ ይቋረጣል። ለአብነት ያህል ጥቂት ክፍሎች እንይ፡-

"ብላ፤ በአምላክህም በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይበልህ (ዘዳ 27:7)። ያልተበላ ቀን ምን ሊኮን ነው?
"ከጉብዝናህም ሚስት ጋር ደስ አይበልህ።" (ምሳሌ 5:18፣ መክ 9:9) ሚስት ከሌለ እንዴት ሊኮን ነው?
"በመልካም ቀን ደስ ይበልህ፤" (መክ 7:14)። ክፉ ቀን ሲመጣ ምን ሊኮን ነው?
"በጉብዝናህ ደስ ይበልህ"(መክ 11:9)።እርጅና ሲመጣ ምን ሊኮን ነው?

መጽሐፍ "ጽድቅን ወደድህ ዓመፅንም ጠላህ፤ ስለዚህ እግዚ አብሔር አምላክህ ከጓደኞችህ ይልቅ በደስታ ዘይት ቀባህ" ይላል (ዕብ 1:9)። ስለዚህ ወገኖቼ ጽድቅን እምትወዱ እና ዓመፅን የምትጠሉ ከሆነ የደስታ ዘይት የእናንተ ነው!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 245
መልዕክት (message) 245
ሰልጥነናል ወይስ ደንቁረናል?

መጽሐፍ ሲናገር"ጌታ ሆይ፥አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ ሰማዮችም የእጆችህ ሥራ ናቸው" ይላል(ዕብ 1፡10)።በራሱ ከጥንት ምድርን በመሠረተ፣ ሰማዮችንም በእጆቹ በሰራ ጌታ እንደ ተወሰነው፥ መጽሐፍ እንደገና መልሶ"እነርሱም ይጠፋሉ
... ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ፥" ይላል። (ዕብ 1፡11)

ያለንበት ዘመን (21ኛው ክፍለ ዘመን) የስልጣኔ ዘመን ነው። እውን ግን ዓለም ሰልጥናለች? እውን እኛ ሰዎች ሰልጥነናል? አይመስለኝም። ባለቤት ባለው ምድርና ሰማይ፥ ያለ ኪራይ እየኖርን፥ ምድርን ለመግዛት ይሄን ያህል ጦርነት፣ ለሚጠፋ ምድር፥ እንደ ልብስ ለሚያረጅ ምድርና ሰማይ ተብሎ ክቡር የሆነውን ሰው መፍጀት፤

ምድር ለዘውም እንድትጠፋ የተወሰነባትን፥የሠራት ጌታ እያየ ጦርነት አልከፍትባትም።ይሄ ስልጣኔ ሳይሆን ድንቁርና ነው። ጌታ ሆይ ለሁላችን ምህረት ይሁን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 246
መልዕክት (message) 246
ወደ ዔደን ገነት አሳብ ....!

መጽሐፍ “ጥንቃቄ ይጠብቅሃል፥ ማስተዋልም ይጋርድሃል፥” ይላል (ምሳ 2:11)። በሌላ ስፍራ ደግሞ”ስለዚህ ከሰማነው ነገር ምናልባት እንዳንወሰድ፥ ለእርሱ አብልጠን ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል።” ይላል (ዕብ 2:1)።

ብዙ ሰው እትላንቱ ማንነቱ ላይ አይደለም፤ብዙ ሰው እትላንቱ ቅንነት ላይ አይደለም፤ እጅግ ብዙ ሰው፥ እትላንቱ የሕይወት መስመር ላይ አይደለም። ብዙ ሰው ቀድሞ ለሰማው እውነት አልተጠነቀቀም፥ ስለዚህም በሆነ አዲስ መረጃ ተወስዷል። በራስ ላይ ክህደት ሰፍኗል። ብዙ ሰው፥ የቀድሞውን የደስታ ሕይወት ተነጥቋል። አንዳንድ ሰው ያለ ይመስላል፥ ነገር ግን የለም። እንዲህ ያለ ነገር የሚፈጠረው፥ቀድሞ ለሰማው ነገር (እውነት) ካለመጠንቀቅ ነው።

እንግዲህ፥ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሰማነው ብሎም ብዙ ርቀት ለሄድንበት እውነት አብልጠን እንጠንቀቅ። አዳም መጀመሪያ የሰማው ከእግዚአብሔር ነው ቀጥሎ የሰማው ከእባብ ነው፤ ለመጀመሪያው አብልጦ አልተጠነቀቀም። ስለዚህም ከዔደን ገነት ተባረረ። እኔ ወደ ዔደን ገነት እመለሳለሁ፤ እናንተስ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 247
መልዕክት (message) 247
ሰው ስጠን..................!

መጽሐፍ ስለ ጌታ ኢየሱስ ሲናገር"እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና።" ይላል (ዕብ 2:18)። በዚህ ጎዳና ከሄዱት አንዱ የሆነው ጳውሎስ ሲናገር "መዋረድን አውቃለሁ፥ መብዛትንም አውቃለሁ፤ በእያንዳንዱ
ነገር ... ሁሉ መጥገብንና መራብንም፥ መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ።" ይላል (ፊልጵ 4:12)።

ከላይ እንደተገለጸው፥ ሁለቱንም አንጻራዊ የሆኑ የሕይወት ምዕራፎች የሄዱ አገልጋዮች ያስፈልጉናል። በእርግጥ በዚህ ዘመን የጉዳዩ ጊዜ ሲመጣ ለመፈተን፣ ለመዋረድ፣ ለመራብ፣ ለመጉደል፣ወዘተ ታስቦ የተጀመረ አገልግሎት ብዙም የለም። በየአገልግሎቱ የሚሰማው"ትወርሳለህ፣ትጥሳለህ፣ትገባለህ፣ ወዘተ" ነው። በቅርቡ የተከፈቱት ደግሞ "ወርሰሃል፣ ጥሰሃል፣ ገብተሃል" ይላሉ። መርህ ተረስቷል።

አገልግሎት፥ መንፈሳዊነቱን ለቅቆ ስነ-ልቦናዊ ከሆነ፥ የሰው ጉዳይና የሰው አጀንዳ ሆኖአል ማለት ነው። ስለዚህ ምንም ትርፍ አይኖረውም። እግዚአብሔር ሆይ ቁርጠኛና መንገዱን ሄዶ - የሚያስኬድ፣ ኑሮውን ኖሮ - የሚያስኖር ሰው ስጠን!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 248
መልዕክት (message) 248
አጉል መግለጫ.............!

ጥሪያቸው ላይ ያሉ እና ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ያሉ ሰዎች እውቅና ይገባቸዋል። ቢያንስ አንድ ነገር በእነርሱ አማካኝነት ተሠርቷል (ተዘጋጅቷል)። "እያንዳንዱ ቤት በአንድ ሰው ተዘጋጅቶአል" መጽሐፍ እንዲል (ዕብ 3:4)።

እንደገና መጽሐፍ ተመልሶ"ቤትን የሚያዘጋጀው ከቤቱ ይልቅ የሚበልጥ ክብር እንዳለው መጠን" ይላል (ዕብ 3:3)። ቤት ሰው ነው (ዕብ 3:4)።የምንኖርበትን ዓላማ በሚገባ አውቀን ሰው እንድንሆን፥ ምክንያት የሆኑ ሰዎች፥ ክብር ይገባቸዋል። መጽሐፍ ክብር ለሚገባው ክብር ስጡ ይላል። (ሮሜ13:7)

ልምምዳችን ግን ይሄን አያመለክትም። በሆነ ሰው ተጠቅሞ ከፍ ማለትና መታወቅ፥ ቀጥሎ የራስን መግለጫ መስጠት። የይሁዳ መለያ ባህሪ ይሄ ነው። አቅሙ ሲገነባ የኖረውና ቤት ሆኖ የተሠራው (የተዘጋጀው) ኢየሱስ ቤት ነው። ያዘጋጀውን ጌታ አሳልፎ ለመስጠት መግለጫ የሰጠው ራሱ ይሁዳ ነው (መዝ 41:9)። በምንም መጠን ይሁን በጠቀሙን ሰዎች ላይ አጉል መግለጫ መስጠት ይብቃ። ለሁላችን ምህረት ይሁን።

መልዕክቱን መሞገት፥ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 249
መልዕክት (message) 249
ያልተዋሐደ ነገር............!

“የሰሙት ቃል”አለ መጽሐፍ ቅዱስ “ከሰሚዎቹ ጋር በእምነት ስላልተዋሐደ አልጠቀማቸውም።” (ዕብ 4:2)

መቼም እምነት የሚመጣው፥ ከመስማት ነው። መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው (ሮሜ 10፥17)። ከመስማት በኋላ መዋሐድ የሚባል ነገር አለ።የተዋሐደ ነገር በተለይም ደግሞ መንፈሳዊ ሲሆን፥በእርግጥ ይዋሐድ እንጂ ሊለይ አይችልም

የሰማው ቃል ከእርሱ ጋር የተዋሐደ ሰው ያስታውቃል። ሌላ ሕይወት የለውም። አማራጭ እሚባል መንገድ የለውምም። አንድ ሕይወት ነው ያለው፣አንድ ዓላማ ነው ያለው፣ሁሉ ነገሩ አንድ ነው። ለዚያ አንድ ዓላማ ኖሮ ሲሞትም በዚያው አንድ ዓላማ ይሞታል። ውሕደት እንዲህ ነው።

የልተዋሐደው ሰው ሲገላበጥ ይኖራል። ዛሬ እዚህ ነው፥ ነገ ደግሞ እዚያ፤ ዛሬ ከፈተ ይባላል፥ ነገ ደግሞ ዘጋ፤ ዛሬ የሆነ መግለጫ ይሰጣል፥ነገ ደግሞ ማስተባበያውን።ጌታ ይርዳን!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 250
መልዕክት (message) 250
እረፍት፥ ዥዋ(ጧ).........!

እረፍት፥ ዥዋ(ጧ)ብሎ መተኛት የሚመስላቸው ሰዎች አያሌ ናቸው። ስለዚህም ከመሥራት መተኛት ይቀልላቸዋል። ነገር ግን መተኛት እንደ መብላት፣መጠጣት፣መውጣት፣መግባት፣ ማሰብ፣ መሥራት፣ ወዘተ አንድ የሕይወት ተግባር ነው።

እረፍት የሥራ መጠናቀቅ ምልክት ነው።መጽሐፍ"ወደ ዕረፍቱ የገባ፥እግዚአብሔር ከሥራ እንዳረፈ፥እርሱ ደግሞ ከሥራው አርፎአልና"ይላል(ዕብ 4:10)።"እግዚአብሔር ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ"(ዘፍ2፡2)፥ሲል ተኛ ማለት እንዳልሆነ ልብ ይሏል

ማረፍ የሚፈልግ ማንም ሥራውን ይሥራ፣የሚጠበቅበትንም ተግባር ይፈጽም። ማንም ሰው ይሁን፥ሥራውን ካልሠራ እና ካላጠናቀቀ፥እርግጠኛ ሁኑ፥እርሱ መቼም አያርፍም። እረፍት ላይ ያሉ ሰዎች፥ ያስታውቃሉ። የሆነ ነገር ይጀምራሉ ከዚያም ያጠናቅቃሉ። አጠናቅቀዋል ማለት አርፈዋል። እረፍት ማለት ምን እንደሆነ ስለማያውቅ፥ ወሬኛ ዝም ብሎ ይተኛ!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 251
መልዕክት (message) 251
ሆኖ መገኘት ነው...........!

መጽሐፍ ቅዱስ “እርሱም በስጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፥ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት፤ ምንም ልጅ ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፤” ይላል። (ዕብ 5፡7-8)

እንግዲህ ልጅነት የክብር ወራሽነት ብቻ ሳይሆን፥ ጊዜው የሚጠይቀውን ሆኖ መገኘት ነው። ብርቱ ጩኸት፣ እንባ፣ ጸሎት፣ ምልጃ፣ ወዘተ በስፍራውና በጊዜው ማቅረብ የልጅ ወግ ነው። “ልጅ” ተብሎ፥ እርሱ አባቱን ከፈራ፣ መታዘዝን ከተቀበለው መከራ ከተማረ፥በእኛ ዘመን ልጅነት ለምን ጽንሰ ሃሳብ ይሆናል? ለምንስ፥ የፍልስፍና እና ሕይወት የሌለበት፥ የውሸት እውቀት ይሆናል?

ስለ ልጅነት ማውራት እና ልጅ ሆኖ መገኘት እጅግ የተራራቀ ጉዳይ ነው። እኔ እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ዓይነት ልጅ መሆን ነው የምፈልገው። እናንተስ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 252
መልዕክት (message) 252
እባካችሁ ወተት እንጠጣ...!

መጽሐፍ “ከጊዜው የተነሳ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ” ብሎ”አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደ ገና ያስፈልጋ
ችኋልና፤የሚያስፈልጋችሁ ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም።” ይላል (ዕብ 5:12)።

በሕይወት መንገድ ላይ፥ አስተማሪ ወይም ተማሪ፣ ከሁለት አንዱ መሆን የግድ ነው። ከሁለቱ ውጪ ያለ ሰው ድንገት ካለ እርሱ ሰው አይደለም፥መልኩ ተቀይሯል (መዝ 49:12፣ 20)።

አስተማሪነት የሕይወት ምሳሌነት ነው።ከሥጋ ሥራ ሳይወጡ አስተማሪነት የለም። እተሰወረ፥ እልፍ ሲል ደግሞ፥ የድፍረት ኃጢአትና ልምምድ ውስጥ ተሁኖ አስተማሪነት የለም።(ሮሜ 2:21)። “እውቀት አለን፣የሆነ ነገር ተገልጦብናል፣ኑ እና እዩ፣ ወዘተ” በሚል ቅስቀሳ ለማገልገል እያጣርን ያለን፥ ነገር ግን ሕይወቱ የሌለን ሰዎች፥ እባካችሁ፥ አርፈን ወተት እንጠጣ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie



PART 253
መልዕክት (message) 253
ሳናውቀው እንዳንጠልቅ...!

መጽሐፍ "አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን" ይልና "...በኋላም የካዱትን፥ እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው፤... ብዙ ጊዜ፥ በእርስዋ ላይ የሚወርደውን ዝናብ፥ የምትጠጣ መሬት፥ ... እሾህና ኵርንችትን ግን ብታወጣ፥ የተጣለች ናት ለመረገምም ትቀርባለች፥ መጨረሻዋም መቃጠል ነው።" ይላል (ዕብ 6:4-8)።

ሰይጣን በደህናው ጊዜ፥ በእግዚአብሔር ገነት በዔድን ነበር (ሕዝ 28:13)፤አሁን ግን ተባሯል፥በዚያ የለም(ሕዝ 28:16)፤ መጽሐፍም "ያየኸው አውሬ አስቀድሞ ነበረ፥ አሁንም የለም፥ ከጥልቁም ይወጣ ዘንድ አለው" ይላል (ዮሐ 17:8)።

የሰይጣን ቁርጡ ታውቋል። ወገኖቼ፥ እኛስ? የት ነን ያለነው? ምን እየሠራንና እያራመድን ነው? ሰይጣን በክፋት እየጠለቀ በመሄዱ፥አሁን ጥልቅ ውስጥ ነው ያለው። እኛም ሳናውቀው ከቀድሞ ቅንነትና ንጽህና ርቀን ጥልቅ ስቶሽ ላይ እንዳንሆን?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**



PART 254
መልዕክት (message) 254
አብርሃም፥ ኢየሱስ፣ ብልጥግና

"እግዚአብሔር" ይላል መጽሐፍ" ለአብርሃም ተስፋ በሰጠው ጊዜ፥...እየባረክሁ እባርክሃለሁ እያበዛሁም አበዛሃለሁ ብሎ፥ ከእርሱ በሚበልጥ በማንም ሊምል ስላልቻለ፥ በራሱ ማለ።" ይላል (ዕብ 6:13-14)። በዚህ መሠረት አብርሃም "በከብት በብርና በወርቅ እጅግ በለጠገ።" (ዘፍ 13:2)። የአብርሃም ብልጥግና የት ድረስ ነው? መጽሐፍ ሲናገር "ለአብርሃም እና ለዘሩም...እርሱም ክርስቶስ።" ይላል (ገላ 3:16)። ክርስቶስ ደግሞ"እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸው መጣሁ" ይላል (ዮሐ 10:10)።

በተስፋ ቃል የአብርሃም ልጆች እንደመሆናችንና በክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም በመወለዳችን (አዲስ ፍጥረት በመሆናችን) ብልጥግና እድል ፈንታችን ነው። ስለዚህ ብልጥግናን በተመ ለከተ ትምህርትም ሆነ ስብከት ቢስፋፋ፥ "ለምን" እሚያሰኝ ጥያቄ አያስነሳም። ካስነሳም፥ ካለማወቅ ወይም፥ ድህነትን ከማፍቀር የሚመነጩ ነው፥ሊሆን የሚችለው።መንግስታችን ራሱ መንፈሳዊ ተቋም ሳይሆን፥ ከድህነት ብልጥግና ይሻላል ብሎ፥ አገሪቱን ወደ ብልጽግና ማማ ለማውጣት "ብልጽግና" የተሰኘ ፓርቲ ከመሠረተ ሩብ ዓመት አስቆጠረ።

አበው "ደግ ተመኝ፥ደግ እንድታገኝ" ይላሉ። እኔም ለትውልዴ ብልጥግናን እሰብካለሁ፣ አስተምራለሁ። እናንተስ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 255
መልዕክት (message) 255
ዓለም ሳይፈጠር ለመጀመር...

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መልከ ጼዴቅ"አባትና እናት የትውልድም ቍጥር የሉትም፥ለዘመኑም ጥንት ለህይወቱም ፍጻሜ የለውም፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል።" ይላል (ዕብ 7:1-3)

ስለዚህ መልከ ጼዴቅ፥ ያለምንም ጥርጥር፥ አልፋና ኦሜጋ (መጀመሪያና መጨረሻ) የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

የኢየሱስ ክርስቶስ ታሪክ፥ ከራሱ ጀምሮ በራሱ የሚጠናቀቅ ስለሆነ ከማርያም አይጀምርም። እርሱ ከእርሷ በፊት ነበረ። እንደውም፥ እርሱ ራሱ፥ ይግረማችሁ ብሎ፥ "እውነት እውነት እላችኋለሁ፥አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ"ይላል(ዮሐ8:58)

ታሪኬ፥ ከአብርሃም ወይም ከማርያም ወይም ደግሞ ከሆነ ሰው እንዲጀምር አልፈልግም።ያጥራል።ከኢየሱስ ይሁንልኝ። ያኔ፥ ታሪኬ ዓለም ሳይፈጠር ይጀምራል። ኢየሱስ ታሪክ ቀያሪ!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በነ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 256
መልዕክት (message) 256
ኃጢአት እንደ ጽድቅ.......!

በእኛ ዘመን፥ ኃጢአት ሆኖ፥ ግን እንደ ጽድቅ የሚከወን ነገር በዝቷል። ተበድሮ፥ እንዳልተበደረ መሆን፣ ሲለው ማረሳሳት። በጸታዊ ጉዳይ መጥመልመል።የተቃውሞ ሱስ።ቃሉን ከቃሉ ባለቤት በላይ ለማቀብ መጣጣር።ባልተሰጠ ስልጣን “እከሌ ትክክል፥እከሌ ደግሞ ስህተት” ባይ ደረጀ መዳቢነት፣ በሌለ ብቃት ራስን በሆነ ሙያ ማሰማራት፣ ወሬ ማተም። ከሠሩበት (ከአገለገሉበት) ተቋም በሠላም መለየት አለመቻል። በአካል ከተቋሙ ተወጥቶም፥በነፍስ ግን በወኪል(ጆሮ ጠቢ) እዛው መሆን መቻል፣ስድብ፣ ዛቻ፥ ያገቡትን ወይም ልጅን ማናናቅ፤ መግደል፣ ወዘተ።

መጽሐፍ”የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት መሥዋዕት አይቀ ርልንም የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ።” ይላል (ዕብ 10፡26-27)

“እግዚአብሔር አይዘበትበትም።” (ገላ 6:7)። በእርሱ ፊት ምንም ነን። መመለስና ንሰሐ መግባት ያዋጣል!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 257
መልዕክት (message) 257
መስዋዕት፥ መሰዋት........!

“አቤል ከቃየል ይልቅ” ብሎ መጸሐፍ”የሚበልጥ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር በእምነት አቀረበ። በዚህ እግዚአብሔር ስለ ስጦታው ሲመሰክር፥ እርሱ ጻድቅ እንደ ሆነ ተመሰከረለት። ሞቶም ሳለ በመሥዋዕቱ እስከ አሁን ይናገራል”(ዕብ 11:4)

ስለ መስዋዕት ማቅረብ፣ ስለ መስዋዕት መሰዋት ሲነሳ ስለ እግዚአብሔር ባህሪ እየተወራ ነው። እግዚአብሔር አንድያ ልጁን የሰዋ አምላክ ነው፤ዛሬ ግን ሊቆጠሩ የማይችሉ ልጆች አባት ሆኖአል።

መስዋዕት መሰዋት ኪሳራ የለውም”የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች።” ይላል መጽሐፍ (ዮሐ 12:24)። ስለዚህ ወገኖቼ የእግዚአብሔርን ቃል እምትወዱ አንደሁ፥ መስዋዕት መሰዋ
ትን ሕይወታችሁ አድርጉ።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 258
መልዕክት (message) 258
ራስን ማብቃት፥ ለዘላለማዊው

ምድር ላይ ለመኖር የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ ቀጥሏል። ለመኖር ሲባል የማይደረግ ነገር የለም። ምድር ላይ ለመኖር ሲባል ከሚወሰዱ እርምጃዎች የመጨረሻው ሰው መግደል ነው። ትንተና አያስፈልገውም። ሰማንያ ዓመት ለመኖር ሰው መግደል? (መዝ 90፡10)

መግደል፥ መቼም ቢሆን የመኖር ዓላማ (purpose) ሊሆን አይችልም። መግደልን ዓላማው አድርጎ የሚንቀሳቀስ ሌባው (ሰይጣን) ብቻ ነው (ዮሐ 10፡10)። ሰይጣን፥ አሁን በሰማይ የለም ተጥሏል። ዘላለም ከሚኖርበት ሥፍራ ሰማንያ ዓመት ወደ ሚኖርበት ምድር መጣል? (ኢሳ 14፡12፣ ሕዝ 28፡17)

ስኬት፥ ዘላለም ወደ ሚኖርበት መሄድ(ለዚያ ራስን ማብቃት) እንጂ፥ እንደምንም ብሎ ሰማንያ ዓመት መድፈን አይደለም። “ሄኖክ ሞትን እንዳያይ በእምነት ተወሰደ፥ እግዚአብሔርም ስለ ወሰደው አልተገኘም። ሳይወሰድ እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመስክሮለታልና፤” (ዕብ 11:5)። አሜን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 259
መልዕክት (message) 259
ቤተሰብን መታደግ.........!

ሰው፥ ቤተሰብ ከመሠረተ በኋላ ቤተሰቡ፥ ላይ ሥራ መሥራት አለበት። ቤተሰብ ድንገት በሚመጣ ሃሳብ አይመራም።እቅድ እምነት፣ ትጋት፣ ትዕግስት፣ ጽናት፣ ተሥፋ፣ ፍቅር እና ወዘተ... አስፈላጊ ነገሮች ናቸው።

መጽሐፍ"ኖኅ ገና ስለማይታየው ነገር ተረድቶ እግዚአብሔርን እየፈራ ቤተስዎቹን ለማዳን መርከብ በእምነት አዘጋጀ" ይላል (ዕብ 11:7)። ቀጥሎ የውኃ ጥፋት አለ፥ ኖኅ ግን ቤተሰቡን ለመታደግ መርከብን በእምነት አዘጋጅቷል።

መጽሐፍ በምሳሌ 27:1 "ቀን የሚያመጣውን፥ ምን እንደ ሆነ አታውቅምና ነገ በሚሆነው አትመካ።" ስለሚል፥ ነገ ምንም ሊፈጠር ይችላል፥ለእኛ ቤተሰብ ላይ የሥራ ጊዜ አሁን (ዛሬ) ነው። ኖኅ፥ በእምነት ለቤተሰቡ መርከብ የሠራው፥ ከጥፋት ውኃ በፊት ነው። ስለዚህም ቤተሰቡን ታድጓል።

እንደ ኖኅ ሁሉ፥ እኛም በእምነት፥ ለቤተሰብ የሚገባውን ነገር ከወዲሁ እናርግ። ማድረግ ያልቻሉ ዛሬ እቤታቸው የሉም።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**



PART 260
መልዕክት (message) 260
ሳያውቁ መሄድ.............!

“አብርሃም...”አለ መጽሐፍ”ርስት አድርጎ ሊቀበለው ወዳለው ስፍራ ለመውጣት በእምነት ታዘዘ፥ ወዴትም እንደሚሄድ ሳያ
ውቅ ወጣ”ይላል (ዕብ 11:8)።አወጣጡ በእምነት ስለ ነበር ወዴት እንደሚሄድ አላወቀም፤በሌላ ስፍራ “እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ።” እንዳለው ይናገራል (ዘፍ 12:1)።

እግዚአብሔር ወደሚያሳየን መውጣት እና እኛ ወደምናየው መውጣት በጣም የተለያዩ መንገዶች ናቸው። እግዚአብሔር ወደሚያሳየን መውጣት የሚጠይቀው እምነት ብቻ ነው።እኛ ወደምናየው መውጣት ግን፥ እምነት አይጠይቅም።

“አየሁ” እና “አውቃለሁ” ባይ በዝቷል። ከዚህ የተነሳ እምነት ላልቷል። የመጀመሪያው እምነት ደብዝዟል።ከምህረት ይልቅ ዙሩን ማክረር ፋሽን ሆኗል።ጌታ ማስተዋሉን ይስጠን።የትም ይሁን፥ እንደ አብርሃም ታዝዤ እወጣለሁ። እናንተስ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**



PART 261
መልዕክት (message) 261
እድሜ እንኳ አልፎ.........!

እምናመልከው አምላክ እግዚአብሔር ነው። ጊዜው አለፈም አላለፈ ማንነቱን (identity) ይገልጣል። አዎ ለሣራ ጊዜው አልፏል። ለእግዚአብሔርስ ጊዜው አላለፈም? በእርሱ ዘንድ የሚያልፍ ጊዜ የለም። አቆጣጠሩ እምነት ይባላል። እምነት ደግሞ አሁን ነው። “በተወደደ ሰዓት ሰማሁህ በመዳንም ቀን ረዳሁህ ይላልና፤ እነሆ፥ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው፤ እነሆ፥ የመዳን ቀን አሁን ነው።” (2 ቆሮ 6:2)

መጽሐፍም “ተስፋ የሰጠው የታመነ እንደ ሆነ ስለ ቈጠረች፥ ሣራ ራስዋ ... ፥ ዕድሜዋ እንኳ ካለፈ በኋላ ዘርን ለመፅነስ ኃይልን በእምነት አገኘች።” ይላል (ዕብ 11:11)።

ኢየሱስ “ለሚያምን ሁሉ ይቻላል”(ማር 9:23)ይላልና ጊዜው አለፈም አላለፈ፥ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ማንነቱን ይገልጥ ዘንድ (ውሳኔን ይሰጥ ዘንድ) የማይከለከል አምላክ ስላለ፥ ተስፋ እንዳንቆርጥ፤ ተስፋ ጸንቶ ይኖራል!!! (1ቆሮ 13፡13)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

Aynalem Mersie




PART 262
መልዕክት (message) 262
ከ...ብዙ ገንዘብ ይልቅ

ብዙ ሰው ስለ ገንዘብ ሲል ራሱን አጥፍቷል። ብዙ ሰው፥ ያለ ይመስላል ነገር ግን የለም። የቀድሞ ንጹህ ማንነቱን ስለ ገን ዘብ ሲል አጥፍቷል፤ለጊዜው በኃጢአት ስለሚገኝ ደስታ ሲል ከቀድሞ ታማኝነትና ቅንነቱ ጎድሏል።

ገንዘብ ይገኝበት እንጂ፣ ደስታ ይገኝበት እንጂ ኃጢአት እንደ ጽድቅ፥ ኑሮ ከሆነ ሰነባብቷል።

“ሙሴ ካደገ በኋላ”ብሎ መጽሐፍ”...ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ ... ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ፤ ...” ይላል (ዕብ 11፡24-26)

“መረጠ” የሚለው ቃል አማራጭ መኖሩን ያመለክታል። እኛ ምን መርጠን እየኖርን ነው?ሕይወት ምርጫ ነው። “ሕይወት ምርጫ አይደለም” እሚል ሰው ካለ፥እሱም “አይደለም” እሚ ለውን አቋም መርጧልና፥ ከምርጫ ነጻ አይደለም። ስለዚህ ኢያሱ እንዳለ “የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን። ” (ኢያሱ24:15)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 263
መልዕክት (message) 263
እናግባ፣ ከፍርድ እናምልጥ!

“መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን” ይልና “ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ... እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል” ይላል (ዕብ 13:4)።በዚህ ክፍል ክቡርና መኝታው ንጹህ ስለ ሆነ መጋባት እና በአንጻሩ ደግሞ፥ ካለማግባት ስለሚፈጠር ሴሰኝነትና አመንዝራነት ተነስቷል ግን “ያላገባ ...” አሚለውን አያካትትም (1 ቆሮ 7:38)።

እነማን ናቸው ሴሰኞች? እነማን ናቸው አመንዝሮች? ክቡርና መኝታውም ንጹህ የሆነውን ጋብቻ የሚሸሹ አይደሉምን? በእ
ነርሱ ላይ እግዚአብሔር እንዲፈርድ ከላይ ተገልጿል።

ሴሰኛና አመንዝራ ሳይሆኑ ከእግዚአብሔር ፍርድ ለማምለጥ ይቻል ዘንድ ብቸኛው መንገድ፥ ክቡርና መኝታው ንጹህ የሆነ መጋባት ነው። ስለ እግዚአብሔር መንግስት፥ ጃንደረባ የሆነ (ያላገባ) ደግሞ የተሻለ አደረገ (1ቆሮ 7:38)። አንሴስን እና አናመንዝር፥ ይልቁን በጊዜ እናግባ፥ ከፍርድ እናምልጥ!!!


መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 264
መልዕክት (message) 264
ከገንዘብ በታች አንኑር.....!

ገንዘብ ከሰዎች ህልውና በላይ የነገሠ ይመስላል። የገንዘብ ፍቅር ብዙዎችን እያቃጠለ ነው። ብዙ ሰው ስለ ገንዘብ ሲል ሞቷል። ገንዘብም ህያው ሆኖ በሰዎች ሞት ላይ ይዳደዳል። ሰዎች ከጉንዳን አንሰው፥ ገንዘብ ደግሞ ዘሁኖ (ዝሆን ሆኖ) ጨፍልቆአቸዋል። ጌታ ሆይ እርዳን!!!

መጽሐፍ"አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለ መውደድ ይሁን ያላችሁም ይብቃችሁ። እርሱ ራሱ፥ አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና፤" ይላል (ዕብ 13:5)።

"ያላችሁ ይብቃችሁ።"
ሰዎች፥ እረ የያዝነውን መጀመሪያ እንጨርስ!
"ራሱ አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአል"
ሩጫው ለመለቀቅ (ለመተው) ነው? እናስተውል!

እኔ ራሴን የገንዘብ ባሪያ አላደርግም። እናንተስ???

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 265
መልዕክት (message) 265
እውቅና ለዋኖቻችን........!

መጽሐፍ “የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፥ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው።” ይላል (ዕብ 13:7)።

እውን፥ የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩንን ዋኖች እናስባለን? የኑሮአቸውን ፍሬ እንመለከታለን?በእምነትስ እንመስላቸዋለን ?ይሄን አለማድረግ ክብር አይደለም።ይባስ መቃወም ደግሞ ሞት ነው (ፊልጵ 1፡28)።

ለዋኖች ተገቢውን እውቅና በመስጠት በዚህ ዓለም ልጆች ተበልጠናል። መጽሐፍ “የዚህ ዓለም ልጆች ለትውልዳቸው ከብርሃን ልጆች ይልቅ ልባሞች ናቸው” እንዲል(ሉቃ 16:8) “ለቃሉ ክብር አለኝ”የምንልና በተቃርኖ የሄድን ሁሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ንስሐ እንግባ!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**



PART 266
መልዕክት (message) 266
ትምህርት፥ እንግዳ/የጠቢብ...

እንግዳ ትምህርት ልዩ ልዩ ዓይነት ነው። የእንግዳ ትምህርት ምንጩ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም።ከእግዚአብሔር ቃል ሊመነጨም አይችልም። ቃሉ ራሱ 'እንግዳ' ስለሚል ለራሱ ለእግዚአብሔር እንግዳ ነው፤ስለዚህ የአጋንንት ነው (1ጢሞ 4፡1-2)።

መጽሐፍ ሲመክር"ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ፤" ይላል (ዕብ 13:9)።

መጽሐፍ በሌላ ስፍራ" ሰው ከሞት ወጥመድ ያመልጥ ዘንድ የጠቢብ ሰው ትምህርት፥ የሕይወት ምንጭ ነው። " ይላል። (ምሳሌ 13:14)። ጠቢብ ማን ነው?ምክርን የሚሰማና ተግ ሣጽንም የሚቀበል፥ እርሱ ጠቢብ ነው (ምሳሌ 19:20)።

ስለዚህ ወገኖቼ፥ ከእንግዳ ትምህርት ይልቅ የጠቢብ ሰው ትምህርት ያዋጣል። ያም ሆነ ይህ፥ የምትማሩት ትምህርት ውጤቱ ወይ ሕይወት ነው ወይንም ደግሞ ሞት ነው። እኔ የጠቢብ ሰው ትምህርትን መርጫለሁ። እናንተስ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 267
መልዕክት (message) 267
የምናካፍለው፥ አንድ ሰው...

መጽሐፍ “መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ ፤እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና” ይላል (ዕብ 13:16)።

በሌላ ስፍራ ደግሞ “የምድራችሁን መከር በሰበሰባችሁ ጊዜ የእርሻችሁን ድንበር ፈጽማችሁ አትጨዱ፥ የመከሩንም ቃር ሚያ አትልቀሙ፤ ለድሆችና ለእንግዶች ተዉት፤” ይላል (ዘሌ 23:22)። ዓላማው ሰዎች ማካፈልን እንዳይረሱ ነው።

ገቢያችሁ ምንድን ነው?ከምንስ ነው? ከንግድ? ከደምወዝ? ከእርዳታ (ድጎማ)? የምታገኙትን ሁሉ ለራሳችሁ ብቻ አትጠ ቀሙ። ይልቁን አካፍሉ። የምታካፍሉት ሰው ይኑር። እንዲህ ያለው መሥዋዕት እርሱን ያስደስተዋልና። ይህን ሳናደርግና አሻራችንን ሳናስቀምጥ፥ ከምድር ላይ እንዳናልፍ፥ አደራ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 268
መልዕክት (message) 268
እምቢታ ዋጋ ያስከፍላል!

“ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ እንዲያቦካ አታውቁምን?”(1ቆሮ 5 :6)እንደሚል መጽሐፍ፥ባሳለፍናቸው ሦስት አስርተ ዓመታት፥ የአገራችን ፖለቲካ በረቀቀ ሲስተም ኢኮኖሚውን፣ ማህበራዊ ህይወቱን፣ባህሉን፣የእምነት ተቋማቱን፣ብቻ ልጅ አዋቂ ሳይል ሰዉን ሁሉ አቡኩቶት ነገር ከተዘበራረቀና ውሉ ከጠፋ ቆየ።

በዚህም ምክንያት አሁን አሁን፥ የመጨረሻው የስልጣን ቃል ለሆነው የእግዚአብሔር ቃል እንኳ፥ ሰዎች ተገቢውን ክብር መስጠት እንዳይችሉ ቃል መፍቻው ፖለቲካው ሆኗል።

መጽሐፍ”ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ...ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ” ይላል (ዕብ 13:17)። ዋኖች በነፍስ ላይ ታላቅ ሥራ የሠሩ፣ ዛሬ ላለን አመለካከትና ንግግር መሠረት ጣዮች ናቸው። የት እንደነበርንና ከማን ጋር እንደነበርን ከንግግራችን ይታወቃል። “ጴጥሮስና ዮሐንስም በግልጥ እንደ ተናገሩ ባዩ ጊዜ፥መጽሐ
ፍን የማያውቁና ያልተማሩ ሰዎች እንደ ሆኑ አስተውለው አደ
ነቁ፥ ከኢየሱስም ጋር እንደ ነበሩ አወቁአቸው፤” (ሐዋ 4:13)

ስለ ነፍሳችን ለተጉ ዋኖች መታዘዝና መገዛት ለምርጫ እና ለአስተያየት የቀረበ ጉዳይ ሳይሆን ቀጭን የጽድቅ ትዕዛዝ ነው። እምቢታ ዋጋ ያስከፍላል። ይሁዳ ጥሩ ምሳሌ ነው። (ሐዋ 1:16-18)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 269
መልዕክት (message) 269
ጥበብ ከጎደለህ፥ የለህም!

“ጥበብ ዓይነተኛ ነገር ናትና ጥበብን አግኝ፤” ይላል መጽሐፍ (ምሳሌ 4:7)። ይሄ ሁሉ ጥፋት የመጣው ጥበብ ከማጣት ነው።ማንም ሰው፣የትኛውም አካል፣አገር ራሱ ሊሆን ይችላል ጥፋት ላይ ካለ፥ የጥፋት ዘመቻ ሰለባ ከሆነ፥ ጥበብን የጠሉ ሰዎች ተነስተዋል ማለት ነው።

በመኖር ደረጃ ድንጋይም ይኖራል። ሰው ሆኖ”ኖረ”እሚባለው ግን በጥበብ የኖረ ብቻ ነው።

መጽሐፍ “ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእር ሱም ይሰጠዋል።” ይላል (ያዕ 1:5)። ጠብና ክርክር እንዴት መጣ?ከጥበብ ጉድለት ነዋ። የኃይል ርምጃ ለምን መውሰድ አስፈለገ? ከጥበብ ጉድለት ነዋ።ስምምነትን መጥላት፥ለምን ተፈለገ? ከጥበብ ጉድለት ነዋ። ተቃውሞስ ለምን? ከጥበብ ጉድለት። ከሠላም ይልቅ ጠብን መውደድስ ለምን? ከጥበብ ጉድለት ነዋ። ሁልጊዜ በተቃርኖ መቆምስ ለምን? ከጥበብ ጉድለት ነዋ።በሕይወት ጉዞ ክፍተት ያለበት ሰው፥በቃ በሰው አያሳብብ፤ህመሙ የጥበብ ጉድለት ስለሆነ፥በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ እርሱም ይሰጠዋል።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 270
መልዕክት (message) 270
ፈተና ላይ ነን፤ ጥቂት ደቂቃ ቀረ!

መጽሐፍ “በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና።” ይላል (ያዕ 1:12)።

ውጤቱ የሕይወት አክሊል ከሆነ፥እንፈተን።ውጤቱ የሕይወት አክሊል ከሆነ፥ አገርም ቢሆን ይፈተን።ወርቅ፥ወርቅነቱ የሚረጋገጠው በእሳት ተፈትኖም አይደል? እኔ ያለሁበት የእምነት ተቋም ካሉት አብይ እሴቶች መካከል አንዱ“ምንም ቢፈጠር አለመደንገጥ”የሚል ነው።ፈታኝ ነገር ሊፈጠር ይችላል ነገር ግን መደንገጥ አያስፈልግም፤ለምን?ከፈተና በኋላ የሕይወት አክሊል አለና።

ዓለም ፈተና ላይ ናት፣ እንደ አገርም ፈተና ነው፣ እንደ ሕዝብ፥ ሕዝቤ ፈተና ላይ ነው፣ እንደ ተቋም ሁሉም በፈተና እየተናጠ ነው፣ልጅ አዋቂው እፈተና ገበታ ላይ ቁጭ ብሎ ተወጥሯል። የሕይወት አክሊል ለማግኘት፥የማለፊያውን ነጥብ ማምጣት ግድ ይላል። ፈተናው እስከ ተያዘለት ደቂቃ ይቀጥል!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 271
መልዕክት (message) 271
አምልኮ? ኧረ አልተጀመረም!




“ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው፤” ይልና መጽሐፍ “ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ፥ ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ፥ በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነቱን መጠበቅ ነው።” ይላል (ያዕ 1:27)።

ከዚህ አንጻር የዘንድሮው አምልኮ አፈር በልቷል ብንል ይጋነን ይሆን?”የአምልኮ መልክ አላቸው”የሚለው ቃል አካል ይዟል ፤ መርዳት አይደለም ወላጆች ያላቸውን እና የሌላቸውን ልጆች እንዲሁም ባልቴቶችን በቅጡ አናውቃቸውም።መረጃው ራሱ ያለው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር ነው።

እናመልካለን እንላለን ግን ወላጅ የሌለውን አንድ ልጅ ሳንረዳ ፤ አንድ ባልቴት በመከራው ሳንጠይቅ የጌታ መምጫ ደረሰ። ራሳችንን በመርዳት እና በመጠየቅ ብቻ ደከምን።አልበቃንም አልቅት ይመስል፥ አሁንም ብንጻልይ ለራሳችን ነው። (ምሳሌ 30፡ 15)። ከእድፍ ራስን ስለመጠበቅ፥ ይቅርብኝ፥ትቼዋለሁ፤

በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው ወደተባለው ንጹሕ የሆነ ፥ ነውርም ወደ ሌለበት አምልኮ ዛሬውኑ በንሰሐ እንመለስ። እከሌ ከእከሌ የለም፥ ቃሉ ለሁላችንም ነው!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 272
መልዕክት (message) 272
ምሕረት አላደርግም???

ምሕረት የማያደርግ ሰው፥ ሲመስለኝ፥ ከብረት ይጠነክራል። ምሕረት አለማድረግ ግን ጥንካሬ ሳይሆን ድክመት ነው።እግዚአብሔር ምሕረት ላይ በሆነበት ዘመን”ምሕረት አላደርግም “ማለት ራስን ከእግዚአብሔር የተሻለ እግዚአብሔር ማድረግ ነው። ይሄ ደግሞ ትልቅ የስህተት ትምህርት ነው።

ይሄን መልዕክቴን አንብቦ “ምሕረት አላደርግም” የሚል ሰው ካለ ሰሞኑን ከማሕበራዊ ድህረገጽ ካነበብኩት የጌታ ድምጽ እጠቅሳለሁ “ዱቄት፣ አህያ፣ሌባ”። ሰደብከን እንዳትሉኝ ብቻ፥ ‘ጌታ አለ’ ተብሎ ካነበብኩት ነው የጠቀስኩት።

ምሕረት አታደርግም? አታደርጊም? አታደርጉም? መጽሐፍ “ምሕረትን ለማያደርግ ምሕረት የሌለበት ፍርድ ይሆናል”ሲል በማያሻማ ዓረፍተ-ነገር ተመኑን አስቀምጧል። (ያዕ 2:13)

ጌታ ከእልህ ያውጣን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 273
መልዕክት (message) 273
እምነትህ አልሠራ አለ?

እምነት እርግጠኝነት ነው።"አምነት አለኝ"የሚል ሰው በጉዳዩ ላይ እርግጠኛ ነኝ እያለ ነው።እርግጠኝነቱን እውን ለማድረግ ግን አንድ ነገር ይቀረዋል፤ እርሱም እርምጃ(ሥራ) ነው።ሥራ የእምነት ሙሉነት ነው።

ብዙ ሰው፥ ሁሉንም ነገር ትቶ፥ ጸሎት ቢጀምር፥ ሁሉም ነገር እንደሚቀየር ያምናል። ችግሩ ድርጊቱ ነው። እምነቱ አለ፥ግን ማን ይንበርከክ? ለመንበርከክ ያስብና አያደርገውም። ጊዜ ውን የሚሰርቁት፥ የማያድግባቸውና የማይለወጥባቸው ጉዳ ዮች ብዙ ናቸው።

እምነት ብቻ፣ የእምነት አዋጅ ብቻ፣ ጬኸት ብቻ፣ ወሬ ብቻ፥ ለውጥ የለም።ችግሩ ምንድን ነው?ሥራውን ማን ይሥራው? መጽሐፍ"ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።" ይለናል (ያዕ 2:26)።

ሥራ እንሥራ። ዙረት፣ ወሬ፣ ሐሜት እና ፕሮፓጋንዳ ይበቃል። ያስፈልጋል ካላችሁም፥ ዩ ቲዩብ ክፈቱ፥ ቢያንስ በስህተትም ቢሆን ብዙ ሰው ሰብስክራይብ፣ላይክ ወይም ሼር ያደርጋል!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

What's on your mind?

Aynalem Mersie



PART 274
መልዕክት (message) 274
ተራጋሚና ጨረባ

መጽሐፍ ሲናገር"በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠ
ሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤" ይላል (ማቴ 5:44-45)። ይህን ቃል ያነበበ ሰው ካልታመመ በስተቀር ሁለት ተጻራሪ ነገሮችን አይፈጽምም። "በአንድ አፍ ሁለት ምላስ" እንዲሉ ሲፈልጉ መባረክ፥ሲፈልጉ ደግሞ መር ገም።

ስለዚህ መጽሐፍ "ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ። ወንድሞቼ ሆይ፥ ይህ እንዲህ ሊሆን አይገባም።" ይላል (ያዕ 3:10)። መራገም ክብር አይደለም፤"እንደሚተላለፍ ድንቢጥ ወዲያና ወዲህም እንደሚበርር ጨረባ፥ እንዲሁ ከንቱ እርግ ማን በማንም ላይ አይደርስም" (ምሳሌ 26:2)። እሰይ!

ሰው በክፉ መንፈስ ካልተጠቃ በቀር፥በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረን ሰው ሊራገም አይችልም። አንደበትን ለእርግማን ዓላማ ለሰይጣን ማከራየት ይበቃል። ከዚህ በኋላ እንባርክ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 275
መልዕክት (message) 275
ኑሮ ይናገር፥ ሥራ ይመስክር

መጽሐፍ"ከእናንተ ጥበበኛና አስተዋይ ማን ነው?"ሲል አንድ ወሳኝ ጥያቄ ያነሳል።

መጽሐፍ ሲመልስም "በመልካም አንዋዋሩ ስራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ።" ይላል (ያዕ 3:13)።

ማነው ጥበበኛ? ማነውስ አስተዋይ? ኑሮው የሚናገር ነዋ። ጥበብና የዋህነትን ያማከለ ሥራው የሚመስክር ነዋ። ቤተ ክርስቲያንም ሆነ አገር፥ አሁን የሚያስፈልጋቸው ጥበበኛ እና አስተዋይ ሰው ነው።ጠቢብና አስተዋይ ሰው፥የሰው ምስክር አያስፈልገውም፥ ኑሮው ይናገራል። በሥራው ያስመሰክራል።

ጌታ፥ በመልካም አኗኗራቸው ሥራቸውን በጥበብና የዋህነት የሚያሳዩ ሰዎች ይሰጠን ዘንድ ልንጸልይ ይገባል።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 276
መልዕክት (message) 276
ሁከትና ክፉ ሥራ?

የትም ይሁን የት፥ሁከትና ክፉ ሥራ ከነገሠ፥በዚያ ቅንዓት እና አድመኛነት ተስፋፍቷል ማለት ነው።እንደሚመስለኝ ቅንዓትና አድመኛነት ተደጋጋፊ ሳይሆኑ አይቀሩም።የቀኑ ናቸው አድማ እሚመቱት።

አብሮ አደግ፣ አብሮን የሠራ፣ አብሮን የኖረ፣ አብሮን የተጓዘና አብሮን የነበረ ብድግ ሲል ቅንዓት፥ከዚያ ደግሞ አድመኝነት፤ ብዙ ሰው የሚፈልገው በልጦ መገኘት ነው፥ካልሆነ እኩልነት ከዚህ ካለፈ የቅንዓትና አድመኛነት ዘመቻ ይጀመራል።

"ቅንዓትና አድመኛነት... ብሎ መጽሐፍ... "... የምድር ነው፥ የሥጋም ነው፥የአጋንንትም ነው፤ቅንዓትና አድመኛነት ባሉበት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ስራ ሁሉ አሉ"ይላል(ያዕ3:14-16)

የሰማይ አምላክ ከዚህ ያውጣን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 277
መልዕክት (message) 277
የሚቀባ መድኃኒት የለምን?

ዓለም ተብሎ በማንም አእምሮ ውስጥ ፍጥረታዊው ግዑዝ አካል (the globe) ይታወሳል። ግዑዙን ዓለም ግን፣ ዓለም የሚያሰኘው በውስጡ የያዛቸው ጉዳዮች ናቸው። “በዓለም ያለው ሁሉ” ብሎ መጽሐፍ “እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት” ይላል (1ዮሐ 2:15-16)።

“ዓለምን መውደድ” ብሎ ደግሞ መጽሐፍ “ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን?እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል።” ይላል (ያዕ 4:4)።

እንግዲህ ከመካከላችን ማን ይድን ይሆን? በዓይን አምሮት ጡዘናል፣ በሥጋ ምኞት ረክሰናል፣ ገንዘብ ለማግኘት ስንል የማንሰራው ትርኢት የለም። የእውነት ታምመናል። “የሚቀባ መድኃኒት የለምን? ወይስ በዚያ ሐኪም የለምን? የወገኔ ሴት ልጅ ፈውስ ስለ ምን አልሆነም? ” (ኤር 8:22)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 278
መልዕክት (message) 278
ትዕቢተኞች እና ትሑታን

ሐዋርያው ያዕቆብ በመልዕክቱ "እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል ይላል።"(ያዕ 4:6)

ካልተምታታብን በስተቀር፥በዚህ ዘመን ትዕቢተኞችና ትሑታን በግልጽ ተለይተዋል። ያልተለዩም በወረፋ እየተለዩ ነው።

ትዕቢተኞችን የመቃወም እና የማሳደድ ዘመቻው አሁን ሙሉ ለሙሉ የእግዚአብሔር ሆኗል።አሁን ሰዓቱ የመንግስት ሳይሆን የመለኮት ነው። ከግለሰብ እስከ አገር፥ ትዕቢተኞችና ትሑታን ስለሚለዩ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሁሉም ይጠራል! አሜን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 279
መልዕክት (message) 279
ማንን ልቃወም? ማንን ልቅረብ?

ከማን እየሸሸን፥ ወደ ማን እየቀረብን፥ እንደሆነ ይታወቀናል። ልብ ይመሰክራል ድርጊት ይናገራል።

መከፋፈል እና መለያየትን እየሰበከ “ወደ እግዚአብሔር እየቀረብኩ ነው፥ ዲያብሎስን ደግሞ እየተቃወምኩ ነው፥” የሚል ሰው ካለ፥ ፍርዱን ለራሱ፥ ለልቡ ትቻለታለሁ”ልባችንም በእኛ ላይ በሚፈርድበት ሁሉ ከእውነት እንደ ሆንን ... እናውቃለን” እንዲል መጽሐፍ (1ዮሐ 3:19)።

ወገኖቼ “ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል።” (ያዕ 4:7-8) የሚለው መልዕክት ስብከት አይደለም፥ከሃሳብ እስከ ድርጊት ያለ የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ነው።ስለዚህ “የእግዚአብሔር ሰው ወይም ሕዝብ ነን”የምንል ሁሉ፥በሃሳብም ሆነ በድርጊት ሰው መቃወም ትተን፥ “ተቃወሙት” የተባልነውን ዲያብሎስ እንቃወም። በአንጻሩ፥ እግዚአብሔር እንዲቀርበን ደግሞ ወደ እርሱ የሚያቀርበንን ነገር አስበን እንከውን። ስለሁሉም ጌታ ይርዳን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 280
መልዕክት (message) 280
ጊዜው የማልቀስ ወይስ የመጠርመስ?

ብዙ ሰው በአሁኑ ሰዓት ለመጨነቅ፣ ለማዘን፣ለማልቀስ፣ለመ ተከዝ እና ራሱን ለማዋረድ ጊዜ እንደሌለው አውቃለሁ። ለመ ጠርመስ፣ ለዓመጽ፣ ለእብሪት፣ ለተቃውሞ፣ ለትቾ፣ ለመከፋ ፈል፣ ገንዘብ ለማግኘት፣ ለመክበር እና ከእግዚአብሔር ቃል በተቃራኒ ለማድረግና ለመኖር ግን ጊዜው በሽ ነው።

መጽሐፍ “እናንተ ኃጢአተኞች፥” ይልና “እጆቻችሁን አንጹ፤ ... ተጨነቁና እዘኑ፥ አልቅሱም፤ ሳቃችሁ ወደ ኀዘን ደስታችሁም ወደትካዜ ይለወጥ።በጌታ ፊት ራሳችሁን አዋርዱ ከፍ ከፍም ያደርጋችኋል።” ይላል (ያዕ 4፡8-10)።

ማንም ተቀበለም አልተቀበለ፥ አሁን ጊዜው በእግዚአብሔር ፊት የምንጨነቅበት፣ የምናዝንበት፣ የምናለቅስበት፣የምንተ ክዝበት፣ ሁላችንም በግልም ሆነ በጋራ ስለ ሠራነው ኃጢአት ራሳችንን በጌታ ፊት የምናዋርድበት ጊዜ ነው። ያኔ ከፍ ከፍ ያደርገናል።ከዚህ በተቃራኒ አንድ ስንዝር ተራመዱና ሞክሩት ፥ ውጤቱን ሳይውል ሳያድር ታገኙታላችሁ። ተጀምሯልም፤ “እግዚአብሔር አይዘበትበትም።” (ገላ 6:7)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 281
መልዕክት (message) 281
በጎውን መሸሽ ኃጢአት ነው!

ሐዋርያው ጳውሎስ “የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና፥ ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም።” ይላል። (ሮሜ 7:19)። የብዙ ሰው የዕለት ከዕለት ፈተና ነው። “ከዚህ በኋላ እንዲህ አላስብም፣አልናገርም፣አልጽፍም፣በቃ ትቻለሁ ፣ እዚህ ነገር ላይ አልሳተፍም፣ እኔን በማይመለከትና ሙያዬ ባልሆነ ጉዳይ አልገባም፣ በቀኝ፣ ኧረ በቃኝ፣ ወዘተ” ሁል ጊዜ ግዝት ነው።

በተለይ ደግሞ መንፈሳዊ አገልጋይ የሆኑና ፖለቲከኛ መሆን የሚያምራቸው እጅግ ይፈተናሉ። ወይ ሳይንሱን (political science) አልተማሩ፥ወይም ተዛማጅ የሆነ ኮርስ አልወሰዱ ወይም ደግሞ ሻል ያለ የፖለቲካ ግንዛቤ ማስጨበጫ አልተ ካፈሉም። ጠዋት አውደ-ምህረት (pulpit) ላይ ይሰብካሉ፥ ከሰዓት ደግሞ ዮ-ቲዩብ ላይ ፖለቲካዊ ትንታኔ ይሰጣሉ፥ማታ በጸሎት ስፍራቸው ይታገላሉ። ፈተና ነው።

መጽሐፍ ሁሉንም ሲመክር “እንግዲህ በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው።” ይላል (ያዕ 4:17)። ምንም ይሁን የምናስበውና የምንሠራው፥ ብቻ በጎ ይሁን። በጎውን እያወቅን ባናደርገው ኃጢያት ነው። ጌታ ይርዳን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 282
መልዕክት (message) 282
ጸሎት ለምን? መዝሙርስ?

የሐዋርያው ያዕቆብ መልዕክቶች ለየት ይላሉ። የአንዳንዶቹ ይዘት ትዕዛዝ ነው"ከእናንተ መከራን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ይጸልይ፤" ይልና "ደስ የሚለውም ማንም ቢኖር እርሱ ይዘምር።" ይላል (ያዕ 5:13)።

እውን በዚህ ዘመን መከራ የሚቀበል ሰው ይጸልያል? ወይስ ይቃወማል? ወይንስ ደግሞ አፀፋዊ መልስ ይሰጣል? እያየን ነው። መጸለይ ማሸነፍ ነበር፥ነገር ግን መጸለይ የተሸናፊዎች (የአቅመ-ቢሶች) ተግባር ተደርጎ ከተቆጠረ ሰነባበተ።

እውን በዚህ ዘመንስ ለደስታው የሚዘምር አለ? ወይስ ለብር እና ለማዳመቅ(አሙቁልኝ)ነው እሚዘመረው?ወይንስ ደግሞ በልጦ ለመገኘት ነው?

በምንም ጉዳይ ይሁን መከራ (ስቃይ) ላይ ነኝ የምትሉ ሁሉ ሌላ መንገድ የለም፥ አርፋችሁ ጸልዩ። የምትዘምሩም ከደስታ ተነስታችሁ ዘምሩ። ጌታ ሆይ ከመምታታት አውጣን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 283
መልዕክት (message) 283
ለአቃብያን ማቀቢያ!

መጽሐፍ “ወንድሞቼ ሆይ፥ ከእናንተ ማንም ከእውነት ቢስት” ይልና”አንዱም ቢመልሰው፥ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልሰው ነፍሱን ከሞት እንዲያድን፥ የኃጢአትንም ብዛት እንዲሸፍን ይወቅ።” ይላል (ያዕ 5፡ 19-20)።

በዚህ ዘመን፥ “ስቷል” የሚባል ሰው ከተገኝ፥ ከላይ መጽሐፉ እንዳለው፥ የመመለስ፣ ነፍሱን ከሞት የማዳን እና የኃጢአትን ብዛት የመሸፈን ሳይሆን፤የመቃወም፣ የማሳደድ፣ ሌሎችንም በማስተባበር የማግለል፥ ከተቻለ እና አቅሙ ከተገኘ ደግሞ፥ የማውገዝ ዘመቻ የመጀመሪያው አማራጭ ነው።

ሐዋርያው ያዕቆብ፥ አንድ ጊዜ ተመልሶ ቢመጣና ሊያደርግ ቢችል፥ ሊያደርግ የሚችለው፥”የማጠቃለያ ምዕራፍ” በሚል ርዕስ ራሳቸውን በራሳቸው አቃቢ እምነት ላደረጉ፥ ማቀቢያ የሚያስቀምጥ ይመስለኛል። ለእኔ ግን ያዕቆብ ሳይሆን ጌታ ኢየሱስ ይምጣ። አሜን፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ቶሎ ና!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 284
መልዕክት (message) 284
ቅዱሳን (የተለዩ) እነማን ናቸው?

እግዚአብሔር ጠርቶኛል የሚል ሰው፥ እንደፈለገ መሆን አይ
ችልም፥ እንደጠራው እግዚአብሔር እንጂ። እንኳን እግዚአብ
ሔር የጠራው አይደለም መንግስት የጠራው እንደ መንግስት
ካላሰበና ካላደረገ፥ ከተጠያቂነት አያመልጥም። እንደ ጠራን አካል
መኖር፥ የሕይወት መርህና ሥርዓት ነው። ከዚህ አንጻር መጽሐፍ
“የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ፥ እናንተ ደግሞ በኑሮአ
ችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ።” ይለናል። (1 ጴጥ 1:16)

“በኑሮአችሁ ሁሉ” በማለቱ በማናቸውም የሕይወት እንቅስቃ
ሴያችን ሁሉ ቅዱስ(የተለየን)ልንሆን የግድ ነው።ቅዱስ የሆነ
ሕዝብ፥ የሚያስበው እንደ እግዚአብሔር ነው፣የሚሠራውም እንደ
እግዚአብሔር ነው።

ተቃዋሚ፣ተራጋሚ፣አስመሳይ፣ወሬኛ፣ሰነፍ፣ሟርተኛ፣ትዕቢተኛ
፣ ተሳዳቢ፣ተቺ፣እብሪተኛ፣አመፀኛ፣ጉረኛ፣ትምክህተኛ፣ ዘረኛ፣
ጠባብ፣ ንፉግ፣ ከፉ፣ አመንዝራ፣ ጉበኛ፣ ወዘተ የሆነ ሰውም
ሆነ ሕዝብ፥ እርሱ፥ የሱ ወገን አይደለም።ጌታ የእሱ የሆኑትን
ያውቃል፤ተቀላቅሎና ተመሳስሎ መኖር ሊያበቃ አንድ ጀንበር የቀረ
ይመስለኛል። ሊነጋ ስለሆነ፥ ፈጥነን ንሰሐ እንግባ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ
ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie



PART 285
መልዕክት (message) 285
የመልስ ምት?

የብዙ ሰው አኗኗር የታይታ ነው። መከባበር እና አንዱ ለአንዱ የመገዛት ባህል የለም። በየቤቱ ጠብ አለ። በየተቋሙ ቁርሾ አለ። የእውነት ሳቅና ጨዋታ ከራቀን ሰነባበተ። ኑሮ ተቻችሎ ሆኗል። ተሰድቦ ዝም አለማለት የጀግንነት መገለጫ ይመስል ድጋፍ አለው። አሁን አሁን መከራ ማድረስ እንደ ክብር፥ መከ
ራ ማየትም ሆነ መቅመስ እንደ ሽንፈት ነው እሚቆጠረው። እንዲህ እየተኖረ "አለን" ይባልልኛል፤ ድንቄም መኖር ¡

ቃሉ ሲናገር "ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና። ... ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም፥ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤" ይላል (1ጴጥ 2፡21-23)።

ፍለጋውን እንድንከተል፥ ምሳሌ ትቶልን እንደሄደው ክርስቶስ፥ መኖር ካልተፈለገ፥ እንደማን ነው መኖር የተፈለገው? ከዚህ በኋላ እየተሳደቡ እና እየደበደቡ መኖር አይቻልም።የሚፈርድ አለ (ዮሐ 8፡50)።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 286
መልዕክት (message) 286
የምን በረራ ላይ ነን?

መጽሐፍ “ለኃጢአት ሞተን፥ ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ፥ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ”ሲል ሐዋርያው ጴጥሮስ የተናገረውን ከቁ. 25 ቀጥሎ “በግዕዝ፥ እንዲህ ተጽፎአል” ብሎ”ወበእንተ ኃጣውኢነ ውእቱ ተሰቅለ ዲበ ዕፀ በሥጋሁ ከመ ያውፅአነ እምኃጣውኢነ ወበጽድቁ ያሕይወነ” ሲል ይናገራል (1 ጴጥ 2:24፥ ፍ1)።

በአንድ ቋንቋ አልበቃ ብሎ ጉዳዩ በሁለት ቋንቋ ቀርቧል።ኧረ እናስተውል!! “ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ” የተባለ አካል ካለ፥ ዛሬም ኃጢአት ተሸክሞ መኖር የምን ፍርጃ ነው? “ለኃጢአት ሞተን”ተብሎ ሰው ዛሬም “ለኃጢያት፥ በተለይም ለመጠጥ፣ጫት፣ሱስ፣ ዝሙት፣ ስርቆት፣ ክፋት፣ ወዘተ ሕያው ነኝ፣ አልሞትኩም “ካለ፥ የለፋበት ደመወዙን አይከለከልም። “የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤” (ሮሜ 6:23)።

ሰው ኃጢአት ሠርቶ ሲጨርስ ደመወዙ ሞት ከሆነ፥ ከሠው ሁሉ ምስኪን ነው።በተገኘበት መጨለጥ፣ከተገኘው ሁሉ ጋር ጋደም ማለት፥ የወሬ ጨፍ ይዞ ሩጫ እና ሌሎች የኃጢአት በረራዎችን እናቋርጥ። ባንበርም ለጽድቅ እናኮብኩብ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 287
መልዕክት (message) 287
ባሎች ሆይ፥ ሚስቶች ሆይ...

ሐዋርያው ጴጥሮስ በትዳር ዙሪያ ሲመክር “እናንተ ሚስቶች ሆይ፥ ከባሎቻችሁ አንዳንዱ ለትምህርት የማይታዘዙ ቢኖሩ፥ ... ንጹሑን ኑሮአችሁን እየተመለከቱ ያለ ትምህርት በሚስቶቻ ቻው ኑሮ እንዲገኙ ተገዙላቸው። ... እንዲሁም፥እናንተ ባሎች ሆይ፥ደካማ ፍጥረት ስለሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፤” ይላል (1 ጴጥ 3:1-7)።

“ባሎች”ብሎ ለትምህርት ያለመታዘዛቸውን ድክመት ሲገልጽ ፥ “ሚስቶች” ይልና ደግሞ፥ የፍጥረት ድክመታቸውን ያስቀም ጣል። ዘረም ቀረ የቃላት መለዋወጥ ካልሆነ በቀር ሁለቱም ጋ ድክመት አለ። አንዳቸው የአንዳቸውን ክፍተት ይሞሉ ዘንድ እና ኪዳኑ እንደሚለው አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ የግድ ነው (ማቴ 19፡5)። “ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም” እን ዲል መጽሐፉ (ዘፍ 2፡18)።

በአንጻሩ መጽሐፍ ሲናገር “በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፥ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ፥ስለ መን ግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ።” ሲል የትዳር ዘመቻው የማያካትታቸውን፥ ይጠቁማል (ማቴ 19: 12)።

ስለዚህ የተጋባን ሁሉ ድክመት እንዳለብን አምነን፥ አንዳችን የአንዳችንን ክፍተት እንሞላ ዘንድ እንትጋ። ወዳጅን አሳልፎ መስጠት አይገባምና!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 288
መልዕክት (message) 288
ከሰማይ በታች፥ አንድ ተገኘ

መጽሐፍ "ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን ... ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ ... በሥጋ ሞተ፥ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፥በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው፤"ይላል (1 ጴጥ 3፡18-19)። ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ እንኳ የምስራች ለመስበክ የሄደው ወደ ወኅኒ (ሲኦል) ነው።

በዚህም ዘመን ወገኖቼ እሱ አልተለወጠም"ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና፥ ዛሬ፥ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።" (ዕብ 13:8)።

ማንም ሊረዳችሁ እማይችልበት፥ ሥፍራ እና ሁኔታ ውስጥ ናችሁ? መቼም ከወኅኒ (ሲኦል) የከፋ ሁኔታና ሥፍራ የለም፥ ግን አትፍሩ። ሞት ይዞ ያስቀረው ዘንድ ያልቻለ (ሐስ 2:24)፣ በሰማይና በምድር ስልጣን የተቀበለ (ማቴ 28:18)፣አልፋና ኦሜጋ (መጀመሪያ እና መጨረሻ) የሆነ፥የእግዚአብሔር ልጅ ተገልጧል። ከሰማይ በታች ስፍራው ድረስ ብሎም ሁኔታው ውስጥ ገብቶ ሊያድን የሚችል አንድ ተገኘ "መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።"(ሐስ 4:12)፥ ኢየሱስ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie



PART 289
መልዕክት (message) 289
ሃሳብ፥ ሥራ ይፈልጋል!

ሐዋርያው ጴጥሮስ"የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት" ብሎ "በመዳራትና በሥጋ ምኞትም በስካርም በዘፈንም ያለልክም በመጠጣት ነውርም ባለበት በጣዖት ማምለክ የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃልና።" ይላል (1 ጴጥ 4:3)።

መዳራት፣ የሥጋ ምኞት፣ ስካር፣ ዘፈን፣ ያለ ልክ መጠጣትና ነውርም ያለበት ጣዖት ማምለክ የተሰኙት ጉዳዮች፥ የሥጋ ሥራ ናቸው፤ የአሕዛብ ፈቃድ ናቸው፤ ኃጢአት ናቸው።

ስለዚህ እንዳራ፣በሥጋ እንመኝ፣እንስከር፣እንዝፈን፣ እንጠጣ፣ ጣኦትንም እናምልክ፣የሥጋ ሥራን እንሥራ፣የአሕዛብን ፈቃድ እናድርግ፣ ኃጢአትን እንሥራ። ይቻላልን? ጉዳዩ የሃሳብ ነው። ማሸነፍም ሆነ መሸነፍ የሚጠናቀቀው ሃሳብ ላይ ነው። "ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው።" (ሮሜ 8:6)። ሃሳባችን ላይ እንሥራ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**



PART 290
መልዕክት (message) 290
ይመርመር!

ተናጋሪ በዝቷል፥ በተለይ በማህበራዊ ድህረ-ገጽ። መድረክ እና አውደ-ምህረት ይዞ የሚናገር፥ ከተሰብሳቢው በልጧል። የአገልጋይ ቁጥር ከመብዛቱ የተነሳ፥ በእግዚአብሔር ኃይል የሚሰጠው አገልግሎት፥ከችሎታ አገልግሎት እማይለይበት ሁኔታ ላይ ተደርሷል።

ጸጋ አይደለም ነገር ግን በመናገር ጥበብ የተካኑና በንግግር ብልሃት፥ ሰው የመሰብሰብ አቅም ያጎለበቱ ሰዎች አሉ። የት እንደ ሰለጠኑ ባይታወቅም፥ ስልጡን ናቸው። የነሱን ድምጽ (ዜማ) ለመስማት፥ ደጋፊዎቻቸው ቢያንስ ቢያንስ በሳምንት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባሉ። የዚህ ዘመን የአገልግሎት ትርኢትም እንደ ንግግር ክህሎቱ ሁሉ በውል የተለየ ማሰልጠኛ ተቋም ባይኖረውም መደበኛ ባልሆነ(informal)የልምድ ልውውጥ ላይ የተመሠረተ ነው።

መጽሐፍ "ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤" ይልና "የሚያገለግልም ቢሆን፥ እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል"ይላል(1 ጴጥ 4:11)፤ ከዚህ ክፍል ጋር ያልተቃኘ ንግግርም ሆነ አገልግሎት ምንም ጥቅም የለውም። ንግግርና አገልግሎት ሁሉ ይመርመር!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 291
መልዕክት (message) 291
ቀይ መብራት ላይ ነን!

መቼም ቢሆን ነፍሰ ገዳይ ለመሆን፣ለሌብነት፣ክፉ ለማድረግ በሌሎች ጉዳይ ለመግባት፣የማይገባን ነገር ለማድረግ፣ወዘተ ጥሪ ወይም ራዕይ የተሰጠው ማንም የለም።ዲያብሎስ ራሱ ያልተጠራበትን አጀንዳ ሲያራምድ ተገኝቶ ነው ከሰፈር የተባረረው። ያልተሰጠንን፥ወይም ያልተላክንበትን ጉዳይ ስናራምድ ተገኝተን፥ ልክ እንደ ዲያብሎስ፥ ከተሰጠን ስፍራና ሕይወት እንዳንባረር። ፍርድ ደርሷል።

መጽሐፍም "ከእናንተ ማንም ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም ክፉ አድራጊ እንደሚሆን፥ወይም በሌሎች ጉዳይ እንደሚገባ ሆኖ መከራን አይቀበል። ክርስቲያን እንደሚሆን ግን መከራን ቢቀበል ስለዚህ ስም እግዚአብሔርን ያመስግን እንጂ አይፈር። ፍርድ፥ ከእግዚአብሔር ቤት ተነሥቶ የሚጀመርበት ጊዜ ደርሶአልና፤አስቀድሞ በእኛ የሚጀመር ከሆነ ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙ መጨረሻቸው ምን ይሆን?" ይላል። (1 ጴጥ 4፡15-17)

ሁላችን ቀይ መብራት ላይ ነን። "አትስረቁ" ብለን እንሰብካለን እኛ ስንሰርቅ የጉድ ነው። የጊዜ፣ የንብረት፣ የሰው፣ የአሠራር (ሞዴል)፣ የገንዘብ፣ የጥቅም፣ የክፋት ስልት፣ ወዘተ ዝርፊያ ላይ ተሰማርተናል።ይህን መልዕክት እያነበብን "እኔ እሆንን?" አንበል (ማር 14:19)። ሁላችንም ምህረት እንጠይቅ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 292
መልዕክት (message) 292
መጨረሻውን የማያውቅ ሯጭ

“ጻድቅም በጭንቅ የሚድን ከሆነ ዓመፀኛውና ኃጢአተኛው ወዴት ይታይ ዘንድ አለው?” (1 ጴጥ 4:18)

ከላይ እንደተመለከተው፥ጻድቅ ነው ግን የሚድነው በጭንቅ ነው።መጽሐፍም”ጻድቅ ሎጥም በመካከላቸው ሲኖር እያየና እየሰማ ዕለት ዕለት በዓመፀኛ ሥራቸው ጻድቅ ነፍሱን አስጨ ንቆ ነበርና” ይላል (2 ጴጥ 2:7-8)

እኛ ከየትኛው ወገን ነን?ማን ነን?ጻድቅ ወይስ ዓመፀኛ? ምን እየሠራን ነው?በመጨረሻው መጽሐፍ የተቀመጠው የመጨ ረሻው ማስጠንቀቂያ፥ እንዲህ ይነበባል “ዓመፀኛው ወደ ፊት ያምፅ፥ ርኩሱም ወደ ፊት ይርከስ፥ ጻድቁም ወደ ፊት ጽድቅ ያድርግ፥ቅዱሱም ወደፊት ይቀደስ...እነሆ፥በቶሎ እመጣለሁ ፥ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።” (ራዕ 22፡11-12)

ስለዚህ”እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን፥የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመ ልክተን፥በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ... እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚ አብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና” (ዕብ 12:1-2)። ኢየሱስን ተከትሎ የሮጠ፥መጨረሻው የእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ነው። መጨረሻውን የማያውቅ ሯጭ፥ ከሰው ሁሉ ምስኪን ነው!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።
በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 293
መልዕክት (message) 293
የኃይል አገዛዝ

መሪ ሆኖ ምሳሌ መሆን መታደል ነው። እንደ እድል ሆኖ መሪ ሆኖ"እከሌ ምሳሌ መሆን ይችላል"የምንለውን ሰው ማግኘት አልቻልንም።ሁሉ ኃይለኞች ናቸው። ሁሉ ቁጡ እና እልኸኞች ናቸው።ሁሉ ይሰደባሉ።ሁሉ ስለ ሚመሩት መንጋ ግምታቸው ዝቅተኛ ነው። የዘመኑ አገዛዝ በወሬ አቀባዮች የተዛባ መረጃ ላይ ተመርኩዞ በኃይል ነው። ድንገትም ጌታ ቢገለጥ ከእጁ የክብር አክሊል ለመቀበል የሚችል መሪ አለ ብሎ ለማሰብ ትንሽ የከብዳል።

መጽሐፍ ግን "ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ" ብሎ"የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ" በማለት ይመክራል (1ጴጥ 5፥3-4)።

እባካችሁ መሪዎች በዙሪያችሁ ላሉ እና የጥሪያችሁን ምሰሶ ለተሸከሙ አእማዶች ራሩላቸው፣ ለመንጋውም ምሳሌ ሁኑ። አንድ እንጨት ብቻውን አይነድም።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**



PART 294
መልዕክት (message) 294
ላለመሰናከል፥ ትጋት

እቀደመው ቅንነት እና ንጽህና ብሎም ትጋት ላይ አለመገኘት የመሰናከል ምልክት ነው። ካልተጋን፥ የምንነጠቀው ወይም ደግሞ (የምንቀማው) ነገር መፈጠሩ አይቀርም። መጽሐፍ "አእምሮአቸውም በጠፋባቸው እውነትንም በተቀሙ፥" ይላል (1ጢሞ6:4-5)።እውነት ማለት ልንመሰክረው የተወለድንበት የመጀመሪያው ዓላማ ነው። እሱን ከተነጠቅን ተሰናክለናል። ለጊዜው ምንም ነገር ልንሠራ እንችላለን፥ ግን የተጠራንበት አጀንዳ ካልሆነ በእርግጥ ተሰናክለናል።

መጽሐፍ ሲናገር "ስለዚህ፥ወንድሞች ሆይ፥ መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ፤ እነዚህን ብታደ ርጉ ከቶ አትሰናከሉምና።" ይላልና (2 ጴጥ 1:10)።

እንግዲህ፥የተጠራንበትን እና የተመረጥንበትን አብይ አጀንዳ እናጽና፥ማለትም ተመልሰን እንያዝ፥አጠንክረን እንሥራውም። ያኔ አንሰናከልም ሌላውንም አናሰናክልም። ከተሰናከለ አካል ጌታ ይጠብቀን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 295
መልዕክት (message) 295
ነቢይነት፥ እዳው ለማን?

ነቢይነት እንደ ማንኛውም አገልግሎት መልካም አገልግሎት ነው።ሲጀመርም አብዛኛውን ጊዜ አጀማመሩ ጥሩ ነው።ነገር ግን እየቆየ ሲሄድ አብዛኞቹ አገልጋዮች ላይ ህጸጽ ይታያል።
የመጀመሪያው ምልክት ሐሰተኝነት ነው። ይሄ ደግሞ በራስ ትክክለኛ ነብይ ሆኖ ለመገኘት ከሚመነጬ ጉጉት ነው።

ሌሎች ደግሞ ጉዳዩን ሊካፈሉ(impartation) በመሰብሰባ
ቸው 'ነቢያቱ' ሳያውቁት አሰልጣኝ(አስተማሪ)ይሆናሉ።ፈጣን ጥፋት፣ ኑፋቄ፣ መዳራት (ብዜት)፣ ወዘተ ይሆናል። በዚህም የእውነት መንገድ ይሰደባል።የዚህ ሁሉ ተጋድሎ ሥርና መሠ
ረት፥ ገንዘብና ዝና መሻት እንደሆነ በሂደት ይገለጣል።

ሐዋርያው ጴጥሮስ በዘመኑ አለ"ሐሰተኞች ነቢያት…በሕዝቡ መካከል ነበሩ…ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ፤ … የዋጃ
ቸውን ጌታ እንኳ ክደው፥ የሚፈጥንን ጥፋት፥ በራሳቸው ላይ እየሳቡ፥ የሚያጠፋ ኑፋቄን አሾልከው ያገባሉ፤ ብዙዎችም በመዳራታቸው ይከተሉአቸዋል በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል። ገንዘብንም በመመኘት በተፈጠረ ነገር ይረቡባችኋል፤" (2 ጴጥ 2፡1-3)

በጽድቅ አገልግለን እንኳ ካልተጠነቀቅን ነቢይነት ልጃችን ባለ እዳ ሊሆን የሚችልበት ከባድ አገልግሎት ነው (2 ነገ 4፡1)። የዘመኑ ነቢያት፥ልጆቻችሁ በታሪክ እዳ እንዳይያዙ፥ ጠንቀቅ!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።
በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 296
መልዕክት (message) 296
የሆነ እንስሳ ስጠን!

እብደት ምንድን ነው? እንዴትስ ይመጣል? ነቢይ የሆነ ሰው ሊያብድ ይችላል?በምን ምክንያት? ከዚህ ቀደም ነቢይ ሆኖ በመጽሐፍ ስለ ማበዱ የተነገረለት አለ?

መጽሐፍ “ኃጢአትም ስንፍና፥ ስንፍናም እብደት እንደ ሆነች አውቅ ዘንድ እኔ በልቤ ዞርሁ” ይላል (መክ 7:25)። እብደት ስንፍና ነው። ስንፍና በገዛ ልብና ማንነት የመታመን ልምምድ ነው። “ሰነፍ በልቡ አምላክ የለም ይላል” (መዝ 14:1)። “እኔ ነኝ ያለሁት” እያለ ነው ማለት ነው። ከዚህ አንጻር ነቢይ የሆነ ሰው፥ የዓመፃን ገንዘብ እና ተያያዥ ዝናን ከመውደድ የተነሳ የጸጋውን ባለቤት ከረሳ፥ መጨረሻው እብደት ነው። እንዲህ ያለው ሰው፥ ሰው ተናግሮ አይመልሰውም፥ ምናልባት አህያ፤

መጽሐፍ ሲናገር “ቅንን መንገድ ትተው ተሳሳቱ፤የባሶርን ልጅ የበለዓምን መንገድ ተከተሉ፤እርሱ የዓመፃን ደመወዝ ወደደ፥ ነገር ግን ስለ መተላለፉ ተዘለፈ፤ ቃል የሌለው አህያ፥ በሰው ቃል ተናግሮ የነቢዩን እብድነት አገደ”ይላል(2ጴጥ2፡15-16)

ጌታ ሆይ፥ በዚህም ዘመን የነቢያቱን እበደት የሚያርም ሰው አጥተናልና የሆነ እንስሳ ስጠን።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 297
መልዕክት (message) 297
የጥፋት ምልክቶች

የመዳን ጉዳይ፥ የትምህርት፣ የዶክትሪን፣ የእውቀት ወይም የአመለካከት ጉዳይ ሳይሆን የወንጌል ጉዳይ ነው። ወንጌል ደግሞ፥ ራሱ እግዚአብሔር ነው። ሰው፥ ከሆነ ሰው (ሰዎች) በጀመረ እውቀት ተሸብቦ እግዚአብሔርን (ወንጌልን) ከተወ፥ ውሻ ወይም እርያ ሆኖአል።የት ይደርሳሉ የተባሉ አገልጋዮች ዛሬ ከወንጌል ርቀዋል።ወንጌል'ወንጌል ስርጭት' እንዳልሆነ ልብ ይሏል።'ወንጌል ስርጭት'ሳይታወቀን ወንጀል(ኃጢአት) ስርጭት እንዳይሆንብን።

መጽሐፍም በዚህ ጉዳይ ሲናገር "በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ከዓለም ርኵሰት ካመለጡ በኋላ ፥ዳግመኛ በእርስዋ ተጠላልፈው የተሸነፉ ቢሆኑ፥ ከፊተኛው ኑሮአቸው ይልቅ የኋለኛው የባሰ ሆኖባቸዋል።አውቀዋት ከተ ሰጣቸው፥ ከቅድስት ትእዛዝ ከሚመለሱ፥ የጽድቅን መንገድ፥ ባላወቋት በተሻላቸው ነበርና። ውሻ ወደ ትፋቱ ይመለሳል፥ ደ ግሞ የታጠበች እርያ በጭቃ ለመንከባለል ትመለሳለች እንደ ሚባል እውነተኞች ምሳሌዎች ሆኖባቸዋል።" ይላል (2 ጴጥ 2፡20-22)።

እትላንቱ ማንነት ላይ ካልሆንን ተቀይረናል።ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማነውና የተነሳንበት፥እንዲሁም ዋጋ የከፈልንበት ወንጌል ግን እስከ ዛሬ አልተቀየረም። መዳን እንዳለ፥ መጥፋት አለ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 298
መልዕክት (message) 298
ኅብረት እና ጨለማ

"አገለግላለሁ"የሚል ሰው ከሚያገለግለው አካል ጋር ኅብረት (unity) አለው፣ ወይም ሊኖረው የግድ ነው። "ኅብረት አለኝ" እያሉ በተቃራኒ (በድብቅ) የሚደረግ ማናቸውም እንቅስቃሴ ጨለማ ነው፤ የውሸት ነው።

"አብረን ነን" እንላለን፣ የምንመላለሰው በተቃርኖ (ለማፍረስ) ነው።"አብረን ነን"እንላለን፣የተለየ ዘመቻ እናካሂዳለን።"አብረን ነን" እንላለን፣ እመገንጠል ጥያቄ ላይ ነን።"አብረን ነን" እንላለን፣ ግን የተገነባውን እማፍረስ ላይ ነን።"አብረን ነን" እንላለን ግን እንከፋፍላለን። "አብረን ነን" እንላለን ግን ብዙ ሰው ዋጋ የከፈለበትን አገር ወይም ተቋም እናፈርሳለን። ታዲያ፣ ከእኛ በላይ ውሸታም ማን ነው? ከእኛ በላይ ጨለማስ ማን ነው?

"ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል" ብሎ መጽሐፍ"በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም"ይላል (1ዮሐ 1:6)። በጨለማ (የውሸት) መመላለስ ይበቃል!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 299
መልዕክት (message) 299
ከማን ወገን ናቸው?

አንዳንድ ሰዎች፥ ከማን ወገን እንደሆኑ በውል አይታወቅም። እንዲህ ዓይነት ሰዎች በማህበረሰብ የሕይወት ጉዞ የበርካታ ችግሮች ምንጭ ናቸው።ችግር ከተፈጠረ፥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ አመንጪዎቹ እነሱ ናቸው። አፈንግጠው እስከሚወጡበት ቀን ድረስ "አጋር ነን"ባዮች ናቸው።ከተቋም (አገር) መፍረስ ወይም ደግሞ መንገራገጭ ጀርባ እነሱ አሉ፤

መጽሐፍ እነኚህን ሰዎች አስመልክቶ "ከእኛ ዘንድ ወጡ፥ዳሩ ግን ከእኛ ወገን አልነበሩም፤ ከእኛ ወገንስ ቢሆኑ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር፤ ነገር ግን ሁሉ ከእኛ ወገን እንዳልሆኑ ይገለጡ ዘንድ ወጡ።" ይላል (1 ዮሐ 2:19)።

ዛሬም መመለስ ያለበት ጥያቄ፥ እነዚህ ሰዎች ከነበሩበት ቦታ ወጥተዋል፥አሁንም ከማን ወገን እንደሆኑ ሊታወቅ አልቻለም ፤ እንዲህ ያሉ ሰዎች እያሉ አገር፣ ማህበረሰብ ወይም ተቋም መገንባት ታላቅ ፈተና ነው። ለማንኛውም ጌታ ይርዳን!


መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie



PART 300
መልዕክት (message) 300
የወደደ፥ ሞቶ ያድናል!

መውደድ(መዋደድ)አካል ከሌለው፥ ከቃል(አንደበት) ጨዋታ የዘለለ ትርጉም የለውም። ዓለም ማህበረሰብን በዚህ ቅርጽ እየሠራች ታስተዳድራለች። በየመድረኩ ንግግር የሚከፈተው 'የተከበሩ(የተወደዱ)'በሚል ፈሊጥ ነው።የቃላት(የአንደበት) ጨዋታ እንጂ እውነትነቱ የለም። እውነት ካልሆነ ውሸት ነው ማለት ነው። ውሸት ደግሞ ውሸትነቱ፥ አካል አልባነቱ ነው።

መጽሐፍ ሲናገር"ልጆቼ ሆይ፥በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ።" ይላል (1 ዮሐ 3:18)። ኧረ መዋደድ እንጀምር።እውነተኛው መዋደድ በሥራና በእውነት ከሆነ ሥራ እንጀምር፤ ነገርን የእውነት ማድረግም እንዲሁ።

"ወድዶኛልና አዳነኝ።" (መዝ 18:19)። የወደደ ያድናል። የመውደድ አካሉ (ጭብጡ) ማዳን ነው። ማዳን መች እንደ መግደል ቀላል ነው፤ትልቅ ዋጋ ያስከፍላል፤ትዕግስት ይጠይቃል። ማዳን፥ስፍራው ድረስ ወርዶ፥የሚከፈለውን ዋጋ ከፍሎ ነው። መግደልማ በጣም ቀላል ነው። ዩ-ቲዩብ ከፍቶ፥ እዛው ቁጭ ብሎ አገር መግደል ይቻላል። ሠርቶ ማዳን ነው ትልቅነት!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 301
መልዕክት (message) 301
አትመኑ፥ መንፈስን ወይስ ነቢይን?

በዚህ ዘመን"መርምሩ"የተባለው መንፈሱን ነው እንጂ ነቢዩን አይደለም። ነቢዩ የሚያንቀሳቅሰው መንፈስ ከእግዚአብሔር ነው ወይስ አይደለም?እጅግ ብዙ ሐሰተኛ ነቢያት ወደ ዓለም እንደወጡ ግልጽ ነው።

መጽሐፍ በዚሁ ጉዳይ ሲናገር "ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ፤ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋል" ይላል (1 ዮሐ 4:1)።

ማንም"ነቢይ ነኝ"የሚል ሰው ሐሰተኛ የመሆን ፍላጎት ያለው አይመስለኝም።የእውነት ማገልገል አየፈለገ ነገር ግን ይስታል ። ሲመስለኝ፥ ግለሰቡ መሻት እንጂ መንፈሱ የለውም፤ በዚህ ላይ ማንነቱና የጸጋ ስጦታው ሳይኖር ሲቀር ደግሞ፥ ችግሩን በበለጠ ያባብሰዋል።

ምን ይሻለናል?ጌታ ሆይ ሙሴም፥የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ነቢያት ቢሆኑ፥ እግዚአብሔርም በእነርሱ ላይ መንፈሱን ቢያ ወርድ፤" እንዳለ፥ ሁላችንንም ነቢያት አድርገህ፥ ከመምታታት አድነን!!! (ዘኍ11:29)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie



PART 302
መልዕክት (message) 302
ማን ነው ሐሰተኛ?

“ክርስቲያን ነኝ” እያልክ ነገር ግን  የምትጠላው ወንድም ካለ አንተ ሐሰተኛ ነህ።“እግዚአብሔርን እወዳለሁ” እንዴት ማለት ቻልክ? አጠገብህ ያለ እና የምታየውን ወንድም ሳትወድድ፥ ያላየኸውን  እግዚአብሔር “እወድዳለሁ” ማለት፥ አስተሳሰቡ ራሱ የወረደ ነው።የብዙ አገልጋዮች ወቅታዊ ችግር ይሄ ነው

መጽሐፍ “ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል?” ይላል (1ዮሐ 4: 20)

ወገኖቼ መቼም ተመልሰን፥ እንደ ቀድሞው ህብረት ማድረግ ባንችልም ነገር ግን ሐሰተኛ ሆኖ ዘመንን ላለመጨረስ እልፍ ሲልም በዚሁ ጉዳይ እንዳይፈረድብን፥ከአንዳንድ ወንድሞች ጋር ያለንን ጉዳይ በምህረት ዘግተን የምንጠላው ሰው ሳይኖር ብን በነጻነት እንኑር። ለዚህም አይደል ክርስቶስ ነጻነት ያወጣን? ራሳችንን በራሳችን ቶሎ እንፍታ!!!

መልዕክቱን  መሞገት፣  ማሔስ  እና  ሌሎችም  እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 303
መልዕክት (message) 303
ለፍላፊ ቃል አቀባይ፥ ዲዮጥራጢስ

በሐዋርያት ዘመን የነበሩ ሰዎች ነበሩ።ዋንኞችን አይቀበሉም ፤ በክፉ ቃል ለፍላፊዎች ናቸው። ወንድሞችን አይቀበሉም። ወንድሞችን የሚቀበል ሲያገኙም ከቤተ ክርስቲያን ያወጣሉ

ስለ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ዮሐንስ በመልዕክቱ ሲናገር “ወደ ቤተክርስቲያን ጻፍሁ፤ዋናቸው ሊሆን የሚወድ ዲዮጥራጢስ አይቀበለንም።...በእኛ ላይ በክፉ ቃል እየለፈለፈ የሚያደርገ ውን ሥራውን አሳስባለሁ፤ ይህም ሳይበቃው ... ወንድሞችን አይቀበልም፥ ሊቀበሉአቸውም የሚወዱትን ከልክሎ፥ ከቤተ ክርስቲያን ያወጣቸዋል።” ይላል (3 ዮሐ 1፡9-10)።

በእኛም ዘመን እንዲህ ያሉ ሰዎች በፖለቲካው፣በኢኮኖሚው በማህበራዊው ህይወት ዘርፍና በእምነት ተቋማቱ ፈልተዋል ። ራሳቸውን ዋና ያደርጋሉ፤ ከራሳቸው ውጪ ማንንም አይቀበሉም፤ ለፍላፊ ቃል አቀባዮች ናቸው፤ ወንድሞችን (ወገን) አይቀበሉም ብቻ ሳይሆን፥ ወንድሞችን (ወገንን) በአሰቃቂ ሁኔታ አጥፊዎች ናቸው፣ለወንድሞች(ለወገን) የሚራራ ሰው ከተገኘ፥ አይደለም ከአገር፥ ከምድረ-ገጽ ያጠፋሉ። ጌታ ሆይ ለእነዚህም ምህረት ይሁን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 304
መልዕክት (message) 304
ለመንጻት፥ ውኃ ወይስ ደም?

አብርሃም በቀትርም በድንኳኑ ደጃፍ እግዚአብሔር በመምሬ የአድባር ዛፍ በተገለጠለት ጊዜ፥መውደዱን ለመግለጥ ውኃ አቅርቦ እግር አጥቧል (ዘፍ 18:4)።ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም እንዲሁ የደቀ መዛሙርቱን እግር በማጠብ፥ እርስ በርስ ይተ ጣጠቡ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቷቸዋል (ዮሐ 13:4-15)።በሌላም የመጽሐፍ ክፍል፥ በውኃ ስለ ሚደረግ መታጠብ እናነባለን። ሁሉ መውደድንና አክብሮትን ለመግለጽ የተደረገ ነው።

“ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን፥” (ራዕ 1:5)

ይሄኛው እጥበት፥ በውኃ ሳይሆን በደም ነው። ጌታ ኢየሱስ፥ ምን ያህል ቢወድደን ነው፥ በደሙ ያጠበን? መጽሐፍ “የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም፥ ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።” ይላል። (1ዮሐ1:7)።ከኃጢአቱ መንጻት የሚፈልግ ማንም ቢኖር ወደ ኢየሱስ ደም አሁኑኑ ይቅረብ፣ ስሙን እየጠራ አሁኑኑ ይንጻ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie



PART 305
መልዕክት (message) 305
መከራ አትፍሩ፥ ሞትም

"እግዚአብሔር የሚባል አምላክ አለ" ብሎ የሚያምን ማንም ሰው፥ በተሰለፈበት የጽድቅ የአገልግሎት ጥሪና ጎዳና መከራ ቢመጣ አይፈራም። በዚህ ዘመን እንደምናየው አሰልቺ የሆነ የውሸት የማስተባበያ ፕሮፓጋንዳ(ስጥ እንግዲህ)ላይ ራሱን አያሰማራም። እውነት ነው ብሎ በያዘውና እውነትነቱ በተረጋገጠው ዓላማው እስከ ሞት ድረስ የታመነ ሆኖ ይኖራል፥ዋጋውም እጅግ ታላቅ ነው።

መጽሐፍ ለእንዲህ ዓይነት ሰው ሲመክር "ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ።... እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።" ይላል (ራዕ 2:10)።

መጨረሻው የሕይወት አክሊል የሆነ ሰው፥ ለምን ይፈራል? ሞትስ ቢሆን ለምን ያስፈራዋል?ሞት የሚፈራ ሽፍጠኛ ነው፣ ሞት እሚፈራ፣ ሞት አራማጅና ሞት አስፋፊ ነው።የደረስንበት ጊዜ ጉልህ ማስረጃ ነው። ጌታ ሆይ ለሁሉ ምህረት ይሁን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 306
መልዕክት (message) 306
የተከፈተ በር፤ ማን ከፈተው?

ዓለም ከተፈጠረ እስከአሁን ብዙ ባለስልጣኖች በምድር ላይ ተነስተዋል።የአብዛኞቹ ታሪክም ተመዝግቧል።የባለስልጣናት አቅም በምንም ጉዳይ በር የመክፈት ወይም የመዝጋት ነው፤ አንዳንድ መሪዎች የጦርነት በር ሲከፍቱ፥ አንዳንድ መሪዎች ደግሞ የልማት በር ይከፍታሉ። አንዳንድ መሪዎች የጦርነት በር ይከፍታሉ ነገር ግን ሳይዘጉት ይቀራሉ፥ በዚህ ምክንያት ብዙ ትውልዶች ይገቡበታል። በሩ እንደተከፈተ ሁሉ የሚዘጋ ነው፥ ግን በስልጣን ነው።

አንድ የተለየ ስልጣን ተገልጧል “የዳዊት መክፈቻ ያለው፤ የሚከፍት፥ የሚዘጋም የሌለ፤ የሚዘጋ፥ የሚከፍትም የሌለ፤ ቅዱስና እውነተኛ የሆነ”ይላል መጽሐፍ ስለኢየሱስ ክርስቶስ
(ራዕ 3:7)።

በኢየሱስ ክርስቶስ የተከፈቱና ማንም ሊዘጋቸው የማይችል በሮች አሉ። ጽድቅ፣ ቅድስና፣ ቤዛነት ፈውስ፣ ነጻነት፣ ሠላም፣ ብልጥግና፣ ወዘተ በእርሱ ነው የሆነው። ስለዚህም ኢየሱስ “በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣ
ልም መሰማሪያም ያገኛል”አለ (ዮሐ 10:9)።ከኢየሱስ ውጪ የሆነ ሕይወት ሁሉ መግቢያ እና መውጫ የሌለው የጨለማ ሕይወት ነው፥ ከንቱ ሃይማኖት ነው።ሃይማኖት በር የለውም!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።
በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 307
መልዕክት (message) 307
ኩል፥ ከማን እንግዛ?

ሰው ስለ ራሱ ያለው ግምት የተሳሳተ ከሆነ እጅጉን ጎስቋላና ምስኪን ነው። በዚህ ጉዳይ፥ መጽሐፍ ሲናገር “ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኛለሁ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም የምትል ስለ ሆንህ፥ ጐስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውርም የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ” ይላል (ራዕ 3፡17)።አብዛኛው ሰው ሕይወቱ እንዲህ ነው። ከገሃዱ ዓለም የሃብት፣ የብልጥግናና የኃይል መስፈርት በመነሳት፥ ራሱ ለራሱ “ሀብታም ነኝ፥ ባለ ጠጋ ሆኛለሁ፥ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም”፥ በሚል አጉል ትምክህት፥ አገር ይረብሻል። በእውነተኛው የመንፈስ ዓለም ሲታይ ግን ጐስቋላ፣ ምስኪን፣ ድሀም፣ ዕውርም የተራቆተም ነው።

ኢየሱስ ሲመክር እንዲህ አለ “ባለ ጠጋ እንድትሆን፥ በእሳት የነጠረውን ወርቅ፥ተጐናጽፈህም የራቁትነትህ ኃፍረት እንዳይገለጥ ነጭ ልብስን፥ እንድታይም ዓይኖችህን የምትኳለውን ኵል ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሃለሁ።” (ራዕ 3፡18)።

ከኢየሱስ ውጪ፥ የምትገዙት የሃይማኖት ኩል ሁሉ፥ እውር ያደርጋችኋል!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 308
መልዕክት (message) 308
የት ነን? ውስጥ/ውጪ?

መጽሐፍ ሲናገር “ውሻዎችና አስማተኞች ሴሰኛዎችም ነፍሰ ገዳዮችም ጣዖትንም የሚያመልኩት ውሸትንም የሚወዱና የሚያደርጉ ሁሉ በውጭ አሉ።” ይላል (ራዕ 22:15)።

የት ነው ያለነው?ውስጥ ወይስ ውጪ?የእድል ወይም የእጣ ጉዳይ አይደለም፥ ማንነትን የመጠበቅ ጉዳይ ነው። ተዘናግተን ውሻ እንዳንሆን፥ አስማት እንዳንሠራ፥ እንዳንሴስን፣ ነፍስ እንዳናጠፋ፣ ጣኦትን እንዳንከተል፣ ውሸትን አፍቃሪና ውሸትን ተዋኝ እንዳንሆን፤ ከዚህ የተነሳም ወደ ውጪ እንዳንጣል!

መጽሐፍም “ጨው መልካም ነው፤ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፈጣል? ለምድር ቢሆን ለፍግ መቈለያም ቢሆን አይረባም፤ ወደ ውጭ ይጥሉታል” ይላል (ሉቃ14:34-35) ጌታ ለዘላለም የውስጥ ሰው ያድርገን “በእግዚአሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።” እንደሚል(መዝ 23:6)።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 309
መልዕክት (message) 309
ከሞቱት የሚመጣ የለም?

ጌታ ኢየሱስ “በቶሎ እመጣለሁ ይላል።” (ራዕ 22:20)

ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ፥ከኢየሱስ ውጪ“በቶሎ እመጣለሁ” ያለ ማንም የለም። ማንም ከሌለ ከእርሱ ውጪ የሚጠበቅ የለም ማለት ነው።ታዲያ የምን የሆነ ሃይማኖት መከተል ነው ? ለምንስ ብለን ነው የሆነ ርዕዮተ-ዓለም የምንከተለው? ኧረ እንንቃ! እመጣለሁ ያለውን መከተል ነው። አይሻልም?

እርሱ ራሱ “እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ፥ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም” ብሏል።
(ዮሐ 8:12)

አሁን በምንከተለው ሃይማኖት ወይ ፍልስፍና ወይም ደግሞ ርዕዮተ-ዓለም ካላረፍን፥በጨለማ ውስጥ ነን። የምንከተለው ብርሃን ከሆነ ግን እርሱ ማንነት(personality)አለው።ነበረ፣ አለ፣ይመጣልም።እንዲህ ያለ ሃይማኖት የለም፥በማንነት ላይ ያነጣጠረ እምነት እንጂ። መጽሐፍ “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል።” ይላል (ዮሐ 3:14-15)።በሌላ ስፍራም “ሞቼ ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፥ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ” አለ ጌታ(ዮሐ 1:18)፤

እኔ ምንም ሃይማኖት አልፈልግም። ይህን ጌታ መርጫለሁ፥ እጠብቀዋለሁም። እናንተስ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 310
መልዕክት (message) 310
በቃ፥ እንለያይ!

መጽሐፍ ሲናገር “እግዚብሔርም፥ ብርሃንንና ጨለማን ለየ።” ይላል። (ዘፍ 1:4)። እግዚአብሔር ተመሳስሎ እና ተቀላቅሎ መኖር አይወድም። “እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ” ብሎአልና (ዮሐ 8:12)፥ ራሱን ከጨለማ (ከሰይጣን) ለይቷል።

እኛንም ይመክራል “ከማያምኑ ጋር፥ በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ፥ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?ክርስቶስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው?..የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው? የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም፥ ከጣዖት ጋር ምን መጋጠም አለው?..ስለዚህ ጌታ ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ፥ ርኵስንም አትንኩ ይላል ሁሉን የሚገዛ ጌታ ፤ እኔም እቀበላችኋለሁ፥ለእናንተም አባት እሆናለሁ እናንተም ለእኔ፥ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ትሆናላችሁ” (2 ቆሮ 6:14-18)

በይሉኝታ ወይም ለጥቅም ወይም ለመኖር ስንል ተመሳስለን እና ተቻችለን የኖርንበት ዘመን ይበቃል። በቃ እንለያይ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 311
መልዕክት (message) 311
ዘመቻው ከሰይጣን ነው!

መጽሐፍ “እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤...ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።እግዚአብሔርም ባረካቸው፥...ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም፤ የባሕርን ዓሦች እና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙ አቸው።” ይላል። (ዘፍ 1:27-28)

እግዚአብሔር ማለት ፈጣሪ ነው፣እርሱ ማለት የሚባርክ ነው ፤በረከቱ ደግሞ የብዜት ነው፣ የሙሌት ነው፣ የመግዛት ነው።

እንዳንበዛ፣ እንዳንሞላ እና እንዳንገዛ የሚደረግ ዘመቻ ሁሉ፥ ከሰይጣን (ከሌባው) ነው። መጽሐፍም ይህን ሲያረጋግጥ፥ “ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመ ጣም” ይላል(ዮሐ 10:10)። ደግነቱ”ሌባ ቢያዝ ሰባት እጥፍ ይከፍላል፥በቤቱም ያለውን ሁሉ ይሰጣል”(ምሳሌ6፡30-31)

እግዚአብሔር የፈጠረውን እና የባረከውን ሕዝብ ለማጥፋት የተነሳችሁ ሰይጣኖች፥ እረፉ። “የእግዚአብሔር እድል ፈንታ ሕዝቡ ነው፤” (ዘዳ 32፡9)። እግዚአብሔር አይዘበትበትም። “አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና”(ዕብ 12:29)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 312
መልዕክት (message) 312
ሥራና ዕረፍት፣ ጥፋትና ድካም

መጽሐፍ "እግዚአብሔርም፥ የሠራውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ፤ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ" ይላል (ዘፍ 2:2)።

ሥራውን የሠራና ያጠናቀቀማ ይረፍ።የሥራ መጨረሻ ዕረፍት መሆኑ ተገቢ ነው።አሁን ግራ ያጋባን አጥፍቶ ማረፍ የማረው ማህበረሰብ መፈጠሩ ነው። አጥፍቶ፥መቼም ዕረፍት የለም። ይህንን ከሰይጣን መማር አለብን። ሰይጣን ዕረፍት ላይ አይ ደለም፣ ሊሆንም አይችልም። መጽሐፍ አሁን ያለበትን ሲናገር "አንተ ... ደክመሃልን? እኛንስ መስለሃልን? ጌጥህና የበገናህ ድምፅ ወደሲኦል ወረደ፤በበታችህም ብል ተነጥፎአል፥ትልም መደረቢያህ ሆኖአል።" ይላል (ኢሳ 14፡10-11)።

የሥራ መጠናቀቅ መጨረሻ ዕረፍት እንደሆነ ሁሉ የጥፋትም መጨረሻ ድካም፣ ወደ ሲኦል መውረድ፣ ብል እና ትል ነው።

ጌታ እግዚአብሔር፥ እንደ ይሳኮር፥ የዕረፍት ሰው ያድርገን!!! (ዘፍ 49፡14-15)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 313
መልዕክት (message) 313
ስንት ዓመቷ ነው?

መጽሐፍ ታሪክ ሲተርክ “የሁለተኛውም ወንዝ ስም ግዮን ነው ፤እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከብባል።” ይላል። (ዘፍ 2:13)።

ስለ ኢትዮጵያ መነገር የተጀመረው መቼ ነው?መቼ ነው ታላቁ መጽሐፍ የዚችን አገር ስም ያነሳው? የኢትዮጵያ እና የግብጽ ግንኙነት እንኳ፥ 1500 ዓመት፥ ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደ ነበር መረጃዎች ያሳያሉ። ዘፍጥረት 2 ስሟ ከተነሳ፥ ኢትዮጵያ የስንት ዓመት ታሪክ ነው ያላት?

መጽሐፍ ስለ እስራኤሎች “ልጅነትና ክብር ኪዳንም የሕግም መሰጠት፥ የመቅደስም ሥርዓት፥የተስፋውም ቃላት ለእነርሱ ናቸውና፤ አባቶችም ለእነርሱ ናቸውና፤ ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ፥ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው፤ አሜን።” ይላል (ሮሜ 9:4-5)።

እጅግ የሚገርመው፥ እግዚአብሔር “የእስራኤል ልጆች ሆይ፥ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?” ይላል።
(አሞጽ 9:7)

አንግዲህ አገር ማክበር ቢያቅተን፣ ሕዝብ ማክበር ቢያቅተን የእግዚአብሔርን ቃል እናክብር። ይህቺን አገር መናቅ ቃሉን መናቅ ነው። “ሰማይና ምድር ያልፋሉ፥ ቃሌ ግን አያልፍም።”
እንዲል ጌታ (ማቴ 24:35)።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።
በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 314
መልዕክት (message) 314
ማበጀትና መጠበቅ




እግዚአብሔር በማንነቱ፣የሚያበጅና የሚጠብቅ አምላክ ነው ከዚህ አንጻር መጽሐፍ"እግዚአብሔር አምላክም"ብሎ"ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤" ይላል (ዘፍ 2:7)፣ እንደገና ደግሞ "እስራኤልን የሚጠብቅ" ብሎ "አይተኛም አያንቀላፋምም።" ይላል (መዝ 121:4)።

ለዚህም ነው "እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው" ተብሎ የተጻፈው (ዘፍ 2:15)።

እግዚአብሔር የትም ያኑረን፥ እንድናበጅና እንድንጠብቅ ነው ፤ እንድናፈርስና እንድናጠፋ እንዳልሆነ ልብ ልንል ይገባል። ማፍረስና ማጥፋት ላይ የተሰማረ ማንም ቢኖር እርሱ ከእግዚአብሔር ቃል ወድቋል!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 315
መልዕክት (message) 315
ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ

መጽሐፍ አፈጣጠራችንንና ወደ እዚህ ምድር አመጣጣችንን ሲዘግብ “ግሩምና ድንቅ ሆኼ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ ፤ሥራህ ድንቅ ነው፥ ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች”ይላል (መዝ 139:14)።

ትንሽ ቆየንና የአጥፊው የሰይጣን ሃሳብ ተባባሪ ሆንን ተገኘን ፥ስለዚህም”ዕራቁታቸውን እንደ ሆኑ አወቁ፤ የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም አደረጉ።” ተባለ። (ዘፍ 3:7)።

ቅጠል(ሰልባጅ) ስንት ቀን ይለበሳል?ወቅቱ ፖለቲካው እጅግ የተጋጋለበት ስለሆነ “ሰልባጅ”ያለው ነጮቹን ሊነካ ፈልጎ ነው እንዳትሉኝ፥ ከምህረት ጋር ቢያንስ ይህቺን ቃል እንድጠቀም ዛሬ ፍቀዱልኝ። ታዲያማ እግዚአብሔር አምላክ “ለአዳም እና ለሚስቱ የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው፥ አለበሳቸውም።”
(ዘፍ 3:21)

ከአጥፊ ጋር ማበር፥ ውጤቱ በደረጃ ሲቀመጥ ጸጋ የሌለው (እራቁት) መሆን፤የማያስጥል ቅጠል መልበስ በመጨረሻም ቁርበት(የማይለወጥ)የሕይወት ስርዓት ላይ መጣል ይሆናል
DON’T FOLLOW SATAN & HIS IDEAS EVER!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 316
መልዕክት (message) 316
ሁለተኛ እድል ተሰጥቷል

አዳም ሲወድቅ"ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ ከዔድን ገነት አስወጣው፤የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ።" ይላል መጽሐፍ (ዘፍ 3:23)።

ለመኖር ከተሰጠን የመጀመሪያ አመቺ አጋጣሚ (opportu nity) ተለያይተናል ማለት በቃ፥ አበቃ ማለት አይደለም። ጌታ የእንደገና አምላክ ነው።ጥያቄው"ሁለተኛ እድል ቢሰጠን እኛ ምን ያህል የተገኘንበትን መሬት ለማረስ (ለማልማት) ዝግጁ ነን?" የሚል ነው።

ወገኖቼ፥አሁንም አልረፈደም።ወደ ሁለተኛው እድል መመለስ ይቻላል። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል "የወደቁ አይነሡምን? የሳተስ አይመለስምን? " (ኤር 8:4)።

እልኸኝነት መጨረሻው ጥፋት ነው። ከኤደን ገነት ላንመለስ ወጥተናል። አሁን ደግሞ እድል እየተሰጠን ነው። መጀመሪያ የተገኘንበትን ምድር እንድናርስ። ይህንን እድል ተጠቅመን ማልማት ካልቻልን ፍጻሜያችን የከፋ ነው። ጌታ ሆይ እርዳን!


መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 317
መልዕክት (message) 317
ተናደድህ? ፊትህ ጠቆረ? አትሰማማ!

ከተናደድክ፣ እየተናደድክ ከሆነ እና ፊትህም እየጠቆረ ከሆነ መልካም ነገር እያሰብክ፣ እያደረግህ፥ለማድረግ እየተዘጋጀህ አይደለም። ኃጢአት በደጅህ እያደባች ነው።የደረስንበት ጊዜ ጥሩ ማሳያ ነው።

በአንድ ወቅት፥ የገዛ ወንድሙንና “ወደ ሜዳ እንውጣ” ብሎ የገደለውን ቃየንን እግዚአብሔር ከግድያው በፊት አስቀድሞ አስጠነቀቀ”ለምን ተናደድህ?ለምንስ ፊትህ ጠቆረ?መልካም ብታደርግ ፊትህ የሚበራ አይደለም?መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅ ታደባለች፤ፈቃድዋም ወደአንተ ነው፥አንተ ግን በእርስዋ ንገሥባት።” አለው (ዘፍ 4፡6-7)። ከማስጠንቀቂያ በላይ ምን አለ? እግዚአብሔር በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ይናገራል(ኢዮብ 33፡14)።ቃየል ማስጠንቀቂያውን ተላለፈ። ወንድሙን “ወደ ሜዳ እንውጣ” ብሎ ገደለ። መከራና ሥጋት በሕይወቱ ተጀመረ። አለመስማት ውጤቱ ይሄ ነው።

“የሚሰማኝ ግን በእርጋታ ይቀመጣል፥ ከመከራም ሥጋት ያርፋል።”(ምሳሌ 1:33)። የራሳችንን ጩኸት መስማት ትተን ልንሰማው የተገባውን ጌታ እንስማ፥ ያኔ ከመከራም ሥጋት እናርፋለን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 318
መልዕክት (message) 318
ወንድምን ያህል ነገር...

እግዚአብሔርም የገዛ ወንድሙን የገደለውን ቃየንን ... "ምን አደረግህ?የወንድምህ የደሙ ድምፅ ከምድር ወደ እኔ ይጮ ኻል። አሁንም የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረገምህ ነህ። ምድርንም ባረ ስህ ጊዜ እንግዲህ ኃይልዋን አትሰጥህም። በምድርም ላይ ኰብላይና ተቅበዝባዥ ትሆናለህ።" አለው። (ዘፍ 4፡9-12)

ወንድምን ያህል ነገር ገድለህ፣ ምንም እንዳላደረገ ነጻ ሰው ምድር ላይ ለመመላለስ ብትሞክር፣ እጣ ፈንታህ የቃየን ነው ፤የገደልከው የወንድምህ ደም ድምፅ የሚሰማው እላይ ነው ፤ምድር በጨለማ ስለተያዘች፣የአንተን ግድያ(የጨለማ ሥራ) ትደብቅልሃለች። ለዚህ ነው፣ ወንድምን መግደል የቀለለው።

እግዚአብሔር "በቀል የእኔ ነው፣ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ" ይላል (ዕብ 10:30)። ቃየንን እንዴት እንደተበቀለው ከላይ በተቀመጠው የመጀመሪያ አንቀጽ (paragraph) ቃል ልብ ይሏል።መልዕክቱ በመሳሪያ ለሚገድሉ ብቻ ሳይሆን በሐሰት መረጃ(propaganda) ለዘመቱ ሁሉ ነው።ጌታ ለንስሐ ጊዜ ይስጠን፣ ይራራልን፣ ይመልሰንም፤ ምህረቱ አያልቅምና።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**



PART 319
መልዕክት (message) 319
መንገዳችንን አናበላሽ!

በአንድ ወቅት ምድር በእግዚአብሔር ፊት ተበላሸች፤ ግፍን ተሞላች። እግዚአብሔርም ምድርን አየ፥ እነሆም ተበላሸች፤ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በምድር ላይ መንገዱን አበላሽቶ ነበርና።
እግዚአብሔርም ኖኅን አለው "የሥጋ ሁሉ ፍጻሜ በፊቴ ደርሶ
አልፏል፤ ...ከምድር ጋር አጠፋቸዋለሁ። ከጎፈር እንጨት መርከ
ብን ለአንተ ሥራ፤..." (ዘፍ 6፥11-14)

ምድር የመበላሸት እድል ሁሌም አላት፤ ግፍን የመሞላትም። እንዴት ትበላሻለች? እንዴትስ ግፍን ትሞላለች? ከላይ "ሥጋን የለበሰ ሁሉ..መንገዱን አበላሽቶ ነበረ"ይላል። ለውድቀታችን ማንንም ተጠያቂ አናድርግ።መንገዳችን ላይ ምን እያደረግን ነው? ምን እያሰብንና፥ ምን እየፈጸምን ነው? ምድር በእኛም ዘመን እየተበላሸችና ግፍ እየተሞላች ከሆነ፥የእኛ አስተዋጽኦ ምን ያህል ነው?አትጠራጠሩ ጥፋት ሲጀመር ጠፊዎች ነን።

በእግዚአብሔር ዘንድ የጅምላ ተጠያቂነት የለም "ለእያንዳን
ዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ
።"እንደሚል፥እንደሄድንበት አስተሳሰብና መንገድ ይወሰናል። (ራዕ 22:12)።

የማህበረሰብ አንቂ ከመሆን በፊት ራስን ማንቃት ይቀድማል
፤ራስን ማንቃት ማለት ደግሞ፥ መንገድን አለማበላሸት ነው!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።
በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 320
መልዕክት (message) 320
አንድ ጊዜ አሰበን!




እግዚአብሔር የሚያስብ አምላክ ነው።እግዚአብሔር ሰውን፣ ማህበረሰብን፣ አገርን፣ ንጉስን፣ የሰጠውን ኪዳን፣ የሰጠውን የተስፋ ቃል፣ ወዘተ የሚያስብ አምላክ ነው። ሲያስብ አንድ እርምጃ ይወስዳል።

መጽሐፍ፥ በአንድ ወቅት እግዚአብሔር ኖኅን፥ በመርከብም ከእርሱ ጋር የነበረውን አራዊቱንም ሁሉ፥ እንስሳውንም ሁሉ እንዳሰበ፤ ይናገርና በመቀጠል ሲናገር “...እግዚአብሔርም፥ በምድር ላይ ነፋስን አሳለፈ፥ውኃውም ጎደለ”ይላል(ዘፍ8:1)

እግዚአብሔር ማንንም አንድ ጊዜ ያስብ እንጂ፥ነፋስ ይልካል ፥የጥፋትን ውኃ ያስወግዳል። “እግዚአብሔር የጥፋት ውኃን ሰብስቦአል፤ እግዚአብሔር ለዘላለም ንጉሥ ሆኖ ይቀመጣል ።” ይለናል የማይጠገበው ህያው ቃል። (መዝ 29:10)

ጌታ ሆይ፥ እንደ ቃልህ የጥፈትን ውኃ ከምድራችን ሰብስብ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 321
መልዕክት (message) 321
ጥሪውን ያየ ሰው፥ እሱ አልሞተም

እግዚአብሔር ወደ ጥሪህ፣ ወደ ራዕይህ፣ ወደ ተፈጠርክበት ዓላማ ሊያመጣህ ሲፈልግ፥ምንም ብትፈልገውና ብትወደው ፥ከነበርክበት፣ከአስተዳደግህ ጋር ቁርኝት ካለው እና ቤተሰብ ከሚባለው ማህበረሰብ ነጥሎ ያወጣሃል። በቤተሰብ መኃል መሆን መልካም ነው ነገር ግን መረሳት የሌለበት ቀደም ሲል በተጀመረ የወላጅ ጥላና እይታ(ራዕይ) ስር ስላለህ፥ ታያለህ ግን የአንተን አይደለም፤ትሠራለህ ግን የተጠራህለትን ጉዳይ አይደለም። እይታ ላይ ነው ምስጢሩ። እይታ ደግሞ ጊዜ እና ቦታ ይፈልጋል። የሚያሳይ ግን እግዚአብሔር ነው።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነንን ሰው ታሪክ፥መጽሐፍ ቅዱስ ያወሳል "እግዚአብሔርም አብራምን አለው።ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደ ማሳይህ ምድር ውጣ።" ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን፤" ይለዋል። (ዘፍ 12፡1-2)

እንግዲህ መለየት ከሚገባን ወቅቱን ጠብቀን እንለይ፣"ታየኝ" ወዳልነው የእኛ እይታ ሳይሆን እርሱ ወደሚያሳየን እንውጣ። መጽሐፍ "ለሞትም እንዳልተኛ ዓይኖቼን አብራ።"ይላል (መዝ 13:4)፥ዓይኑ የበራለትና እግዚአብሔር ጥሪውን ያሳየው ሰው ፥እሱ አልሞተም!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**



PART 322
መልዕክት (message) 322
የሚረግምህም ሁሉ..........

ለአባታችን አብርሃም እና ለዘሩ (ለእኛ) ከተገባ የኪዳን ቃል መካከል "የሚባርኩህንም እባርካለሁ፥ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።" የሚል ይገኝበታል። (ዘፍ 12:3)

በዚህ መልዕክት ውስጥ "የሚረግሙህንም፥ እረግማለሁ፤" የሚለውን ማስጠንቀቂያ፥ሁሉም ልብ ሊለው ይገባል። ሰውን መራገም፣ ማህበረሰብን መርገም፣ አገርን መርገም፣ ሰውና የሰው የሆነን ነገር ሁሉ መርገም ምላሹ ከእግዚአብሔር ነው
። በአንድ ወቅት፥ በለዓም የተባለ ነቢይ እስራኤልን ሊራገም ወጥቶ፥ "እግዚአብሔር ያልረገመውን እንዴት እረግማለሁ?"
ብሎ ሳይረገም ተመልሷል። (ዘኍ 23:8)

ታዲያ እኛ፥ ማን ስለሆንን ነው እምንራገመው? ማንስ ነው የመራገሙን ስልጣን የሰጠን? ዛሬ ዛሬ ከመራገም አልፈው የሚያስፈራሩ እና የቃል ስልጣን በራሳቸው የወሰዱ ሰዎች ተፈጥረዋል፥ "ቃል ካወጣሁ ያልቅልሃል"፣ "አንዴ ከተናገርኩ በቃ"፣ "በአንድ ቃል አጠፋሃለሁ"፣ "ከረገምኩህ አትነሳም"፣ "እንትናን እኔ ቃል አውጥቼበት ነው እንዲህ ሆኖ የቀረው"፣ ወዘተ።

ቃሉ "የሚረግምህም ሁሉ የተገመ ይሁን።" እንደሚል ከዚህ ቃል በተቃራኒ ሊረግምህ/ሊረግምሽ የሚነሳ ሁሉ የተረገመ ይሁን !!!
(ዘኍ 24:9)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።
በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 323
መልዕክት (message) 323
እስከ ሽምግልና፥ ሽበት መኖር

የሳይንስን ቃል ማወቅና በሳይንስ ቃል መኖር ለስንት ዓመት ያህል እንደሆነ ባይታወቅም፥በእግዚአብሔር ቃል መኖር ግን በታወቀ ክፍለ ዘመን ውስጥ መኖር እና በረከት ነው።

መጽሐፍ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሆነን ሰው ያነሳል"አብርሃምም ሸመገለ በዘመኑ አረጀ፤ እግዚአብሔር አብርሃምን በሥራው ሁሉ ባረከው።" ይላል (ዘፍ 24:1)። ይህንን የሚያነብ ሰው "እንዴት?" ሊል ይችላል። "እንደተሰጠው የተስፋ ቃል" የሚል ነው መልሱ። "የተስፋ ቃሉስ ምን ይላል?" ጥያቄው ሊቀጥል ይችላል። መልሱ እንደሚከተለው ነው፡-

ጌታ አለ"እስከ ሽምግልና ድረስ እኔ ነኝ፥ እስከ ሽበትም ድረስ እሸከማችኋለሁ፤ እኔ ሠርቻለሁ እኔም አነሣለሁ፤ እኔ እሸከማ ለሁ እኔም አድናለሁ።" (ኢሳ 46:4)።

ምርጫው የእናንተ ነው። ሳይንስ የነገራችሁን ቃል አምናችሁ በዕድል መኖር፥ አልያም ከፍ ሲል በነቢዩ ተነግሮ በክርስቶስ የተፈጸመውን ዘላለማዊ ሕይወት (እስከ ሽምግልና / ሽበት) መኖር። አሜን ይሁንልን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie

PART 324
መልዕክት (message) 324
ክብራችንን አናቃልል!

ሰው ማዕረጉን ወይም ክብሩን (dignity)፥ ስለ ጥቅም ብሎ በገዛ እጁ አሳልፎ ከሰጠ ወይም ከሸጠ በኋላ ተራ ሰው ሆኖ ለመመላለስ ይገደዳል።

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆንን ሰው መጽሐፍ ያነሳል"ዔሳውም 'እነሆ፥ እኔ ልሞት ነኝ፤ ይህች ብኵርና ለምኔ ናት?'አለ። ያዕቆብም። 'እስኪ በመጀመሪያ ማልልኝ' አለው።ማለለትም፤ ብኵርናውንም ለያዕቆብ ሸጠ። ያዕቆብም ለዔሳው እንጀራና የምስር ወጥ ሰጠው። በላ፥ ጠጣም፥ተነሥቶም ሄደ፤ እንዲሁም ዔሳው ብኵርናውን አቃለላት።" (ዘፍ 25፡32-34)

ማንነታችንን፣ ክብራችንን፣ ስማችንን፣ እኛነታችንን፣ ጸጋችንን ለገንዘብና ለሃብት ወይም ለጥቅም ስንል አናቃልል።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 325
መልዕክት (message) 325
ከተናገረህ፥ አይተውህም!

እግዚአብሔር ያዕቆብን አለ"የነገርሁህን ሁሉ እስካደርግልህ ድረስ አልተውህምና።" (ዘፍ 28:15)

እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር (እስኪያደርግ) እስኪፈጽም ድረስ የማይተው አምላክ ነው ማለት፥ ያንን የማድረግ ብቃት ያለው ሌላ አካል ባለመኖሩ ነው።እርሱ ቃል የመናገር ወይም የመግባት ብቻ ሳይሆን፥ በማድረግም ብርቱና የማይከለከል አምላክ ነው።

ሌላው አስገራሚ ነገር፥እግዚአብሔር ከተናገረ፥ የተናገረውን ሁሉ በመፈጸም የታወቀ ነው። በዚህ ረገድ መጽሐፍ "እግዚአ ብሔርም እንደ ተናገረው ሣራን አሰበ፤ እግዚአብሔርም እንደ ተናገረው ለሣራ አደረገላት።" ይላል (ዘፍ 21:1)።

ወገኖቼ እግዚአብሔር በቃሉ ምን ብሏል?
"አልጥልህም፥ አልተውህም።"? (ኢያሱ 1:5)፤
"አልለቅህም ከቶም አልተውህም፤" ? (ዕብ 13:5)፤

እንግዲያውስ ጠላትን እንዲህ በሏት፥ "ጠላቴ ሆይ፥ ብወድቅ እነሣለሁና፥በጨለማ ብቀመጥ እግዚአብሔር ብርሃን ይሆን ልኛልና በእኔ ላይ ደስ አይበልሽ።" (ሚክ 7:8)።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 326
መልዕክት (message) 326
ስእለት ለማን ነው?

ስእለት መሳል መልካም ነገር ነው። የምንሳለውም፥ መፈጸም ለሚችል አምላክ ብቻ ነው። ፍጡራን፥ ፍጡር ናቸውና ስእለት የመቀበልም ሆነ የመፈጸም አቅም የላቸውም። ለዚህም ነው ያዕቆብ እንዲህ ብሎ ስእለት የተሳለው "እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን፥ በምሄድባትም በዚች መንገድ ቢጠብቀኝ፥ የምበላውንም እንጀራ የምለብሰውንም ልብስ ቢሰጠኝ፥ ወደ አባቴ ቤትም በጤና ብመለስ፥ እግዚአብሔር አምላኬ ይሆንልኛል፤ ...ከሰጠኸኝም ሁሉ ለአንተ ከአሥር እጅ አንዱን እሰጥሃለሁ" (ዘፍ 28፡20-22)

ስለ ስዕለት መጽሐፍ በብዙ ክፍሎች ላይ ያመለከተ ቢሆንም ባስጠነቀቀበት ክፍል፥ "ለአምላክህ ለእግዚአብሔር፥ ስእለት በተሳልህ ጊዜ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ፈጽሞ ይሻዋልና፥ ኃጢአትም ይሆንብሃልና መክፈሉን አታዘገይ።" ይላል። (ዘዳ 23:21)

እንግዲህ ከሌሎች አጉል ልምምዶች ወጥተን ስእለት መሳል እንለማመድ፥ የተሳልነው በሆነ ጊዜም ለመክፈል አንዘግይ። ጌታ በነገር ሁሉ ማስተዋልን ይስጠን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 327
መልዕክት (message) 327
ምህረት፥ ትልቅ ባለጠግነት!

ምህረት ትልቅ ሃብት ነው። አንዱ የእግዚአብሔር ባለጠግነት ምህረት ነው፥ “እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ስለ ሆነ፥” እንደሚል መጽሐፍ። (ኤፌ 2:4)

ምህረት ከመስዋዕት ይልቅ ይመረጣል፤ መጽሐፍ “ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም” ይላልና (ማቴ 12:7)። ከዚህም በላይ መጽሐፍ “ምሕረትህ ከሕይወት ይሻላልና” ይላል (መዝ 63:3)። ከዚህም እልፍ ባለ መጽሐፍ “ምሕረትን ለማያደርግ ምሕረት የሌለበት ፍርድ ይሆናልና፤ ምሕረትም በፍርድ ላይ ይመካል።” ይላል (ዕቆ 2:13)።

ምህረት ማግኘት፥ እውነተኛ ባለጠግነት እንደሆነ ከያዕቆብ ምስክርነት ማየት ይቻላል”ለባሪያህ ከሠራኸው ከምሕረትህ እና ከእውነትህም ሁሉ ትንሽ ስንኳ የማይገባኝ ነኝ። በትሬን ብቻ ይዤ ይህን ዮርዳኖስን ተሻግሬ ነበርና፥አሁን ግን የሁለት ክፍል ሠራዊት ሆንሁ።” ይላል (ዘፍ 32:10)።

የእግዚአብሔር ባለጠግነት መገለጫውን፣ እርሱ የወደደውን ከመስዋዕት፥ከሕይወትና ከፍርድ ከፍ ያለውን፥ ያን ምህረቱን ለማግኘት አጥብቀን እንለምን፣ እንፈልግ፣ እናንኳኳም!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 328
መልዕክት (message) 328
ስልጣን፣ መለያ፣ ባህሪ ነው፥ ስም

ስም ስልጣን ነው፣ ስም መለያ ነው፣ ስም ባህሪ ነው። ከዚህ አንጻር ስም ተጽእኖው ከፍተኛ ነው። ስም ከጠፋ (ከተበላሸ) የሚጠፋው (የሚበላሸው) ስልጣን ነው፣ መለያ ነው፣ ባህሪ ነው።

ስም በቀላሉ አይገኝም፥ በዋጋ እንጂ። መጽሐፍ ስለ ያዕቆብ ስም ለውጥ ሲናገር"ስምህ ማን ነው? እርሱም።'ያዕቆብ ነኝ' አለው።አለውም፥ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል። ከእግዚአብሔርም ከሰው ጋር ታግለ
ህ አሸንፈሃልና።" ይላል (ዘፍ 32፡27-28)።

የእግዚአብሔር ልጅ ራሱ፥ ስም ያገኘው፥ ሞትን ድል አድርጎ ነው። "የባሪያን መልክ ይዞ፥ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ።በዚህ ምክንያት ደግሞ፥ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ
፥መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው።" (ፊልጵ 2፡7-11)

ስሙን ያጣ አካል፥ ማንነቱን (መገለጫውን) አጥቷል። ስምን ከሚያሳጣ ተግባር ልንሸሽ ይገባል። ለስም ክብር ይኑረን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie



PART 329
መልዕክት (message) 329
ህልም የሌለው፥ ህልሙ ማሳደድ ነው

መጽሐፍ ሲናገር “ያዕቆብን ወደድሁ ኤሳውን...ጠላሁ”ይላል (ሮሜ 9:13)።”ለምን?” ማለት አይቻልም።እርሱ የሚምረውን ይምራል፥ ለሚራራለትም ይራራለታል። እንግዲህ፥ ምሕረት፥ ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም፥ ከሚምር ከእግዚአብሔር ዘንድ ነውና (ሮሜ 9፡15-16)።

ከዚህ ጋር ተያይዞ፥እግዚአብሔር ለተለየ አጀንዳ ሲለይህ ደስ የማይላቸው ሰዎች ወይም የማህበረሰብ ክፍሎች በድንገት ይፈጠራሉ።በተለይም ደግሞ ወንድሞች(ወገኖች) የተባሉት ሲሆኑ ጉዳዩ ያስገርማል።በዚያ ላይ ህልም(ራዕይ) ሲሰጥህ ደግሞ ተቃውሞውና ማሳደዱ የባሰ ይቀጣጠላል።

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ዮሴፍን መጽሐፍ “ወንድሞቹም አባታቸው ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ እንዲወደው ባዩ ጊዜ ጠሉት፥ በሰላም ይናገሩትም ዘንድ አልቻሉም።ዮሴፍ ሕልምን አለመ፥ ለወንድሞቹም ነገራቸው፤ እነርሱም እንደ ገና በብዙ ጠሉት” ይላል (ዘፍ 37፡4-5)።

በዘመናት መሃል ለምልክት ብቅ የሚሉና የተለየ ነገር ያላቸው ሰዎች ሲገኙ ማሳደዱ ይበቃል። ህልማቸውን (ራዕያቸውን) ይስሩበት። አሳዳጅ (ተቃዋሚ) ከሆንክ፥ ህልም የለህም!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 330
መልዕክት (message) 330
በጎ ተጽእኖ መፍጠር፥ ክብር

ከፀሐይ በታች ሁሉ ከንቱ ነው ያለው፥የሰባኪው የዳዊት ልጅ “ለጻድቃን የሚደረገው ሥራ፥ የሚደርስላቸው ኀጥኣን አሉ።” ይላል (መክ 8:14)።እንደ ጻድቅ፥ለኀጥእ የሚተርፍ ሕይወት መገንባት ታላቅነት ነው።እንደ ጻድቅ፥ኀጥእ “እኔም በኖርኩት” የሚለው ዓይነት ሕይወት መምራት ምንኛ ታላቅነት ነው?

መጽሐፍ በሌላ ስፍራ ደግሞ “እግዚአብሔር የግብፃዊውን ቤት ስለ ዮሴፍ ባረከው፤የእግዚአብሔር በረከት በውጪም በግቢም ባለው ሁሉ ላይ ሆነ።” ይላል (ዘፍ 39:5)

መኖር ማለት፥ በጎ ተጽእኖ መፍጠር ማለት እንደሆነ፥ ከላይ በተነሱ ክፍሎች ማየት ይቻላል። ለመኖር ለመኖር ድንጋይም ይኖራል። ሰውን የተለየ የሚያደርገው በማህበረሰብ ላይ በጎ ተጽእኖ ፈጥሮ ሲያልፍ ነው። ኡኩይ የሆነ ተጽእኖ መፍጠር ግን ክብር አይደለም። ሰው ሆኖ የተፈጠረ ሰው፥ እንደ ሰው፥ በሚኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ በጎ ተጽእኖ ፈጥሮ ማለፍን እንደ መብት ሳይሆን የሕይወት ግዴታው ሊያደርግ ይገባል። መረሳት የሌለበት ነገር ፥“ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞቷል” (1 ቆሮ 15፡3)።የሞተልን እሱ፥ የጸደቅን እኛ ነን። ሰው ገድሎ ለመጽደቅ መሞከር እጅግ ነውር የሆነ የዘመናችን ተሞክሮ ነውና፥ አያዛልቅም። የጌታ ምህረት ይብዛልን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 331
መልዕክት (message) 331
ሕልም እና ትርጉም

ብዙ ሰው ሕልም ያያል።ስለ ራሱ፣ ስለ ሌላ ሰው፣ ስለ ተቋም ፣ ስለ አገር፣ስለ ወዘተ።ሕልም ደግሞ የሚተረጎም ነገር ነው። ሁሉ ያየውን ሕልም በራሱ የመተርጎም አቅም ቢገነባ ባረፍን ነበር ነገር ግን አልሆነም። ሕልም በማየቱ ብቻ፥ የሚመጻደቅ በዛ። ሕልም ማየት ጥሩ ነው፥ መተርጎም ግን ቁልፉ ጉዳይ። "ምነው?" እንዳትሉኝ።ሕልም አይተው ደግሞም ጠፍቶባቸው አፋልጉኝ ከዚያም ተርጉሙልኝ ባዮች የትዬለሌ ናቸውና።

መጽሐፍ በወህኒ ቤት ስለ ነበሩ ሁለት ባለስልጣናት ሲናገር " 'ሕልምን አልመን፥ የሚተረጉምልን አጣን' አሉት። ዮሴፍም አላቸው። ሕልምን የሚተረጉም እግዚአብሔር የሰጠው አይ ደለምን? እስቲ ንገሩኝ። አላቸው" ይላል። (ዘፍ 40:8)

በዚህ ዘመን፥ እግዚአብሔር የሰጣቸው ሕልም ተርጓሚዎች አያስፈልጉንም ትላላችሁ? የሚታየውን ሕልም ሁሉ እንደ ጌታ እግዚአብሔር ቃል የሚተረጉሙ ሰዎችን ጌታ ያብዛልን።ነገር ግን ሕልም በሥራ ብዛት እንደሚታይ ልብ ይሏል(መክ 5:3)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 332
መልዕክት (message) 332
ተደጋጋሚ ሕልም (መገለጥ)

ድንገት የሚሆን ምንም ነገር የለም፤ሁሉ ታቅዶ ነው፣በዓላማ (purpose) ነው ወይም በመርህ ነው። የየትኛውም እቅድ፣ ዓላማም ሆነ መርህ የመጀመሪያ ደረጃ መገለጥ ነው። ከመገለጥ መንገዶች አንዱ ሕልም ነው። ሕልም በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ከተደጋገመ፥ እንዲፈጸም ወይም እንዲደረግ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቆርጧል ማለት ነው።

መጽሐፍ ሲናገር “ሕልሙም ለፈርዖን ደጋግሞ መታየቱ ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቈረጠ ስለ ሆነ ነው፥ እግዚአብሔር ፈጥኖ ያደርገዋል።” ይላል (ዘፍ 41:32)

ዛሬ እየሆነ ባለው ነገር ብዙ መጨነቅ እና መወዛገቡ ብዙም ውሃ አያነሳም። አርፍደናልና። ተደጋጋሚ ሕልሞች ሲታዩ የት ነበርን? እግዚአብሔር በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሲገልጥ (ሲናገር) የት ነበርን?ምንም የሚቀየር ነገር የለም፥የሁሉ ጌታ ሊያደርግ የወደደውን ሁሉ ፈጥኖ ያደርገዋል።የሚጠበቅብን ነገር ቢኖር አንድ ነው፥እርሱም አሁንም በተደጋጋሚ በሚታዩ ሕልሞች ዙሪያ አበክሮ መጸለይ። አይመስላችሁም?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

Aynalem Mersie



PART 333
መልዕክት (message) 333
ምናሴና ኤፍሬም ይሆናል!

ብዙ ነገሮች ተደርገውብን ግን ረስተናል፣ ብዙ ነገሮች ተፈጽመውብን ግን ረስተናል።"ሊረሳ አይችልም" የተባለ ነገር ሆኖብን ግን ረስተናል፣ ተመልሶ ለማሰብ የማይቻል ነገር አድርገውንም ረስተናል። ያስረሳን እግዚአብሔር ካልሆነ ማን ሊሆን ይችላል?

መጽሐፍ ሲናገር "ዮሴፍም፥ የበኵር ልጁን ስም ምናሴ ብሎ ጠራው፥እንዲህ ሲል።እግዚአብሔር መከራዬን ሁሉ አስረሳኝ፤" (ዘፍ 41፡51)

ብዙ ሰው እየሆነ ያለውን "እንዴት ረሳዋለሁ?" ሊል ይችላል። ግን እንረሳዋለን፥የዬሴፍ አምላክ የእኛም አምላክ ነው።እርሱ አልተለወጠም። እርሱ ትላንትና፥ ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው (ዕብ 13፡8)።

መከራችንን መርሳት ብቻ አይደለም፥ በመከራ ውስጥ እናፈራለንም። ዬሴፍ የሁለተኛ ልጁን ስም "ኤፍሬም ብሎ ጠራው እንዲህ ሲል። እግዚአብሔር በመከራዬ አገር አፈራኝ።" (ዘፍ 41፡52)። መከራ ባየንበት አገር እናፈራለን፥ እንበዛለን። ቃሉ የታመነ ነው "እግዚአብሔር ታላቅ ነገርን አደረገላቸው ተባለ" የሚለውን ቃል አካል እናያለን (መዝ 126:2)። ስሙ ይክበር!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 334
መልዕክት (message) 334
የወጋ ቢረሳ፥ የተወጋ ...!

ሕልም(ራዕይ) የሌለው ምንም ነገር አድርጎ ሊረሳ ይችላል። ባለ ሕልም (ባለ ራዕይ) ግን እንዴት አድርጎ ሊረሳ ይችላል? አንድ ቃል ትዝ አለኝ "ሴት ከማኅፀንዋ ለተወለደ ልጅ እስከማ
ትራራ ድረስ ሕፃንዋን ትረሳ ዘንድ ትችላለችን? አዎን፥ እርስዋ ትረሳ ይሆናል፥ እኔ ግን አልረሳሽም" (ኢሳ 49፡15)። የሚረሳ አካል ሊኖር ይችላል፥መርሳት ግን የማይችል(መርሳት ፍጹም ያልተፈቀደለት)፥ባለ ጉዳዩ አለ። መልዕክቱን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ሲባልም ነው በተለመደ ተረትና ምሳሌ ርዕስነት መጀመር የተፈለገው።

የገዛ ወንድሞቹ በሀያ ብር የሸጡት ዮሴፍ ለዚህ ርዕሰጉዳይ ጥሩ ማሳያ ነው "ዮሴፍም በምድር ላይ ገዥ ነበረ፥ እርሱም ለምድር ሕዝብ ሁሉ እህል ይሸጥ ነበር፤ የዮሴፍ ወንድሞች በመጡ ጊዜ በምድር ላይ በግምባራቸው ሰገዱለት። ዮሴፍ ወንድሞቹን አይቶ አወቃቸው፤ተለወጠባቸውም፥ክፉ ቃልንም ተናገራቸው።'እናንተ ከወዴት መጣችሁ?' አላቸው። እነርሱም
'ከከነዓን ምድር እህል ልንሸምት የመጣን ነን' አሉት።ዮሴፍም ወንድሞቹን አወቃቸው፥እነርሱ ግን አላወቁትም"ይላል ታሪኩ (ዘፍ 42፡6-8)።

መጽሐፍ ሲናገር "ለወንድሞቼ እንደ ሌላ፥ ለእናቴ ልጆችም እንደ እንግዳ ሆንሁባቸው፥" ይላል (መዝ 69:8)። በጽድቅ የሚሄድ ሁሉ እድል ፈንታው እንዲህ ነው፤ አየን፥ ደስም አለን!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 335
መልዕክት (message) 335
የተላከ፥ ሕልም (ራዕይ) ያለው

መጽሐፍ ሲናገር “የጌታንም ድምፅ፥ ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል? ሲል ሰማሁ። እኔም፥ እነሆኝ፥ እኔን ላከኝ አልሁ” ይላል(ኢሳ 6:8)።በሌላ ስፍራ ደግሞ “ካልተላኩ እንዴት ይሰ ብካሉ?” ይላል (ሮሜ 10:15)።

የተላከ(መልዕክተኛ)የግድ ያስፈልጋል።መልዕክት የተቀበለና የተላከ በሌለበት እንዴት ነው የሚሆነው? እንደ መልዕክተኛ ኢየሱስ ባይመጣ ምን ነበር የሚሆነው?መልዕክት በሌለበት ከየት ወዴት ይኬዳል? የቱ ጋ ጀምረን፥ የቱ ጋ ነው የምንጨር
ሰው? መጽሐፍ “እነሆ፥ መልእክተኛዬን እልካለሁ” ይላል (ሚ ልክ 3:1)። በሌላ ስፍራ ደግሞ፥ ራሱ የተላከው መልዕክተኛ ሌሎች መልዕክተኞችን ይልካል “አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ” ይላል (ዮሐ 20:21)።

“ሁላችንም አንድ ነን”(we are equal) በሚል መንፈስ መሪ እንዲሆን የተላከን ሰው (መልዕክተኛ)፥ መቀበል አለመፈለግ መለኮት ያስቀመጠውን መርህ አያስለውጥም። ዬሴፍ አለ፥ “እግዚአብሔርም በምድር ላይ፥ ቅሬታን አስቀርላችሁ ዘንድ፥ በታላቅ መድኃኒትም አድናችሁ ዘንድ ከእናንተ በፊት ላከኝ።”
(ዘፍ 45:7)።ዬሴፍ ከወንድሞቹ መካከል ሕልም(መልዕክት) አለው። የጋራ ሕልም (መልዕክት) የለም። ጌታ እንደ ዬሴፍ ሕልም (መልዕክት) ያለው ወንድም (መሪ) ይስጠን። እኛም መሪ (መልዕክትኛ) እንቀበል ዘንድ ጌታ ልብ ይስጠን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።
በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 336
መልዕክት (message) 336
አሞሮች ከበዙ፥ በድን አለ

ያዕቆብ የበኩር ልጁን ሮቤልን "እንደ ውኃ የምትዋልል ነህ፤ አለቅነት ለአንተ አይሁን፤ ወደ አባትህ መኝታ ወጥተሃልና፤ አረከስኸውም፤ ወደ አልጋዬም ወጣ።" ይለዋል። (ዘፍ 49፡3-4)።

የበኵር ልጅ ምንም እንኳ የኃይል፥ የጕብዝና መጀመሪያ እና የክብር አለቃና የኃይል አለቃ ነው ቢባልም አቋም የሌለው ወላዋይ ከሆነና ለአባቱ ክብር የሌለው፥ እንደ ሮቤልም አባቱ መኝታ (ማረፊያ) ላይ ዘሎ ፊጥ የሚል ከሆነ፥ አለቅነት ለእሱ አይገባም፥ ለኃላፊነትም (ለመሪነት) ብቁ አይደለም።

አቋም የሌለው(እሚዋልል) ሰው አለቅነት ይከብደዋል።በዚያ ላይ ለአባት የተገባውን ክብር ሲንቅ ወይም የአባትነትን ወግ ሲጥስ መጨረሻው ምን ሊሆን እንዲችል መገመት ይቻላል። መጽሐፍ ሲናገር "በአባትዋ የምታላግጥን ... ዓይን የሸለቆ ቍራዎች ይጐጠጕጡአታል፥ አሞራዎችም ይበሉአታል።" ይላል (ምሳሌ 30:17)። አባት መቼም መሪ ነው።

ከመንፈሳዊ ወግና ስርዓት፥ በራስ አስተሳሰብና አመለካከት አፈንግጦ መውጣት አሞራነት ወይም የአሞራ ሲሳይ መሆን ነው። "በድን ወዳለበት በዚያ አሞራዎች ይሰበሰባሉ።"(ማቴ 24:28)። የደረስንበት ዘመን ጥሩ ማሳያ ነው። አሞራ የበዛ አይመስላችሁም? ጌታ ሆይ ምህረትህን አብዛልን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 337
መልዕክት (message) 337
NO MORE !!!

ያዕቆብም ከልጆቹ መካከል፥ ጦር ስለሚሰብቁ ሁለት ልጆቹ ስለ ስምዖን እና ሌዊ ሲናገር “ሰይፎቻቸው የዓመፃ መሣሪያ ናቸው። በምክራቸው፥ ነፍሴ አትግባ፤ ከጉባኤአቸውም ጋር፥ ክብሬ፥ አትተባበር፤ በቍጣቸው ሰውን ገድለዋልና፥በገዛ ፈቃዳቸውም በሬን አስነክሰዋልና። ቍጣቸው ርጉም ይሁን፥ ጽኑ ነበርና፤ ኵርፍታቸውም፥ ብርቱ ነበርና፤... እከፋፍላቸዋለሁ፥ በእስራኤልም እበታትናቸዋለሁ።” ይላል (ዘፍ 49፡5-7)።

ኢየሱስ ሲናገር “ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና” (ማቴ 26:52)። በሌላ ስፍራ መጽሐፍ “በሰይፍ የሚገድል ማንም ቢኖር ራሱ በሰይፍ እንዲገደል ይገባዋል።” ይላል (ራዕ 13:10)

ስምዖንና ሌዊ ምን ዓይነት ልጆች ናቸው?ያዕቆብን የሚያህል እግዚአብሔር የጠራው አባት (መሪ) ባለበት አገር ሰይፎችን ለዓመፃ ማንሳት ምን ይሉታል?

“አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፤” እንደተባለ፥ እንደ ስምዖን እና ሌዊ ጦር እየሰበቁ፣ ጦርነት እየጎሰሙ፣ ጦርነት እያስፋፉ፣ ወዘተ መቀጠል አይቻልም። (ገላ 6:7)። NO MORE!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 338
መልዕክት (message) 338
የይሁዳ ነገድ መሆን ይፈልጋሉ?

በጸና የትንቢት ቃል ወደ ገዥነትና ወደ ስልጣን መምጣት እና በኃይል ወይም በጉልበት ወይም ደግሞ በድግምት ገዥነት (ስልጣንን መቆናጠጥ) የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው።

መጽሐፍ ጥሩ ምሳሌ የሚሆንን አንድ ነገድ ያነሳል፥የይሁዳን ነገድ “ወንድሞችህ አንተን ያመሰግኑሃል፤እጅህ በጠላቶችህ ደንደስ ላይ ነው፤ የአባትህ ልጆች በፊትህ ይሰግዳሉ፤ ይሁዳ የአንበሳ ደቦል ነው። ... ከአደን ወጣ፤ እንደ አንበሳ አሸመቀ፥ እንደ ሴት አንበሳም አደባ። ያስነሣውስ ዘንድ፥ ማን ይችላል? በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፥ የገዥም ዘንግ ከእግ
ሮቹ መካከል፥ገዥ የሆነው እስኪመጣ ድረስ፤ የአሕዛብ መታ
ዘዝም ለእርሱ ይሆናል።ውርንጫውን በወይን ግንድ ያስራል፥ የአህያይቱንም ግልገል በወይን አረግ፤ልብሱን በወይን ያጥባ
ል፥መጎናጸፊያውንም በወይን ደም።ዓይኑም ከወይን ይቀላል
፤ጥርሱም ከወተት ነጭ ይሆናል።” (ዘፍ 49፡8-12)

ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ፥ ጌታ ኢየሱስ የወጣው ከዚህ ነገድ ነው (ራዕ 5፡5)። እርሱ ሰላማችን ነው፤ ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትን የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ፤ ጥልን በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታረቀ። (ኤፌ2፡14-16)

የይሁዳ ነገድ ለመሆን መስፈርቱ፥ ኢየሱስን መቀበል ነው!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።
በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART PART 339
መልዕክት (message) 339
ይሳኮር፥ የኢትዮጵያ ገበሬዎች

ወቅታዊ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ሰማንያ ከመቶ የሚሆን ህዝባችን የሚተዳደረው በግብርና ነው። ግብርና ጥንካሬን ይጠይቃል።ግብርና ከእንሰሳት እርባታ ጋር የተቆራኘም ነው። ግብርና ልማትና እረፍት ነው። ግብርና ሌላውን ለመርዳት (እንጀራ ለማብላት ሲባል) ዝቅ ማለትንና በጽናት መሥራትን ይጠይቃል፤ ገበሬነት ክቡር ነው።

ከያዕቆብ ልጆች አንዱ ገበሬ ነበር፥ “ይሳኮር አጥንተ ብርቱ አህያ ነው፥ በበጎች ጕረኖም መካከል ያርፋል። ዕረፍትም መልካም መሆንዋን አየ፥ ምድሪቱም የለማች መሆንዋን፤ ትከሻውን ለመሸከም ዝቅ አደረገ፥ በሥራም ገበሬ ሆነ።”(ዘፍ 49፡14-15)

እናንተዬ፥ ይሳኮር እና የኢትዮጵያ ገብሬዎች የሚገናኙበት ነገር ይኖር ይሆን? መቼም “ይሳኮር ኢትዮጵያዊ ነው” የሚል አዲስ የሃሳብ ትውፊት በድፍረት ባቀርብ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ጥሩ ላይሆን ይችላል ብዬ ስላሰብኩ፥ ትቼዋለሁ።

ሌላው የይሳኮርን ነገድ ለየት የሚያደርግ ታሪክ “እስራኤልም የሚገባውን ያደርግ ዘንድ ዘመኑን የሚያውቁ ጥበበኞች ሰዎ
ች የይሳኮር ልጆች አለቆች ሁለት መቶ ነበሩ፤ ወንድሞቻቸው
ም ሁሉ ይታዘዙአቸው ነበር።” ይላል (1 ዜና 12:32)።

እግዚአብሔር ትውልዳችንን በሁሉም መስክ እንደ ይሳኮርና እንደ ይሳኮር ልጆች በረከት ያድርግልን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 340
መልዕክት (message) 340
ዳን፥ ጨካኝ የዳኞች ወገን

መጽሐፍ “ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ” ይላል (ፊልጵ 2:3)። ዓለም እየተበከለ፥ አገር እየተበላሸ፣ ሰው እየጠፋ፣ መርህ እየተጣሰ የመጣው ግን “ለወገኔ/ለብሔሬ/ለዘሬ” በሚል ፈሊጥ ነው።

ወገንተኝነት/ብሔርተኝነት/ዘረኝነት ለማነጽ ቢሆን ኖሮ፥ምንኛ ከዚህ በላይ በተስፋፋና ሁሉ ቀኝ እጁን በሰጠ፥ ደስም ባለን። ነገር ግን የሴራና ጥፋት ጎዳና መሆኑን፥በኃይል እንድንኖረው ተገደን በራሳችን ላይ ተረጋገጠ። ቅዱስ በተባለው መንፈሳዊ አገልግሎትም ሁሉ ለማነጽ እንዲሆን ቃሉ ያዝዛል “እንግዲህ
፥ ወንድሞች ሆይ፥ ምንድር ነው? ... ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው፥ ትምህርት አለው፥ መግለጥ አለው፥ በልሳን መናገር አለው፥መተርጎም አለው፤ሁሉ ለማነጽ ይሁን”(1ቆሮ14:26) ለዝና ፣ ለሀብት፣ ለመሰልጠን፣ለትችት፣ወዘተ ግን አይደለም።

ከያዕቆብ ልጆች ዳን የተባለው ነገድ የዳኞች ወገን ነው “ዳን በወገኑ ይፈርዳል፥ከእስራኤል ነገድ እንደ አንዱ።ዳን በጐዳና ላይ እንደ እባብ ይሆናል፥ በመንገድም እንደ ቀንዳም እባብ፤ ፈረሱን ከሰኮናው ይነክሳል፥ፈረሰኛም ወደ ኋላው ይወድቃል
(ዘፍ 49፡16-17)። ዳን ሥራው ዳኝነት ነው፣ ፍርድ መስጠት ነው፣ መበየን ነው። ፍርድ ለማንም ነው። ወገኔ/ብሔሬ/ዘሬ የሚባል ነገር የለም።ፍርድ፥ መንከስ ካለበት፥እንደ እባብ ይዞ ይነክስሃል፣ መጣል ካለብህ፥ አንቆ ይጥልሃል፤ባህሪው ነው።

እግዚአብሔር በሁሉም መስክ እንደዳን ጨካኝ የሆኑ፥ማንም ምንም ቢላቸው፥ወንበሩ የሚጠይቀውን እርምጃ ከመውሰድ የማይመለሱ ሰዎች ይስጠን፥ ያብዛልንም!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።
በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 341
መልዕክት (message) 341
እናሸንፋለን !!!!!!!!!!!!!!!!

ማሸነፍ ሁልጊዜም በጽድቅ ሲሆን መሠረቱ የጸና ነው። ጌታ እግዚአብሔር ሁልጊዜም አሸናፊ ነው፥ግን በጽድቅ ነው።እሱ ተሸንፎ አያውቅም፥ አምላክ ስለሆነ ሳይሆን፥ አመጽ በእርሱ ዘንድ ስለሌለ ነው።በዓመፅ ማሸነፍ የለም "ኃጢአት ዓመፅ ነው።" (1ዮሐ 3:4)።

ከያዕቆብ ልጆች አንደኛው፥ልክ እንደ ኢትዮጵያውያን ጥቃትን አይወድም።መጽሐፍ ስለ እርሱ"ጋድን ዘማቾች ይዘምቱበታል ፤እርሱ ግን ተከታትሎ ይዘምትባቸዋል"ይላል (ዘፍ 49:19)። ጋድ አባቱ ያዕቆብ እንዳወጣበት የበረከት ቃል ሲዘመትበት አያታገስም፥ ሽንፈትንም አሜን ብሎ አይቀበልም።

ሌላ አንድ ታሪክ ደግሞ አለ "በፊቱ መውደቅ የጀመርህለት መርዶክዮስ ከአይሁድ ወገን የሆነ እንደ ሆነ በፊቱ ፈጽሞ ትወድቃለህ እንጂ አታሸንፈውም" ይላል መጽሐፍ (አስቴር 6:13)። አይሁድ ሲባል፥ አሁን ባለንበት አዲስ ኪዳን የስጋ ሳይሆን በመንፈስ የሆነ አይሁድነትን ይመለከቷል። (ሮሜ 2:28-29)። በመንፈስ አይሁድ ለመሆን ደግሞ ዳግመኛ ከኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ የግድ ነው። (ዮሐ 3:3-21)። "ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና፤ ዓለምን የሚያሸንፈው እምነታችን ነው።" እንደሚል (1 ዮሐ 5:4)።

እመኑ፥ እናሸንፋለን፣ እናሸንፋለን፣ እናሸንፋለን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 342
መልዕክት (message) 342
የዕለት እንጀራ፥ የዘላለም እንጀራ

ጌታ ኢየሱስ “ሰው” ብሎ “በእግዚአብሔር ቃል ሁሉ እንጂ፥ በእንጀራ ብቻ አይኖርም”ያለው እንደተጠበቀ ሆኖ(ሉቃ 4:4)፤ለሰው ልጅ ከሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነገሮች አንዱ፥ እንጀራ ነው።ያዕቆብ ከልጆቹ መካከል አንዱን ስለ እንጀራ ሲባርከው “አሴር እንጀራው ወፍራም ነው፥ ለነገሥታቱም ደስ የሚያሰኝ መብልን ይሰጣል።” ይላል (ዘፍ 49:20)።

ጌታ ኢየሱስም ጸሎት ባስተማረበት የመጽሐፍ ክፍል “የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፤” ይላል (ማቴ 6:11)።

በሌላ የመጽሐፍ ክፍል ደግሞ “የመላክትን እንጀራ ሰው በላ ስንቅንም እስኪተርፋቸው ላከላቸው።” ይላል (መዝ 78:25)

መጽሐፍ ስለ መጨረሻውና ስለ እውነተኛው እንጀራ ሲያወራ ኢየሱስ ስለ ራሱ የተናገረውን ይጠቅሳል “የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤...ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።” ይላል፤ (ዮሐ 6፡48-51)

የዕለት እንጀራ፥ የዕለት ነው፤ ነገር ግን ዘላለማዊውን እንጀራ እሱም የኢየሱስ ክርስቶስ ስጋና ደም ትካፈሉ ዘንድ ይገባል። “የምንባርከው የበረከት ጽዋ፥ ከክርስቶስ ደም ጋር፥ ኅብረት ያለው አይደለምን? የምንቆርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን?”... የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ ልትጠጡ አትችሉም፤ ከጌታ ማዕድና ከአጋንንት ማዕድ ልትካፈሉ አትችሉም።” (1 ቆሮ 10:16-21)

አንዱን እንምረጥ፤ ኢየሱስን ወይም አጋንንትን። ሌላ የለም!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።
በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 343
መልዕክት (message) 343
ንግግር በጸጋ !

መጽሐፍ “ያማረ ቃል”ብሎ“የማር ወለላ ነው፤ለነፍስ ጣፋጭ ለአጥንትም ጤና ነው።” ይላል (ምሳሌ 16:24)። ክፉ ቃል፣ ርግማን፣ ሟርት፣ስድብ፣ጠብና ክርክር ለምን አስፈለገ? ምን ሆነናል?ሌላው ቀርቶ ቃሉ “ክፉን በክፉ ፈንታ ወይም ስድብን በስድብ ፈንታ አትመልሱ በዚህ ፈንታ ባርኩ እንጂ፥ በረከትን ልትወርሱ ለዚህ ተጠርታችኋልና።”ይል የለም እንዴ? (1 ጴጥ 3:9)

የዕቆብ አንደኛውን ልጁን ሲባርክ “ንፍታሌም የተፈታ ሚዳቋ ነው፤ መልካም ቃልን ይሰጣል።” ይላል (ዘፍ 49:21)።

መልካም ቃል መልካም ነው።ሰው በክፉ ካልተጠቃ በስተቀር የማይገባ ቃል አይናገርም። በክፉ የተጠቃ የትኛውም ሰው፥ መልካም ቃል ለማውጣት ይቸገራል። በተለይ በማህበራዊ ድህረ-ገጽ፥ስድብና ትችትን ዋና ሥራቸው ያደረጉ ሰዎች ቤት ይቁጠራቸው። ክፉ ቃል፣ ርግማን፣ ሟርት፣ ስድብ፣ ጠብ እና ክርክር ነውር ነው። በዚህ ላይ ስለተሰማሩ ሰዎች መጽሐፍ፥ “መጨረሻቸው ጥፋት ነው፥ ሆዳቸው አምላካቸው ነው፥ ክብ
ራቸው በነውራቸው ነው፥ አሳባቸው ምድራዊ ነው።” ይላል። (ፊልጵ 3:19)

“ለእያንዳንዱ እንዴት እንድትመልሱ እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ ሁልጊዜ፥ በጨው እንደ ተቀመመ፥ በጸጋ ይሁን።” እንደሚል፥ ጌታ ፀጋውን ያብዛላችሁ!!! (ቆላስ 4:6)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 344
መልዕክት (message) 344
በምድርም እንበዛለን!

የገዛ ራሱን ሕዝብ የማይጥል አምላክ ነው፥ እግዚአብሔር። መጽሐፍም “እግዚአብሔር ሕዝቡን አይጥላቸውም” ሲል ምስክርነቱን ይሰጣል። (መዝ 95:4)

የእርሱ በሆነውና “ርስቴ”ባለው ሕዝብ ላይ ክፉ ቃል መናገር ኃጢአት ነው።አገልጋዮችን (ሌዋውያንን)ሲሆን ደግሞ ጉዳዩ ትንሽ ጠና ይላል። በሌዊ ቀልድ የለም “የሚነሣበትን ወገብ ውጋው፥ የሚጠሉትም አይነሡ።” ብሏልና (ዘዳ 33፡11)

ከዚህ ቀደም በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የተነሳ አንድ ወገን ምን እንዳጋጠመው ታሪክ ይነግረናል “የፈርዖን ፈረሶች ከሰረገሎቹ ከፈረሰኞቹም ጋር ወደ ባሕር ገቡ። እግዚአብሔርም የባሕሩን ውኆች መለሰባቸው...ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ጣለ።” ይለናል (ዘጸ 15:19-21)።

ከዚህም በላይ መጽሐፍ በእግዚአብሔር ሕዝብ ስለሚደርስ ጫና እና ውጤቱ ሲናገር“እንዳስጨነቁአቸው መጠን እንዲሁ በዙ፥ እጅግም ጸኑ፤” ይላል (ዘጸ 1:12)።

እናንተን የሚነካ የዓይኑን ብሌን የሚነካ ነውና፥ፍጹም አትፍሩ ትበዛላችሁ፣ እጅግም ትጸናላችሁ!!! (ዘካ 2:8)።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 345
መልዕክት (message) 345
ጌታ ሆይ ተገለጥ፥ ፍረድም!

እግዚአብሔር አምላክ የሕዝብን መከራ፣ የሕዝብን ስቃይ እና ሰቆቃ፣የሕዝብን ጩኸት የሚያይ ከዚያም የሚፈርድ አምላክ ነው።ሕዝብ ሁል ጊዜም ቢሆን መከራ፣ስቃይ፣ሰቆቃ፣ጩኸት የሚደርስበት በአስገባሪዎች ነው።አስገባሪ ስራው ማስገበር ስለሆነ፥ለዘላለም እያስገበረ የመኖር ሕልም ስላለው ለውጥ ይመጣል ብሎ ለመገመት ያዳግተዋል። የአስገባሪ ውድቀት የሚጀምረውም “ለውጥ አለ”ብሎ ማሰብ አለመቻሉ ጋ ነው። ስለዚህ አስገባሪ በኃይል ብቻ እያስገበረ ይኖራል።ከፍ ካለው በላይ ግን ከፍ ያለ ይመለከታል (መክ 5፡8)።

ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆን አንድ ታሪክ፥መጽሐፍ እንድ ስፍራ ላይ ያነሳል “እግዚአብሔርም አለ፥ በግብፅ ያለውን የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ፥ከአስገባሪዎቻቸውም የተነሣ ጩኸታ ቸውን ሰማሁ፤ስቃያቸውንም አውቄአለሁ፤..አወጣቸው ዘንድ ወረድሁ” ይላል (ዘጸ 3:7-8)።

ተስፋ መቁረጥ አያስፈልግም፥”ለሁሉ ዘመን አለው፥ ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ፥ ጊዜ አለው።” (መክ 3:1)። ሁሉን የሚችል አምላክ ይወርዳል(ይገለጣል)፥ ይፈርዳልም። ፍርድ ለሁሉ ነው፤ለአስገባሪ፣ለአጨብጫቢ፣ለአራጋቢ፣ለአለብላቢ ፣ለአጃቢ፣ ወዘተ። የሚያመልጥ የለም። ምህረቱ ያግኘን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 346
መልዕክት (message) 346
ዘላለማዊ እንጀራ ተገኘ !

መጽሐፍ የፋሲካን ሥርዓትና አፈጻጸም ሲናገር “ወገባችሁን ታጥቃችሁ፥ጫማችሁን በእግራችሁ፥በትራችሁንም በእጃችሁ አድርጋችሁ እንዲህ ብሉት ፈጥናችሁም ትበሉታላችሁ፤እርሱ የእግዚአብሔር ፋሲካ ነው።” ይላል (ዘጸ 12:11)።

የፋሲካ ወግና ሥርዓት ይሄ ብቻ አይደለም፥ ትውልድ ተሻጋሪ ነው። “ለልጅ ልጃችሁ ሥርዓት ሆኖ ለዘላለም ታደርጉታላችሁ።” ይለናል መጽሐፍ (ዘጸ 12:14)። አጀማመሩ

ፋሲካ አጀማመሩ ነውር የሌለበት፥ የአንድ ዓመት ተባት የሆነ ጠቦትን ከበጎች ወይም ከፍየሎች በመውሰድ”የእስራኤልም ማኅበር ጉባኤ ሁሉ ሲመሽ ይረዱት”በሚል ትዕዛዝ ነበር(ዘጸ 12:5-11)። በእሳት የተጠበሰውን፣ ሥጋውን እና ቂጣውን፣ እንጀራውን፣ከመራራ ቅጠል ጋር በዚያች ሌሊት ይበሉ ነበር። (ዘጸ 12:8)

ፋሲካ አሁን የደረሰበትን ደረጃና ክብር መጽሐፍ “ፋሲካችን” ይልና “ክርስቶስ ታርዶአልና፤”ይላል (1 ቆሮ 5:7)። እንግዲህ እንድንበላው ራሱን አሳልፎ የሰጠን ከሰማይ የወረደ እንጀራ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።እርሱን የተቀበለ ለዘላለም አይራብም (ዮሐ 6:48-58)።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 347
መልዕክት (message) 347
እግዚአብሔር ተዋጊ ነው!

ዓለም ወደ መጨረሻው ሰዓት ለመምጣት እየዳኸች መሆኗን የሚጠቁሙ የምጥ መጀመሪያ ምልክቶች መታየት ከጀመሩ ውሎ አድሯል። ከእነዚህ ምልክቶች አንዱ እና በብዙ አገሮች የተስተዋለው፥ በእኛም አገር በቅርቡ ይፋ የወጣው ግፍ እና በደልን "የኔ ወገን አይደለም" ተብሎ በሚታሰብ ማህበረሰብ ላይ መፈጸም ነው። እንዲህ ያለውን ሰይጣናዊ አስተሳሰብ፥ ሰው ይዋጋ እና ያጠፋ ዘንድ አቅምም ሆነ ብቃት ስለሌለው ሙሉ ለሙሉ ኃላፊነቱን የሚወስድ፥ውጊያውንም የሚዋጋው ራሱ እግዚአብሔር ነው።

430 ዓመት አብረው ኖረው በኋላ በግብጻውያን ስለተፈጸመ በደልና ግፍ መለየት ግድ የሆነባቸው የእስራኤላውያን ታሪክ ጥሩ ማሳያ ነው፥ "አትፍሩ፥ ዛሬ የምታዩአቸውን ግብፃውያንን ለዘላለም አታዩአቸውምና ቁሙ፥ ዛሬ ለእናንተ የሚያደርጋትን የእግዚአብሔር ማዳን እዩ፤እግዚአብሔር ስለእናንተ ይዋጋል ፥እናንተም ዝም ትላላችሁ"ይላል መጽሐፍ (ዘጸ 14፡13-14)፤ ግብጻውያን በዚያን ጊዜ የሰለጠነ(mechanized) ብርጌድ የነበራቸውና በዓለም ላይ የናኙ ነበሩ።እስራኤላውያን ደግሞ ጡብ ሠራተኞች። ውጊያው ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ነበር ውጤቱ ይነግረናል"ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ጣለ"ይለናል መጽሐፍ (ዘጸ 15:21)።

እግዚአብሔር ተዋጊ ነው፥ ስሙም እግዚአብሔር ነው (ዘጸ 15:3)። ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣሉ ደግሞ፥ "ይደቅቃሉ" ተብሎ ተጽፏል (1ሳሙ 2:10)። እናምናለን፥ እንሻገራለን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 348
መልዕክት (message) 348
በመርህ፥ የሚታደግ አምላክ

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር የረሳን የሚመስልበት ጊዜ አለ። እግዚአብሔር የሚረሳ አምላክ አይደለም፥ ይልቁኑ ያስበናል። በአንድ ወቅት ምድር፥ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በዘነበ ዝናብ በውኃ ጠፍታ ነበር። ውኃውም ከአምስት ወራት ላላነሰ ጊዜ በምድር ላይ አሸንፎ ነበር። ኖኅ እና ቤተሰቡ ለግማሽ ዓመት በተዘጋ መርከብ ውስጥ ነበሩ። እውን እግዚአብሔር፥ ሰውን (ሕዝብን) ይረሳልን?

መጽሐፍ "እግዚአብሔርም ኖኅን፥ በመርከብም ከእርሱ ጋር የነበረውን አራዊቱን ሁሉ፥እንስሳውንም ሁሉ አሰበ፤..በምድር ላይ ነፋስን አሳለፈ፥ውኃውም ጎደለ፤"ይላል (ዘፍ 8:1)። እሱ አስማተኛ አይደለም፥ የመርህ አምላክ ነው፤ ነፋስን አሳለፈ፥ ውኃውም ጎደለ።

በሌላ አንድ ታሪክ ደግሞ መጽሐፍ ሲናገር "ሙሴም በባሕሩ ላይ እጁን ዘረጋ፤እግዚአብሔር ሌሊቱን ሁሉ ጽኑ የምሥራቅ ነፋስ አምጥቶ ባሕሩን አስወገደ፥ባሕሩን አደረቀ፥ ውኃውም ተከፈለ። የእስራኤልም ልጆች በባሕሩ መካከል በየብስ ገቡ፤ ውኃውም በቀኛቸውና በግራቸው እንደ ግድግዳ ሆነላቸው" ይላል (ዘጸ 14፡ 21-22)።

እውነት ነው አገራችን ሌሊት ላይ ነች፥ ግን ችግር የለም አርሱ እንደልማዱ ጽኑ የምስራቅን ነፋስ እያመጣ ነው፤ ያለጥርጥር እንሻገራለን፥ ባሕር ራሱ ወደ ፊት የለም!!! (ራዕ 21:1)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 349
መልዕክት (message) 349
የተደረገውን እንኳ አይተን እንመን

አንዳንድ ሰው ካላየ አያምንም። እንደውም አንዳንድ ሰዎች “ማየት ማመን ነው” የሚለውን አባባል እንደ መጽሐፍ ቃል መርህ አድርገው ይጠቀሙበታል።

እስራኤላውያን፥ በልዩ ልዩ ድንቅና ተዓምራት ብዙ ዘመናትን ያሻገራቸውን አምላክ “አመኑ” የተባለው የሆነ የሚታይ ነገር አይተው ነው “እስራኤልም እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ ያደረጋትን ታላቂቱን እጅ አዩ፤ ሕዝቡም እግዚአብሔርን ፈሩ፤ በእግዚአብሔርም በባሪያውም በሙሴ አመኑ”(ዘጸ 14:31)

ከሐዋርያት መካከል፥ “የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ፥ ጣቴን በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም”ያለ ነበር(ዮሐ 20:25)።ነገር ግን ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው (ዮሐ 20:29)።

በመሠረቱ አይቶ ማመን ምንም ማለት አይደለም ነገር ግን አይቶ መርሳት ነው ትልቁ ህመም።መጽሐፍ ሲናገር“መልካም ሥራውንና ያሳያቸውን ተኣምራቱን ረሱ” ይላል(መዝ 78:11)፤

እንደ እስራኤላውያን ሁሉ በእኛ አገርም በአሁኑ ጊዜ የዚህ በሽታ ሰለባ የሆኑ ሰዎች እዚህና እዚያ (here and there) ይስተዋላሉ። የበሽታው ምልክት ቋንቋቸው ነው፥ “ኢትዮጵያ ፈርሳለች”። ሰው እንዴት በተፈጠረበት አገር ላይ ያሟርታል። አግዚአብሔር ያደረገልንን ነገር ከመቼው ረሳነው? መፍረስ የለም። አፈርሳለሁ ለሚልም መጽሐፍ “ቅጥርን የሚያፈርስን እባብ ትነድፈዋለች።” ይላል (መክ 10:8)። ጌታ ይርዳን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**



PART 350
መልዕክት (message) 350
አባትህንና እናትህን አክብር!

አባትንም ሆነ እናትን መናቅ፣ አለመስማት፣ ማጣጣል፣ ቸል ማለት፣ ማንጓጠጥ፣ ምንም እንደማያውቁ ማሰብ (በወቅቱ አገላለጽ፥ ሙድ መያዝ)፣ ወዘተ ጤናማ አይደለም።

መጽሐፍ ሲናገር"በአባትዋ የምታላግጥ፥የእናትዋንም ትእዛዝ የምትንቅን ዓይን የሸለቆ ቍራዎች ይጐጠጕጡአታል፥ አሞራ ዎችም ይበሉአታል።" ይላል (ምሳሌ 30:17)።

በአንጻሩ ደግሞ "አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም።" ይላል መጽሐፍ (ዘጸ 20:12)።

ሐዋ. ጳውሎስ በድጋሚ "መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር፤ እርስ ዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት"ሲል ይጠቅሳል (ኤፌ 6:2-3)።

ከዚህ በኋላ፥ በቀረን ዘመን መጽሐፍ "ልጄ ሆይ፥ የአባትህን ትእዛዝ ጠብቅ፥የእናትህን ሕግ አትተው፤ሁልጊዜም በልብህ አኑረው፥በአንገትህም እሰረው።ስትሄድም ይመራሃል፤ስትተኛ ይጠብቅሃል፤ ስትነሣ ያነጋግርሃል።" እንደሚል፥ አውርተነው ሳይሆን ቃሉን አድርገነው(ኖረነው)እንለፍ!(ምሳሌ 6፡20-22)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 351
መልዕክት (message) 351
ማን ይናገረን? ነቢይ ወይስ...

መጽሐፍ “የሚሰማኝ ግን በእርጋታ ይቀመጣል፥ ከመከራም ሥጋት ያርፋል።”ይላል (ምሳሌ 1:33)። በእርጋታ የተቀመጠ ማነው? ከመከራ ስጋትስ ያረፈ አለ?ፈልገን ነበር ግን አጣን። እግዚአብሔር በአንድ መንገድ በሌላም ይናገራል፤ ሰው ግን አያስተውለውም። (ኢዮብ 33፡14)

በዚህ ዘመን እንዲሁ ራሱ እግዚአብሔርን ከመስማት“ነቢይ” መስማት የተመረጥበት ባህል ዳብሯል። ጥንት “ማን ጋ ሄጄ ላስጠነቁል?” ነበር ይባል የነበረው። አሁን ደግሞ “ማን ጋ እንሒድና እናስተንብይ?” ሆኖአል ጨዋታው።እግዚአብሔርን ከመስማት ሰውን መስማት ይሻላል?

በአንድ ወቅት እስራኤላውያን ሙሴን “አንተ ተናገረን እኛም እንሰማለን፤ እንዳንሞት ግን እግዚአብሔር አይናገረን” አሉት ይላል መጽሐፍ (ዘጸ 20:19)።

ብሞትም ልሙት፥ እኔስ ራሱ እግዚአብሔር ይናገረኝ፥ ሙሴ አይናገረኝ!!!

እንደውም መጽሐፍ “ከጥንት ጀምሮ” ይልና “እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማት በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፤” ይላል(ዕብ 1፡1-2)።
እንዲህ ከሆነ፥ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን አጠናለሁ ፤ እናንተስ?

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 352
መልዕክት (message) 352
ጆሮዬን ልበሳ ወይስ አልበሳ?

እግዚአብሔር ለሙሴ"በፊታቸው የምታደርገው ሥርዓት ይህ ነው። ዕብራዊ ባሪያ የገዛህ እንደሆነ ስድስት ዓመት ያገልግ ልህ፥ በሰባተኛውም በከንቱ አርነት ይውጣ። ...ባሪያውም ... "አርነት አልወጣም" ብሎ ቢናገር፥ጌታው ወደ ፈራጆች ይው ሰደው፥ወደ ደጁም ወደ መቃኑ አቅርቦ ጆሮውን በወስፌ ይብ ሳው፤ ለዘላለምም ባሪያው ይሁን።" አለው (ዘጸ 21፡1-6)።

የዚያ ዘመን ጆሮን በወስፌ የመበሳት ተምሳሌት፥ የዘላለም ባሪያ (አገልጋይ) ለመሆን ነው። አንድ ሰው ጆሮውን በወስፌ ተበስቷል ማለት፥ ራሱን ለባርነት ለአገልግሎት ቀድሷል እንደ ማለት ነው። ከዚህ አንጻር የእኛ ዘመን አገልግሎት እንዴት ያለ ነው?ስንት ዓመት የደረሱ የጽድቅ አገልጋዮች ተመዝግበዋል ? በአካል ሳይሆን በመንፈስ ጆሮአቸውን ለመበሳት የበቁት አገልጋዮቻችን ስንት ደረሱ?

አሁን አሁን፥ በእንድ ሥፍራ፥ በአገልጋይነት ዓመት መቆየት በራሱ ተዓምራት ነው።ትንሽ የቆየ ከተገኘም "አንተ እዚያ ምን እያደረግህ ነው?" ይባልልኛል።ሰውን እንደ ሰው ቤት ሠራተኛ ከአገልግሎት ማስኮብለል ነውር ቢሆንም ተገልብጦ እንደ ክብር መቆጠር ከጀመረ ውሎ አድሯል፥መጽሐፍ" ክብራቸው በነውራቸው ነው" እንደሚል(ፊልጵ 3:19)። "አገልጋዮቻችን" እባካችሁ ተረጋጉ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 353
መልዕክት (message) 353
ስድብ፥ እርግማን ክፉ በሽታ

የበታችነት (inferiority) ክፉ በሽታ ነው። በበሽታው የተያዘ ሰው የተለያዩ ምልክቶች ይታዩበታል። ከሚታዩት ምልክቶች እጅግ የከፉትና በብዙ ሰዎች ላይ በቀላሉ ከሚታዩት ሁለቱ፥ ስድብ እና እርግማን ናቸው። እነዚህን ተግባራት በፈራጆችና አለቆች ላይ ቀልሎን ስንፈጽም ደግሞ በሽታው ወደ ጋንግሪን ይቀየራል። ጋንግሪን፥ ያለው እድል መቆረጥና መቆረጥ ብቻ ነው።

መጽሐፍ በዚህ ጉዳይ ላይ ሲያሳስብ “ፈራጆችን አትስደብ፥ የሕዝብህንም አለቃ አትርገመው።”ይላል(ዘጸ 22:28)። ጌታ ኢየሱስ ሲናገር “የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤” ይላል።
(ዮሐ 14:23)። ጌታ ኢየሱን የምንወድ ከሆነ ቃሉን መጠበቅ ነዋ። እየተሳደቡና እየተራገሙ ክርስትና የለም።እንዲህ ያለው ሕይወት ክርስትና ሳይሆን ግልሙትና ነው። የሕዝብን አለቃ እየተሳደቡና እየተራገሙ”ክርስትያን ነኝ”ወይም”አገልጋይ ነኝ” ማለት፥መዘበት ነው።”አትሳቱ፤እግዚአብሔር አይዘበትበትም”
ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳል፤” (ገላ 6:7)።

ይህን መልዕክት የምናነብ ወገኖች፥ በሽታው ከምድራችን እንዲወገድ እና በበሽታውም የተያዙ ሰዎች፥ ከበሽታው ነጻ እንዲወጡ ልንጸልይ ይገባል። በዚህ መልዕክት ድንገት ቅር የተሰኘ ካለ እሱም ተመርምሮ ነጻነቱን ቢያረጋግጥ መልካም ይሆናል። ጌታ ሁላችንንም ይማረን፥ ይራራልንም!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie



PART 354
መልዕክት (message) 354
ከትምህርት ያለፈ ነው፥ መስጠት

ስለ መስጠት ሲወራ እሚወራው ስለ እግዚአብሔር ሕይወት ነው። እግዚአብሔር ባለ ጠጋ አምላክ ነው (ሮሜ 10:12)። እኛንም ወደ ብልጥግና ለማምጣት ሲል አንድያ ልጁን ድሀ ይሆን ዘንድ አሳልፎ ሰጥቷል። (2 ቆሮ 8:9)፤ "ግን ለምን?" የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። መልሱ ከመጽሐፍ፡-

"የሰው ስጦታ፥ መንገዱን ታሰፋለታለች፥ በታላላቆችም ፊት ታገባዋለች።"የሚል ነው (ምሳሌ 18:16)።ከጠባብ መንገድ ወጥቶ አማራጭ ወዳለው ሰፊ ስፍራ ለመግባት መፍትሔው መስጠት ነው።ከታላላቆች ተርታ ለመገኘት ብቸኛው መንገድ መስጠት ነው። አለመስጠት ውጤቱ ጥበት እና ከታናናሾች ተርታ መሆን ነው።

ራሱ እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል "ስጦታ ያመጡልኝ ዘንድ ለእስራኤል ልጆች ተናገር፤ ...ወርቅ፥ ብር፥ ናስም፥ ሰማያዊና ሐምራዊ ቀይም ግምጃ፥ጥሩ በፍታም፥የፍየልም ጠጕር፥ቀይ የአውራ በግ ቁርበት፥ የአቆስጣ ቁርበት፥የግራርም እንጨት፥ የመብራት ዘይት፥ለቅብዓት ዘይትና ለጣፋጭ ዕጣን ቅመም፥ መረግድም፥ ለኤፉድና ለደረት ኪስ የሚደረግ ፈርጥ።" ምን የቀረ ነገር አለ ወገኖቼ? (ዘጸ 25፡1-8)

የመስጠት ሕይወት ከእኛ"አሥራት በአዲስ ኪዳን አለ ወይስ የለም?" የሚል ትምህርት አጅግ ያለፈ ነው። ስለዚህ ወገኖቼ አርፈን እንስጥ። ለነገሩ ማንም፥ምንም የለውም። ብንሰጥም ተሰጥቶን ነው።"ለዘሪ ዘርን ለመብላትም እንጀራን በብዙ የሚ
ሰጥ እርሱም የምትዘሩትን ዘር ይሰጣችኋል" እንደተባለ። (2 ቆሮ 9:10)። "የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፤"(ሮሜ 12:8)


መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 355
መልዕክት (message) 355
ስድ ማነው? የኮበለለ?

ብዙ ሰው መሪ እንዲኖረው አይፈልግም።"እኛ ወንድሞች ነን" በሚል ከመጽሐፍ ባፈነገጠ ፈሊጥ፥ ሁሉ ለራሱ መሪ ከሆነ ሰነባብቷል። ለመንፈሳዊ መሪ የማይገዛ ማሕበረሰብ ለአገር መሪ ይገዛል ማለት ዘበት ነው። ወቅታዊው የአገራችን ሁኔታ ለዚህ ጉልህ ማስረጃ ነው። ያለመሪም ለመኖር ማሰብ ትርፉ ድካም ነው። አንዳንድ ሰውም "እኔን የሰው መሪ አይገዛኝም፥ መሪዬ እግዚአብሔር ነው" በሚል ከመጽሐፍ የተቃረነ የግል ፍልስፍና በራሱ ዓለም ይመላለሳል፥ሌሎች እንዲህ እንዲኖሩ ይቀሰቅሳል። ከዚህ አንጻር ትላንት በመሪ ስር የነበሩ፥ ዛሬ ነጻነታቸውን አውጀዋል፥ ስለዚህም ሸፍተዋል።

"ሕዝቡም ሙሴ ከተራራው ሳይወርድ እንደ ዘገየ ባዩ ጊዜ፥ ወደ አሮን ተሰብስበው። ይህ ከግብፅ ምድር ያወጣን ሰው ሙሴ ምን እንደ ሆነ አናውቅምና ተነሥተህ በፊታችን የሚሄዱ አማልክት ሥራልን አሉት።" (ዘጸ 32:1)

ስለ እነዚህ የሙሴን አመራር መታገስ ስለተሳናቸው ሰዎችም መጽሐፍ ሲናገር፥ "በጠላቶቻቸው ፊት እንዲነወሩ፥ አሮን ስድ ለቅቋቸዋልና ሕዝቡ ስድ እንደ ተለቀቁ" ይላል (ዘጸ 32:25)። ስድ ማለት ትርጉሙ፥ የፈለግከውን(የወደድከውን)መናገርም ሆነ ማድረግ መቻል ማለት ነው፤ምክንያቱም መሪ የለማ፣ሃይ ባይ የለማ።

እስረኛ ላደርጋችሁ በማሰብ መልዕክቱን አልጻፍኩም። ጌታ የነጻነት አምላክ ነው። ዛሬም ከመሪ ስር መኮብለል ይቻላል፤ ኩብለላ አዲስ ነገር አይደለም። "ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ወደኋላ ተመለሱ፤ወደፊትም ከእርሱ ጋር አልሄዱም። ኢየሱስ ለአሥራ ሁለቱ፥ 'እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን?' አለ። ስም. ጴጥሮስ 'ጌታ ሆይ ወደ ማን እንሄዳለን?አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፤" አለው ይላል (ዮሐ 6፡66-68)። ከመሪ ጋር የመሆን ምስጢር እርሱ የተቀበለውን የመካፈል ብሎም የማደግ ጉዳይ ነው። ሁሉ ሰው ከዚህ ቀደም የመራው መሪ ውጤት ነው። ከንግግሩ (ከቃሉ) ይታወቃል።

ጌታ ሆይ፥ ኮብላይና ስድ እንዳንሆን ማስተዋልን ስጠን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**



PART 356
መልዕክት (message) 356
መሪ ሰው ነው፥ እንጂ.......

መሪ ስሜታዊ ሊሆን አይገባም። ምንም ተፈጠረ ምንም፥ረጋ ማለት ያስፈልጋል። አንዳንዱ ገንዘብ ወይም ሀብት ሲመጣ አይችልም፥ ምድር ትጠብበዋለች። አንዳንዱ ደግሞ ክብርን መቆጣጠር ያቅተዋል፣ አንዳንዱ ዝና፣ አንዳንዱ እውቅና እና ተከታይ ሲበዛ ይሸመደመዳል፣አንዳንዱ እርከን(standard) ሲቀይር ሰውን ሁሉ በሙሉ ዓይኑ ለማየት ይከብደዋል። ሌላ ደግሞ አለ፥ በሆነ ባልሆነው ግስላ ልሁን ባይ። ኧረ መሪዎች ተረጋጉ!!!

መጽሐፍም ለዚህ ጉዳይ ማሳያ የሚሆን አንድ ታሪክ ያነሳል "እንዲህም ሆነ፤ወደ ሰፈሩ ሲቀርብ ጥጃውንም ዘፈኑንም አየ የሙሴም ቍጣ ተቃጠለ፥ጽላቶቹንም ከእጁ ጥሎ ከተራራው በታች ሰበራቸው።የሠሩትንም ጥጃ ወስዶ በእሳት አቀለጠው ፥ እንደ ትቢያም እስኪሆን ድረስ ፈጨው፥ በውኃውም ላይ በተነው፥ ለእስራኤልም ልጆች አጠጣው።"(ዘጸ 32፡19-20)

ምንነካው ሙሴ?ያ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ምን ሆኖ ነው ቀልጦ የተሠራን ጥጃ ፈጭቶና በውኃ በጥብጦ ሕዝብ እንደ ቅባት እህል የሚያስጎነጨው። ኧረ ቀስ።መሪዎች እናንተ እኮ ሰዎች ናችሁ። በትምክህታችን እግዚአብሔርን አናስቸግረው "በውኑ በገዳይህ ፊት። እኔ አምላክ ነኝ ትላለህን? ነገር ግን በገዳይህ እጅ ሰው ነህ እንጂ አምላክ አይደለህም።" ይላል መጽሐፍ (ሕዝ 28:9)። ኧረ ቀስ፥ ከተቻለ BE HUMBLE!!!

መሪዎች ሆይ፥ እንዳንወድቅ ከፈለግን ስለ ለራሳችን ያለንን የተሳሳተ ግምት እናስተካክል! (ዳን 5፡27)

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie



PART 357
መልዕክት (message) 357
በእውቀት ይፈጸም፣ ኪዳን

ነገ፥ ለውድቀት ምክንያት ሊሆኑ ከሚችሉ ሰዎች ጋር ኪዳን መግባት ትልቅ ስህተት ነው።የውድቀት ፍቺው ምንም ሊሆን ይችላል፥ ውድቀት-ውድቀት ነው።

መጽሐፍም ሲመክር “በመካከልህ ወጥመድ እንዳይሆኑብህ ፣ አንተ በምትሄድባት ምድር፥ ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ቃል ኪዳን እንዳታደርግ ተጠንቀቅ፤” ይላል (ዘጸ 34:12)።

እማንዘልቅበት ጉዳይ ውስጥ ለምን እንገባለን? ምን ሲደረግ ኪዳንስ እንፈጽማለን?አልተጠራንበት ስፍራ ለምን እንገባለን? ለምንስ ኪዳን እንፈጽማለን?መጨረሻችን አልሆነ ፕሮግራም ውስጥ ለምን የተወሰነ ዓመት እንቆያለን? ለምንስ ቃል ኪዳን እንፈጽማለን? ትርፉ ወጥመድ ነው። ለውድቀታችን ብሎም ከጥሪያችን ለመዘግየታችን ማንም ተጠያቂ አይደለም፥ እኛ ራሳችን እንጂ። ጣታችንን በእከሌ (በእነከሌ) ላይ አንቀስር።

መጽሐፍ በሌላ ስፈራ “ከማያምኑ ጋር፥ በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር፥ ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?” ይላል (2 ቆሮ 6:14)።

እንግዲህ፥ከዚህ ቀደም ከተጓዝነው መንገድ እንማር፤ ደግሞ እንወቅ። እንኳን ከባዕድ ጋር አይደለም፥ እግዚአብሔር ራሱ ጽድቁን ያሳይ ዘንድ፥ በኪዳን ወገን ያደረገን በእውቀት ነው። “እንወቅ፤ እናውቀውም ዘንድ እግዚአብሔርን እንከተል” ይል የለ መጽሐፉ (ሆሴ 6:3)።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 358
መልዕክት (message) 358
ጾምና ጸሎት፥ with clear motive

በዚህ ዘመን እንደ ቀድሞው ዘመን ሁሉ ጾምና ጸሎት መያዝ እየተለመደ መጥቷል። “አገልጋይ ነኝ” የሚሉ ሰዎች “የአርባ ቀን ጀምሬአለሁ”፣ “የአንድ ወር ልጨርስ ነው”፣ “የአምሳ ቀን አጋመስኩ”፣”የሁለት ወር፥ታውጇል”፣ወዘተ ሲሉ ይስተዋላል፤ በግል ሕይወት ላይ የሚታይ ተጨባጭ ለውጥ፥ እምብዛም አይታይም፣ ሰዉ ሁሉ ሊከተለው የሚችልና የእግዚአብሔርን ፍርሃት የሚፈጥር ውጤት ግን ያን ያህል አይንፀባረቅም።

የሙሴን ታሪክ ለንጽጽር ብናነሳ”በዚያ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ” ብሎ”እንጀራም አልበላም፥ውኃም አልጠጣም። በጽላቶቹም፥ አሥሩን የቃል ኪዳን ቃሎች ጻፈ። ...ከሲና ተራራ በወረደ ጊዜ ...እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ ተነጋገረ የፊቱ ቁርበት እንዳንጸባረቀ አላወቀም ነበር። አሮንና የእስራኤል ልጆች ሁሉ፥ ሙሴን ባዩ ጊዜ፥ እነሆ የፊቱ ቁርበት አንጸባረቀ፤ ወደ እርሱም ይቀርቡ ዘንድ ፈሩ” ይላል (ዘጸ 34፡28-30)።

ከእግዚአብሔር ጋር የመቆየቱ መርሐ-ግብር ከሙሴ የታቀደ ሳይሆን ከራሱ ከእግዚአብሔር የመጣ ነው። እንደዚሁ ሁሉ ጾምና ጸሎትም ለተሻለ ውጤት የሚያበቃው ከጌታ በመጣ ምሪትና ግልጽ ምክንያት (clear motive) ተከትሎ ሲደረግ ነው። ጌታ እንዲህ እንድናደርግ ማስተዋል ይስጠን!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 359
መልዕክት (message) 359
ሌላ እሳት እና እሳት

እሳት ሁሉ እሳት ተብሎ ስለቀረበና ስለ ተቀጣጠለ እሳት ነው ብሎ መቀበል የኋላ ኋላ እውነተኛው እሳት ሲገለጥ ለችግር መዳረግ ይመጣል፥ግፋ ሲልም በእውነተኛው እሳት መበላት ይሆናል።

መጽሐፍ ሲናገር "የአሮን ልጆች ናዳብና አብዩድ በየራሳቸው ጥናውን ወስደው እሳት አደረጉበት፥በላዩም ዕጣን አኖሩበት፥ በእግዚአብሔርም ፊት እርሱ ያላዘዘቻውን ሌላ እሳት አቀረቡ ። እሳትም ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ በላቸው፥ በእግዚአብ ሔርም ፊት ሞቱ።" ይላል (ዘሌ 10፡1-2)።

አሁንም በእኛ ዘመን ከአገልግሎት ጋር በተያያዘ እሳት እዛም እዛም ተለኩሷል።ጥያቄው"እሳቱ እግዚአብሔር ያዘዘው ነው ወይስ አይደለም?" የሚል ነው። ካልሆነ፥ የለኮስነው ወይም የጫርነው እሳት ያልተሰጠንን ስለሆነ ዋናው እሳት የተገለጠ ጊዜ እንጠፋለን።

ኢየሱስ ሲናገር "በምድር ላይ እሳት ልጥል መጣሁ፥ አሁንም የነደደ ከሆነ ዘንድ ምን እፈልጋለሁ?" ይላል (ሉቃ 12:49)። ማንም ቢሆን ምድር ላይ እንዲጥል የተሰጠውን እሳት(ጥሪ) ብቻ ይፈጽም ዘንድ ይገባዋል።የተሳካልን መስሎን ሌላ እሳት ስናቀጣጥል፥ በአሮን ልጆች የደረሰው እንዳይደርስብን።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**



PART 360
መልዕክት (message) 360
ለምጽ እንዳይወጣብህ/ሽ !

በሆነ ጉዳይ “ኢትዮጵያዊ ነው/ናት” ከተባለ ሰዉ ሁሉ ጥያቄ ይፈጠርበታል። የጉዳዩ ባለቤት ኢትዮጵያዊ ስለሆነ/ነች ብቻ ትችት፣ ተቃውሞ፣ አድማ፣ ወዘተ ይጀመራል። ኢትዮጵያዊነት ይሄን ያህል ተጽእኖ ፈጣሪነት ከሆነ፥ አይደለም አንዴ ሺ ጊዜ ኢትዮጵያዊ ልሁን።

ከዚህ ጋር በተያያዘ፥ መጽሐፍ አንድ አስተማሪ ታሪክ ያነሳል፥ “ሙሴም ኢትዮጵያይቱን አግብቶአልና ባገባት በኢትዮጵያይቱ ምክንያት ማርያምና አሮን በእርሱ ላይ ተናገሩ።... እግዚአብ ሔርም ተቈጥቶባቸው ሄደ።...ማርያም ለምጻም ሆነች፥እንደ አመዳይም ነጭ ሆነች፤...አሮንም ሙሴን‘ጌታዬ ሆይ፥ስንፍና አድርገናልና፥ በድለንማልና እባክህ፥ ኃጢአት አታድርግብን።’ አለ ይላል (ዘኍ12:1-11)።

ያ እግዚአብሔር ዛሬም አልተለወጠም፥ያው ራሱ ነው፤ብድግ ብለህ ዛሬም፥ ኢትዮጵያዊን መናገር አትችልም። ይቆጣሃል፤ ለምጻም ትሆናለህ። ከወቅታዊው ሁኔታ መማር ያስፈልጋል። ኢትዮጵያዊነትን ተቃውሞ ከለምጽ የሚያመልጥ አይኖርም። በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ ሆነው ከዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት ተቃራኒ አቋም ያላቸው ሰዎች የሕይወት ለምጽ ይታይባቸዋል፥ ነጻነትን የተነጠቁ ስሜታውያን ናቸው። እንዲህ ላሉ ሰዎች፥ መፍትሄው፥ እንደ ሙሴ መጸለይ ነው።

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 361
መልዕክት (message) 361
የሐሰት መረጃ (propaganda)

የውሸት ሪፖርት/መረጃ (propaganda) ማሰራጨት አሁን አሁን በስፋት እየተለመደ መጥቷል።"ተቆጣጥረናል፣ይዘናል፣ በቅርቡ እንገባለን፣እንጨርሳቸዋለን፣ማንም አያስጥላቸውም ፣ ስልታዊ ማፈግፈግ እያደረግን ነው፣የተረፉት ቢበዛ ከሁለት ብርጌድ አይበልጡም፣ወዘተ"የሚሉና ያልተናበቡ መረጃዎች እዚያም እዚያም ይወጣሉ። እውነት ካልሆነ ነገሩ ውሸት ነው ማለት ነው። ውሸት ደግሞ፥ እግዚአብሔር የሚጸየፈው፥ ክፉ ወሬ ነው። የክፉ ወሬ (መረጃ) አቀናባሪዎች መጨረሻቸው፥ መቅሠፍት ነው።

መጽሐፍ በዚህ ጉዳይ አንድ ታሪክ ያስታውሰናል"ምድሪቱንም ሊሰልሉ ሙሴ ልኮአቸው የተመለሱት ሰዎች ክፉ ወሬም ስለ ምድሪቱ እያወሩ በእሱ ላይ ማኅበሩ ሁሉ እንዲያጕረመርሙ ያደረጉ፥ ክፉ ወሬ ያወሩ፥ እነዚያ ሰዎች፥ በእግዚአብሔር ፊት በመቅሠፍት ሞቱ።ነገር ግን ምድሪቱን ሊሰልሉ ከሄዱ ሰዎች የነዌ ልጅ ኢያሱና የዮፎኒ ልጅ ካሌብ በሕይወት ተቀመጡ"
ይላል (ዘኍ 14፡36-38)።

ሐሰት አባት አለው "እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ። ...እርሱ...ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነው።" ይላል (ዮሐ 8:44)
የሐሰት መረጃ (propaganda) የሚያሰራጭ ማንም ቢኖር እርሱ "አባቴ ማን ነው" እያለን ነው? ይልቅ ንስሐ እንግባ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**

PART 362
መልዕክት (message) 362
በእግዚአብሔር ፊት እሚጓደድ መሪ

አገልጋይ ሆኖ የጽድቅ ድፍረት ያለው ማግኘት እጅግ ግሩም ነው።መሪ ወይም አገልጋይ ሆኖ"የማይነቀፍ፥የአንዲት ሚስት ባል፥ ልከኛ፥ ራሱን የሚገዛ፥ እንደሚገባው የሚሰራ፥ እንግ?ዳ ተቀባይ፥ለማስተማር የሚበቃ፥የማይሰክር፥ የማይጨቃጨቅ ነገር ግን ገር የሆነ፥የማይከራከር፥ገንዘብ የማይወድ፥ልጆቹን በጭምትነት...እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር ፤" ማግኘት ታላቅ እድል ነው። (1 ጢሞ 3፡2-4)

በተለይ"ገንዘብ የማይወድ"የሚለው ሰማይ ካልወጣን እዚህ መኖሩን እጠራጠራለሁ። በዚህ ምክንያት ዛሬ እከሌ ከእከሌ በማይባልበት ሁኔታ የአገልጋዮች ንጥቂያ (ዘረፋ) እና በደል ተንሠራፍቷል። በውጨ ስላሉቱ አይወራም፥ እንደው ዝም!!!

አንድ በአገልግሎቱ የተመሠከረለትን ሰው፥ መጽሐፍ ያነሳል "ሙሴም ...እጅግ ተቈጣ፥ እግዚአብሔርንም... እኔ ከእነርሱ አንድ አህያ ስንኳ አልወሰድሁም፥ ከእነርሱም አንድ ሰው አልበደልሁም" ይላል(ዘኍ 16:15)።ስለ ራሱ የጽድቅ ብቃት በእግዚአብሔር ፊት እንዲህ እሚጓደድ መሪ ሲገኝ ምንኛ ደስ ይላል። እንዲህ ያሉና ለጽድቅ የጨከኑ መሪዎችን ያብዛልን!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 363
መልዕክት (message) 363
“ምድሪቱ ተከፍታ ትዋጣቸው” አንልም!

ጥሪ ያለህ መሪ ስትሆን፥ የሚነሱብህ አይጠፉም። መጽሐፍ “ቆሬ ...፥ የኤልያብ ልጆች ዳታንና አቤሮን የፋሌትም ልጅ ኦን በሙሴ ላይ ተነሡ።...ከእስራኤልም ልጆች ሁለት መቶ አምሳ ሰዎች ከእነሱ ጋር ወሰዱ፤ ከጉባኤው የተመረጡ ዝናቸውም የተሰማ የማኅበሩ አለቆች ነበሩ።” ይላል (ዘኍ 16፡1-2)።

ታሪክ እንደሚነግረን፥ ጥሪ ባለውና በጽድቅ ተጽእኖ በፈጠረ መሪ ላይ የተነሱ ሁሉ አልተረፉም። ከላይ በመግቢያው ላይ እንደተቀመጠው፥ በነቆሬ ተመርተው በሙሴ ላይ የተነሱትን ሰዎች ፍጻሜ መጽሐፍ ይነግረናል “ምድሪቱም አፍዋን ከፍታ እነርሱን ቤተ ሰቦቻቸውንም፥ ለቆሬም የነበሩትን ሰዎች ሁሉ፥ ዕቃዎቻቸውን ሁሉ ዋጠቻቸው። እነርሱም ለእነርሱም የነበሩ ሁሉ በሕይወታቸው ወደሲኦል ወረዱ፤ምድሪቱ ተዘጋችባቸው ፥ ከጉባኤውም መካከል ጠፉ።” ይላል (ዘኍ 16፡32-33)። እግዚኦ ነው!!!

በእኛ ዘመንም ቢሆን እያየን ያለነው ተመሳሳይ አካሄድ ነው። ጥሪ ባለው መሪ ላይ አሁንም ሰልፍ አለ። በነቆሬ እንደሆነው “ምድሪቱ ተከፍታ ትዋጣቸው” አንልም።የተቀበልነው መንፈስ የደህንነት መንፈስ ነው።እንጸልያለን ወደ ልባቸው ይመለሳሉ!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

Aynalem Mersie




PART 364
መልዕክት (message) 364
ጥብቅና፥ ለተቃዋሚዎች

መጽሐፍ"ሙሴም"ይልና፥ እንደመሪ"የኤልያብን ልጆች ዳታንና አቤሮን እንዲጠሩአቸው ላከ፤እነሱም አንመጣም፤ምድረ በዳ ትገድለን ዘንድ ወተትና ማር ከምታፈስሰው ምድር ያወጣኸን አይበቃህም? ደግመህ በእኛ ላይ ራስህን አለቃ ታደርጋለህ? ...ወተት እና ማር ወደምታፈስስ ምድር አላገባኸንም፥ እርሻና ወይንም አላወረስኸንም። የእነዚህንስ ሰዎች፥ ዓይኖቻቸውን ታወጣለህን? አንመጣም" በማለት በመሪያቸው በሙሴ ላይ በማመፅና በመነሳታቸው፥ ምድር ተከፍታ ዋጠቻቸው። (ዘኊ 16፡ 12-14፣ 32-33)

በጣም የሚያስደንቀው ነገር በማግስቱ የሆነው ታሪክ ነው። "የእስራኤል ልጆች ማኅበር ሁሉ፥ 'እናንተ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ገድላችኋል'ብለው በሙሴና በአሮን ላይ አጕረመረሙ ። ....በቆሬም ምክንያት ከሞቱት ሌላ በመቅሠፍቱ የሞቱት አሥራ አራት ሺህ ሰባት መቶ ነበሩ"ይላል(ዘኊ 16:41-49)፤

አንዳንድ ሰው የትላንቱን እያነሳ የተቃዋሚ ደጋፊ እና ጠበቃ መሆን ይወዳል። አብሮ መጥፋቱ አይቀሬ ነው።ምክንያቱም፥ የተቃዋሚዎች መጨረሻ ታውቋልና፥ " በአንድም ነገር እንኳ በተቃዋሚዎች አትደንግጡ፤ይህ ለእነርሱ የጥፋት፥ ለእናንተ ግን የመዳን ምልክት ነው፥ ይህም ከእግዚአብሔር ነው" እን
ዲል መጽሐፉ (ፊልጵ 1:28)።የትላንትን ነገር እንደ አዲስ እየ
መዘዙ ቅስቀሳ እና ተቃውሞ ማድረግ፥ የራስ መጥፊያ ነው። ጌታ ለሁላችንም ምህረት ያድርግ!!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!

facebook

What's on your mind?

**Aynalem Mersie**




PART 365
መልዕክት (message) 365
ተራጋሚ፥ የተረገመ

መራገም ክብር አይደለም። “ዋ! እኔ ከረገምኩህ... ” በማለት ማስፈራራት፥ የበታችነት(inferiority)ምልክት(symptom) ነው። በእርግማን የተካኑ ሰዎች፥በምላሹ ራሳቸው የተረገሙ ይሆናሉ። የርግማን ልምምድ ያላቸው ሰዎች፥ እርጉም የሆነ የሕይወት ዘዬ ውስጥ እንደሚመላለሱ የታወቀ ነው።”እንዴት አወቅህ?”እንዳትሉኝ።ጥናት አያስፈልገውም፤የሆነ መንፈሳዊ መገለጥም አይጠይቅም። በቃል ተረጋግጧል፡-

“የሚመርቅህ ሁሉ የተመረቀ ይሁን፥ የሚረግምህም ሁሉ የተገመ ይሁን።” (ዘኍ 24፡9)

“የሚባርኩህንም እባርካለሁ፥ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤” (ዘፍ 12:3)

ስለዚህ፥ ሰውን ወይም ሕዝብን ወይም ደግሞ ተቋምን፥ ከፍ ሲል ደግሞ አገርን የምትራገሙ፥ ይቅርባችሁ። አያዋጣም። የኋላ ኋላ የቃል መፈጸሚያ እንዳትሆኑ። ጌታ ሆይ ምህረት!!

መልዕክቱን መሞገት፣ ማሔስ እና ሌሎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ሼር ማድረግ በጎ ተግባር ነው።

በነገው መልዕክት እንገናኝ!!